International Labour Organization

Financial Education

Better Regional Migration Management

UKaid from the British people

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት



ገንዘብን በአግባቡና በእዉቀት መጠቀም

የቅጂ መብት © የዓለም ሥራ ድርጅት እ. ኤ.አ.2021
በመጀመሪያ እ. ኤ.አ.2021 ታተመ

የዓለም ሥራ ድርጅት ህትመቶች ሁሉ ዓለም አቀፉን ሁለተኛ የህትመት መብት ድንጋጌ ፕሮቶኮልን ተከትለው የሚፈፀሙ ናቸዉ። ነገር ግን ህትመቶቹን እንደ መረጃ ምንጭነት በመጥቀስ ረገድ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን የህትመቶቹን ውስን ክፍሎች በመቅዳት መጠቀም ይቻላል። ሕትመቶቹን ለመቅዳት ወይም ለመተርጎም ወይም ለተለየ ጉዳይ ለመጠቀም የሚያስችል መብት ለማግኘት እንዲቻል በቅድሚያ የፈቃድ ማመልከቻ በዓለም ሥራ ድርጅት የህትመት ውጤቶች ዝግጅት የመብትና የፈቃድ ክፍል የዓለም ሥራ ድርጅት CH-1211 ጀኔቫ 22 ስዊዘርላንድ በሚል የፖስታ አድራሻ ወይም በኢሜይል rights@ilo.org ማቅረብ የዓለም ሥራ ድርጅት ይህን ዓይነት አሰራር እንዲኖር ያበረታታል።

የማባዛትና ህትመቶቹን ሙሉ በሙሉ መጠቀም የሚያስችል መብት የተመዘገቡ ቤተ መፃህፍቶች፣ ተቋማት እና ሌሎች ተጠቃሚ አካላት በተሰጣቸው ፈቃድ መሰረት ቅጅዎችን የማድረግ መብት አላቸዉ በየሃገራት ደረጃ ያለውን ዝርዝር የዓለም ሥራ ድርጅት ህትመት ቅጅ መብት ለማወቅ የዓለም ሥራሥራ ድርጅት በይነ መረብ www.ifrro.org ላይ ማየት ይቻላል።

ቋንቋ ፡አማርኛ
9789220362747 ህትመት
9789220362754 በየነ መረብ ፒዲኤፍ

በዓለም ሥራ ድርጅት ህትመት ዝግጅት የተሳተፉ አካላትን እውቅና የመስጠት አካሄድ የተባበሩት መንግስታት አሰራርን የተከተለ ሲሆን በዚያ ውስጥ የሚጠቀሱና የሃገራትን ህጋዊ ሁኔታ፣ የግዛታቸዉን ገፅታና ድንበር፣ እንዲሁም መሪዎችን የሚገልፁ መረጃዎች በሙሉ የሰነዱ አዘጋጆች እንጂ የዓለም ስራ ድርጅት አይደለም/አይሆንም። በህትመቱ ውስጥ የሚገለፁት ሃሳቦችና አመለካከቶች ስራውን ለማከናወን በተሳተፈ አካል ፊረማ የተረጋገጠ ውል መሰረት የተቀመጡ ሲሆኑ የዓለም ሥራ ድርጅት እነዚህን ተቀብሎ እንዳፀደቀና የራሱ አድርጎ እንደወሰደ ተደርጎ መቁጠር እይቻልም በሰነዱ ውስጥ የተካተቱት አባባሎችም ሆነ አመለካከቶች ኃላፊነቱ የህትመቱ ደራሲ ብቻ ነው።

በዋቢነት የተጠቀሱት ስሞችና ተቋማት እንዲሁም የንግድ ዉጤቶችና አሰራሮች በሙሉ የዓለም ሥራሥራ ድርጅት ፈቃድ/ይሁኝታን አግኝተዉ የተገለፁ ተደርጎ መወሰድ የለባቸውም መጠቀስ ሲገባቸዉ ሳይጠቀሱ ቢቀሩም ይህ የአሰራር-ሙጣስ ጥፋቱ የህትመቱ አዘጋጆች እንጂ የድርጅቱ አይደለም። የዓለም ስራ ድርጅት ህትመትና የዲጂታል ዉጤቶች ዝግጅት ዝርዝር መረጃን በተመለከተ የድርጅቱ በይነ-መረብ www.ilo.org/publns መጎብኘት ያስፈልጋል።

የዓለም ስራ ድርጅት ህትመትና የዲጂታል ዉጤቶች ዝግጅት ዝርዝር መረጃን በተመለከተ የድርጅቱ በይነ---መረብ www.ilo.org/publns መጎብኘት ያስፈልጋል

ምስጋና

የእዚህ መፅሐፍ ዝግጅት በበላይነት የተመራዉ በሚሰተር ጉሰታቮ ፒሬፐሊቺ ሆኖ አጠቃላይ ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ስራ የተከናወነዉ በዓለም ሥራ ድርጅት የፋይናንስ ፕሮግራም ባልደረባ በሆኑት በያሱራ አህመድ አማካኝነት ነዉ። መፅሐፉን የማዘጋጀት ስራ በቴክኒክና በፈይንንስ የተደገፈዉ በአካባቢ የተሻለ/የተሳካ ፍልሰት አመራር ፕሮግራም አባላትና ለእዚህ ተብሎ በተቀጠረዉ የአገር ዉስጥ አማካሪ አቶ ታምሩ እሸቴ ጠቃሚ ግብዓት ጭምር ነዉ።

ዝግጅቱ በተጨማሪም በታህሳስ 2021 በተካሄደ የመፅሀፉን ይዘት የማበልፀግና ይፋ የማድረግ አዉደጥናት ጥናት ላይ በተሳተፉ ባለድርሻ አካላት አስተያየትና የማበልፀጊያ ግብዓት እንዲዳብርና የመጨረሻ መልክ ሊይዝ ችሏል።

የፅሁፉ አርትዖት የተከናወነዉ በበይነስ በንትቺኩ ሲሆን ካርቱንና በዉሥጡ የተካተቱ ስዕሎች የተዘጋጁት በሳምባ ሲሴ እና ዲዛይኑ በሚሼል ዴ ጂሴስ ነዉ።



ማውጫ

መግቢያ 6

1. መሰረታዊ ጉዳይ 6
2. የስልጠናዉ መጽሐፍ አቀራረብ 7
3. ከትምርህርቱ ተዋንያን ጋር ትዉዉቅ 8
   ተዋናይ 1 ስም፡ ወርቅነሽ 8
   ተዋናይ 2 ስም፡ ገመቹ 9
   ተዋናይ 3 ስም፡ ዳዊት 10
   ተዋናይ 4 ስም፡ ትርሐስ 11

ሀ) ግብን መቅረፅና ከቤተሰብ ጋር መግባባት ላይ መድረስ 12

1. ግብን መቅረፅ 13
2. ስለ ግቦችህ ከቤተሰቦችህ ጋር ተነጋጋር /ተወያይ! 14
3. የራስህን ግብ ወጪንና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በትክክል ለይቶ ማወቅ 16
4. የቁጠባ ዕቅድ እንዲኖርህ በማድረግ ግብህን ስኬታማ ማድረግ 17
5. ስደት ትክክለኛ ምርጫ ስለመሆኑ ወስን 23
6. የስደት የገንዘብ ወጪን መቀመር 25

ለ) ገንዘብህን በጥበብ ያዝ/ተጠቀም 27

1. በብልሃት ገንዘብን ተጠቀም! 28
2. በጀትን ማዘጋጀት 33
3. በበጀት መወሰንና በጀትን መመዝገብ 42
4. የሂሳብ መዝግብዎን ይያዙ 50

ሐ) የቁጠባ ዘዴዎችንና አገልግሎቶችን ይወቁ 51

1. የቁጠባ ዘዴዎችን ይምረጡ! 52
2. የቁጠባ ውጤቶችን በብልህነት ይምረጡ 56

አባሪዎችና ቁልፍ ሰነዶች 63
የመልመጃ መልሶች 64

መ) የብድር ውጤቶችን በብልህነት ይጠቀሙ 67

1. ፕሮጀክቶችዎን በገንዘብ ለመደገፍ ዘዴ ይምረጡ 68
2. ብድርዎን በብልህነት ይምረጡ! 72
3. የብድርዎን ዋጋ ያስቡ 75
4. ባለዕዳ እንዳይሆኑ ይጠንቀቁ! 84

አባሪና ቁልፍ/ ጠቃሚ ሰነዶች 88
የመልመጃዎች መልሶች 89

ሠ) የገንዘብ መክፈያና ማስተላለፊያ መንገዶችን ይምረጡ **93**

1. የክፍያ መንገዶችን በጥንቃቄ/በደህንነት ይጠቀሙ 94
2. ገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኞችን ማወቅ 99
3. ገንዘብ እንዴት መቀበልና መላክ እንደሚቻል 105

አባሪ እና አስፈላጊ ሰነዶች 109
የመልጃዎቹ መልሶች 110

ረ) የየገንዘብ ተቋማትን ማወቅና በብቃት መጠቀም **113**

1. የገንዘብ ተቋማትን ማወቅ 114
2. የገንዘብ ተቋማትን በራስ መተማማን መጠቀም! 120

ለጥያቄዎች መልስ 133

ሸ) አደጋ አሰተዳዳርና ኢንሹራንስ **137**

1. አደጋን ማስተዳደር 138
2. ለድንገተኛ አደጋ ገንዘብ ለመመደብ ጠቃሚ ምክር 142
3. የኢንሹራንስ/መድህን ፖሊሲዎን መረዳት 143
4. የኢንሹራንስ ፖሊሲን መጠቀም 147
5. ትክክለኛውን የኢንሹራንስ አገልግሎት መመረጥ 151

አባሪና ቁልፍ ሰነዶች 153
የጥያቄዎቹ መልሶች 153

ጭውውት አምዶች **155**

የወርቅነሽ ጭውውት ገጽ 155
የገመቹ ጭውውት ገጽ 161
የዳዊት ጭውውት ገጽ 167
የትርሃስ ጭውውት ገጽ 173
ትርጉም 179

መግቢያ

1. መሰረታዊ ጉዳይ

አሁን በእጃችሁ የሚገኘዉ ይህ መፅሀፍ ለሰልጣኞች የገንዘብ አያያዝ ትምህርት እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነዉ። መጽሀፉ በመሰረታዊነት የተዘጋጀዉ የገንዘብ አያያዛቸዉን ለማሻሻል ለሚፈልጉ ለፍልሰት ለተዘጋጁና ከፍልሰት ለሚመለሱ ዜጎች ነዉ።

ይህ መፅሀፍ ስልጣኞችን የተለያዩ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን ማለትም የቁጠባ፣የብድር፣የገንዘብ ማሰተላለፊያና የኢንሹራንስ ድርጅቶችን በመጠቀም ከመሰረታዊ ገንዝብ ማግኛ፣ አወጣጥ፣ ገዘብን እንዴት ጥንቃቄን በተከተለ መልኩ ለተለያዩ ጉዳዮች ለማዋል እንደሚቻል መሰረታዊ እዉቀትእና ክህሎት እንዲያገኙ ለማስቻልና እና ለእዚህ ከሚረዱ የተለያዩ መንገዶች ጋር ለማሰተዋወቅ የተዘጋጀ ነዉ።

ለገንዘብ አያያዝ ትምህርት ስልጠና የሚያገለግሉት ማቴሪያሎች ፋይዳቸዉ ለፍልሰት የተዘጋጁና ከፍልሰት የተመለሱ ወገኖችን የራሳቸዉና የቤተሰብ ገንዘብና ገቢን በሚገባ ለመያዝና ለማሰተዳደር ስለሚችሉበት መሰረታዊ እዉቀትና ከህሎት እንዲኖራቸዉ ለማድረግ ነዉ። መጽሃፉ ለማሳያነት የተጠቀመባቸው መርጃዎች ከእዚህ የሚከተሉትን የትምህርት ይዘቶች ማለትም የገንዘብ አያያዝ ፣ ግቦችን መወሰን፣ በራስ መተማመን ላይ የተመሰረተ ተግባቦት፣ፍልሰት የሚያስከትለዉን ወጪ በሚገባ ማወቅና ማስላት፣ ቁልፍ የገንዘብ አያያዝ በሚገባ ለይቶ ማወቅ (ቁጠባ፣ብድር፣ክፍያዎች፣ዲጂታል የሆኑ ተቀማጭ ክፍያዎች እና ኢንሹራንሰ የመሳሰሉ)፣ዲጂታል የሆኑ ደመወዝና ተያያዥ ክፍያዎችን በሚገባ ማወቅና መጠቀም መቻል፣የፋይናንስ ተቋማትን በሚገባ ማወቅና አስፈላጊዉን ግንኙነትና ድርድር መፈፀም እና ገንዘብን ያለምንም ችግርና ሊከሰት ከሚችል ተያያዥ ስጋቶች ነፃ በሆነ መልኩ ማስተላለፍ መቻል የመሳሰሉትን ያካትታሉ። ሥልጠናዉ በተጨማሪ በገንዘብ ላይ ከመወሰን ጋር የተያያዙ በወንዶችና በሴቶች፣ በአዛዉንቶችና በወጣቶች መካከል የሚኖሩትን ያልተመጣጠኑ ዕዉቀትና የግኑኝነት አቅም ልዩነት ችግሮችን ለማቃለል ያስችላል ይህ የስልጠና ማኑዋል በአሁኑ ሰዓት በጨርቃጨርቅና በአልባሳት እንዱስትሪዎች ዉስጥ እየሰሩ ላሉ ሰራተኞችና ወደፊት ሴክተሩን የሚቀላቀሉ ወገኖች የሚገጥማቸዉን መልካም አጋጣሚዎችና ተግዳረቶችን/ችግሮችን በሚገባ የሚያሳይ ነዉ ።

ይህ የስልጠና ማዕቀፍ የተዘጋጀዉ በዓለም ሥራ ድርጅት ሲሆን አዘገጃጀቱም መሰረት ያደረገዉ ድርጅቱ ከእዚህ በፊት ለተለያዩ የስራ ዘርፎች ብሎ ከነደፋቸዉ የፋይናንስ ትምህርት ማቴሪያሎች ነዉ።ይህ መፅሐፍ ቀደም ብሎ ለጆርዳን አገር ተብሎ የተዘጋጀዉን ለሌሎች በሚያገለግል መልኩ ተለውጦ የቀረበ ነዉ።


የሰልጣኞቹ መፅሐፍ የሚገለግለዉ ለአሰልጣኞች ተብሎ ከተዘጋጀዉ መመሪያ ጋር ጎን ለጎን ለሰልጣኙ የተዘጋጀ ነው።ይህ የሰልጣኞች መፅሐፍ የአሰልጣኝ መመሪያን የሚያግዝ ሆኖ የተዋናያን ባህሪይ ፣ልዩ ልዩ የግለ ታሪክ ጥናት፣መልመጃዎች እና ለሰልጣኞች የሚያገለግሉ ዋቢና ማጣቀሻዎችን የያዘ ነዉ። መጽሐፉ በተጨማሪ የስልጠና ቁልፍ ጉዳዮችና እያንዳንዱ ሰልጣኝ እንዴት አድርጎ ገንዘቡን እንደሚይዝና በትክክል እንደሚጠቀምበት የሚያሳዩ ለሥልጠናዉ የሚያገለግሉ ዘዴዎችን አካቷል። መጽሃፉ የተዘጋጀው በስልጠናው ለሚሳተፉ ወንድና ሴት ሰልጣኞች እንዲያገለግል ሆኖ ነው። በስልጠናዉ ወቅት መጽሃፉ እንደማጠቀሻ መጽሃፍ እና የመልመጃ መጽሃፍ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል።

ይህ የስልጠና መፅሐፍ የተዘጋጀዉ የተሳካ/የተሻለ የአካባቢ የፍልሰትአሰተዳደርን ፕሮጄክት አፈፃፀምን መሠረት በማድረግ ነዉ።ፕሮጄክቱም ተግባራዊ የሚሆነዉ በዓለም ስራ ድርጀት ሆኖ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር በነበሩ የተባበሩት የጋራ ብልጽግና እና ዕድገት አገራት የዉጪ አስተዳደር ቢሮ ትብብር በጋራ የተዘጋጀ ነዉ ።

2. የስልጠናዉ መጽሐፍ አቀሁሊብ

የፏይናንስ ትምህርት ምንኑትና ስለምን?

የገንዘብአያያዝትምህርትማለትየራስንገንዘብበአግባቡለመያዝናለመጠቀምየሚያስችል እዉቀት ከህሎትለመግኘት የሚያስችል ተገቢ መሳሪያ ነዉ። ይህ የሚትከታተሉት ስልጠና ለወደፊቱ ለሚኖራችዉ የተለያዩ የስራ ፕሮጄከቶችን ለማቀድና ለማዘጋጀት የሚያስችላችዉነዉ።ገቢን፣አወጣጥን፣ባጀት ማድረግን፣መቆጠብን፣ብድርንና ሌሎች ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚገባ ለመጠቀም የሚረዳ ነዉ።



ከእዚህ ሌላ ገንዘብን በሚመለከት ከቤተሰብ፣ከዘመድ ከአሰሪ፣አብሮ ከሚሰራ ወገኖች በሚገባ ተግባቦት ለመፍጠር በእዚህ ሂደት ችግሮች ሲፈጠሩ በቶሎ ለመለየት የተለየ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ገንዘብን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ መሳሪያዎችን ትማራላችሁ።እንደ ብድር ፣ቁጠባ ገንዘብ ማሰተላለፍ ወይም ኢንሹራንስ ያሉ የፋይናንስ አገልግሎቶች ለእናንተ ሚስጢር አይሆኑም።

የስልጠናውን መጽሃፍ እንዴት ትጠቀማላችሁ?


የገንዘብ አያያዝ ስልጠና በሚሰጥበት ሁሉ ይኼን የሰልጣኞች መፅሐፍ መጠቀም ያስፈልጋል። የትምህርቶቹ ምዕራፎች ቅደም ተከተሎች በስልጠናዉ ወቅት በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነትና በየትምህርት ጊዜያት በሚሰጡት ትህምርቶች ላይ የተመረኮዙ ናቸዉ። ነገር ግን በሚያስፈልግበት ጊዜ የትኛዉንም የመፅሐፉን ምዕራፍ ክፍል ማንበብ ይቻላል።

በመጽሃፉ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተካተቱት ጭውውቶችና ትረካዎች በተዋናዮቹ ጭውውትና ትረካ የገንዘብ አያያዝ ትምህርቱን እያዋዙ ሰልጣኞቹ ትምህርቱን በሚገባ እንዲረዱ ለማድረግ ነው።ትረካዎቹንና ቀልዶቹን በየስልጠናዉ ክፍለ ጊዜ የምታገኝኋቸዉ ስለሆነ ስለእነርሱ ማወቅ ያስፈልጋል። የሥልጠናውን መጽሃፍ በየርዕሱ በሚገባ እንድታነቢቸዉ እንገፋፋችኋለን ፡መፅሐፉ ብዙ መልመጃዎችና ራሳችሁ የምትሞሉት የተግባር ቅጾች ይዟል።

3. ከትምርህርቱ ተዋንያን ጋር ትዉዉቅ

የስልጠናዉ ፕሮግራም የአራት ዋና ዋና ተዋንያንን ታሪክ እና ልምዶችን የያዘ ነዉ።

ሰለእዚህ ስለተዋናያኑ የሚገልፅ ታሪክ በእዚህ ዓይነት ቀርቧል።



ተዋናይ 1
ወርቅነሽ

ስም: ወርቅነሽ

የምትወክለው ገጸ ባህሪ: *ተመላሽ*

የመኖሪያ አካባቢ: *ከተማ /አማራ ክልል*

ፆታ: *ሴት*

ዕድሜ: *30 ዓመት*

የጋብቻ ሁኔታ: *ከሊባኖስ ከስደት የተመለሰችዉ ከሦስት ዓመት በፊት ነበር።ከባለቤቷና ከልጇ ጋር አብራ ትኖራለች።*

የስራ ሁኔታ: *በአንድ ሆቴል ዉስጥ በፅዳት ሰራተኛነት በጊዜያዊነት ሰትሰራ ከስራ መልስ ደግሞ በቤቷ የጥልፍ ስራ ታከናዉናለች። ባለቤቷ ደግሞ በግንባታ ስራ ተቀጥሮ ይሰራል።*

የትምህርት ደረጃ: *12ኛ ክፍል ያጠናቀቀች*

ለገንዘብ ያላት ዝንባሌ: *በጣም የተረጋጋ*

ለገንዘብ ያለው አመለካከት:

- *መደበኛ የገንዘብ ተቋማትን ትጠቀማለች*
- *ሁልጊዜም ዓላማዋን ታስቀድማለች*
- *በጣም የተረጋጋችና በተቻላት መጠን ከገቢዋ ለመቆጠብ የምትሞክር ናት*

ዓላማዋ/የወደፊት ዕቅድዋ:

- *የራሷ የተፈላ ቡና የሚቀርብበት ሱቅ እንዲኖራት ትፈልጋለች*
- *መሬት ገዝታ የራሳቸዉን የመኖሪያ ቤት ለመንገባት ትፈልጋለች*
- *ለጌጥና ለጥልፍ ስራዋ የሚረዱ ግብዓቶችን ለመግዛት ትፈልጋለች*
- *ባለቤቷም ለልጇ አልጋ ለመስራት የሚረዳዉን ዕቃዎች ለመግዛት ይፈልጋል*
- *ሁለቱም ደብረ ብርሃን የሚኖሩትን የባለቤቷን ቤተሰቦች ለመጎብኘት ይፈልጋሉ*

ተጨማሪ ባህሪያት:

- *ባለቤቷ ከበደይባላል*
- *ወንድ ልጇ አለማየሁ (ዕድሜዉ ሁለት ዓመት) ነው።*
- *ወንድሟ አባይነህ ይባላል።*
- *ጓደኛዋ ሊባኖን የምትኖር ከዲጃ ናት*
- *የከበደ ቤተሰቦች*



ተዋናይ 2
ገመቹ

ስም: ገመቹ

የወከለው ገጸ ባህሪ: *ከስደት ተመላሽ*

የመኖሪያ ቦታ: *ገጠር/ኦሮሚያ*

ፆታ: *ወንድ*

ዕድሜ: *28*

የጋብቻ ሁኔታ: *በስደት ሳዉዲ አረቢያ ነበር ነገር ግን በሀገ ወጥነት ምክንያት ተይዞ በግዳጅ ወደአገሩ የተመለሰ ነዉ። አሁን ከባለቤቱና ከሁለት ህፃናት ጋር በወላጆቹ ቤት ዉስጥ ይኖራል ።*

የሥራሁኔታ: *በሳዉዲ አረቢያ በነበረበት ጊዜ ህገ ወጥ ስደተኛ ስለሆነ መኪና በማጠብ ስራ ይተዳደር ነበር። አገሩ ከተመለሰ በኋላ በቅርብ ጊዜ ለተመላሾች በተዘረጋዉ የስራ ዕድል አማካኝነት የትልቅ የጭነት መኪና ሾፌር ሆኖ እየሰራ ይገኛል። ከባለቤቱ ጋር በመሆን ሱቅ በመክራየት አነስተኛ ንግድ በመክፈት በመስራት ላይ ይገኛሉ። የወደፊት ህልሙ የራሳቸዉን መኖሪያ ቤት በመስራት በአንድ ሰፊ ክፍል ዉስጥ ከባለቤቱ ጫልቱ ጋር ንግድ በመክፈት መስራት ነዉ።*

ቤተሰብ:
- *ከባለቤቱ ጋር በመሆን የከፈቱት አነስተኛ ንግድ አላቸዉ*


የትምህርት ደረጃ: *10ኛ ክፍል አጠናቋል።*

ለገንዘብ ያለዉ ዝንባሌ: *ቆጣቢ .*

ለገንዘብ ያለው አመለካከት:
- *ከመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት ጋር የመስራት ፍላጎት አለዉ*
- *ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በዲጂታል የክፍያ መንገዶችን መጠቀም ጀምሯል*

ዓላማዎች:
- *የንግድ ስራቸዉን ስም በባነር መልክ የሚሰቀልበት ግድግዳ መስራት*
- *ለሴት ልጃቸዉ ብስክሌት መግዛት*
- *በቤተሰብ ባዶ ቦታ ላይ ቤት መሰሪያ የሚያገለግሉ የግንባታ ግብዓት መግዛት*

ተጨማሪ ባህሪያት:
- *ባለቤቱ፤ ጫልቱ*
- *ሁለቱ ህፃን ልጆች፣ ቢልሱማ እና ዲነግዴ*
- *ጎረቤቶቹ፤ባይሳ እና አያንቱ*



ተዋናይ 3
ዳዊት

ስም: ዳዊት

የሚወክለው ገጸ ባህሪ: *ለስደት የተዘጋጀ*

የመኖሪያ ቦታ: *ከተማ አዲስ አበባ*

ፆታ: *ወ*
ዕድሜ: *19*

የጋብቻ ሁኔታ: *ያላገባ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር*

የሥራ ሁኔታ: *ከሰውዲ አረቢያ ከስደት የተመለሰ ሲሆን እዚያ ያለዉን የአሁኑን ሁኔታ እየተከታተለ የሚያዉቅ ሰለሆነ ሁኔታዉ ሲሻሻል ወደእዚያዉ ተመልሶ ለመሄድ ፍላጎት አለዉ ።እዚህ ቋሚ ስራና መተዳደሪያ የለዉም። በጓደኛው ቲ-ሸረት መሸጫ ሱቅ ጓደኛውን እየረዳ ያሳልፋል።*

ቤተሰብ:

- *አባቱ በፋበሪካ ዉሰጥ የሚሰሩና የመላዉን ቤተሰብ አባላት ኑሮ በፋብሪካ ሥራ በሚያገኙት ገቢ ያስተዳድራሉ።*

ትምህርት ደረጃ: *9ኛ ክፍል ያጠናቀቀ*
ለገንዘብ ያለ ዝንባሌ: *የተረጋጋ*

ለገንዘብ ያለዉ አመለካከት:

- *በተቻለ መጠን ከሚያገኘዉ ገቢ ጥቂቱን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ተመልሶ ለመሄድ ዓላማ ለመጠቀም ይቆጥባል።*
- *ከገንዘቡ ጋር ያለዉ ሁኔታ የተደራጀና ትኩረት የሚሰጥ ነዉ ነገር ግን ግቡን ገና አላሳካም*

ዓላማዎች:

- *በህጋዊ መንገድ በመደበኛ የዉጭ አገር ሥራ ስምሪት በኩል በመዉጣት የተሻለ ገንዘብ ማግኘት*
- *በረጅም ጊዜ ደግሞ የእንግሊዝኛ ቋንቋ በመማር የአስነብኝነት ስራ በቋሚነት ለመስራት ይፈልጋል*

ተጨማሪ ግላዊ ሁኔታዎች:

- *ቤተሰቦቹ : አባቱ አቶ ፍስሐ እና እናቱ ወ/ሮ ትዕግስት*
- *ጓደኛዉ: ጌድዮን*
- *የሳዑዲ አረቢያ ጓደኛዉ: አባይነህ*
- *ሌላዉ ጓደኛዉ: ከፍያለዉ*



ተዋናይ ፋ
ትርሐስ

ስም: ትርሐስ

የዉክልና ዓይነት: *ለስደት የተዘጋጀች*

የመኖሪያ ቦታ: *ገጠር /ትግራይ*

ፆታ: *ሴት*

ዕድሜ: *20*

የጋብቻ ሁኔታ: *ያላገባች ከቤተሰቦቿ ጋር በገጠር የምትኖር*

የኢኮኖሚ ሁኔታ: *በግብርና ዉስጥ በወቅታዊ ሰራተኝነት የምትሳተፍ ወደዉጭ አገር በስደት በመዉጣት ገንዘብ በማግኘት የህፃናት መጫወቻ መሸጫ ትንሽ ሱቅ ለመክፈት ትፈልጋለች*

ቤተሰብ:
- *የትርሐስ እህት ከፍተኛ ባለዉለታ ጓደኛዋ ነች*
- *የትርሐስ ቤተሰቦች በግብርና ሥራ በወቅታዊ ሰራተኝነት ተቀጥረዉ ይሰራሉ*

የትምህርት ደረጃ: *የአንደኛ ደረጃ ትምህርት*

ለገንዘብ ያለ ዝንባሌ: *ያልተደራጀ*

ለገንዘብ ያላት አመለካከት:
- *መደበኛ የገንዘብ ተቋማት ለመጠቀም ፍላጎት አላት*

ዓላማዎች:
- *እንደ እህቷ ወደ ሊባኖስ በስደት በመሄድ በቤት ሰራተኝነት በመሰማራት ገንዘብ በመቆጠብ ማጠራቀም*
- *ከሊባኖስ በመመለስ የራስ መተዳደሪያ ስራ መክፈት*
- *ቤተሰቦቿ፤ አርአያ እና ለተብርሃን*
- *እህቷ፤ ራሐዋ*



U

ግብኝ መቅረፅና ከቤተሰብ ጋር መግባባት ላይ መድረስ

FINANCIAL QUIZ EDUCATION

U1. የሚከተለዉ ፈሊጣዊ አነጋገር ምን ማለት ነዉ? "ሰዉ ወዴት እንደሚቀዝፍ የማያዉቅ ከሆነ የነፋሰ ዓይነትና አቅጣጫ መረዳት አያስፈልገዉም"

- ☐ **ሀ.**በባህር በሚገባ ለመቅዘፍ ተስማሚ ነፋስ እንዲኖር ያስፈልጋል
- ☐ **ለ.**ወዴት እንደምትጓዝና ተጨባጭ ግብ ካለህ በህይወትህ ዘመን የቀረፀሃቸዉ የምትተገብራቸዉ እቅዶችና ስራዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል
- ☐ **ሐ.**ተስማሚ የሆነ ነፋስ ካለ ጀልባ መቅዘፍ ቀላል ይሆናል

U2. የወደፊት ግብህ ላይ ለመድረስ ተክክለኛዉ መንገድ ምንድን ነዉ?

- ☐ **ሀ.**የአጭርና የረጅም ጊዜያት ግብ በመቅረፅና ተፈፃሚ እንዲሆኑ በየጊዜዉ ከገቢ ላይ ቁጠባ ማድረግ ያስፈልጋል
- ☐ **ለ.**ግብ እንዲኖርና ተፈፃሚነታቸዉን ተስፋ ለማድረግ በራስ ላይ እምነት እንዲኖረን አስፈላጊ ይሆናል
- ☐ **ሐ.**ግብ እንዲኖረኝ ገና ወጣት ስለሆኑኩኝና ይኼን ለወደፊቱ ሲደርስበት አስቤ የማደርገዉ ነዉ

U3. በቴሰቦችህ እንደገና በአካባቢያቸዉ የሚደረግ በዓል ገንዘብ ጠየቁህ

- ☐ **ሀ.**ማንም ሁልጊዜ ለቤተሰቡ እንደሚያደርገዉ የጠየቁትን ገንዘብ እልክላቸዋለዉ
- ☐ **ለ.**ጥያቄአቸዉን አጥብቄ በመቃወም ገንዘቡን አልክላቸዉም
- ☐ **ሐ.**የወደፊት ግቤንና የቁጠባ ዕቅደን በሚገባ እንዲረዱኝ በሃሳቡ ዙሪያ በመወያየትና ከእዚህ አኳያ እንዴት ሊረዳቸዉ እንደሚችል ማስረደት

U4. የቁጠባ እቅድ ምንድነዉ?

- ☐ **ሀ.**የገንዘብ አገልግሎት
- ☐ **ለ.**ግብህን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ወጪዎች፣ መቸ ተግባራዊ እንደሚሆን፣ መቼ እዉን እንዲሆን ምን ያህል መቆጠብ እንዳለብህ በግልፅ የሚታይበት እቅድ ነዉ
- ☐ **ሐ.**የገንዘብ ሳጥን ነዉ

U5. ወደ ወጭ በፍልሰት ለመዉጣት ከመወሰንህ በፊት ምን ማድረግ አለብህ

- ☐ **ሀ.**ወደ ባንክ ቤት በመሄድ የገንዘብ ብድር ማግኘት እንደሚችል ማረጋገጥ
- ☐ **ለ.**በመሄድና በመቅረት መካከል ያለዉን ጥቅምና ጉዳት በሚገባ መለየት ለመዉጣት ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅ በማወቅ ላይ የተመሰረተ ምርጫ ማድረግ
- ☐ **ሐ.**ከእዚህ በፊት ዉጭ ሄደዉ የነበሩት ሰዎችን ብቻ በሚገባ በመስማትና የሚነግሩን ሁሉ እዉነት እንደሆነ በማመን

U6. በፍልሰት ወደዉጭ ለመዉጣት የሚያስፈልግ ገንዘብ እንዴት ይሰላል?

- ☐ **ሀ.**ለጉዞ ዝግጅት ፣በጉዞ ላይና የምንሄደበት ቦታ ስንደርስ አገር ቤት ቤተሰባችንን ለመርዳት የመሳሰሉ ዋና ዋና ወጪዎችን ለይቶ በዝርዝር ማሰቀመጥ
- ☐ **ለ.**ወደ ተቀባይ አገር ለመጓዝ የሚያስፈልግ ወጪን በመገመት
- ☐ **ሐ.**ከስደት የተመለሱትን ወገኖችየሚነግሩን ጉዳየችና ታሪኮች በሚገባ በመስማት

መልስ: U.1 ለ፣ U.2 ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ U.3 ሐ፣ U.4 ለ፣ U.5 ለ፣ U.6 ሀ

1. ግብዣ መቅረፅ

ትርጉም

ግብ ማለት ለመሆን ወይም ለመለራት የሚፈለገውን ነገር በቅድሚያ ማቀድ ነው።ግብ መቅረፅ በህይወት ዘመንህ ለመለራት የምትፈልገውን በትክክል ማለቀመጥ መቻልና ይኼም ከወን ከንዲሆን ለማለቻል ምን መለራት ከንደሚገባህ ለማወቅ የሚረዳ ነው።



ከተዋናዉያኖቻችን ዉስጥ አንዷ የሆነችዉን ወርቅነሽን እንተዋወቃት

የመነሻ ጥናት ተ.ቁ.1

የወርቅነሽ ታሪክ


ወርቅነሽ ዕድሜዋ 30 ዓመት ነዉ ከሊባኖስ ከስደት የተመለሰችዉ ከሶስት ዓመት በፊት ነበር ወደ አገርዋ ኢትዮጵያ ከተመለሰች ከበደን አግብታ አሁን አለማየሁ የሚባል የሁለት ዓመት ወንድ እናት ናት የባሌቤቷ አባትና እናት መኖሪያ ደብረብርሃን ነዉ።

ወርቅነሽ በአንድ ሆቴል ዉስጥ በፅዳት ሰራተኛነት በጊዜያዊነት ተቀጥራ ሰትሰራ በተጨማሪም የእጅ ጥልፍ ስራ ትሰራለች። የጥልፍ ስራዉን ክህሎት ያገኘችዉ ከእናቷ ሲሆን በተጨማሪም ከጥቂት አመት በፊት ሙያዉን ለማሳደግ በአንድ የስልጠና ማዕከል በመግባት በሥልጠና አዳብራለች። በጣም ጎበዝ ሰዉ ነች። ባለቤትዋ ከበደም አልፎ አልፎ በግንባታ ስራ ላይ ተሰማርቶ ይሰራል አሁን ግን ስራ ሰሌለው አሰቸጋሪ ጊዜን እያሳለፈ ነዉ።

ማታ ማታ ልጃቸዉ አለማየሁ ከተኛ በኃላ ባንድ ላይ ተቀምጠዉ ስለ ወደፊት ኑሮአቸዉ ዕቅድ ይወያያሉ ።ወርቅነሽ ብዙ ግቦች አላት ለእጅ ጥልፍ ስራዋ የሚረዱ የጥልፍ ክር፣መርፌ እና ጨርቅ ገዝታ ለሚሟላት ትፈልጋለች አብዛኛዉን ጊዜ ሻርፕ እና የአልጋ ልብስ ትሰራለች። አሁን ግን በእጅ የተሸመኑ የጥጥ ቀሚሶችን በፊት ለፊታቸዉ መሰቀል በመጥለፍ ለማዘጋጀት ትፈልጋለች። ከበደ ደግሞ ለልጃቸዉ መጫወቻ ለመስራት የሚስፈልጉ ዕቃዎችን ለመግዛት ይፈልጋል በተጨማሪም ከበደ ወረርሺኙ ከተነሳ በኃላ ቤተሰቦቹን ጠይቆ ስለማያዉቅ ሄዶ ለመጠየቅች ይፈልጋል።

ለብዙ ጊዜ የወርቅነሽ ህልሟ የራሷ የሆነ ቡና ቆልቶና አፍልቶ መሸጫ ቦታ እንዲኖራት ነዉ።እዘህም ቦታም ትኩስ የተቆላ ጥሬ ቡናና እና የተፈላ የጀበና ቡና ለገቢያተኛ የማቅረብ የቆየ ፍላጎት አላት ።ከበደ እና እርሷ በጋራ ደግሞ ለቤት መስሪያ የሚያገለገል ግብዓቶች በመግዛት መኖሪያ ቤት የመስራት ፍላጎት አላቸዉ።


የወርቅነሽ ህልም ምንድን ናቸዉ?
እዚህ ፃፏቸዉ





የሥልጠና መርጃ ሀ.1.1.

የእኔ ግቦች

ስለ ግቦች አስበህ ወይም ግቦችህን ለይተህ ታዉቃለህ ወይ?
ከሆነ እዘህ ጋር ለይተህ ፃፋቸዉ ወይም ሳላቸዉ!







አስታዉስ

ሁሉም ግቦችህ በጣም ጠቃሚና አሰፈላጊ ናቸዉ! አንዳንዳቹ ግቦች በቶሎ እዉን ሊሆኑ የሚችሉ ኖቸዉ።


⚠ **በጣም ጠቃሚ፡** ገንዘብህን በሚገባ መያዝና መጠቀም ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሊከሰቱ የሚችሉ ጭንቀትና ሃሳብ ይቀንሳል።

2. ስለ ግቦችህ ከቤተሰቦችህ ጋር ተነጋጋር /ተወያይ!

ግብዎን ከቤተሰብዎ ጋር ለመወያየት ጠቃሚ ምክር

- በግቦችህ ላይ ከቤተሰቦችህ ጋር ከመነጋገርህ በፊት ስለምትፈልገዉና ነገር እና ለምን እንደምትፈልግ ለይተህ አሰብበት
- ስለ ግቦችህ ለመነጋገር አትፍራ ሁሉም ወንድና ሴት፣ወጣት ሽማግሌ ሳይባል ሁሉ የራሱን ግብ እንዲኖረዉ መብት አለዉ
- አጋር/ተባባሪ ከቤተሰቦችህ ፈልግ ቀደም ብለህ ያነጋገርከዉና ሊረዳህ የሚችል የምታከብረዉ ከቤተሰቦችህ አጋር ይኑርህ
- በግቦችህ ላይ ከትዳር ጓደኛ ወይም ከሌሎች የቤተሰቦችህ አባል ጋር ከመወያየት በፊት እነርሱ የሚገኙበት ተሰማሚ ሰዓትና ጊዜ ምረጥ
- በግቦችህ ላይ ስትወያይ በራስ ላይ መተማመን ይኑርህ የሌሎችን ሀሳብና አሰተያየት ጣልቃ ሳትገባ በሚገባ በጥሞና አድምጥ
- ቤተሰቦችህን የምታከብርና በምትይዛቸዉ አቋም ዙሪያ አክራሪነት አታሳይ
- አለመግባባት እንኳን ቢኖር ጉዳዮችን በሚገባ መርምር ሁሉንም የቤተሰብ አባላት የሚያስማማና የሚያግባባ ሃሳብ ፈልግ

አድርግ...	አታድርግ...
• በራስ ተማመን • የምትፈልገዉን በሚገባ አስቀምጥ/ግለፅ • ባልደረባህን/ጓደኛህን በሚገባ አዳምጥ • ለሌላ ሰዉ ሀሳብና አሰተያየት ቦታ/አክብሮት ስጥ • አክብሮትን አሳይ • ጭምት ሁን ግትር አትሁን • ምንም እንኳን ከሌሎች ተቀባይነት ማግኘትን ብትጠብቅም ሃሳብህን በሚገባ ግለፅ	• ግድ የለሽ ወይም ባሌጌነት • መጮህ • ጣልቃ መግባት • መናደድ • ንቀትና ስድብ • አንድን ሃሳብና ነጥብ መደጋገም • ወዲያሁኑ የሌላ ሰዉን ሃሳብ ማጣጣል • አቋምን የመከላከል አዝማሚያ መያዝ • እርጋታ ያለማሳየት



⚠ **አስፈላጊ ጉዳይ**: ስለ ገንዘብ መወያየት የተለያዩ ስሜቶችን ይቀሰቅሳል ።ስለሆነም ይኼን ሃሳብህን የምታካፍለው የምታመነዉን ሰዉ ፈልግ።ስለ ስለስሜትህ አለመወያየትና አለመነጋገር የአዕምሮ ጤና ችግር ያስከትላል።

3. የሁስህን ግብ ወጪንና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በትክክል ሉይቶ ማወቅ

ለማሳካት ያሰብከውን ግብ የሚጠይቅህን ወጪ በሚገባ ለይተህ ታዉቃለህ ?

ግብህ የሚጠይቅህን ወጪ በሚገባ ለይተህ ታዉቃለህ ወይ? የሚታዉቅ ከሆነ ከላይ በገለፅካቸዉ ስር ወጪዎቹን አስቀምጥ። የማታዉቅ ከሆነ በተቻለ መጠን ለማስቀመጥ መሞከር አለብህ በዚህ መንገድ ብቻ ነዉ ግብህን ለማሳካት ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግህ ለማወቅ የምትችለዉ ለመጀመሪያ ጊዜ ግምታዊ ስሌት በማስቀመጥ በኃላም ስህተት ካለ ማረም ትችላለህ።

በቅድሚያ የምታደርገዉን 1
ቀጥሎ ቅድሚያ የምትለዉን ደግሞ 2 በማለት አስቀምጥ

ቁጥር	የግል ወይም የቤተሰብ ግብ	ግብ	ግምታዊ ዋጋ

አስታዉስ

አሰቀድመን ካሰብንበትና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ዉሳኔ ለማድረግ የሚያስችል መረጃ ከሰበሰብን ግባችንን እዉን ለማድረግ ቀላል ያደርገዋል። ቀድመን ግባችንን ለማሳካት ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቀን ማጥናት ተገቢ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ በጥንቃቄ የተደረገ ጥናት ማከናወን አስፈላጊ ነዉ (የአከፋፋይና የገበያ ሁኔታን የሚያሳዩ መረጃዎችን መሰብሰብ)

ዋጋ በየጊዜዉ እንደሚጨምር መርሳት የለብህም ስለእዚህ የጥንቃቄ ስሌት ማድረግ ማለት በቅርብ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ወጪዎች ጨምረዉ ግባችንን እንዳንመታ እንዳያደርጉ ከቀድሞ በላይ የተወሰነ መቆጠብ አሰፈላጊ ይሆናል።

4. የቁጠባ ዕቅድ እንዲኖርህ በማድረግ ግብህን ስኬታማ ማድረግ



የግል ሁኔታ ጥናት ቀ.2

የገመቹ የቁጠባ ዕቅድ

ገመቹ የ28 ዓመቱ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ በግዴታ ተይዞ እሰከተመለሰበት ድረስ ሳዉዲ አረቢያ ይኖር ነበር አሁን ከባለቤቱ ጫልቱ እና ከሁለት ልጆቹ (ቢሊሱማ 10 ዓመት) (ዲኔግዴ 6 ዓመት) ጋር አብሮ ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖራል።

ሳዉዲ አረቢያ በነበረበት ወቅት በህገ ወጥ ስደተኝነት መኪና በማጠብ ሥራ ተሰማርቶ ይኖር ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሰ ከጥቂት ጊዜ በኃላ በትርፍ ጊዜ ቅጥር የከባድ ተሽከርካሪ ሾፌርነት ለተመላሾች በተመቻቸው ፕሮግራም የስራ ዕድል አግኝቶ በመስራት ላይ ይገኛል። ከእዚህ በተጨማሪ ከባለቤቱ ጋር በተከራዩት ትንሽ ሱቅ ዉስጥ አነሰተኛ ንግድ ስራ ከፍተዉ ይሰራሉ።

ገመቹ እና ባሌቤቱ ጫልቱ አንዳንድ ምኽት ሻይ እየጠጡ ስለወደፊት ሁኔታቸዉ ይወያያሉ። ብዙ ግቦች/ዓላማ አላቸዉ ግን ግቦቻቸዉን እዉን ማድረግ ቀላል እንዳልሆነ ያዉቃሉ። ገመቹ ለልጇ ለብሊሱማ ቀጣይ ልደት በዓል ብስኪሌት ሊገዛለት ይፈልጋል። በተጨማሪም ጫልቱ ለሱቃቸዉ ግድግዳ ለመስራትና ሱቁን ለማስተዋወቅ የሚያስችል የሚለጠፍ ማስታወቂያ ለመግዛት ትፈልጋለች።ይህ ደግሞ የንግድ ስራቸዉን እንዲያደግ ለማድረግ እንደሚረዳ ገምታለች።

የገመቹ ሕልም ከባለቤቱ ጋር ሆኖ ለሚከፍቱት የራሳቸዉንሱቅ የሚሆን ክፍል ጨምሮ ብዙ ክፍሎች ያሉት መኖሪያ ቤት መስራት ነዉ። ከእዚህ በተጨማሪ ጫልቱ ደግሞ የነፃ የገንዘብ አያያዝ ትምህርት በመከታተል ከገመቹ ጋር በመሆን የገንዘብ አያያዛቸዉን እዉቀት ላይ በተመሰረተ መልኩ በማካሄድ ገንዘብ በሚገባ ለመያዝ ትፈልጋለች።

ገመቹ ለእያንዳንዱ ግቦቹ እዉን ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ወጪዎችን ለይቶ በማጥናት መቾ ሊያሳካቸው እንደሚችል ጊዜዉን አስቀምጧል። ይኼን እዉን ለማድረግ የሚያስችል የገንዘብ መጠን ላይ ለመድረስ በየወሩ ስንት መቆጠብ እንዳለባቸዉ አስልቶ ደርሶበታል። በእዚህ መሰረት ገመቹ የቁጠባ ዕቅድ የሚባለዉን አዘጋጅቷል ። ይኼ ደግሞ ገመቹ እና ባለቤቱ ግባቸዉን እዉን ለማድረግ በየወሩ ምን ያህል ገንዘብ መቆጠብ እንዳለባቸዉ ትክክለኛ እይታ እንዲኖራቸዉ ያስችላቸዋል።

እስቲ የገመቹን የቁጠባ ዕቅድ እንመልከት!

የእኔ የቁጠባ ዕቅድ


የእኔ ግብ	ግቤን ለማሳካት የሚፈልግበት ጊዜ	ግቤን ለማሳካት የሚያስፈልግ ወጪ	ከግብ ስኬት በፊት ያሉ ወራት ቁጥር	ሌሎች የገንዘብ ምንጮች	ግብን ለማሳካት እንዲቻል በየወሩ የቁጠባ መጠን
የቅርብ ጊዜ ግብ/ ከ12 ወራት በታች/					
ለሱቅ ግድግዳ ለመስራትና የሚሰቀል ማስታወቂያ ለመግዛት	የእዚህ ዓመት ህዳር	3000 ብር	3 ወር		1000 ብር
የመካከለኛ ጊዜ ግብ /ከ1 እስከ 3ዓመት ድረስ/					
ለሴት ልጃቸዉ ልደት ቢስኪሌት መግዛት	የሚቀጥለዉ ዓመት መስከረም	9000 ብር	12 ወራት		750 ብር
የረጅም ጊዜ ግብ /ከ3አመታት በላይ/					
ለቤት ግንባታ የሚረዱ ግብዓቶችን መግዛት	የሚቀጥለዉ ሦስት ዓመት ታህሳስ	100,000 ብር	36 ወራት	ተመላሾችን ለማቋቋም ከተዘረጋ ፕሮግራም 46000 ብር	1500 ብር
ግቤን ለማሳካትእንዲቻለኝ በየወሩ የማጠራቅመዉ መጠን ድምር በቀኝ በኩል የተዘረዘሩት ድምር					3250 ብር



⚠ **በጣም አስፈላጊ: ገመቹ የአጭር ጊዜ ግቡን ካሳካ የቁጠባ ዕቅዱንና በየወሩ የቁጠባ መጠኑን በማስተካከል የተቀሩትን ደግሞ እዉን ለማድረግ መጣጣር ያስፈልገዋል።**

የሥልጠና መርኻ U1.2

የቁጠባ ዕቅዴ



አሁን የእናንተ ተራ ነዉ!

አሁን እስቲ የሰራነዉን በማጠቃለል ከእዚህ በታች በተቀመጠዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የታሰቡትን ግቦች፣የቅድሚያ ጉዳዮች ወጪዎች ግባችንን የምናሰካበት ጊዜ እና ሌሎች የገቢ ምንጮች የመሳሰሉትን መረጃዎችን ማስቀመጥ እንሞክር

▶ የስልጠና መርጃ

U1.2

የቁጠባ ዕቅዴ					
	ግቤን የማሳካበት ጊዜ	ግቤን ለማሳካት የሚያስፈልግ ወጪ	ግቤን ለማሳካት የቀሩኝ ወራት	ሌሎች የገቢ ምንጮች (አስፈላጊ ሲሆን)	ግቤን ለማሳካት በየወሩ መቆጠብ የሚኖርብኝ መጠን
የአጭር ጊዜ ግብ(ቦች) :					
የረጂም ጊዜ ግብ(ቦች) :					
ከቤተሰቦች ጋር የሚጋራቹዉ የቅርብ ጊዜ ግቦች:					
ከቤተሰቦቼ ጋር የሚጋራቹዉ የሩቅ ጊዜ ግቦች:					
ግቦቼን ለማሳካት በየወሩ መቆጠብ ያለበኝ መጠን ድምር((በስተቀኝ ካለዉ የሰንጠረዥ ከፍል የተዘረዘሩት ድምር):					

የአንተ ተራ

ግቤን ለማሳካት በዋናነት

. . . . . .

መቆጠብ ያለብኝ ነው።

ተጠንቀቅ !

በዋናነት ለመቆጠብ የተቀመጠውን
መቆጠብ ካልተቻለ ሌላ ግብ
ማሳቀመጥ ያለብኝ ነው።

ወጪዎችን መቀነስ፣ወይም
ለአሁኑ የተወሰኑትን ግቦች
በመሰረዝ ወይም ግብን ለማሳካት
የተቀመጠውን ጊዜ ወደሌት
በማለተካከፍ ነገሮች ቅድሚያ

ግቦችህን ነገዳለቀመጥክ በማዋት
ምሳሌ ግብ 1 እና ግብ 2ን መቀየር
ነትችልም ግን ግብ 3 እና ግብ 4ን
ልትቀይር ትችላለህ።

⚠ጥም አስፈላጊ

የቁጠባ ነቅድ ማለቀመጥ ጥቢት
ማድረግ ይጠይቃል። በተለይም
ለመቆጠብ ያሰብነውን መጠን ካልቻልን
ሁለን በጣም ማጨናነቅ ነያስፈልግም።
ሁልጊዜም የቁጠባ ነቅዳችንን
መቀያየር ነንጨሚቻል ማለታወለ
ያስፈጋል።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.3

የወርቀነሽ ችግሮች

ወርቀነሽ ከወንድሟ ዓባይነህ ጋር ሆነዉ ሻይ እየጠጡ አሁን የምትሰራዉን የሆቴል ስራ በተመለከተ የማታ ፈረቃ ትታ በቀን ተቀይራ ለመስራት እንደምትፈልግ ለስራ አስኪያጅ ለማሰረዳት እንዳቀደች አጫወተችዉ። በማታ ፈረቃ ስትሰራ ከስራ ወደ ቤቷ የምትመለሰዉ አምሽታና በጣም ደክሟት ነዉ። ስራአስኪያጁም ሃሳብዋን የማይቀበላት ከሆነና የሆቴል ስራዋን ማቋረጥ የምትገደድ ከሆነ ከወትሮዉ የበለጠ ለመቆጠብ እየተጣጣረች ነዉ። ካላቸዉ የገንዘብ ፍላጎትና የታራ ግባቸዉን እዉን የማድረግ ጥረት የተነሳ ይኼን ሃሳቧን ለከበደ ለማካፈል አስቸጋሪ ሀኖባት ነበር ሆኖም ግን በሰተመጨረሻ ስትነግረዉ ሊረዳት ችሏል።

አባይነህ የሚገጥሙትን ችግሮች ለእርሷ ላለመናገር እንደወሰነ ሃሳቡን አካፈላት በኢኮኖሚ ምክንያት የሚከሰተዉን የኑሮ ዉጣ ዉረድ ለብቻዉ እንደሚይዘዉና የራሱን የግል ወጪዎችን እስከ መጨረሻ ድረስ በመቀነስ የቤተሰቡን ባጀት በመደጎም መቀጠል እንዳለበት ወሰነ።

የራሱን የግል ወጪዎችን ከቀነሰም በኃላ እንኳን አንዳንዴ ለቤተሰቡ የሚያስፈልጋቸዉን ምግብ መግዣ ግንዘብ ያጣል ይህም ጫና በእርሱ ላይ ስለሚወድቅ ለችግሩ መፍትሄ ለመፈልግ ይጣጣራል።

የሥልጠና መርጃ ሀ2.1

የድርሻ ጨዋታ ድርጊት:

ግጭትና ስምምነት



የሃሳብ ግጭት 1

ዳዊት የሚቀጥለዉ ዓመት ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመሄድ ፍላጎት ስላለዉ እዚያ ለሚሄድበትና ለሚቆይበት የሚረዳ ገንዘብ መቆጠብ ይጠበቅበታል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ጓደኛዉ ጌድዎን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ሄዶ ነበር። ለመመለስ ወስኖ ተመልሷል አሁን ኢትዮጵያ ዉስጥ አግብቶና የራሱ የቲ ሸርት ሱቅ ከፍቶ ይሰራል። ጌድዎን ዳዊት ወደ ሳዑዲ የመሄዱን ሃሳብ ትቶ ገንዘብ በማጠራቀም ከእርሱ ጋር በመሆን የቲ ሸርት ንግድ እንዲከፍት ይገፋፋዋል። ዳዊት ስለ ግቡ በሚገባ ያዉቃል ነገር ግን በግቡ በመፅናት ለመቀጠል በብዙ የሚደግፈዉን ጓደኛዉን ማሳዘን አልፈለገም ዳዊት የጓደኛዉ ሃሳብ ሳይቀበል አይሆንም ማለት ሌሎች ጓደኞቹ በጣም እንዲናደዱበት ያደርጋል ስለሆነም ምን ማድረግ ይገባዋል?

በታሪኩ ዉስጥ የተካቱትን ተዋናዉያንን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የድርሻ ጨወታ በማዘጋጀት ለቸግሩ መፍትሄ የምትለዉን አሰቀምጥ በድርሻ ጨወታ ዉስጥ እንዲሳተፍ ከመረጥከዉ ተዋናዉያን ዉስጥ አንዱ የትክክለኛ ተግባቦት ሀግ የመጠቀም ድርሻ ይዘ መጫወት አለበት።

የሃሳብ ግጭት 2

ዳዊት የሚቀጥለዉ ዓመት ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመሄድ ፍላጎት ስላለዉ እዚያ ለሚሄድበትና ለሚቆይበት የሚረዳ ገንዘብ መቆጠብ ይጠበቅበታል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ጓደኛዉ ጌድዎን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ሄዶ ነበር ግን ለመመለስ ወስኖ ተመልሷል አሁን ኢትዮጵያ ዉስጥ አግብቶና የራሱ የቲ ሸርት ሱቅ ከፍቶ ይሰራል ጌድዎን ዳዊት ወደ ሳዑዲ የመሄዱን ሃሳብ ትቶ ገንዘብ በማጠራቀም ከእርሱ ጋር በመሆን የቲ ሸርት ንግድ እንዲከፍት ይገፋፋዋል ዳዊት ስለ ግቡ በሚገባ ያዉቃል ነገር ግን በግቡ በመፅናት በመቀጠል በብዙ የሚደግፈዉን ጓደኛዉን ማሳዘን አልፈለገም ዳዊት የጓደኛዉ ሃሳብ ባለመቀበል አይሆንም ማለት ሌሎች ጓደኞቹ በጣም እንዲናደዱበት ያደርጋል ስለሆነም ምን ማድረግ ይገባዋል?

በታሪኩ ዉስጥ የተካቱትን ተዋናዉያንን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የድርሻ ጨወታና ለቸግሩ መፍትሄ የምትለዉን በማዘጋጀት አሰቀምጥ በድርሻ ጨወታ ዉስጥ እንዲሳተፍ ከመረጥከዉ ተዋናዉያን ዉስጥ አንዱ የትክክለኛ ተግባቦት ሀግ ተግባራዊ የማድረግ ሚና መጫወት አለበት።

የሃሳብ ግጭት 3

ገመቹ በየጊዜዉ ለሚከሰቱ ድንገተኛ ጉዳዮችና የአነስተኛ ንግድ ሱቁን ቀስበቀስ ለማሻሻል ለማሳደግ እንዲቻለዉ ገንዘብ ማስቀመጥ ጀምሯል። ዲነግዴ ወንድ ልጁ የእግር ኳስ መጫወቻ እንዲገዛለት ጠየቀዉ ገመቹም ልጁ የጠየቀዉን ኳስን ማግኘት የብዙ ጊዜ ፍላጎቱ እንደሆነ ያዉቃል ነገር ግን ለሌሎች ቅድሚያ ለሚሰጣቸዉ ጉዳዮች ገንዘብ መቆጠብ ስላለበት ፍላጎቱን ለሟሟላት ጊዜዉ አይደለም ስለእዚህ ምን ማድረግ አለበት?

በታሪኩ ዉስጥ የተካቱትን ተዋናዉያንን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የድርሻ መፍትሄ የምትለዉን በማዘጋጀት አሰቀምጥ በድርሻ ጨወታ ዉስጥ እንዲሳተፉ ከመረጥከዉ ተዋናዉያን ዉስጥ አንዱ የትክክለኛ ተግባቦት ሀግ ተግባራዊ የማድረግ ሚና መጫወት አለበት።

የሃሳብ ግጭት 4

ትርሐስ ዓላማዋን ለማሳካት እንዲቻላት ገንዘብ በትራሷ ስር ታስቀምጣለች አንድ የስራ ባልደረብዋ ህዳዋን ለመክፈል እንዲቻላት ገንዘብ እንድታበድራት በተደጋጋሚ ጊዜ ጠይቃታል ትርሐስ ጓደኟ የጠየቀችዉን ብድር በመስጠት ለመተባበር ብትፈልግም ግን እርሷ ለሌሎች ጉዳዮቿ ማሳኪያ የተቻላትን ገንዘብ መቆጠብ አለባት ስለእዚህ ምን ማድረግ አለባት?

የተካቱትን ተዋናዉያንን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የድርሻ መፍትሄ የምትለዉን በማዘጋጀት አሰቀምጥ በድርሻ ጨወታ ዉስጥ እንዲሳተፉ ከመረጥከዉ ተዋናዉያን ዉስጥ አንዱ የትክክለኛ ተግባቦት ሀግ ተግባራዊ የማድረግ ሚና መጫወት አለበት።

ጠቃሚ መልዕክቶች

- የምትፈልገዉንና ነገር በትክክል የምታዉቅና ግቦችህን በሚገባ ካስቀመጥክ ዕቅዶችህን በቀላሉ ለማሰካት ትችላለህ፣
- አንዳንድ ግቦች በፍጥነት ይሳካሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ዓመታትና አሰርተ ዓመታት ይፈጃሉ በመሆኑ ግቦች የአጭር ፣የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ተብለዉ መከፈል ይኖርባቸዋል፣
- የሰዎች ግቦች በህይወት ዘመን እና በጊዜ ሂደት ዉስጥ ሊለወጡ ይችላሉ እናም የተለያዩ የቤተሰብ አባላት ልዩ ልዩ ግቦች ይኖራቸዋል በመሆኑም የቤተሰብ የተለያዩ ግቦች እርሰ በእርሱ የሚስማሙና አብረዉ መሄድ መቻል አለባቸዉ፣
- በቤተሰብ አባላት በተለይም በርቀት ማለትም በከተማ በክልልና በአገር ተለያይተዉ ለሚኖሩ እርስ በእርሳዉ ጥሩ ተግባቦት እንዲኖራቸዉ ያስፈልጋል ፣
- ግብን በትክክል ማስቀመጥና በእዉንና በተምኔት መካከል ልዩነት ባስቀመጠ መልኩ መቅረፅ ስኬታማነታቸዉን ለማረጋገጥ ይረዳል
- የአንድ ግብ ስኬት የሚጠይቀዉን ትክከለኛ ወጪና እሴት በትክክል ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን መያዝ ጠቃሚ ይሆናል፣
- በገንዘብና በማህበራዊ ዙሪያ በሚከሰቱ ለዉጦች የተነሳ ግቦቻችን ለማሳካት ዉድ ሲሆን ግትርነትን በሚያስቀር መልኩ ግቦቻችንን መከለስ የግድ ይላል ፣
- ግቦቻችንን ሳንዘነጋ ሁሌ ማሰታወስ ለስኬታማነታቸዉ እርግጠኛነት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል
- የቁጠባ ዕቅድ መኖር ግቦቻችንን ስኬታማ እንዲሆኑ አብዝቶ ይረዳል

ማስታወሻዎች

5. ስደት ትክክለኛ ምርጫ ስለመሆኑ ወስን



የግል ሁኔታ ጥናት ተ.ቁ.4

የትርሐስ እናት የስደት እይታ

እኔ ለተብርሐን እባላለሁ። ትርሐስና ራህዋ የሚባሉ ሴት ልጆች እናት ነኝ። ራህዋ ታላቋ ልጄ ናት። ራህዋ ከአንድ ዓመት በፊት ለስራ ብላ በስደት ወደ ሊባኖን ሄደች። እኔም ይኼን ዕድል በማግኘቷ ደስተኛ ነበርኩ። ነገር ግን በእዚያዉ መጠን ደግሞ ከእኔ ርቃ ሌላ አገር ለመኖር ስለሄደች አዝኜ ነበር። ለኑሮአችን የሚሆን በየወሩ ገንዘብ ትልክልን ነበር ። እኛም ይኼን በማግኘታችን በቀን ሦስት ጊዜ ምግቦች አቅርበን መብላት ቻልን ስለሆነም የራህዋ ስደት ዉሳኔ ለእኛ የፋይናንስ/ገቢ ሁኔታ ፀጋና ጥሩ አጋጣሚ ነበር።

ነገር ግን ልጄ ወደ ሊባኖን ለስራ ከወጣች ጀምሮ ቤት ዉስጥ ትረዳኝ የነበረዉ ጎድሎበኛል። በእዚህ ረገድ አገኝ የነበረዉ እርዳታ ቀንሶብኛል ። ራህዋ ከእህቷ ከትርሐስ ጋር በመሆን ቀን ቀን በስራ በጣም ያግዙኝ ነበር። አሁን ትርሐስ ጭምር እህቷን ተከትላ ወደ ሊባኖን በስደት ለመሄድ እንደምትፈልግ አምናለሁ። የሁለቱን እርዳታ በከፍተኛ ሁኔታ እንደማጣ እርግጠኛ ነኝ ።የራሳቸዉን ዕድል ሁኔታና ልምድ ለማዳበር እንዲቻላቸዉ በሚወስዱት ዉሳኔ ደስተኛ ነኝ ።ነገር ግን ደግሞ እዚሁ ሆነዉልኝ ልጆች ወልደዉ አያት ቢያደርጉኝ ደስተኛ ነኝ።

⚠ **ትኩረት የሚሰጥበት ጉዳይ:** ሰዎች ብዙ ጊዜ ለስደት ጠቀሜታ ብቻ ትኩረት ይሰጣሉ ሆኖም ስደት ግን ጉዳትም ይኖረዋል

የስደት ጠቀሜታዎችና ጉዳቶች
((ስደት ከሚያደርጉ አካላት እይታ)

ጥቅሞች	ጉዳቶች
• ብዙ ገንዘብ ማግኘት • ቤተሰብ ለኑሮ የሚየስፈልጋቸዉን ማለትም ምግብ የጤና እንክብካቤ የትምህርትና የመብራት አገልግሎት ወጪን መሸፈን መቻል • አዲስ ክህሎት መቅሰም • አዲስ ስራ መስራትና ሌላ ልዩ ልምድ ማግኘት • ራስን የመቻልና የነፃነት ስሜት እንዲሰማ ማድረግ • ለወደፊቱ መቆጠብ መቻል	• ስደት ለወደፊት ለመክፈል አዳጋች የሆነ ዕዳ ዉስጥ እንደመግባት ሊመሰል ይችላል • ዉጪ አገር ስራ ቶሎ ላይገኝ ይችላል • በመዳረሻ አገር ያለዉ ከፍተኛ የኑሮ ዉድነት • ተይዤ ወደ አገር እመለሳለሁ የሚል ስጋት በተደጋጋሚ መስማት (በሄድንበት አገር ዉስጥ ህጋዊ ነዋሪ ካልሆን) • በአደገኛና በጎጂ ስራ ምክንያትና የወሲብ ጥቃት ስለባ የመሆን ስጋት (በተለይም በሄድንበት አገር ህጋዊ ነዋሪ ካልሆን) • በቤተሰብ በኩል ብዙ ገንዘብ እንደሚገኝ መጠበቅ • ብቸኝነትና መገለል • ከተሰደዱበት አገር ሲመለሱ በማህበረሰብ የመገለል ሁኔታ

ጠቃሚ መልዕክቶች

- ሰዎች የሚሰደዱት በብዙ ምክንያቶች ነዉ፡ ብዙ ገንዘብ ለማፍራት ፣የተለያዩ ልምዶች ለማግኘት ፣ለመማር፣አዳዲስ ክህሎቶች ለመቅሰምና በአገራቸዉ የሚከሰት ግጭትን ለመሸሽ፣
- የስደትን ጠቄሜታ በሚገባ ለይተህ ማወቅ ይጠበቅብሃል ማለትም ከሂደቱ የሚታተርፈዉን እንዲሁም የሚየስከትለዉን ጉዳትና ወጪ በሚገባ ማጥናት ይጠበቅብሃል ማለትም አንተም ሆንክ ቤተሰቦችህ የሚታጡትን ሁሉ
- የስደት ጥቅምና ጉዳት በገንዘብ ዙሪያ ብቻ የታጠረ አይደለም ከማህበራዊና ከቤተሰብ ግንኙነት ጋርም በጣም የተሳሰረ ነዉ
- ከስደት ጋር የተያያዙ የሰህተት መረጃዎች ይሰራጫሉ። ሰዎች ከሚናገሩት በተቃራኒ ገንዘብ አገር ቤት ሆነ ሌላ አገር ከመሬት ላይ አይሰበሰብም!

6. የስደት የገንዘብ ወጪን መቀመር

ስደት ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ዉድ የሆነ ሂደት ነዉ አንተ/አንቺ ግን በትክክል ስደት ምን የህል ወጪ እንደሚጠይቅህ /ሽ ታዉቃለህ/ሽ?



የሥልጠና አጋዥ ሀ.3.1

ዝርዝር የስደት ወጪ ቀመራ



በፍልሰት ለመሳተፍ አስቤ አለዉ: .....

.....

.....

የፍልሰት መዳረሻዬ: .....

	ምን ያስወጣኛል?	እንዴት እከፍላለሁ?
የዝግጅት ወጪ		
የጉዞ ወቅት ወጪ		
በሚሄድበት አገር ወይም ከተማ ወጪ		
የመመለሻ ወጪ		
በአገር ቤት ለቤተሰብ የሚወጣ ወጪ		
ጠቅላላ የወጪ ድምር		

⚠ **ጠቃሚ ጉዳይ:** ለመሰደድ ከመወሰን በፊት ሂደቱ የሚጠይቀዉን ወጪና ለራስና ለቤተሰብ የሚያስገኘዉን ጥቅም በሚገባ ለይቶ ማወቅ በጣም ይጠቅማል።

ቁልፍ መልዕክቶች

- ይህ ሰንጠረዥ አንተና ቤተሰቦችህ ስደት የሚጠይቀዉን ጠቅላላ ወጪ ለመቀመርና ለይቶ ለማወቅ የሚረዳ ጠቀሚ መሳሪያ ነዉ
- ወጪን በሚገባ ካወቅክ(ሽ) የስደት ጠቄሜታ የሚያስከትለዉ ጉዳት ምን እንደሆነና ወይም የቤተሰብ አባል በስደት ወደ ዉጪ በመሄድ መስራት የሚያዋጣ መሆኑን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ደረጃ ላይ ለመድረስ የሚያበቃ ነዉ
- ሰራተኛ በስደት ወደ ዉጪ አገር ወጥቶ ለመስራት የሚያስፈልግ ትክክለኛ ወጪ ለይቶ ማወቅ ከባድና አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑን አስታዉስ ቤተሰቦች አባሎቻቸዉ በተቻለ መጠን በስደት ወደዉጪ በመሄድ ለመስራት ትክክለኛ የሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ለማድረግ፣ ሂደቱ የሚየሰከትለዉን አሉታዊ ሁኔታ በትክክል ለመገምገም እንዲያስችላቸዉ ትክክለኛ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች ማለትም ለምሳሌ ከመንግስት ተቋማት፣ የፍልሰት የመረጃ ማዕከላት፣ከሰራተኛ ማህበራት ከስደት ተመላሾች መሰብሰብ ይችላሉ።
- ሰዎች ስለ ስደት የሚነግሩህን ሁሉ አትስማ ሰዎች ራሳቸዉን ለመከላከልብለዉ አንዳንዴ ስለሂደቱ ትክክል የሆነ ነገር ትተዉ እዉነተኛ ያልሆነ የተሳሳተና ዉሸትን ይናገራሉ ። ከአሉባልታ በተቃራኒ የአገር ቤትም ሆነ የዉጪ አገር ጎዳናዎች በወርቅ አይለበጡም። እንደሚታሰበዉ ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ አይደለም።

ማስታወሻዎች



ገንዘብህን በጥበብ ያዝ/ተጠቀም

FINANCIAL QUIZ EDUCATION

ለ1. ጊዜዉ የወር መጨረሻ ነዉ የወር ደመወዜን ተቀብያለዉ:

- ☐ **ሀ.** ከእዚህ በፊት ያየሁትን ቆንጆ ጃኬት ለመግዛት ቶሎ ብዬ በፍጥነት ወደ ገበያ እሄዳለሁ
- ☐ **ለ.** የተወሰነዉን ደመወዜን ለግቦቼ ማሳኪያ ለብቻ አሰቀምጣለዉ
- ☐ **ሐ.** ለጓደኛዬ ልደት ቀን በዓል ትልቅ ስጦታ እገዛለዉ

ለ2. ባጀት ማለት:

- ☐ **ሀ.** ገንዘባችንን ላቀድነዉ ግብ ማሳኪያ እንዲሆን የምንወስንበት፣የምናቅድበትና የምንጠቅምበት መሳሪያ ነዉ።
- ☐ **ለ.** ወጪአችንን የምንመዘግብበትና የምንዝበት
- ☐ **ሐ.** ሰንጠረዥ

ለ3. ሦስቱ የባጀት ዋና ክፍሎች ምን ምን ናቸዉ?

- ☐ **ሀ.** ቀን፣ ገቢ እና ወጪ
- ☐ **ለ.** ገቢ፣ ወጪ እና ቁጠባ
- ☐ **ሐ.** ወጪ፣ ገቢ እና ፊሪማ

ለ4. እንዴት አድርጌ ባጀቴን እከታተላለሁ?

- ☐ **ሀ.** ብዙ ኃለላፊነቶች ስላሉብኝ ባጀቴን በሚገባ ለመከታተል ያስቸግረኛል
- ☐ **ለ.** በዕድል ስለማምን ገቢዬን ባጀት አላደርግም
- ☐ **ሐ.** ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ገቢዬንና ወጪዬን እመዘግባለሁ

መልሶች: ሀ.1 ፡ ለ.2 ፡ ሐ.3 ፡ ሐ.4



1. በብልሃት ገንዘብን ተጠቀም!

ጥያቄዎች

- አንተ ገንዘብ የማዉጣት ወይም የመቆጠብ የምትወድ ነህ?
- ለምሳሌ የምትፈልገዉን ለማድረግ ተሰፋ ትቆርጣለህ?

ትርጉም


ቁጠባ ማለት ለወደፊቱ ልታሳካቸዉ ካሰበካቸዉ ግቦች ከንዲሆን ገንዘብህን በሙሉ ሳታጠፋ የተወሰነዉን የማለቀመጥ ሂደት ነዉ።

መልመጃ

የራስህን ሁኔታ ከግምት በማስገባት ማዉጣት አስፈላጊ የሆኑትን ወጪዎችን (በተለምዶ አስፈላጊ የሚባሉትን) እና በአማራጭነት ከሚወጡ ወጪዎች (በተለምዶ ፍላጎት የሚባሉትን) መካከል ምረጥ! ከምስሎቹ ዉስጥ አስፈላጊ የሆኑትን ከፍላጎት ወጪዎች በመለየት አክብብ።


የሥልጠና መርጃ ሉ1.1

የፍላጎት ስዕላዊ ካርዶች






የሎተሪ ትኬት




ሞተር ብስክሌት




የሳህን ምግብ



ጥሬ ገንዘብ ማውጫት



መኖሪያ / መጠለያ



ትምህርት ቤት



ስማርት ስልክ



ውሃ



ሲም ካርድ



የጤና ጥበቃ




መብራት




የለስላሳ ጣሳ



የሲኒማ ትኬት



አይስ ክሬም




ውድ የሆኑ ጫማዎች



ሲጋራ




ፍላት ስክሪን ቲቪ



ካሜራ



የድምፅ ስራዓት



የቆዳ መንከባከቢያ

ለኔ መግዛት እፈልገለሁ.....

ለእኔ አስፈላጊ የሆኑ?	ምን ያህል እንደሚያወጡ?
የአስፈላጊ ጠቅላላ ድምር	
እንዲኖረኝ የምፈልጋቸዉ?	**ምን ያህል እንደሚያወጡ?**
ጠቅላላ ፍላጎት	

ትኩረት ይደረግ!

ተጠንቀቅ! አንዳንድ ጊዜ ለአንዳንዶቹ አሰፈላጊ የሁኑት ለሌሎች ደግሞ እንዲኖራቸዉ የሚፈልጉት ይሆናሉ።

የዘረዘርኪቸዉን ነገሮች በሙሉ ለመግዛት በቂ ገንዘብ ይኖረኛል ወይ?

☐ አዎ ☐ አይደለም

በቂ ገንዘብ ከሌለኝ ልተዋቸዉ የሚወስንባቸዉ የሚከተሉት ናቸዉ::

ማስታወሻዎች

⚠ **አስፈላጊ:** **የተሻለ ሁኔታ ላይ ለመሆን ትሞክር ይሆናል አንዳንድ ሰዎች ይኼን ሁኔታ በጊዜያዊነት ትልቅ እንደሚሆን ይገልፃሉ ይህ በእዚህ ሁኔታ የሚቆየዉ ለጥቂት ጊዜ ነዉ። ተጠንቀቅ! ባጀትህ በቂና የማያወለዳ ከሆነ ጊዜ ወስደህ አስፈላጊ ከሆኑትና ሊኖርህ ከምትፈልጋቸዉ ለይተህ ማወቅ ይጠበቅብሃል ካልሆነ ግን ለምትፈልገዉ ጉዳይ ወደ ኃላ በቂ ገንዘብ ካጣህ ለከፍተኛ ጭንቀት ሊዳርግህ ይችላል።**

ከእዚህ በታች የተገለፁትን ተዋናዮችን ታሪክ ካነበብክ በኃላ ምን እንደደረሰባቸዉ አስተያየት ስጥ ምን የተለየ ነገር ማድረግ ነበረባቸዉ?

የግል ሁኔታ ጥናት 1

የዳዊት ቤተሰብ ድንገተኛ ችግር

ዳዊት ከስደት ከሳዑዲ አረቢያ የተመለሰዉ ከጥቂት ወራት በፊት ነበር። የሚኖረዉ ከቤተሰቡ ከአቶ ፍስሐ እና ከወይዘሮ ትዕግስት ጋር ነዉ። ዳዊት ለመተዳደሪያ የሚሆነው ስራ የለዉም። ጊዜዉን የቲ ሸርት መሸጫ ያለዉን ጓደኛውን በማገዝ ያሳልፋል አባቱ አቶ ፍስሐ ቤተሰቡን የማስተዳደር ኃላፊነት የወደቀዉ በእርሳቸው ጫንቃ ላይ ሲሆን ይኼን የሚፈፅሙት በፋብሪካ ዉስጥ በሚሰሩት ስራቸዉ ነዉ።




ባለፈዉ ሳምንት ወ/ሮ ትግስት በጤናቸዉ ላይ መጥፎ ስሜት ይሰማቸዉ ጀመር። በሚገባ ለመተንፈስ አልቻሉም በተጨማሪም ትኩሳት ነበራቸዉ ዳዊትና አባቱ አቶ ፍስሐ በሁኔታዉ በጣም ተጨነቁ እናም ለበሽታዉ የሚሆን መደሃኒት መግዛት አስፈለጋቸዉ። በመሆኑም እቤታቸዉ አቅራቢያ ከሚገኘዉ መድኃኒት መደብር ሄደዉ ለመግዛት ወሰኑ። የወሩ መጨረሻ በመሆኑ አቶ ፍስሐ ደመወዛቸዉን የሚቀበሉት የሚቀጥለዉ ሳምንት ነዉ ስለሆነም ዳዊት በቲ ሸርት መሸጫ ቤቱ ከሚረዳዉ ከጥሩ ጓደኛዉ ከኔድዮን ገንዘብ መበደር አሰፈላጊ ሆነ። ጌዲዮን ዳዊት በሱቁ ዉስጥ ስለሚረዳዉ ከሚሰጠዉ ወርዓዊ ድጎማ ዉስጥ 40 ብር አበደረዉ። ወር ሲደርስም አርባዉን ቀንሶ ቀሪዉን ሃምሳዉን እንደሚሰጠዉ ተስማሙ ዳዊትም የተበደረዉን ገንዘብ የተባለዉን መድኃንት ከመድኃኒት ቤት በመግዛት ተጠቀመበት ወ/ሮ ትግስትም መድኃኒቱን ከወሰዱ በኃላ ከህመማቸዉ ቶሎ ተፈወሱ።

የግል ሁኔታ ጥናት 2

የገመቹ ጊደኛ የአያንቱ ችግር

ገመቹና እና ጫልቱ ከጎረቤቶቻቸዉ ከአያንቱና ከባይሳ ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸዉ። አያንቱ መኖሪያቸዉ አቅራቢያ ካለዉ መንገድ አጠገብ ትንሽ የፀጉር ማስዋቢያ ቤት አላት። የፀጉር ቤት ሥራዋ ዉጤታማ መሆን የጀመረዉ ዘግይቶ ነዉ ።ገንዘብ አያያዝ ሰርዓትን በሚገባ በመማሯ በብዛት ትርፍ ማግኘት የጀመረችዉ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ነዉ። የፋይናንስ ተቋሞችን ስለማታዉቅ አብዛኛዉን ጊዜ የሚታገኘዉን ገቢ ባሏ ባይሳ ባንክ ቤት እንዲያስገባ ትሰጠዋለች። አንድ ቀን ከስራ በምትመለስበት ጊዜ ለፀጉር ቤቷ የሚያስፈልጋትን ዕቃ ለመግዛት ገንዘብ እንዲሰጣት ባይሳን አሰበች። ሆኖም ቤት ሰትደርስ ባሏ በገንዘቡ አሮጌ መኪና እንደገዛበት ደረሰችበት። ገንዘቡን ስትጠይቀዉም ገንዘቡን ለምትለዉ ዕቃ መግዣ ለመጠቀም እንደማትችል ነገራት። አያንቱም በሁኔታዉ እጅግ በመናደድ በአካዉንታቸዉ ዉስጥ ያለዉን ገንዘብ መጠን በማረጋገጥ ገንዘብ ለማዉጣት ቀጥታ ወደ ባንክ ቤት ሄደች፡ ፡ እዚያም ስትደርስ አከዉንቱ ያለዉ በባሏ ስም እንጂ በእርሷ እንዳልሆነና የተረፈችዉን ገንዘብ እንኳን ለማዉጣት እንደማትችል አረጋገጠች፡ ፡ በመሆኑም በጉዳዩ እጅግ አዘነች።



ለመቆጠብ የሚረዱ ጥቂት ነጥቦች

- በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ የተወሰነ ገንዘብ ለብቻዉ አስቀምጥ
- ዕቃዎች የሚሰበሩ ወይም ተሰብረዉም ከሆነ ለመጠገን የሚቻል ከሆነ አዲስ ዕቃ አትግዛ
- ትንሽ የሆነ ስጦታ ለቤተሰቦችህ ግዛ ስለእገዛህና እርዳታህ ቀድመህ ከእነርሱ ጋር ተነጋገር
- ከተቻለ ለበዓልና ማህበራዊ ዝግጅቶች ብዙ ወጪ አለማዉጣት
- በገንዘብ ቦርሳችን ዉስጥ ብዙ ገንዘብ አለመያዝ (ገንዘብ ሰዉ የማያይበት የተደበቀ ቦታ ወይም ባንክ ቤት ማስቀመጥ)
- ገንዘብ ለቤተሰቦችህ ወይም ለዘመዶችህ የምትልክ ከሆነ ያለህን በሙሉ አትላክላቸዉ ለድንገተኛና ለሚያስፈለግህ ጉዳይ የሚሆን ገንዘብ አስቀር
- ለምን እንደምትቆጥብ እንድታስታዉስ ሁልጊዜ ግቦችህ አስብ

ቁልፍ መልዕክቶች

- ገንዘብ የግድ እንዲወጣባቸዉ የሚያስፈልጋቸዉና በ አማራጭነት ሊያዙ የሚችሉትን መለየት መቻል ያስፈልጋል
- ለድንገተኛ ጉዳይ መቆጠብ በጣም አስፈላጊ ነዉ
- ከሌሎች በገቢነት የተገኘን ገንዘብን በሚገባ መያዝ
- ቁጠባ ማለት የጊዜዉን ፍላጎታችንን በመተዉ ወደፊት እንደርስበታለን ብለን ላስቀመጥነዉ ግብ መሳካት መስራት ነዉ
- ቁጠባ ሙሉ ደህንነት እንዲሰማን ያደርጋል

ማስታወሻዎች


2. በጀትና ማዘጋጀት

የሥልጠና መርጃ ሉ.2.1

የባጀት ምስሎች


(የማንበብና መፃፍ ከሀሎታቸዉ ዝቅ ላለ)











































የሥልጠና መርጃ ሉ.2.2
የተዋንያን ባዶ ባጀት




ስለ ወርቅነሽ ሁኔታና እንዴት ባጀቷን እንደምታዘጋጅ የበለጠ እንወቅ

የወርቅነሽ ቤተሰብ ባጀት

የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
የወርቅነሽ ለቤተሰቧ ገቢ አስተዋጽዖ	
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	
የተለያየ ገቢ	
ከግንባታ ስራ የሚገኝ የከበደ ገቢ	
የአሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ ሽያጭ	
የተለያየ ገቢ ድምር	
ድምር ገቢ	

ወጪዎች	
አስፈላጊ ወጪዎች	
ምግብ	
የተንቀሳቃሽ ስልክ /ሞባይል ካርድ	
ለህክምና አገልግሎት	
ዉሃና መብራት	
ትራንስፖርት	
የቤት ኪራይ	
የአስፈለጊ ወጪ ንዑስ ድምር	
የአማራጭ ወጪዎች	
ምስል ለመስራት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች	
ለወደ ደብረብርሃን ጉዞ	
የአማራጭ (ፍላጎት) ንዑስ ድምር	
የገቢ ወጪዎች	
አጠቃላይ ድምር	





የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.3

የወርቅነሽ ቤተሰብ ባጀት - ክፍል 1

ትናትና የወሩ የመጨረሻ ቀን ነበር። ወርቅነሽና ከበደ ገቢያቸዉን እንደገና ለማየት ወሰኑ በመጀመሪያም የወርቅነሽን የግል ገቢና ወጪ በሚገባ ማጤን ጀመሩ ሁልጊዜም ሳታቋርጥ ለእጅ ስራዋ የሚሆን ገንዘብ ለብቻ ታስቀምጣለች። በመጨረሻም የተጣራ የወር ገቢዋ 8000 ብር እንደሆነ በማስላት ደረሱበት። እንዳለፈዉ ወር ሁሉ ወርቅነሽ ከወር ገቢዋ 6000 ለቤተሰቧ የተቀረዉን 2000 ደግሞ ለራሷ ባጀት ለማዋል ወሰነች።


የከበደ ከቀን የግንባታ ስራ ገቢዉ 4500 ብር ነዉ። በተጨማሪ ከበደ በትርፍ ሰዓቱ የጠገነዉን አሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ በተጨማሪነት ለጎሬበታቸዉ በ500 ብር ሸጡ።

የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.4

የወርቅነሽ ቤተሰብ ባጀት - ክፍል 2

ወርቅነሽና ከበደ የሚቀጥለዉ ወር ገቢያቸዉን ካሰሉ በኃላ እንዴት ወጪዎቻቸዉን እንደሚቆጣጠሩ ዕቅድ ነደፉ። በመጀመሪያ 3500 ብር ለቤታቸዉ ኪራይ ይከፍላሉ፣ ለዉሃና ለመብራት ደግሞ 150 ብር ያወጣሉ፣ ለትራንሰፖርት 750 ለጤና/ ህክምና 100 ባጀት ይዘዋል። የቅድሚያ ክፍያ ተንቀሳቃሽ ስልካቸዉ 100ብር ያስወጣቸዋል የአለማየሁ የህጻን አልጋ ለማሰራት 1000 ብር ይጠይቃል። በመጨረሻም በወሰኑት መሰረት የከበደን ቤተሰብ ደብረብርሃን ሄዶ ለመጠየቅ 500 ብር ወጪ ያስወጣቸዋል።

ወርቅነሽ ከገቢዋ የተወሰነዉን ለብቻ ታስቀምጣለች፡ ከእዚህም ዉስጥ የተወሰነዉን ለራሷ ወጪ ሌላዉን ደግሞ ለጥልፍ ስራዋ ታዉላለች። በእዚህ ወር የራሷን ወጪ፣ ለሚቀጥለዉ ወር 400 ብር ለሜሞሪ ካርድ እና አዲስ ቀሚስ ለመግዛት እንደሚታወጣ በማስላት አቅዳለች።



የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
ወርቅነሽለቤተሰብ የሚታደርገዉ ድጋፍ	ብር 6000
ድርሻ	
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	**ብር 6000**
ተለዋዋጭ ገቢ	
ከበደ ከግንባታ ስራዉ የሚያገኘዉ ገቢ	ብር 4500
የኮሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ ሽያጭ	ብር 500
የተለዋዋጭ ገቢ ንዑስ ድምር	**ብር 5000**
ጠቅላላ ገቢ	**ብር 11000**
ወጪዎች	
አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች	
ምግብ	ብር 3500
የሞባይል ካርዮ	ብር100
ጤና/ህክምና	ብር 100
መብራትና ዉሃ	ብር 150
ትራንስፖርት	
የቤት ኪራይ	ብር 750
የአስፈላጊ ወጪዎች ንዑስ ድምር	ብር 3500
አማራጭ ወጪዎች	**ብር 8100**
ለህጻን አልጋመሰሪያ የሚያስለግሉ ዕቃዎች	
ለደብረብርሃን ጉዞ	ብር 1000
የአማራጭ ወጪዎች ንዑስ ድምር	ብር 500
ጠቅላላ ወጪ ድምር	**ብር 1500**
ከወጪ ቀሪ ገቢ	**ብር 9600**



የሥልጠና መርጃ ሉ.2.3

የቤተሰብ ባጀት ሁኔታ

የወርቅነሽ ቤተሰብ ባጀት

የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
ወርቅነሽ ለቤተሰብ የሚታደርገዉ ድጋፍ ድርሻ	ብር 6, 000
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	**ብር 6, 000**
የተለያየ ገቢ	
ከበደ ከግንባታ ስራዉ የሚያገኘዉ ገቢ	ብር 4,500
የአሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ ሽያጭ	ብር 500
የተለያየ ገቢ ንዑስ ድምር	**ብር 5,000**
ጠቅላላ ገቢ	**ብር 11,000**

ወጪዎች	
አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች	
ምግብ	ብር 3,500
የሞባይል ካርድ	ብር 100
ጤና/ህክምና	ብር 100
መብራትና ዉሃ	ብር 150
ትራንስፖርት	ብር 750
የቤት ኪራይ	ብር 3,500
የአስፈላጊ ወጪዎች ንዑስ ድምር	**ብር 8,100**
አማራጭ ወጪዎች	
ለህጻን አልጋመስሪያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች	ብር 1000
ለደብረብርሃን ጉዞ	ብር 500
የአማራጭ ወጪዎች ንዑስ ድምር	**ብር 1,500**
ጠቅላላ ወጪ ድምር	**ብር 9,600**

ከወጪ ቀሪ ገቢ	**ብር 1,400**

የሥልጠና መርጃ ሉ.2.4

የተዋናይ የግል ባጀት ሁኔታ



የወርቅነሽ የግል ባጀት ሁኔታ

የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
ከጊዜያዊ የሆቴል የጽዳት ስራዋ የምታገኘዉ ገቢ	ብር 5000
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	**ብር 5000**
የተለያየ ገቢ	
ከእጅ ጥልፍ ሰራ የምታገኘዉ	ብር 3000
የተለያየ ገቢ ንዑስ ገቢ	**ብር 3000**

ጠቅላላ ድምር	
ወጪዎች	
አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች	
ለቤተሰብ በጀት የሚደረግ መዋጮ	ETB 6, 000
	ETB 400
የአስፈላጊ ወጪዎች ንዑስ ድምር	**ETB 6,400**
አማራጭ ወጪዎች	
አዲስ ቀሚስ	ETB 100
የአማራጭ ወጪዎች	**ETB 100**
ጠቅላላ ወጪ ድምር	**ETB 6,500**

ከወጪ ቀሪ ገቢ	**ETB 1, 500**

ጥያቄዎች

- **ባጀት አዘጋጅተሃል ወይ?**
  ☐ አዎ ☐ አይደለም

- **ካጋዘጀህ በፅሁፍ ነዉ ነወ ወይስ በአእምሮህ የምታስታዉሰዉ ነዉ?**
  ☐ በፅሁፍ የተዘጋጀ ☐ በአእምሮህ የምታስታውስ

ትርጉም

ባጀት ማለት የገንዘብ አጠቃቀምን ለዓላማ ማሳኪያ አንዲሆን ለመወሰንና ለማቀድ የሚያገለግል መሳሪያ ነዉ::

⚠ **አስፈላጊ** **ጥሩ ሁኔታ ላይ ካልሆንክ ወይም ትንሽ ሀዘን ካለብህ ባጀት ማዘጋጀት አሰልቺና ብዙ ጊዜ ትኩረት የሚጠይቅ ይሆናል። ምን እንደሚሰማህ ለምትወዳቸዉና ለሚቀረቡህ ያለህበትን ሁኔታ በመንገርና አስፈላጊ የሆነ እገዛ በመጠየቅ የበጀት ዝግጅት ስራህን ቀስ በቀስ አከናዉን ። ራስህ ላይ ጫና አታብዛ!**

መልመጃ

በስልጠናዉ ወቅት ወርቅነሽና ቤተሰቧ እንዴት አድርገዉ ባጀታቸዉን እንደሚያዘጋጁ አይተሃል አሁን የአንተ ተራ ነዉ! የራስህን ባጀት አዘጋጅ!

ጥንቃቄ አድርግ ከሰንጠረዡ በታች ያለዉ ከገቢ ላይ ወጪ ተቀንሶ ዉጤት ከዜሮ በታች መሆን የለበትም። ከሆነ ግን በቂ የሆነ ገቢና ለምታወጣዉ ወጪ ገንዘብ አይኖርህም ማለት ነዉ። በተጨማሪም ለዓላማህ ማሳኪያ የሚሆን የምትቆጥበዉ ገንዘብ የለህም ።

በጥቂት ወራት ዉስጥ ከፍተኛ ወጪ ይኖርብኛል ብለህ የምትገምት ከሆነ ወጪዉን ለመቋቋምና ከባጀት ዉጭ እንዳትሆን በተቻለ መጠን የተወሰነ ገንዘብ ቆጥብ።



የሥልጠና መርጃ ሉ.2.5

የእኔ ባጀት

የእኔ ባጀት

የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	
የተለያየ ገቢ	
የተለያየ ገቢንዑስ ድምር	
ጠቅላላ ገቢ ድምር	

ወጪዎች	
አሰፈላጊ የሆኑ ወጪዎች	
የኤሌትሪክ ሀይል እና ውሃ	
ምግብ	
ትራንስፖርት	
የጤና እንክብካቤ /ህክምና	
ግንኙነት (የስልክ መስመር ክፍያ እና የኢንተርኔት መስመር ክፍያ)	
ብድር መክፈል	
ኪራይ	
የአስፈላጊ ወጪ ንዑስ ድምር	
የአማራጭ ወጪዎች (የፍላጎት)	
የአማራጭ ወጪዎች ንዑስ ድምር	
የአጠቃላይ ወጪ ድምር	

ገቢ - ወጪ	

ከወርቅነሽ ሁኔታ ጋር እንቀጥል



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.5

የወርቅነሽ ቤተሰብ ባጀት - ክፍል 3

ወርቅነሽና ከበደ የተወሰነ ጉዳይ አጋጥሟቸዋል ባጀታቸዉን በጥንቃቄ ቢያቅዱም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በገንዘብ አቅማቸዉ ላይ ችግር ፈጥሯል። ሆቴሉም በመንግስት መመሪያ ምክንያት ለጥቂት ጊዜ ይዘጋል ።ወርቅነሽም በአገሪቱ በታወጀዉ ስራ መዝጋት ምክንያት የጌጣ ጌጥ ስራ ዉጤቶችን ለመሸጥ አልቻለችም። በእዚህ የተነሳ ለቤተሰብ ባጀት የምታዋጣዉን 6000 ብር በመቀነስ አቅሟ የሚፈቅደዉ 4000 ብር ብቻ ማዋጣት ነዉ ።ከእዚህ በላይ ጎሬቤቷ የገዛዉን ዕቃ አልፈልግም በማለት በመወሰኑ ምክንያት የሸጠችበትን 500 ብር መመለስ ይኖርባታል።

በወጪ ደረጃ ብዙ ጊዜ ቤት ዉስጥ መቆየት በመጀመራቸዉ የዉሃና የመብራት ወጪአቸዉ ቀድሞ ለመክፈል ካቀዱት 150 ብር ወደ 200 ጨምሯል።

ማስታወሻዎች



የሥልጠና መርጃ ሉ 2.6

የተሰተካከለ በጀት ባህሪዎቹ

የወርቅነሽ ቤተሰብ በጀት

የገቢ ምንጭ	መጠን
ቋሚ ገቢ	
ወርቅነሽ ከገቢዋ ለቤተሰብዎ መዋጮ	ETB 4,000
የቋሚ ገቢ ንዑስ ድምር	**ETB 4, 000**
የተለያየ ገቢ	
ከበደ ከግንባታ ስራ የሚያገኘው ገቢ	ETB 4,500
የተለያየ የገቢ ንዑስ ድምር	**ETB 4,500**
ጠቅላላ ገቢ	**ETB 8,500**


ወጪዎች	
አስፈላጊ ወጪዎች (መሰረታዊ ፍላጎቶች)	
ምግብ	ETB 3,500
የሞባይል ካርድ	ETB 100
ለጤና አግልግሎት	ETB 100
ለመብራትና ውሃ	ETB 200
ለትራንስፖርት	ETB 750
ለቤት ኪራይ	ETB 3,500
ለመሰረታዊ ፍላጎት ንዑስ ድምር	
አማራጭ ወጪዎች /ለፍላጎት/	**ETB 8,150**
ለህጻን አልጋ መስሪያ ቁሳቁሶች	ETB 1000
ለደበረብርሃን ጉዞ	ETB 500
ንዑስ ድምር /ፍላጎት/	**ETB 1,500**
ጠቅላላ ወጪ	**ETB 9,650**

ገቢ - ወጪ	**ETB 1,150**

ቁልፍ/ጠቃሚ መልዕክት

- ገቢዎትን ለማሰተዳደር የሚያገለግል መሳሪያ አለ። በጀት።
- በጀትዎን ለማዘጋጀት ገቢዎን እና ወጪዎን ማስላት ያስፈልጋል። በስሌቱ በየወሩ ሊያስቀምጡ የሚችሉትን ሊወስኑ ያስችላል።
- በድንገተኛ ሁኔታ ወይም የገንዘብ ሁኔታዎ ሲለወጥ ያለበዎትን ወጪ ለመሸፈን እና ለሚያስቡት ግብ ለማስቀመጥ ባጀትዎን ማሰተካከል አለብዎት።
- ባጀት ወደ ግብዎ ለመድረስ የሚያወጡትን ወጪ እና የሚያሰቀምጡትን ገንዘብ ለመወሰን ይረዳዎታል።

3. በበጀት መወሰንና በጀትን መመዝገብ




የግል ታሪክ ጥናት ቁጥር 6

የወርቅነሽ ቤት አስተዳደር

ወርቅነሽና ከበደ ብዙ ዕቅድ አላቸው። እቅዳቸውን ለማሳከት በተቻለ መጠን መቆጠብ አስፈልጓቸዋል።ወርቅነሽ ትላንትና ብዙ ግዜ ለስራ ከሚጓዝዝ ወንድሟ አባየነህ የስልክ ጥሪ ደርሷታል፡ ፡ አባይነህ በመንገድ ላይ አደጋ ስላጋጠመው እና ለህክምና የሚከፍለው ገንዘብ ስለሌለው ገንዘብ እንድትልክለት ጠየቃት። ወርቅነሽ በጣም ተጨንቃ ወንድሟ የጠየቃትን ገንዝብ ላከች።

ከሰዓት በኋላ ወርቅነሽ ከከበደ ጋር ስለወንድሟ ሁኔታ አወሩ። ባጀታቸውን አጢነውት/ገምግመው ተመጣጣኝ በጀት እንደሌላቸውና ሌላ ወጪ ማውጣት እንደማይችሉ ተረዱ።

ወደ ደብረብርሃን የሚያደርጉት ጉዞን ወደ ሌላ ጊዜ ለማዛወር እና ለምግብና መጓጓዣ በተቻለ መጠን ለመቆጠብ ተነጋግረው ወሰኑ።





የግል ታሪክ ጥናት ቁጥር 7

የገመቹ በጀት አስተዳደር



ባለፈው ወር ገመቹ ወጪው ብዙ መሆኑን አውቆ ሁል ጊዜ ወጪዎቹን መከታተል እንዳለበት ተረድቷል። ትላንትና ጎሮቤቱ ባይሳ ለኤሌክትሪክ ክፍያ ለመክፈል ገንዘብ ስሌለው ገንዘብ እንዲያበድረው ጠይቆታል። ካለው በጀት ትርፍ የሆነ ገንዘብ ስለሌለው ብድሩን ለመስጠት ወላውሏል። ነገሩን ሲያስበው ከሳውዲ አረቢያ እንደተመለሰ ጎረቤቱ ባይሳ ብዙ ጊዜ ረድቶታል። ስለዚህ ገነዘቡን ሊያበድረው ወሰነ። ከሳምንት በኋላ የገመቹ አባት ታመው ውድ መድሃኒት አስፈለጋቸው። ገመቹ ለመደሃኒት መግዣ የሚሆን በቂ ገንዘብ የለውም። ባይሳ የተበደረውን ገንዘብ እሰካሁን አልመለሰለትም። ገመቹ ኢ መደበኛ ከሆነ ገንዘብ አበዳሪ ገንዘብ መበደር አለበት።

ጥያቄዎች

- ወርቅነሽ በበጀቷ ለመወሰን ምን ማደረግ አለባት?
- በጀት ለመወሰን እርግጠኛ ለመሆን ብዙ መንገዶች አሉ።ብዙ ሰዎች እንደ ሞባይል መተገበሪያ ሂሳብ የመመዘገቢያ ሰንጠረዥ እንደወርቅነሽ ይጠቀማሉ።

በበጀት የምንወሰንባቸውን መንገዶች እሰቲ እንወቃቸው።

⚠ **ጠቃሚ: ነገሮች ጥሩ በማይሆኑበት ጊዜ ጥሩ የአእምሮ ጤንነትን ለመጠበቅ የዕለት ተዕለት ተግባራት ማከናወን ጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በጀትዎን ተከታትሎ መመዘገብ በበጀት ለመወሰን ትኩረት ማድረግ እና እንዴት እየሰሩ እንዳሉ ለመፈተሽ ጥሩ ልምምድ ሊሆን ይችላል።**

ማስታወሻዎች

የሥልጠና መርጃ ሉ.3.1

የገቢ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ

ገቢ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ

ስም _____

ወር _____

ዓመት

ቀን	የገቢ ምንጭ ርዕስ	የገቢ መጠን

የሥልጠና መርጃ ሉ 3.2

የወጪ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ

የወጪ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ

ስም _____


ወር _____

ዓመት

ቀን	የወጪ ዓይነት ርዕስ	የወጣ መጠን	የታቀደ ወይም ያልታቀደ	
			አዎ	አይደለም
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐

ጠቅላላ ወጪ	
ጠቅላላ ገቢ	
ቁጠባ (=ገቢ - ወጪ)	

በበጀት ለመወሰን ጠቃሚ ምክሮች



- ሁልጊዜ ምን ያህል ለማውጣት እናዳቀድክ አሰታውስ።
- ለአልታሰቡ የወጪ ፍላጎቶች በጀት ውስጥ አካት።
- ገንዘብዎን በቀላሉ ሊያጠፉት እንዳይችሉ የማይደረስበት ቦታ ይቆጥቡ ።
- ያወጡትን ወጪ ምን እንደሆነ ይመዝግቡ።
- ከበጀት በላይ ወጪ አለማውጣትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
- በአንድ ነገር ላይ ብዙ ወጪ ካወጡ በሌላው ላይ ትንሽ ወጪ ያውጡ።
- ያቀዱትን ወጪ ለመቀነስ ዝርዝር ያዘጋጁ።
- በበጀት ለመወሰን በጀትዎን ሲያዘጋጁ ቤተሰብዎ እንዲሳተፍ ያድርጉ።



የሥልጠና መርጃ ሉ3.3

የወርቅነሽ ቤተሰብ የግብይት ካርዶች

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 1 ቀን ወርቅነሽ ለቤተሰብ በጀት 6000 ብር አዋጥታለች

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 1 ቀን ከበደ 4500 ብር ከግንባታ ካገኘው ገቢ አዋጥቷል።



የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 1 ቀን
150 የኢትዮጵያ ብር
ከፍለዋል

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 1 ቀን 3500 የኢትዮጵያ ብር
ለወር የሚሆናቸውን የምግብ ወጪ
በፖስታ አስቀምጠዋል

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 2 ቀን 700 የኢትዮጵያ ብር
ለትራንስፖርት በፖስታ አስቀምጠዋል።

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 10 ቀን 3500 ብር
ለኪራይ ከፍለዋል።

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 12 ቀን 100 የኢትዮጵያ ብር ለህክምና
ለብቻ አስቀምጠዋል።

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 15 ቀን ለአለማየሁ የህጻን አልጋ
ለማሰራት 1000 ብር አውጥተዋል።

የወርቅነሽ ቤተሰብ

የካቲት 15 ቀን የወርቅነሽ ቤተሰብ ፍሪጅ
ለማሰጠገን 500 ብር ያስፈልጋቸዋል



መልመጃ

ከላይ ያሉት ሁለቱን የገቢና የወጪ መመዝገቢያ ሰንጠረዦች መጠቀም ችላላችሁ። በወርቅነሽና በበቤተሰባ ምን እያተካሄደ እንደሆነ እስቲ እናረጋግጥ

የገቢ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ


ስም: የወርቅነሽ ቤተሰብ
ወር: የካቲት
ዓመት: 2022

ቀን	የገቢ ምንጭ ስም/ርዕስ	የገቢ መጠን
1.2.22	የወርቅነሽ መዋጮ	ብር 6,000
1.2.22	የከበዳ መዋጮ	ብር 4,500
ጠቅላላ ገቢ		ብር10,500

የወጪ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ


ስም: የወርቅነሽ ቤተሰብ
ወር: የካቲት
ዓመት: 2022

ቀን	የወጪ ዓይነት ስም/ርዕስ	የወጪ መጠን	የታቀደ ወይም ያልታቀደ	
			አዎ	አይደለም
1.2.22	መብራትና ውሃ	ብር150	☒	☐
1.2.22	የምግብ ወጪ	ብር 3.500	☒	☐
2.2.22	የትራንስፖርት /የመንገዝ	ብር 700	☒	☐
10.2.22	ካራዎ	ብር3,500	☒	☐
12.2.22	ለህክምና ኣግልግሎት	ብር 100	☒	☐
15.2.22	የህጻን ኣልጋ ማሰሪያ	ብር1,000	☒	☐
15.2.22	ለፍሪጅ ጥገና	ብር 500	☐	☒
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
ጠቅላላ ወጪ		ብር 9,450		
ጠቅላላ ገቢ		ብር 10,500		
ቁጣባ (= ገቢ - ወጪ)		ብር1,050		



አሁን የእርስዎ ተራ ነው።።

የገቢና የውጪ መመዝገቢያ ሰንጠረዦችና ጠቃሚ ሰነዶች ከዚህ የማሰተማሪያ መጻፍ መጨረሻ ላይ ተያይዞ ያገኙታል። የራስዎትን ገቢና ወጪ ለመመዘግብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።።



ቁልፍ መልዕክቶች

- ሁልጊዜ ምንያህል ለማውጣት ያቀዱትን ያስታውሱ።።
- ላልተጠበቀ ወጪ ፍላጎት የሚሆን በበጀት ውስጥ ማካተት
- በበጀት ለመወሰን በበጀት ዝግጅት ወቅት ቤተሰብን ማሳተፍ
- ጠቅላላ ገቢን ማወቅ አሰፈላጊ ነው። ምን ያህል ጠቅላላ ገቢ እንደሚያገኙ ማወቅ ገንዘብዎን ለመቆጣጠር አስፈላጊ እርምጃ እና ለወጪዎች አስቀድመው እንዲያቅዱ ያስችልዎታል። ጠቅላላ ወጪዎን ማወቅ በጀትዎን ለመቆጣጠር አስፈላጊ ነዉ ። ካሰቡት በላይ ተጨማሪ ወጪ እንዳወጡ ሲመለከቱ ወጪዎችዎን ማስተካከል ይችላሉ።

⚠ **ይጠንቀቁ ! መደበኛ ያልሆነ ገቢ ካለዎት ማለትም በየወሩ የተለየ መጠን የሚያገኙ ከሆነ አማካይ ገቢዎትን ተጠቅመው ባጀትዎን ማዘጋጀትና አነስተኛ ገቢ ያገኙበትን ጊዜ ለማመጣጠን ተጨማሪ ገቢ ሲያገኙ መቆጠብ ይችላሉ።**

4. የሂሳብ መዝግብዎን ይያዙ



የግል ሁኔታ ታሪክ ቁጥር 8

ትርሃስ የተወሰኑ ደረሰኞችን መጣል

ትርሃስ ሰፈሯ ካለ ሱቅ በዱቤ ትገዛለች። ባለሱቁ ሁሌ ግዢ ስትፈጽም የገዛችውን ዕቃ በመዝገቡ እየመዘገበ ያወጣችውን ወጪእንድታውቅና እንድትከታተል ደረሰኝ ይሰጣት ነበር። ትርሃስ በገንዘብ ጉዳይ ዝንጉ ስለሆነች ደረሰኞቹን መያዙን ትኩረት አልሰጠችውም። ይልቅ በባለሱቁ ላይ እምነት አሳድራለች። በወሩ መጀመሪያ አንድ ቀን ያለባትን እዳ ለመክፍል ስለፈለገች ባለሱቁን ምን ያህል እዳ እንዳለባት ጠየቀችው። ባለሱቁ 1150 ብር እንዳለበት ሲነግራት እሷ ካሰበችው የ150 ብር ብልጫ እንዳለው አወቀች። ለባለሱቁ የሆነ ስህተት መኖሩን ገለጸች። ባለሱቁም ምንም ስህተት እንዳልተፈጠረ እና ከፈለገችም እቃውን ስትወስድ የመዘገበበትን ዝርዝር እንደሚያሳያትና ለዚህም ማረጋገጫ ደረሰኝ እንደሰጣትና ያለባትን ጠቅላላ ዕዳ እንድትከፍል ጠየቃ።ትህራስም ደረሰኞቹን ባለማስቀመጧ በጣም ተበሳጨች።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁጥር 9

ዳዊት የሂሳብ መረጃ አያያዝ

ዳዊት እና ቤተሰቡ ለቤታቸው የመብራት ክፍያ ለመክፈል ዳዊት በወሩ መጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ይሄዳል። አንድ ቀን በጓደኛው ጌዲዮን ቲሸርት ሱቅ ውስጥ እየሠራ እያለ እናቱ የመብራት አገልግሎት ስለተቋረጠ ጠራችው። እሱም በጣም ተናዶ ቅሬታ ለማቅረብ ወደ ኩባንያው ቢሮ ይሄዳል። መብራት ኃይል ያለው ሰራተኛ የሁለት ወር የመብራት አገልግሎት ክፍያ እንዳልከፈሉ ነገረው። እሱ ግን እንደከፈሉ እርግጠኛ ነበር። የመብራት ኃይል ሠራተኛውም ሁኔታውን ለመገምግም ተከፍሏል የሚል ማህተም ያረፈበትን ደረሰኝ እንዲያቀርብ ዳዊትን ጠየቀው። ዳዊት ወደ ቤት ተመልሶ የሂሳብ መዝገቦችን፣ ደረሰኞችን እና ጠቃሚ ሰነዶነችን በሚያስቀምጥበት ሳጥን ውስጥ ፈለገ። በሳጥን ውስጥ ተከፍሏል ተብሎ ማህተም የተመታበትን ክፍያ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ አገኘ። ደረሰኙን ይዞ ወደ መብራት ኃይል ተመልሶ ለመብራት ኃይል ሰራተኛው አቀረበ። ኩባንያው የመብራት አገልግሎቱን እንደገና እንዲያገኙ አደረገ። ዳዊትም ደረሰኙን በማሰቀመጡና ለዚህ ዓይነት ጊዜ ስለጠቀመው በጣም ተደሰተ።

⚠ **ጠቃሚ:** ብዙ ጭንቀቶች ካሉዎት የባንክ ደብተርዎን፣ ዲጂታል የኪስ ቦርሳ መለያዎን መፈተሽ ወይም ወጪዎን መገምገም ለበለጠ ጭንቀት እና ምቾት ማጣት ይዳርጎታል። ነገር ግን ያስታውሱ፡ ነገሮችን ችላ ማለት ወይም ስለ ገንዘብ አለማሰብ ወደፊት ነገሮችን ሊያባብስ ይችላል።

የሥልጠና መርጃ ሉ.ፋ.1

የገቢ መከታተያ ቅፅ

የኔ የገቢ መከታተያ ቅፅ

ስም: _____

ወር: _____

ዓመት:

ቀን	የገቢ ምንጭ መግለጫ	የገቢ መጠን
ጠ ቅ ላ ላ ገ ቢ		

የሥልጠና መርጃ ሉ.ፋ.2
የወጪ መከታተያ ቅፅ

የኔ የወጪ መከታተያ ቅፅ

ስም: _____

ወር: _____

ዓመት:

ቀን	የወጪ ዓይነት ስም/ርዕስ	የወጪ መጠን	የታቀደ ወይም ያልታቀደ	
			አዎ	አይደለም
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐
			☐	☐

ጠቅላላ ወጪዎች	
ጠቅላላ ገቢ	
ቁጠባዎች (= ገቢ – ወጪዎች)	



የቁጠባ ዘዴዎችንና አገልግሎቶችን ይወቁ

FINANCIAL EDUCATION QUIZ

ሐ1. በእርስዎ አመለካከት የተሻለ የቁጠባ ዘዴ/ መንገድ ምንድን ነው?

- ☐ ሀ. የበለጠ አመቺ ስለሆነ ገንዘቤን እቤቴ አስቀምጣለሁ።
- ☐ ለ. የበለጠ አስተማማኝ ስለሆነ ገንዘቤን ባንክ አስቀምጣለሁ።
- ☐ ሐ. እዚያ ብዙ ጓደኞች ስላሉኝ ገንዘቤን በማዟዟር አስቀምጣለሁ።
- ☐ መ. እያንዳንዱ ዘዴ የራሱ ጥቅምና ጉዳት አለው። ለእኔ ፍላጎቶች የበለጠ ትክክል የሆነውን ዘዴ ከመምረጤ በፊት በጥንቃቄ ገምግሜዋለሁ።

ሐ2. በጥቂት ዓመታት ውስጥ ንግድህን ለመጀመር ትፈልጋለህ። ላንተ የበለጠ ትክክል የሆነው የቁጠባ ሂሳብ የትኛው ነው/ምንድን ነው?

- ☐ ሀ. መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ፣
- ☐ ለ. የኮንትራት ቁጠባ ሂሳብ፣
- ☐ ሐ. የጊዜ ተቀማጭ ሂሳብ፣

ሐ3. የቁጠባ ዘዴዎችን በሚመርጡበት ጊዜ ከመስፈርቶቹ አንዱ የሆነውን ደህንነትን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።

- ☐ ሀ. ዕውነት
- ☐ ለ. ሀሰት

መልሶች፡ ሀ፣ ሐ፣ ሀ፣ ሀ



1. የቁጠባ ዘዴዎችን ይምረጡ!


አሁን እርስዎ የግል በጀትዎን አዘጋጅተዋል (ወይም የቤተሰብዎን በጀት) ፣ በየወሩ ምን ያህል መቆጠብ እንዳለብዎትና ለእያንዳንዱ ግብዎ ምን ያህል መቆጠብ እንዳለብዎት አውቀዋል።

የሥልጠና መርጃ ሐ.1.1

የቁጠባ ዘዴዎች



ወርቅነሽ የአካባቢው ባንክ ደንበኛ ናቸው። የቁጠባቸውን አብዛኛውን ክፍል ከቤታቸው አጠገብ ካለው ባንክ ማስቀመጥን ይመርጣሉ።



ገመቹ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋም ደንበኛ ሲሆን በየወሩ አነስተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ይቆጥባል።



ዳዊት የዕቁብ ቁጠባ አባል ሲሆን እዝያው መቆጠብ ይወዳል ምክንያቱም ከቡድኑ ውስጥ የእሱ ተራ ሲሆን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ያገኛል። ሣዑዲ አረቢያ ውስጥ ለሚያጋጥመው ድንገተኛ ወጪ ለመጠቀም አቅዷል።



ትርሃስ ደግሞ እቤትዋ ውስጥ አልጋዋ ስር ታስቀምጣለች።

ጥያቄዎች

- ከላይ የተገለፁት ባሕርያት ምን ዓይነት የቁጠባ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል?
- መደበኛ፣ ግማሽ መደበኛ ወይም ኢመደበኛ ናቸው?
- እያንዳንዱ ዘዴ የራሱ የሆነ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት። በዚህ ማስተማሪያ መጨረሻ ለተቀመጡት ጥያቄዎች በተሰጡ መልሶች ክፍል የቁጠባ ዘዴዎች ጥቅምና ጉዳት የተብራራበትን ሰንጠረዥ ያገኛሉ።

በሰንጠረዡ ውስጥ ተጨማሪ ባሕሪያቶችን ለማካተት ያስታውሱ።

- ስለ ገንዘብዎ ደህንነት፣
- ገንዘብዎን ማውጣት በፈለጉ ጊዜ መቻልዎን፣
- ገንዘብዎን ለማውጣት የሚያጋጥሙ መዘግየቶችን፣
- ብዙ ወይም መጠኑ ትንሽ የሆነ ገንዘብ መቆጠብ እንደሚቻል፣
- ከቆጠቡት ላይ ብድር ይሰጥ እንደሆነ፣
- የቆጠቡት ገንዘብ ወለድ ይኖረው እንደሆን፣





ጠቃሚ! ደህንነቱ የተጠበቀ የቁጠባ ዘዴ መጠቀምዎ/ መምረጥዎ ጥሩ/ የተረጋጋ ስሜት እንዲሰማዎ ይረዳዎታል። ስለገንዘብዎ ደህንነት ሁልጊዜ የሚጨነቁ ከሆነ ይህን ስጋትዎንሊቀንስልዎ/ ሊያቆምልዎ የሚችል ምን አማራጮች በእጅዎ ላይ እንዳሉ ያስቡ።

የእርስዎ ተራ!

የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎችን ጥቅምና ጉዳቶች አውቃለሁ። ግቦቼንና በጀቴን እየተመለከትኩ ለፕሮጀክቶቼ የተሻለው የቁጠባ ዘዴ :
የቁጠባ ዘዴዎች

የእኔ ግቦች	የቁጠባ ዘዴ

ቁልፍ መልዕክቶች

- ቁጠባዎች በአደጋ ጊዜ ደህንነት እንዲሰማዎ ያደርጋሉ።
- ጥቂት ፍላጎቶች/ አሰቸኳይ ጉዳዮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ ፣ የማይታወቁ ሊኖሩ ይችላሉ። ቁጠባ ግን የወደፊት ፍላጎቶችን እንዲያቅዱ ወይም መተንበይ እንዲችሉ ይረዳዎታል።
- ሁሉም ነገር ሲስተካከል/ ሁሉም ነገር በትክክል ሲሄድ ቁጠባ የሚፈልጉትን እንዲሰሩ ወይም እንዲኖርዎት እንዲያቅዱ ያደርግዎታል።.
- ለፍላጎትዎ የበለጠ የሚስማማውን የቁጠባ ዘዴ ለመጠቀም የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎችን ሊያውቁ ይገባል።



2. የቁጠባ ውጤቶችን በብልህነት ይምረጡ

የቁጠባ ውጤት ማለት ለምሳሌ የመደበኛ ቁጠባዎች ሂሳብ 4% ወለድ የሚያመነጭ/የሚያመጣ ወይም የጊዜ (ቋሚ) የአምስት ዓመታት የማጠራቀሚያ ሂሳብ ነው።

ትርጉም

የቁጠባ ውጤት ማለት የምናውቃቸውን የቁጠባ ባሕሪያቶችን የያዘ የቁጠባ ዘዴ ነው። ከነሱም:

- የወለድ መጠን
- ለመቆጠብ ምቹ/ለማውጣትም ለመቺ የሆነ
- የተመቻቸና ለመጠቀም ቀላል የሆነ
- የቁጠባዎች ሂሳብ ለመክፈት መለፍርቶች ያሉት
- ደህንነት
- የቁጠባዎች ወጪ (የመክፈቻ ወጪ፣ ለማለተዳደር ወይም ሂሳብዎን ለመዝጋት፣ የግዢና ሽያጭ ልውውጦችን)
- መዝጋት

በገንዘብ ተቋማት የሚጠየቁ ሦስት ዋና የቁጠባ ውጤቶች

መደበኛ የቁጠባዎች ሂሳብ: ማጠራቀም በሚፈልጉበት ጊዜ ወይም በማንኛውም ጊዜ ገንዘብዎን መጠቀም እንዲችሉ የተዘጋጀ ነው።

ሒላማ የተደረገ /የኮንትራት ቁጠባዎች ሂሳብ: ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ግብዎን ለማሳካት(ለቤት፣ ለትምህርት፣ ለጋብቻ፣ ለንግድ.....) በወር የተወሰነ ገንዘብ በማስቀመጥ መቆጠብ ሲፈልጉ እንዲጠቀሙ የተዘጋጀ ነው። ቀድሞ ማውጣት የተከለከለ ወይም የሚያስቀጣ መሆኑን ያስታውሱ።

የጊዜ (በቋሚነት) ማጠራቀሚያ ሂሳብ: ለረጂም ጊዜ ግብዎችዎ ማሳኪያ ገንዘብዎ እንዲጠራቀም /እንዲጨምር ከፈለጉ (ላለመንካት ቃል ገብተው የሚያስቀምጡት ጥቅል የገንዘብ መጠን) እንዲጠቀሙት የተዘጋጀ ነው።

የእያንዳንዱ ዓይነት ውጤት ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት (ለምሳሌ የተለያየ የወለድ ምጣኔ)። በሚቀጥሉት ገፆች ለእነዚህ ውጤቶች ለእያንዳንዳቸው አንድ ባጠቃላይ ሦስት በራሪ ወረቀቶችን ያገኛሉ። በዚህ የማስተማሪያ መጨረሻ በመልመጃዎች መልስ ክፍል የእያንዳንዱን በራሪ ወረቀት መረጃ የሚያብራራውን የማወዳደሪያ ሰንጠረዥ ያገኛሉ።



የሥልጠና መርጃ ሐ.2.1
የመደበኛ ቁጠባ ሂሳብ

የመደበኛ ቁጠባ ሂሳብ



በማንኛውም ጊዜ
ገንዘብዎን ይጠቀሙ

በማንኛውም ጊዜና በሚፈልጉበት ወቅት ቀላል፣ ችግር የሌለበትና ምቹ የሆነ ገንዘብዎን ማስቀመጫና ማውጪያ መንገድ ሲሆን የእኛ መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ገንዘብዎን ሲያስተዳድር ተለዋዋጭነትን ይፈልጋል። ለማውጣትም ሆነ ለማስገባት ባንኩን በቅድሚያ ማሳወቅ አይጠበቅብዎትም፡ ፡ ካፒታልዎ ዋስትናዎ ነው። በራስዎ ዕርምጃ በጊዜ ብዛት ካፒታልዎን እንዲያሳድጉ ያደርግዎታል።

ጥቅሞች

- ከአደጋ ነፃ አገልግሎት
- የእርስዎ ቁጠባዎች ደህንነት
- የወለድ መጠን: 1%
- በማንኛውም ጊዜና እስከፈለጉበት ጊዜ ድረስ ገንዘብዎን ማጠራቀም ይችላሉ።
- በማንኛውም ጊዜና ካለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ገንዘብዎን ማውጣት ይችላሉ።
- አግልገሎቱን ሲጠቀሙ ምንም ክፍያ የለውም
- የባንክ ሂሳብ ቁጥሮን በነፃ መክፈትና መዝጋት
- አነስተኛው ቁጠባ መቆጠብ መቻል : ለምሳሌ የኢት.ብር 500.00
- ለድንገተኛ ሁኔታዎች ተስማሚ የሆነ
- ለማስቀመጥ ወይም በኤቲኤም ካርድ በነጻ ለማውጣት ፣
- በአገሪቱ ያለውን ማነኛውም ኤቲኤም መጠቀም መቻል (ይህ ምናልባት ክፍያዎችን ሊጨምር ይችላል)

ዓይነት:
ያልተገደበ



መስፈርቶች

- ሕጋዊ መታወቂያ (ብሔራዊ መታወቂያ፣ ፓስፖርት ወይም ሌላ ሕጋዊና ወቅታዊ መለያ ቅፅ)
- የመኖሪያ ማረጋገጫ

የሥልጠና መርጃ ሐ.2.2
የታለመ/የኮንትራት ቁጠባ ሂሳብ

የታለመ/የኮንትራት ቁጠባ ሂሳብ



በእርግጠኝነት ለወደፊት ገንዘብ መቆጠብ ከፈለጉ:

ይህ የቁጠባ ዓይነት የመቆጠብ ግብዎን በጣም ቀላል ያደርግልዎታል፣ በራስዎ ዕርምጃ ገንዘብ እንዲያስገቡ/እንዲቆጥቡ ይፈቅድልዎታል፣ በየወሩ ለሚያስገቡት ገንዘብ በቅድሚያ ያልዎትን ቁርጠኝነት ለማሟላት አማራጭ ይሰጥዎታል። ከ12 እስከ 48 ወሮች ባለው ጊዜ የተለያዩ የወለድ መጠኖችን መምረጥ ይችላሉ።

የቁጣባው ዘዴ ዋና ዋና ባሕርያቶች

- ለ48 ወራቶች እስከ 3% ዓመታዊ የወለድ መጠን፣
- ሂሳብ ቁጥሩን ለመክፈት ቢያንስ የኢትዮጵያ ብር 1000.00 ማስገባት፣
- የባንክ ሂሳብዎን በነፃ ለመክፈት፣ለማስተላለፍ፣ ለመዝጋት፣
- የማለቂያ/የማብቂያ ጊዜው ሲደርስ ሂሳቡ ይዘጋል፣
- ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ፕሮጀክትዎን ለመተግበር ወዲያው ብድር ማግኘት ይችላሉ፣
- የታሰበውን መጠን ካወጡ ቀረጥ ላይከፍሉ ይችላሉ ግን የወለድዎን ግማሽ ያጣሉ፣

መስፈርቶች

- ደንበኛችን መሆን፣
- ወቅታዊ/ጊዜው ያላለፈበት መታወቂያ (ፓስፖርት ወይም ሌላ ሕጋዊና ወቅታዊ የመታወቂያ ቅፅ)፣
- የመኖሪያ ማረጋገጫ፣



ጊዜ:
ከ12 እስከ 48 ወሮች ይምረጡ፣

የሥልጠና መርጃ ሐ.2.3

የጊዜ(ቋሚ)የማጠራቀሚያ ሂሳብ

የጊዜ ማጠራቀሚያ ሂሳብ



ብርዎን ይስሩበትና የበለጠ ገንዘብ ያግኙ

ይህ የቁጠባ ሂሳብ ዓይነት ከፍተኛ የወለድ መጠን እንዲያገኙ ይረዳዎታል። በዚህ ሂሳብ ያስቀመጡት ገንዘብ ዝግ ስለሆነ ለወደፊት ኢነቨስትመንቶችዎና ሌሎች ላቀዱአቸው አስፈላጊ ወጪዎች በትክክል ይረዳዎታል። በካፒታልዎ ላይ ጥሩ ትርፍ ሲያገኙ ከቁጠባዎ ለመጠቀም እንዳይነሳሱ ትክክለኛው የቁጠባ ሂሳብ ዓይነት ነው።



ጊዜ:
ከ 3 ወሮች እስከ 5 ዓመት

ዋና ባሕሪያቶች

- በገበያው ውስጥ እስከ 4% የሚደርስ ከፍተኛ የወለድ መጠን። የወለድ መጠኑ ቋሚና በቅድሚያ የታወቀ ነው።
- አነስተኛው የመግቢያ መጠን የኢትዮጵያ ብር 25,000.00፣
- የሂሳብ ቁጥሩን ለመክፈት፣ለማስተላለፍና ለመዝጋት ክፍያ የለውም፣
- ለማስገባት አስገዳጅ አይደለም፡ በሚችሉበት ጊዜ ገንዘብ ያስገባሉ፣
- ቶሎ ማውጣት ያስቀጣል፣
- በማጠራቀምዎ በነፃ ሰርተፊኬት ያገኛሉ፣
- ከእኛ ጋር የቁጠባ ታሪክዎን ያሳድጉና ለፕሮጀክትዎ ብድር ያመቻቹ፣

መስፈርቶች

- የገንዘቡን ምንጭ ማረጋገጫ፣
- ወቅታዊ/ ጊዜው ያላለፈበት መታወቂያ (ብሔራዊ መታወቂያ፣ፓስፖርት ወይም ሌሎች ሕጋዊና ወቅታዊ የመታወቂያ ቅፅ)
- የመኖሪያ ማረጋገጫ

ግባችው እንዲሳካ የሚረዳቸው የትኛው የቁጠባ ሂሳብ እንደሆነ ባሕሪያቸውን በመረዳት እንዲወስኑና መክፈት እንዲችሉ አሁን ስለተለያዩ የቁጠባ ዓይነቶች ብዙ አውቀዋል።

የሥልጠና መርጃ ሐ.2.4

ግቦችን ወደ ቁጠባ ውጤቶች ሁኔታ ማገናኛ ካርድ




ግቦችን ወደ ቁጠባ ውጤቶች ሁኔታ ማገናኛ ካርድ ፣ 1

ሁኔታ 1

ወርቅነሽ የራስዋ የሆነ የቡና ሱቅ እንዲኖራት ትፈልጋለች። ጥራት ያለው የተቆላ ቡናና የተፈላ ቡና በስኒ መሸጥን ትፈልጋለች። በጥሩ ቦታ ላይ ያለ አነስተኛ የቡና ሱቅ ያለው ጓደኛዋ ሱቁን በስድት ወር ጊዜ ውስጥ ለኪራይ እንደሚያደርስላት የነገራት ሲሆን ወርቅነሽ ቢያንስ ለስድስት ወራቶች ቁጠባዋን ማውጣት/ማጥፋት አልፈለገችም።

ምን ዓይነት የቁጠባ ሂሳብ መምረጥ ይኖርባታል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት



ግቦችን ወደ ቁጠባ ውጤቶች ሁኔታ ማገናኛ ካርድ ፣ 2

ሁኔታ 2

ገመቹ የራሱን ቤት የመስራት ግቡን ለማሳካት የተጠራቀመ ጥቂት ቁጠባዎች ያሉት ቢሆንም በቂ ባለመሆኑ ከጎን ለሦስት ዓመት የሚቆይ ቋሚ መጠን ያለው ገንዘብ በየወሩ ለመቆጠብ ማመቻቸት ይፈልጋል። ይህንን ገንዘብ ለሌሎች ዓላማዎች እንዲያውል የሚገፋፋውን አይፈልግም።

ምን ዓይነት የቁጠባ ሂሳብ መምረጥ ይኖርበታል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት




ግቦችን ( ) ውጤቶች ሁኔታ ማገናኛ ካርድ ፣

ሁኔታ 3

ዳዊት በሚቀጥለው ዓመት ወደ ሣዑዲ አረቢያ መሄድ ይፈልጋል በመሆኑም ለዚህ ዓላማ በተቻለ መጠን መቆጠብ ይኖርበታል። በመሆኑም ቁጠባዎቹን ለሌላ ዓላማ እንዲጠቀም መነሳሳትን አይፈልግም። የአስቸኳይ የባንክ ሂሳብ ደብተር መክፈት እንደሚያስፈልገው ማሰብና ገንዘቡንም በቶሎ ማውጣት መቻሉንም ይፈልጋል።

ምን ዓይነት የቁጠባ ሂሳብ መምረጥ ይኖርባታል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት



ግቦችን ( ) ውጤቶች ሁኔታ ማገናኛ ካርድ ፣

ሁኔታ 4

አንዳንድ ጊዜ ትርሐስ ጥሬ ገንዘብዋን በቤት ውስጥ በፍራሿ ስር በማስቀመጥዋ ደህንነት እንደሌለው ይሰማታል። ይህንን ገንዘብ ባንክ ማስቀመጥ ለእሷ የተሻለ ይሆን ነበር በማለት ትደነቃለች። ይንን ገንዘብ ለማጥፋት የሚያነሳሳትን አትፈልግም። እንዲሁም ለአስቸኳይ ጉዳይ የሚሆናትን በበቂ መቆጠብ ትፈልጋለች።

ምን ዓይነት የቁጠባ ሂሳብ መምረጥ ይኖርባታል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ጠቃሚ መረጃዎች

እያንዳንዱ ዓይነት ምርት/ውጤት የራሱ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት (ለምሳሌ የተለያየ የወለድ መጠን)። የቁጠባ ውጤትን ለመምረጥ የተለያዩ ምርቶችን/ውጤቶችን ባሕሪያቶች ማወቅ ብቻ ሳይሆን ራስዎን በደንብ ማወቅዎን ጭምር ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ይጠይቁ፡

- *የግል ሁኔታዎ: ገቢዎ ምንድን ነው? ወጪዎችዎ (ዕዳ መክፈልን ጨምሮ)? ምን ያህል ይቆጥባሉ? ሁሉም ጥሩ ሲሆን ምን ያህል ለብቻ ያስቀምጣሉ? ገንዘብዎን የተሻለ በማስተዳደር ምን የህል ለብቻ አመቻቹ? የውጭ ዜጋ ወይም በውጭ አገር የሚኖሩ ዜጋ ከሆኑ በገንዘብ ተቋማት የቁጠባ ሂሳብ ይከፍታሉ?*
- *ግቦችዎ:- ለምን ዓላማ መቆጠብ ፈለጉ? ለአስቸኳይ ሁኔታዎች? ለመማር? ቢዝነስ ለመፍጠር ኢንቨስት ለማድረግ? ወደ ቤት መመለሻ? ለመኖሪያ? ለጡረታ?*
- *የእርስዎ ቁጠባ ወሰን: ለምን ያህል ጊዜ መቆጠብ ይፈልጋሉ / ገንዘብዎን በዝግ ሂሳብ ማስቀመጥ?*
- *የእርስዎ ባሕሪይ: የሚመጣውን ችግር መውሰድ ይፈልጋሉ ወይም አይፈልጉም? ከፋይናንስ ገበያው ጋር የማይተዋወቁ ከሆን ችግር ያለበት ኢንቨስትመንት ውስጥ አይግቡ!*

⚠ ***የሐሰት ማስታወቂያዎችን ይጠንቀቁ! በተለይ በአጭር ጊዜ ካለ ችግር/ኪሳራ ከፍተኛ ገቢ የሚያመጡ መሆኑን የሚያረጋግጥ የቁጠባ ውጤቶች የሌሉ መሆኑን ያስታውሱ።***

የቁጠባ አገልግሎትን ከመምረጥዎ በፊት የገንዘብ ተቋሙን ምን ምን ጥያቄዎችን እንጠይቅ?

- *በምፈልግበት ጊዜ ማውጣት እችላለሁ?*
- *የወለድ መጠኑ ስንት ነው?*
- *ለወለድ ምጣኔው ቀረጥ መክፈል አለብኝ? ከሆነስ ስንት?*
- *በቁጠባዎቼ ብድር መውሰድ እችላለሁ?*
- *የቁጠባ ዕቅዶች ይለዋወጣሉ? (በሌላ አነጋገር በተወሰነ ቀን የተወሰነ መጠን ማስቀመጥ*
- *የቁጠባ ሂሳብ በምከፍትበት ጊዜ አነስተኛ የማጠራቀም መጠን አለው ወይም ሁልጊዜ በሂሳብ ቁጥሩ ላይ መቀመጥ/ መታየት ያለበት አነስተኛ መጠን አለ?*
- *የሚያስፈልገኝን መጠን ባወጣ እቀረጣለሁ ከሆነስ ስንት ነው?*
- *የዚህን ዓይነት የሂሳብ ቁጥር በመደበኛነት ሰዎች እንዴት ይጠቀማሉ?*
- *እንደ ሌላ አገር ዜጋነቴ አዚህ የባንክ ሂሳብ ደብተር መክፈት እችላለሁ? ምን ምን ሰነዶችን ይጠይቁኛል?*

ቁልፍ መልዕክቶች

ለእያንዳንዱ የቁጠባ ግብ ተስማሚ የቁጠባዎች አግልግሎት አለ።

⚠ **አስፈላጊ እነዚህን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ወደ ገንዘብ ተቋማት መግባት ሊያስፈራዎት ወይም ሊያስጨንቅዎት ይችላል። በራስ መተማመን እስከሚሰማዎት ድረስ ሁልጊዜ ጓደኛዎን ወይም ባልደረባዎን እንዲያካሂድዎት መጠየቅ ይችላሉ።**

አባሪዎችና ቁልፍ ሰነዶች

የቁጠባዎችን ዘዴ በሚመርጡበት ጊዜ ከግምት መወሰድ/መታየት ያባቸው ባሕሪያቶች

ቀላል/ቋሚ ያልሆነ/የተለያዩ ወጪዎች

ይህ ደግሞ ሰዎች ቁጠባቸውን ለማውጣት እንዴት ቀላል ወይም ከባድ እንደሆነ ያመለክታል። ለምሳሌ የሂሳቡ ባለቤት ምን ያህል ወጪዎችን ከእሱ ወይም ከእሷ ሂሳብ በየወሩ ማውጣት እንደተፈቀደላቸው ወይም ባንኩ ወይም የገንዘብ ተቋሙ ኤቲኤሞች ወይም በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ባሉ ቅርንጫፎች (የሂሳቡ ባለቤት የሂሳብ ቁጥሩን በቀላሉ የእሱን ወይም የእሷን ሂሳብ ቁጥር በቀላሉ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ) እንዳለው የሚያሳይ ነው።

ለአጠቃቀም ምቹና ቀላል

ደንበኞች በተቻለ ፍጥነት ገንዘባቸውን ማውጣት መቻላቸውንና ምቾትን ይወዳሉ ይፈልጋሉም። ለምሳሌ ጥቂት ሰዎች ራሳቸው ሥራ ላይ ባልሆኑበት ጊዜ ባንካቸው ክፍት እንዲሆን ይፈልጋሉ።

የቁጠባ ሂሳብ መክፈቻ መስፈርት

ብዙ ሰዎች የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ሀብታም መሆን አለብህ ብለው ያስባሉ። ይህ ሁልጊዜ እውነት አይደለም። ጥቂት ባንኮች የቁጠባ ሂሳብ መክፈት ከፈለግህ ትንሽ ማስቀመጥን (ወይም ምንም) ይፈልጋሉ። ሆኖም መስፈርቶቹ ብሔራዊ መታወቂያን፣የመኖሪያ ማረጋገጫና/ወይም ክፍያ የተፈፀመባቸው አገልግሎቶችን (ይህ ለብዙ ሰዎች ቀላል አይሆንም በተለይ ለተፈናቀሉ ሰዎች) ሊያካትቱ ይችላሉ።

ደህንነት

ሰዎች ገንዘባቸውን እቤት ማስቀመጥን በሚመርጡበት ጊዜ የመሰረቅ ወይም የመጥፋት አደጋ አለው። ጥቂት መንግስት የሚቆጣጠራቸው የገንዘብ ተቋማት ትንሽ ለሚቆጥቡ ዋስትና ይሰጣሉ። በሌላ አነጋገር ቢከስሩም የቆጠቡትን አያጡም።

ወለድ መጠንና የቀረጥ ጥቅሞች

በመደበኛ (ወይም በግማሽ መደበኛ) ተቋም በሚቆጥቡበት ጊዜ ገንዘብዎን በተባለው ተቋም በማስቀመጥዎ ይሸለማሉ። ሽልማቱ ወይም ወለዱ በአጠቃላይ ያስቀመጡት የገንዘብ መጠን በመቶኛ ነው። በመደበኛ ተቋሞች በመቆጠብዎ የታክስ ጥቅሞች ሊኖሩ ይችላሉ።

መዝገት

ከባንክ ሂሳብዎ ቁጠባዎችዎን ያወጣሉ? እንዴትና በምን ሁኔታ? ገንዘብ በአስቸኳይ ቢፈልጉ የመረጡት የቁጠባ ዘዴ በሚታመን ጊዜ ውስጥ ሁሉንም ገንዘብዎን እንዲያወጡ መፍቀድ ይኖርበታል። ቁጠባው በዓይነት ሲሆን (ለምሳሌ ንብረት ወይም እንስሳት) ንብረትዎን ከመሸጥዎና እጅዎን ገንዘቡ ላይ ከማድረግዎ በፊት ቀናቶችን ወይም ወራቶችን መጠበቅ ይኖርብዎታል።

የቁጠባዎች ዋጋ (ክፍያዎች)

በሕጋዊ ተቋማት ገንዘብ ሲያስተላልፉ፣ በኤቲኤም ገንዘብ ሲያወጡ ወዘተ ሊያስከፍልዎት ይችላሉ። ገንዘብ በአስቸኳይ በሚያስፈልግዎ ጊዜ የተሻለ የቁጠባ ዘዴ መኖር ባልዘገየ ሁኔታ የቆጠቡትን ገንዘብ እንዲያወጡ ይፈቅድልዎታል።


የቁጠባ ስትራቴጂዎ ዓላማና ግቦች

የቁጠባዎን ምክንያት መሰረት በማድረግ ጥቂት ዘዴዎች ከሌሎች በተሻለ ሊስማማዎት ይችላል (ለምሳሌ ለቤት ወይም ለአፓርታማ መቆጠብ ትልልቅ ድምሮች በሚሳተፉበት ቦታ መደበኛ ዘዴ ፍራሽ ስር ገንዘብዎን ከማስቀመጥ የበለጠ ተስማሚ ይሆናል)። .

የመልመጃ መልሶች

የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎች ጥቅምና ጉዳት (ሐ1)

የቁጠባ ዘዴ	ጥቅሞች	ጉዳቶች
መደበኛ / ሕጋዊ • ባንኮች • ፖስታ ቤት • የተመዘገቡ አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት • የተመዘገቡ የቁጠባና ብድር ሕብረት ሥራ ማህበራት • ኢንሹራንስ ካምፓኒዎች (ለረጅም ጊዜ ቁጠባዎች ውጤት እንደ የሕይወት ኢንሹራንስ) • ሞባይል መተግበሪያዎች • ረቀቅ መተግበሪያዎች	• አስተማማኝ አማራጭ • ሚስጢራዊነቱ (ምን ያህል ገንዘብ በባንክ እንዳለ ከቁጠባ ሂሳቡ ባለቤት ውጪ ሌላ ሰው አለማወቁ)። • ገንዘብዎን እንዲያወጡ የሚፈታተንዎት አይበዛም (ጥያቄዎችን ላለመቀበል የቀለለ) • ወለድ ሊያገኙ ይችላሉ • ሌላ የገንዘብ አገልገሎቶች (የጡረታ ቁጠባ ሂሳቦች፣ብድሮችወዘተ...) • በተሸለ መንገድ ገንዘብዎን ማስተዳደር (የቁጠባ ሂሳብ መግለጫዎች) • የክፍያ ሰነዶችን ያፋጥናል። ባንኩ ኢንተርኔት ወይም የሞባይል ባንክ አገልግሎቶችን ይሰጣል በሚጠቀሙበት ጊዜ የባንክ ሂሳብዎን መጠን ማረጋገጥና ቁጠባዎን 24 ሰዓት በቀን ማስተዳደር ይችላሉ። • ብዙ ባንኮች በወኪሎቻቸው በኩል ስለሚሰሩ አገልግሎታቸውን የበለጠ ተደራሽ ያደርገዋል። • ዲጂታል አቅራቢዎች ያልዎትን ገንዘብ በቀን 24 ሰዓት እንዲያስተዳድሩና እንዲከታተሉ ይፈቅዱልዎታል።	• አነስተኛ ገቢ ላለው፣ ላልተማሩ ሰዎች፣ ተገደው ለተፈናቀሉ ሰዎች በቀላሉ የማይሰጥ መሆኑ። • ተገደው የተፈናቀሉ ሰዎች በቀላሉ የማያገኙትን መታወቂያ ወረቀት ወይም የመኖሪያ ማስረጃ ሊጠየቁ ይችላሉ። • አብዛኛውን ጊዜ የባንክ ሠራተኞች ዓላማቸው ምርቶችን መሸጥ የሆነ የሽያጭ ባለሙያዎች ሲሆኑ ከደንበኞች ፍላጎት ይልቅ የባንኩን ሊያስቀድሙ ይችላሉ። • የክፍያ ተመኖች ከምርት ምርት ስለሚለያዩ በጣም ትንሽ ሊሆን ይችላል። • አንዳንድ ምርቶች የባንክ ሂሳብ /አካውንት ለመክፈት አነስተኛውን የተቀማጭ መጠን እዲያሟሉ ስለሚጠይቅ ይህ እንደ ችግር/ዕክል ሊሆን ይችላል። • ለባንክ ሂሳብዎ ክፍያ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። • ባንክ ተራ በመጠበቅ ጊዜ ይባክናል። • የተለያዩ ምርቶችና ክፍያዎች ውስብስብ በመሆናቸው ስህተት የመስራት ፍራቻ ይኖራል። • የመክፈቻ ሰዓቶች የተገደቡ መሆን (በምሽቶችና በዕረፍት ቀናት መዘጋቱ) • የኢኮኖሚ ወይም የፖለቲካ አለመረጋጋት ውጤት፡ የገንዘብ ቀውስ፣ የውጭ ምንዛሪ መጨመር፣ ገንዘብ ማውጣት መከልከል/መዘጋት፣ ገንዘብ ይዞ ከአገር መውጣት አለመቻል (የምንዛሪ ቁጥጥር)።



ማስታወሻዎች

የቁጠባ ዘዴ	ጥቅሞች	ጉዳቶች
ከሌል መደበኛ • የቁጠባ ቡድን • ራስን መርዳት ቡድን • የገጠር ባንኮች • የገጠር የቁጠባና ብድር ማሕበራት (ገቁብማ) • ያልተመዘገቡ ጥቃቅን የገንዘብ ተቋማት • ያልተመዘገቡ ቁጠባ ብድር ህበረት ስራ ማህበራት • ያልተመዘገቡ የብድር ተቋማት	• በቀላሉ ተደራሽ • ብዙ ጊዜ ይቆጥባሉ ማለት ዕውነታው ብድር ያገኛሉ • ከቁጠባዎች ከተሰጠ ብድር ወለድ ሊያገኙ ይችላሉ። • ስለሚያጠራቅሙት መጠን ድግግሞሽ እንዲሁም ቁጠባን የሚያበረታታ የቁጠባዎች ቡድን ሕጎች። • ስነ ሥርዓት • በሕብረት መስራትና በአባላት መካከል ማሕበራዊ ትስስርን ማጠናከር	• ጥቂት ዋስትናዎች • ከቁጠባዎ ላይ ወለድ እንደሚያገኙ እርግጠኛ አይደሉም። • የተወሰነ ወይም ብድር አይሰጥም። • ለመቆጠብ ወይም ገንዘብዎን ለማውጣት የአባላትን ማረጋገጫ ይፈልጋል። • አባላቱ በሕጉ ያለመገዛት ችግር (ምሳሌ አንድ ሰው ከአባላቱ ገንዘብ ከወሰደ በኋላ ሊሰወር/ ሊጠፋ ይችላል።) • ሕጋዊነትን የሚጠይቅና ችግር ቢያጋጥም ለፖሊስ ማመልከት ላይቻል ይችላል።. • የቁጠባው ቡድን አባላት የሞት አደጋ ማጋጠም። • የቁጠባ ቡድኑን ለመቀላቀል የኔት ዎርኩ አካል መሆን ይኖርብዎታል። • የቁጠባው ቡድኖች የሚሰሩት በከፍተኛ የመውደቅ አደጋ ውስጥ ነው (በባለ ሥልጣኖች የአስተዳደር ክትትል የለም)
በከፊል መደበኛ • እቤት ውስጥ (በጥሬ ገንዘብ፣በደህና ቦታ ወይም በገንዘብ ሳጥን ውስጥ) • በዓይነት (ወርቅ፣ ጌጣጌጥ፣ ከብት፣ መሬት፣ንብረት ወዘተ...) • ነጋዴ፣ዘመድ፣ጓደኛ ገንዘብ ማስቀመጥ።	• ለማግኘት ቀላል ነው። • ያገኙት ንብረት ዕሴቱ ሊጨምር ይችላል • ገንዘብዎን ለመመለስ ንብረትዎን መሸጥ ይኖርብዎታል (በገበያው ሕግ መሰረት) • ጓደኛ፣ዘመድ ወይም ነጋዴ ሁልጊዜ ዝግጁ ናቸው • በዓይነት መቆጠብ ሌሎች ጥቅሞች አሉት፡ ምርት ወይም የወተት ሽያጭ (ከብቶች ከሆኑ) ጌጣጌጥ በአስፈላጊ ዝግቶች ጊዜ ሊጌጥ/ሊደረግ ይችላል። • በዓይነት ቢቆጥቡ (ከብት፣ንብረት) ገንዘብ ሊያገኙ ይችላሉ (ከስጋ ሽያጭ፣ወተት ከማከራየት....)።	• አስተማማኝ አይደለም፡ በረጅም ጊዜ ውስጥ ዕሴቱ ሊጠፋ ይችላል፣ የስርቆት ስጋት፣ መታመም ወይም መሞት (በከብቶች ሁኔታ) • ገንዘቡን ለማጥፋት ጠንካራ ማነሳሳት ሊኖር ይችላል (ገንዘብዎን እቤትዎ ካስቀመጡ) • በአደጋ ጊዜ ለመዝጋት አስቸጋሪ (ዕቃውን መሸጥ ጊዜ ሊወስድ ይችላል) • በዓይነት የሚቀመጥ ቁጠባን ዋጋ በተመለከተ፡ ለከብቶቹ ምግብና የህክምና ወጪዎችን፣ የንብረት ጥገናዎች፣



ምናባዊ ብሮሸሮችን በመጠቀም የቁጠባ ዓይነቶች ማወዳደሪያ ሰንጠረዥ

	መደበኛ ቁጠባዎች	የኮንትራት ቁጠባ	በጊዜ ቁጠባ
የውጭ አገር ሠራተኛ ቢሆኑ መክፈት ይችላሉ?	የሚቻል ይመስላል	የተሰጠ መረጃ የለም	የተሰጠ መረጃ የለም
የሂሳብ ቁጥሩን በሚከፍቱበት ጊዜ እንዲያስቀምጡ የሚጠየቁት አነስተኛ ገንዘብ አለ ወይም ምንጊዜም ገንዘብ መክፈል	10 የአሜሪካን ዶላር	20 የአሜሪካን ዶላር	500 የአሜሪካን ዶላር
በማንኛውም ጊዜ ማውጣት ይችላሉ? ማንኛውም ቅጣት ወይም ክፍያ አላቸው?	አዎ ካለ ምንም ዋጋ	አዎ ግን ወለድ ያጣሉ	አዎ ከቅጣት ጋር
የወለድ መጠኑ ስንት ነው?	1%	3%	4%
የቁጠባ ሂሳብ ቢከፍቱ ገንዘብ መበደር ይችላሉ?	አይደለም	አዎ ከጥቂት ጊዜ በኋላ,	አዎ ከጥቂት ጊዜ በኋላ
የቁጠባ ጊዜው እንደሁኔታው ነው ወይም በተወሰነ ቀን ውስጥ የተወሰነ ገንዘብ ማስገባት አለብህ?	መለዋወጥ ይችላል	በየወሩ የማስገባት ቁርጠኝነት አለው	መለዋወጥ ይችላል
በኤቲኤም ማስቀመጥ ወይም ቁጠባየን ማውጣት እችላለሁ?	አዎ	አይደለም	አይደለም

የመልመጃ መልሶች

ግቦችን ወደ ቁጠባ ውጤቶች ሁኔታ ማገኛኛ ካርዶች፣ (የሥልጠና መርጃ ሐ.2.4)



1

የሁኔታዎች መልስ

ወርቅነሽ በአጠገቧ ያስቀመጠችውን ገንዘብ ለማጥፋት እንዳትነሳሳ በጊዜ ማጠራቀሚያ የቁጠባ ሂሳብ በባንክ ለመክፈት መሞከር አለባት።።።



2

የሁኔታዎች መልስ

ገመቹ ለተወሰነ ጊዜ በየወሩ በቋሚነት እንዲያስቀምጥና እንዲቆጥብ የሚረዳው የኮንትራት ቁጠባ ሂሳብ ነው።



3

የሁኔታዎች መልስ

ዳዊት መደበኛ የባንክ ሂሳብ ለመክፈት መሞከር አለበት፡ ፡ በዚህ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ የሚጠቀመው ጥቂት ገንዘብ በየወሩ ለብቻ ማስቀመጥ መቻል አለበት። ወይም በየጊዜው ማስቀመጥ መቻልና ለሣዑዲ አረቢያ ጉዞው ካጠራቀመው መውሰድ መቻል ይኖርበታል።



4

የሁኔታዎች መልስ

ትረሐስ መደበኛ የባንክ ሂሳብ ለመክፈት መሞከር አለባት። በዚህ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ለአስቸኳይ ጊዜ የምትጠቀመው ጥቂት ገንዘብ በየወሩ በጎን ማስቀመጥ መቻል አለበት። ወይም በየጊዜው ማስቀመጥ መቻልና ለሌላ ዓላማዎች መጠቀም ።



፴

የብድር ውጤቶችን በብልህነት ይጠቀሙ

FINANCIAL QUIZ EDUCATION

መ1. ፕሮጀክትን በገንዘብ ለመደገፍ የተሻለው መንገድ ምንድነው ብለው ያስባሉ?

- ☐ ሀ. ገንዘብ መበደር.
- ☐ ለ. ቁጠባዎችዎን ይጠቀሙ.
- ☐ ሐ. ቁጠባዎችዎን ይጠቀሙና ገንዘብ ይበደሩ
- ☐ መ. የእርስዎን ፍላጎቶችና ሀብቶችን አመዛዝነው የተሻለውን አማራጭ ይምረጡ።

መ2. ብድርን በሚመርጡበት ጊዜ እጅግ በጣም አስፈላጊው ጉዳይ ምንድን ነው?

- ☐ ሀ. የወለድ መጠን
- ☐ ለ. የሚከፈልበት ሁኔታ
- ☐ ሐ. ከሌሎች የተሻለ በጣም አስፈላጊ መስፈርት የለም ሁሉንም አጥንተን ለእኛ ፍላጎቶችና ግላዊ ሁኔታዎች የሚስማማውን ብድርና አበዳሪውን መምረጥ ነው
- ☐ መ. የአበዳሪው የቦታ ቅርበት

መ3. ለብድር ጊዜዎች የማይሆን ሁኔታ ምንድነው?

- ☐ ሀ. የወለድ መጠን.
- ☐ ለ. ዋስ
- ☐ ሐ. በጀት.
- ☐ መ. ቅጣቶች

በ፡፫˙መ ፡፶፡፫˙መ ፡መ፡፲፡መ ፡ቷሃፃመ

1. ፕሮጀክቶችዎን በገንዘብ ለመደገፍ ዘዴ ይምረጡ

ባለፈው ትምህርታችን የተለያዩ የቁጠባ አማራጮች ተመልክተናል። በዚሁ መሰረት አሁን የተለያዩ የገንዘብ ማግኚያ ዘዴዎችን በማነጻጸር የፕሮጀከት ግብን ለማሳካት እንሞክራለን። ለመጠቀም የገንዘብ ግባችንን ማሳካትና ፕሮጀክቶቻችንን በገንዘብ መደገፍ ነው።

የሥልጠና መርጃ መ.1.1

የገንዘብ አጠቃቀም ታሪኮች



ገመቹ

በቅርብ ጊዜ የገመቹ ቤት ፍሪጅ ስለተሰበረ ገመቹ በረዶ ቤት ያለው አዲስ ፍሪጅ መግዛት ይፈልጋል፡ ፡ትንሽ ካሰበ በኋላ ወደ አዲሱ ቤታቸው ከገቡ ለሱቁና ለቤተሰቡ በጋራ መጠቀም ስለሚችሉ የበረዶ ቤት የተገጠመለት ፍሪጅ ለመግዛት ከገንዘብ ተቋም ገንዘብ ለመበደር ወሰነ::

የገንዘብ አጠቃቀም ታሪኮች



ዳዊት

ዳዊት ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖራል። አባቱ ፍስሐ ፋብሪካ ውስጥ ይሰራሉ። ግን ከጥቂት ቀናት በፊት የስራ መሳሪያ ወድቆባቸው አደጋ ስለደረሰባቸው ወደ ሆስፒታል ሄደው ዶክተሩ ኤክስሬይ መነሳት እንዳለባቸውና መድሃኒትም እንደሚያስፈልጋቸው የነገራቸው ቢሆንም ለዚህ የሚሆን በቂ ገንዘብ የላቸውም። ዳዊትም ቁጠባውን በሙሉ ለዕቁብ ስለሚከፍል አባቱን ለማሳከም በአካባቢው ካሉ ኢመደበኛ አበዳሪ ገንዘብ ለመበደር ወሰነ።

የገንዘብ አጠቃቀም ታሪኮች



ወርቅነሽ

ወርቅነሽ የእጅ ጥልፍ ትሰራለች። ይህንን ሙያ የተማረችው ከእናቷና የቴክኒክ ችሎታዋን ለማሳደግ ከወሰደችው ሥልጠና ነው፡ ፡ የተለያዩ ምርቶችን በመስራት ገበያ ወስዳ ትሸጣለች። ብዙ ጊዜ ሻርፖችና ብርድ ልብሶች ትሰራለች። ግን አሁን በእጅ ከተፈተለ ጥጥ ከፊቱ መስቀል የተጠለፈባቸው ቀሚሶችን መስራት መጀመር ትፈልጋለች። የጥልፍ ክሮችን፣መርፌዎችንና ጨርቆችን መግዛት ትፈልጋለች። እንደ ቁጠባው አካል በተለየ ሁኔታ ለንግድዋ የሚሆን ባንክ ታስቀምጣለች፣ ወርቅነሽ በባንክ ሂሳብዋ ባለው ቁጠባዋ የምትፈልጋቸውን አቅርቦቶች ለመግዛት ትጠቀማለች።

የገንዘብ አጠቃቀም ታሪኮች



ትሪሐስ

የትረሐስ ስልክ ትንሽ አሮጌ ስለሆነ አንዳንዴ እህቷ በምትደውልበት ጊዜ መስመሩ ካለምንም ምክንያት ይጠፋል። በስልኳ የቪዲዮ ጥሪ ማድረግ አይቻልም፡ ፡ አዲስ ለመግዛት በቂ ቁጠባ ስለሌላት አሮጌ ስልኳንና ከራሕዋ ጋ ማንም የማይጠቀምበትን የቤት ዕቃ ለመሸጥ ወሰነች። በዚያ ገንዘብ የተሻለ ስልክ ትገዛለች።

ሰዎች ፕሮጀክትን በገንዘብ ለመደገፍና ለማሳደግ እንዲችሉ የሚያደርጉ አጠቃላይ አራት መንገዶች አሉ።

1. እንደ ትረሐስ ንብረት መሸጥ
2. እንደ ወርቅነሽ የግል ቁጠባን ይጠቀሙ
3. እንደ ዳዊት ከጓደኞች እና ሌሎች ኢመደበኛ የብድር ምንጮች/ ከቤተሰብ ገንዘብ መበደር።
4. እንደ ባንክ ካሉ የገንዘብ ተቋማት፣ ከጥቃቅን የገንዘብ ተቋማት፣ ወይም ከተመዘገቡ ብድርና ቁጠባ ኮኦፐሬቲቮች እንደ ገመቹ ገንዘብ መበደር።

ከዚህ የመመማሪያ መጽሃፍ መጨረሻ በመልመጃዎች መልስ ክፍል የስልጠና ድጋፍ መ.1.3. የእያንዳንዱን የገንዘብ ዘዴ ጥቅሞቹንና ጉዳቶቹን የሚገልፅ ሰንጠረዥ ያገኛሉ።



የሥልጠና መርኃ መ.1.2

የሁለት ነጋዴዎች ታሪክ

ገጠመኝ

እርስዎ ጌዴዎን ነዎት የዳዊት ጥሩ ጓደኛና በኢትዮጵያ ውስጥ ከነቴራ የሚሸጥ ትንሽ ንግድ/ቢዝነስ ይመራሉ። ዛሬ እንደ እርስዎ በገበያ ላይ ከነቴራ የሚሸጠውን ጓደኛዎን ከፍያለውን ሊጠይቁ/ሊጎበኙ ነው። ዳዊትንም ጋብዘውታል።

ከፍያለው ንግዱን እንዴት እንደሚመራ ብዙ ጥያቄ ይጠይቁ። ከፍያለውም እርስዎ እንዴት እየሄዱበት እንደሆነ ማወቅ ፈልገዋል።

ይህን ንግድዎን እንዴት እንዳስፋፉትና እንዳዘጋጁት የሚገልፅ ነው።
ለብዙ ወራቶች ሊባኖስ ሰርተው ባጠራቀሙት 25.000 ብር ንግድዎን ጀምረዋል። ጥቂት ያገለገሉ የቤት ዕቃዎችን በመሸጥ 7,500 ብርም አለዎት።

እንዲሁም ንግድዎ በጣም ትንሽ ስለሆነ ቀስ በቀስ ለማሳደግ ዕቅድ አለዎት።ብሔራዊ ባንክ አጠገብ በቅርብ ቀን ለከፈቱት ንግድዎ ለመመደብ በከፈቱት የቁጠባ ሂሳብ በሳምንት 1500 ብር በጎን ለማስቀመጥ ወስነዋል። በዚህ መንገድ በእያንዳንዱ 3 ወይም 4 ወር ንግድዎን ለማሳደግ በቂ ገንዘብ ቆጥበዋል (ለምሳሌ ባነር መግዛት ወይም ግድግዳውን ቀለም መቀባት)። አሁን በብዙ መጠን ከነቴራና የተለያየ ምርት ይገዛሉ። ጓደኛዎ ዳዊትን የትርፍ ጊዜ ሥራ በመስጠት ይረዱታል። ብዙ ትርፍ ሲያገኙ ብዙ ይቆጥባሉ በንግዱ ውስጥ ትልቅ ኢንቨስትመንት ይሰራሉ።

ከፍያለው

አንተ ከፍያለው ነህ ገበያ ውሰጥ ትንሽ የከነቴራ ንግድ አለህ። ጓደኛህ ጌዴዎንም ተመሳሳይ ሱቅ አለው።ዛሬ አንተ፣ ጌዴዮንና ዳዊት ቡና ለመጠጣት ትገናኛላችሁ።

ጌዴዎን ለንግዱ እንዴት ገንዘብ እንደሚያወጣና እንደሚያስፋፋ ማወቅ ፈልገሃል። እንዴት እንደምትሰራም ማወቅ ይፈልጋል። ይህ አንተ ንግድህን እንዴት እንደምትሰራውና እንዳስፋፋኸው ለማወቅ ነው።

በልዩ ፕሮግራም ወጣቶችን ከሚደግፈው ኤምኤፍአይ ከተባለ ተቋም በተበደሩት 50.000 ብር ላይ የቆጠቡትን 30.000 ብር ጨምረው ጀመሩ። ይህ ብድር የተከራዩትን ሱቅ እንዲያሻሽሉ/ እንዲያስተካክሉ አቅም ሰጥቶዎታል። በዚህ ማሻሻያ ፀጥ ባለው መንገድ ላይ ባማረው ሱቅዎ ብዙ ደንበኞችን ተቀብለው ለማስተናገድ ችለዋል።

የዕዳ ክፍያዎን ጨምሮ የየሳምነት ወጪዎችዎን በሙሉ ከፍለዋል። ሆኖም በየሳምንቱ መቆጠብ የቻሉት 750 ብር ብቻ ነው።

አንድ ቀን በከተማው ጭንቅንቅ የገበያ ቦታ ላይ አንድ ትንሽ ሱቅ ተከፈተ። ሱቁም የሚከራይ በመሆኑ ለንግድዎ መልካም አጋጣሚ ስለሆነ ቢከራዩት የሚሸጡትን ዕቃ በዕጥፍ እንደሚጨምር አስበዋል። ስለዚህ ሌላ ሰው ከእርስዎ በፊት እንዳይከራየው ፈጣን ውሳኔ ወስነው ከእህትዎ ባል 45000 ብር ተበደሩ።

ጥያቄዎች

- ጌዴዎንና ከፍያለው ንግዳቸውን ማስፋፋት የሚችሉት እንዴት ነው?
- ከሁለቱ የንግድ ቤቶች መካከል የትኞቹ ናቸው የሚሳካላቸው? ለምን?
- የትኛው ሰው ነው ከፍተኛ አደጋ የገጠመው?
- ለጌዴዎንና ለከፍያለው ምን ምክር ይሰጧቸዋል?

⚠ **ጠቃሚ ምክር : ብዙ የገንዘብ ኃላፊነቶች መኖር ውጥረትን ውጥረትን በማምጣት የአዕምሮ ጤናን ይጎዳል። በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ስሜት ሲሰማዎት ምክር ለመጠየቅ አያወላውሉ።**

ማስታወሻዎች

የእርስዎ ተራ!

ግቦቼንና በጀቴን በማየት ግቦቼን በገንዘብ ለመደገፍ ያሰብኩት:

ግቦቼ	የተሻለው በገንዘብ የመደገፊያ መንገድ

ቁልፍ መልዕክቶች

- ግቦችዎን በገንዘብ ለመደገፍ ብዙ መንገዶች አሉ።
- እያንዳንዱ አማራጭ የራሱ ምክንያትና ለፍላጎትዎና ላቀረቡት ጥያቄ/ፕሮፖዛል የበለጠ ተስማሚውን አማራጭ በጥንቃቄ መረዳትና መገምገም ያስፈልጋል።
- የተለያዩ የፋይናንስ መንገዶችን/አማራጮችን መቀላቀል ይችላሉ። (መበደርና መቆጠብ)
- ለቤተሰብዎ በተለይም በግቦችዎ ለሚሳተፉ (ባል/ሚስት፣እናትና አባት፣ ልጆች፣ ወንድምና እህት) ስለ ገንዘብ አማራጮች ይንገሩዋቸው።



2. ብድርዎን በብልህነት ይምረጡ!



የተለያዩ የብድር ምንጮች አሉ። እንደ ባንኮች፣አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት ወይም ልዩ የብድር ካምፓኒዎች የመደበኛው ኢኮኖሚ አካል በመሆናቸው ለማንኛውም መበደር ለሚፈልግ ሰውና ተቋም የተለየ ቅደመ ሁኔታን አስቀምጧል፡ ፡ ጥቂቶቹ ለድሆችም ቢሆን የብድር ማግኛ መንገዶችን ለማቅለል ሞክረዋል። ሌሎቹ ደግሞ የቡድኑ አባል እንዲሆኑ እንደ ኢንሹራንስ ወይም ጥቂት የቆጠቡት ገንዘብ እንዲኖርዎት ይፈልጋሉ።

ትርጉም

ብድር፡ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ኤሎች ዕዎች በማለያዝ ለሌላ ወገን ለወዳፊት በወለድ ወይም በገንዘብ ክፍያዎች የሚከፍል ገንዘብ መለጠት ነው።

ብድር/ክሬዲት፡ ተበዳሪ ዋጋ ያለው ዕቃ ላሁን ወለዶ ወዳፊት በጥቂት ቀናት ውለጥ ለአበዳሪው ከወለድ ጋር ለመመለስ የኮንትራት ለምምነት የፈፀመበት ነው።

ወለድ፡ ለተወሰነ ጊዜ ከአበዳሪው ተወለዶ ጥቅም ላይ ለዋለ ገንዘብ የሚከፈል።



የሥልጠና መርጃ መ.2.1

ከብድር ጋር የሚገናኙ ሁኔታዎችና ትርጉሞች

ብድርን ከትርጉሙ ጋር ያዛምዱ። እርግጠኛም ባይሆኑ አይጨነቁ። በዚህ መፅሐፍ መጨረሻ ለመልመጃዎች በተቀመጡ መልሶች ውስጥ እርግጠኛውን ምላሽ ያገኛሉ።

ወለድ	ለደንበኞቹ በጣም ተለማሚና/ወይም ኩርኩሯን ብድር (የቤቶችና ቁጠባ ባንክ) ለካገኝ ከባንኮችና ኮኬኦች የኬዮናንስ ተቋማተ የሚኮኪለው ሙያዊ ክፍያ።
የብድር ዳካ	ተበዳሪው ለአበዳሪው ከተበደረው ገንዘብ በተጨማሪ የተበደረውን ገንዘብ ለመመለቀም የሚኮከፍለው ተጨማሪ የገንዘብ መመጠን።
ቅጣት	ወለድን ላይጨምር አበዳሪው የለጠው ዋና የገንዘብ መመጠን።
ዋና	ኩርለዎ ዕዳዎን መኮኪይ ላይችኩ ሊቀሩ የሚኮፍልዎ ለው ማለት ነው። ይህ ለው የኩሉን/የኩሊን ፔረማ በለምምነት ወርቀቱ ካይ ኩንዲያለቀምጥ በኩበዳሪው ይጠየቃል። ዋለትናው ንብረትም ኪሆን ይችላል።
ዋለ /ማለያዣ	ኩሊ/ኩሉ ብድሩን መኮኪይ ላይችኩ ሊቀሩ ተበዳሪው ድምሩን ለኩበዳሪው መኮኪይ ይኖርበታል (ምላኬ በድንገት ንብረት ቢመረለበት፣ መኪና፣ ቁጠባዎች....)
የዕፎይታ ገዜ	ኩመኩ ገዜ በቤት መኩ ለመኩ ወይም በኮኬይ ብድርን መኮኪይ።
ኩንደገና ማለብ	ኩኩበዳሪው ተቋም ለኘሮጀክቱ ኩተቲቀድልዎ ጠቅላላ ገንዘብ ላይ በመቶኛ ተኮፍኩ ተጨማሪ ብድር ኩመመውለድዎ በቤት የተለጠዎት ገንዘብ ነው። ይህ መዋጮ በተለይ የንብረት ወይም የቁጠባ መመመረለን ኩንዲገጋ ያደርጋል።
ብድር ቶኩ መኮኪይ	ብድር በመለዱበትና የመጀመሪያ ክፍያ በሚቲፅሙበት መኳኳል ያላ የተቲቀደ ገዜ (ለሁን ይግዙ በሳኳ ይኮኪኩ)።
የቤቶችና ቁጠባ ባንክ	ኩቅጣት ውጪ የብድር ለምምነትን መለረዝ: "የመለጋገያ ገዜ" ኩቅፅበታዊ ግዝ ይኩላለኩልዎታል።
የግል መዋጮ	ኩኬዮናንስ ተቋም ብድር ለመመውለድ ያልዎትን ንብረት በዋለትና ለቀርበው ብድር መለዱ። ብድሮችን ባልኩኪኩበት መቅት ኩበዳሪው ንብረትዎን በመመውረለ ኩና በመሸጥ መኩመውን ብድርና ቅጣቶችን ማለመከለ ይችላል። ሆኖም ተበዳሪው በሞርገጅ ያለያዘውን ንብረት ግዳጁን ኩለኩኩኪለ ድረለ የንብረት ባለቤትነትን ኩያጣመውም።

ጥያቄዎች

• በእርስዎ ሀሳብ አበዳሪ በሚመርጡበት ጊዜ ምን ማመዛዘን ይኖርብዎታል?

አበዳሪ በሚመርጡበት ጊዜ ከግምት ማስገባት ያለብዎት አስፈላጊ ሁኔታዎች።

- የወለድ መጠን (ቋሚ/ተለዋዋጭ)
- ዓመታዊ የክፍያ መጠን በመቶኛ፣ የተወሰደው ብድር ትክክለኛ ዋጋ (የአሰተዳደር ወጪዎች፣ ኢንሹራንስ)
- ሊበደሩ የሚችሉት መጠን
- ብድር ለማግኘት ምን ያህል ቀላል ነው (ምሳሌ ብድሩን ከማግኘትዎ በፊት ምን ያህል ቆጠቡ፣የዋስትናው መጠን....)
- መስፈርቶች (ማቅረብ ያለብኝ ሰነዶች፣ ብድሩን እንደማገኝ ያለኝ ተስፋ፣
- ገንዘቡን በዚህ ፍጥነት እንዴት አገኙ?
- ዘግይተው በመክፈልዎ የሚኖረው ቅጣት
- ከቤትዎ ያለው ርቀት
- ዘግይቶ ሲከፈል የዕዳው መሰብሰብያ ዘዴ/መንገድ (በሕግ፣ ማሳቀቅ፣ማስፈራራት)
- የዕፎይታ ጊዜ
- ብድሩን ለተወሰነ ዓላማ የመጠቀም ግዴታ (ለቤት፣ ለምርታማ ኢንቨስትመንት.....)
- ጊዜውን ለማራዘም የመቻል ወይም የዕፎይታ ጊዜ መሰጠትን
- ሌላ/አማራጭ የገንዘብ አገልግሎቶች መፈለግ መቻል፡ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ፣ገንዘብ ማስተላለፍ፣ የወጪ ካርድ፣ ሞባይል ስልክ ወይም ኢንተርኔት አገልግሎቶች....)
- ሞት፣ሕመም ወይም የተበዳሪዎች ሁኔታ መቀየር ሲያጋጥም ያሉ ማስተካከያዎች



ቁልፍ መልዕክቶች

- የብድር አገልግሎቶችን በውጤታማነት ለመጠቀም የብድርን ቃላቶች/አበባሎች በደንብ መረዳት ያስፈልጋል።
- በተቀመጠው የመክፈያ ጊዜ መሰረት ብድሩን መክፈል የተበዳሪው ኃላፊነት ነው።
- ብድር መበደር ማለት ከባድ ነገር ነው። እንደ ቀላል አይውሰዱት።
- ሀብታም ማለት ዕዳዎቹን የሚከፍል ሰው ነው (ምሳሌያዊ አነጋገር)!
- ብድርና አበዳሪውን በብልህነት ለመምረጥ በመጀመሪያ ምን አገልግሎቶች/ምርቶች እንዳሉና አበዳሪዎች እነማን እንደሆኑ ለማወቅ በተቻለ መጠን መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል። በተገኘው መረጃ መሰረት የበለጠ ለፍላጎትዎችዎ የሚስማሙትን ምርቶች/አገልግሎቶች መምረጥ ይችላሉ።
- የሚመርጡት አበዳሪ በፕሮጀክትዎ ባሕሪይና ብድሩን በመውሰድ ሊያሳኩ ባሰቡት ግብ ላይ ይመሰረታል።

3. የብድርዎን ዋጋ ያስቡ

የመክፈል አቅም

ለምሳሌ በጥንቃቄ ካሰቡ በኋላ ፕሮጀክትዎን በገንዘብ ለመደገፍ ብድር ለመውሰድ ስለወሰኑ እንኳን ደስ አለዎት! ምንያህል እንደሚፈልጉ ስለሚያውቁ ትክክለኛውን አገልግሎት ለማግኘትና የገንዘብ ተቋሞችን ለማየት ውስጥዎን ዝግጁ አድርገዋል። ሊያገኙአቸው ከመሄድዎ በፊት ግን ብድሩን ለመክፈል ያልዎትን አቅም ጊዜ ወስደው ሊያስቡ ይገባል።

በብዙ አገሮች ውስጥ ተፈፃሚ በሚሆነው ሕግ መሰረት አንድ ሰው ዕዳውን ከእርሱ/ከእርሷ የወር ገቢ ከመቶኛ በላይ መክፈል የለበትም። ይህም እንደየ አገሩ ሁኔታ ከወር ገቢ ላይ በ30 እና 40% መካከል ይሆናል። ከተጠቀሰው በመቶኛ ካለፍን ከአቅም በላይ የሆነ የዕዳ ተጋላጭነት ይኖራል። ከዚህም በላይ ያበደረውን ሰው ከገቢው ላይ ከተወሰነው በመቶኛ በላይ ብድሩን እንዲከፍል ያደረገ የገንዘብ ተቋም በሕግ ይቀጣል። ግን መጠንቀቅ! ይህ በመቶኛ የመጨረሻው ገደብ ሲሆን ከ30% በላይ እንዲከፍል ማድረግ አይመከርም።

⚠ **ግን መጠንቀቅ!** ይህ በመቶኛ የመጨረሻው ገደብ ሲሆን ከ30% በላይ እንዲከፍል ማድረግ አይመከርም።



እንደ ምሳሌው የገመቹን የመክፈል አቅም እናሰላለን።

የግል ሁኔታ ጥናት ቁ. 1.

የገመቹ ብድር የመክፈል አቅም

ገመቹ ሁኔታዎችን በጥንቃቄ በመገንዘብ ይመራል። በትርፍ ሰዓቱ የከባድ መኪና ሾፌር ሆኖ ከሚሰራው 6,000.00 ብር ቋሚ ገቢ ያገኛል።

ገንዘቡን በነፃነት ከትንሽ ንግድ ያገኛል። አንዳንድ ጊዜ ሱቁ ጥሩ ስለሚሰራ ሌላ ገቢ አላቸው። ሆኖም ከወር ወር ይለያያል(ለዚህ ስሌት ዓላማ ይህን ተለዋዋጭ ገቢ ከግምት አይወሰድም)።

ወርሃዊ ገቢ፡ ብር 6,000.00
ዕዳዎቹን በየወሩ ለመክፈል ያለው አቅም፡ ከወርሃዊ ገቢው ላይ 30% › ብር 1,800.00

በዚህ ስሌት ላይ በመመስረት ገመቹ ከብር 1,800.00 በላይ በየወሩ መክፈል አይችልም/አይፈቅድለትም (ኮንትራት ካረገባቸው ሁሉም ብድሮች ላይ)።

ግላዊ አቅም

አሁን አንተ! ብድር ለመክፈል ያለህን አቅም አስላ።

ወርሃዊ ገቢ: 100%

ብድር ለመክፈል ወርሀዊ አቅም: ..... 30% ከወርሃዊ ገቢ

⚠ **አስፈላጊ: የመክፈል አቅምህን ከግምት ያስገባ የገንዘብ ብድር አዕምሮህ እንዲቀለው ያደርጋል።**



የሥልጠና መርጃ መ.3.1

የብድር ባሕሪያትን ዋጋ ማስላት

ገመቹ ማቀዝቀዣ የተገጠመለት ፍሪጅ ለመግዛት ብር 30,000 እንደሚያስፈልገው አስልቶ የሚከተሉትን የገንዘብ ብድሮች አገኘ። ከፍላጎቱ አንፃር ትንሹ ውድ የትኛው እንደሆነ ለመለየት እየሞከረ ነው።


የብድሩ/የውጤቱ ስም	የንግድ ባንክ	አነስተኛ የፋይናንስ ማሕበር	መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት
ዓመታዊ የመክፈል ስሌት በመቶኛ መጠን(ኤፒአር)	21.5% በዓመት	18% በዓመት	16.5% በዓመት
የብድሩ ጊዜ	3 ዓመት (36 ወሮች)	2 ዓመት (24 ወሮች)	1 ዓመት ተኩል (18 ወሮች)
በየወሩ የሚከፈለው መጠን	ብር 1,137.97	ብር 1,497.72	ብር 1,892.79
የተከፋይ ጠቅላላ መጠን (በወር የሚከፈለው የብድር መጠን x ሚከፈልባቸው ወሮች)	ብር 1,137.97 x 36 = ብር 40,966.92		
ትክክለኛው የብድር ዋጋ (መከፈል ያለበት ጠቅላላ መጠን ሲቀነስ በገመቹ የተጠየቀው የካፒታል መጠን)	ብር 40,966.92 – ብር30,000.00 = ብር 10,966.00		

ለእርስዎ!

በአነስተኛ የገንዘብ ማሕበር የተጠየቀው ብድር ትክክለኛ ዋጋ ምን ያህል ነው? (1)

እንዲሁም መንግስታዊ ባልሆነው ድርጅ የተጠየቀው ትክክለኛው የብድር ዋጋ? (2)

ገመቹ ሊያገኝ የሚችለው የመጨረሻው ውድ ብድር የትኛውን ነው? (3)



⚠ **ማስጠንቀቂያ!** ርካሹ ብድር ለገመቹ ፍላጎት እንደ አስፈላጊነቱ የበለጠ ተስማሚ ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ብድሩን በየወሩ በከፍተኛ ክፍያ መክፈል አስቸጋሪና ፈታኝ ሊሆን ስለሚችል ገመቹ በየወሩ ለማግኘት በሚጠብቀው ገቢ ላይ ይወሰናል።

(1) መከፈል ያለበት ጠቅላላ መጠን= ብር 35,945.28 (ብር 1,497.72 x 24). ትክክለኛ የብድሩ ዋጋ = ብር 5,945.28 (ብር 35,945.28 - ብር 30,000.00)።

(2) መከፈል ያለበት ጠቅላላ መጠን= ብር 34,070.22 (ብር 1,892.79 x 18). የብድሩ ዕውነተኛ ዋጋ= ብር 4,070.22 (ብር 34,070.22 - ብር 30,000.00)።

(3) ትክክለኛው መልስ መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት ነው።

የሥልጠና መርጃ መ.3.2


የሀሳብ ብሮሸሮች ብድርን ያስተዋውቃሉ



የንግድ ባንክ የምንፈልገው:

- ዓመታዊ የክፍያ ስኬት፡21.5%
- የብድሩ ጊዜ፡ 3 ዓመት
- የወር ክፍያዎች
  1,137.97ብር
  (ከ30,000.00 ብር ብድር)
- የዕፎይታ ጊዜ፡ የለም
- ከፍተኛው የብድር መጠን፡
  80,000.00ብር
- ሁኔታዎች፡
  - አነስተኛው የግል ሁኔታ፡ ምንም አይፈለግም
  - ደንበኞች ቢያንስ ከ3 ወር የባንክ ደንበኛ የነበሩ መሆን አለባቸው
- ለሥሙ ፈጣሪ የገንዘብ አገልግሎት የሌለው ወይም የሥልጠና ኮርሶች አይሰጡም ፡፡
- ደንበኞች ብድሩቸውን መክፈል እንደሚችሉ የሚገልፅ የገንዘብ መግለጫ ሚስጢር እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ ፡ ፡

አሁን ንግድዎን ለማስፈፀት የተሻለ ብድር!



የምንሰራው፡

- ዓመታዊ የክፍያ ስሌት: **18.00%**
- የብድሩ ጊዜ: **2 ዓመት**
- ወርሀዊ ክፍያዎች፡ **1,497.72 ብር (ለ30,000.00 ብር ብድር)**
- የዕፎይታ ጊዜ፡ **6 ወሮች**
- ከፍተኛው የብድር መጠን፡ **40,000.00 ብር**

ሁኔታዎች:

- ደንበኞች ለ3 ወር ሥልጠና እንዲወስዱ ይጠየቃሉ
- ለስራ ፈጣሪው በንግድ አስተዳደርና በገንዘብ አያያዝ ትምህርት ሥልጠና የመውሰድ አጋጣሚ፣
- ለክፍያ በተቀመጡት ጊዜያቶች በሙሉ ግላዊ ክትትል/ሱፐርቪዥን፣
- አነስተኛው ግላዊ መዋጮ፡ የፕሮጀክቱን ዋጋ 20%፣
- በአካል ለሚገኙ ንግዶች ብቻ፡ ብድሩ የተጠየቀላቸው ንግዶች ቢያንስ 6 ወርና ከዚያ በላይ የቆዩ መሆን አለባቸው።።
- **በገበያው የሚገኝ ረጅም የክፍያ ጊዜ፣ አነስተኛው የወለድ መጠን፣ አሁኑኑ ይምጡና ይጎብኙን!**

የእርስዎ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት የእርስዎ ምርጥ አበዳሪ



የፕሮጀክትዎችዎን ዕድገት እንደግፈለን/እናስኬዳለን/ እናካሂዳለን ፣

- ዓመታዊ የክፍያ ስሌት: 16.5%
- የብድሩ ጊዜ፡ 18 ወሮች
- ወርሃዊ የዕዳ ክፍያ፡ ብር 1,892.79 (ከተበደሩት ብር 30,000.00)
- የዕፎይታ ጊዜ፡ የለም
- ከፍተኛው የብድር መጠን፡ ብር 30,000.00

- **ሁኔታዎች፡**
  - አነስተኛው የግል መዋጮ፡ የፕሮጀክቱን ዋጋ 10%
  - ዋስ ያስፈልግዎታል
  - ብድሩን መክፈል እንደሚችሉ ለማረጋገጥ የባንክ የወጪና የገቢ ዝርዝር መግለጫዎን ማቅረብ ይኖርብዎታል፣
  - ቢያንስ ለኢንተርፕሩነርነሮች የሚሰጠውን አንድ ኮርስ የንግድ አስተዳደር/ የገንዘብ አያያዝ ትምህርት የተመለከተ ሥልጠና መውሰድ ግዴታዎ ነው፣

የሥልጠና መርጃ መ.3.3

የብድርና የአበዳሪን ባሕሪ ለመምረጥ የሚስቡ ጉዳዮችን የሚያብራራ ሠንጠረዥ (ባዶ)

ምክንያቶች	ብሔራዊ ባንክ	አነስተኛ የገንዘብ ማሕበር	ለእርስዎ የተሸለ የብድር ባንክ
ዓመታዊ የክፍያ ስሌት/ የብድሩ ዋጋ			
ብድሩን በቀላሉ ለማግኘት/ ሁኔታዎች			
እሱ/እሷ መበደር የሚችሉት መጠን			
የመከፈያ ጊዜ ፍጥነት			
የገንዘብ አገልግሎቶች ያልሆኑ ድጋፎች ወይም ማገኘት			

የእርስዎ ተራ!

የእኔ ግቦች፣ የእኔን በጀትና የእኔን የመክፈል አቅም በመመልከት የብድር አገልግሎቶች/ውጤቶች ያስፈልጉኛል?

☐ አዎ ☐ አይደለም

አዎ ከሆነ ለምን ግብ? .....


ምን ያህል መጠን? .....

አሁን ለመረጃ እንዲሆንዎት በአካባቢዎ ያሉ የገንዘብ ተቋማትን ይመልከቱና በገመቹ ሰንጠረዥ ውስጥ ይሙሉ። ግን ለተወሰነው ግብ ብድሩ ያስፈልግዎታል።

⚠ **ማስጠንቀቂያ!** የብድር ገልግሎቶችን/ውጤቶችን ለማወዳደር በአጠቃላይ ብድሩ ምንያህል ዋጋ እንደሚያስከፍልዎ መጠየቅ ይኖርብዎታል (ያም ማለት ለተበደሩት ገንዘብ ከሚከፍሉት በተጨማሪ ምን ያህል መክፈል እንዳለብዎት)። ይህም ብድር ለወሰዱት ብር የሚከፍሉትን የወለድ መጠን፣ የአስተዳደር ወጪዎች፣ ኢንሹራንስ/ለመድን ድርጅትና ሌሎች ለሚፈለጉ አገልግሎቶች የሚከፈለውን ይጨምራል። በመሰረቱ የረጅም ጊዜ ብድሮች በጣም ውድ ስለሆኑ እንደ ገመቹ አነስተኛ የወለድ መጠን ያላቸውን ብድሮች ያስተውሉ!

የአግልገሎት ስም			
ዓመታዊ ምጣኔ በመቶኛ (ዓምበመ)			
የብድሩ ጊዜ			
በየወሩ የሚከፈለው መጠን /በየወሩ መከፈል ያለበት መጠን (ወርሃዊ ክፍያው)			
የተከፋይ ጠቅላላ መጠን (የብድሩ ጊዜ X በየወሩ የሚከፈለው መጠን)			
ዕውነተኛው የብድር ዋጋ (የሚከፈለው ድምር መጠን ሲቀነስ የተጠየቀው ዋና ብድር/ካፒታል)			

ለፍላጎቴ ምርጡ ውጤት : .....



የሥልጠና መርጃ መ.3.4

መደበኛ የገንዘብን እና ኢስላሚክ ገንዘብን በመጠቀም የቤት ግዥ ሁኔታ



መደበኛ የገንዘብ ተቋም

ከአካባቢው ሕብረተሰብ አንዲት ሴት 100 የውጭ ምንዛሪ በሚያወጣ ዋጋ ንብረት መግዛት ፈለገች፡ ከባንክ ብድር ወስደው ንብረቱን ገዙና ንብረቱን ወዲያውኑ ተረከቡ። ለ 20 ዓመት ሙሉ 120 የውጭ ምንዛሪ ለወሰዱት ብድር ይከፍላሉ። የብድሩ ዋጋ 20 የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ሲሆን ሲሰላም እንደሚከተለው ነው፡ (120-100= 20)


የእስልምና ገንዘብ ተቋም

ከአካባቢው ሕብረተሰብ አንድ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሴት 100 ውጭ ምንዛሬ ዋጋ የሚያወጣ ንብረት መግዛት ፈለጉ። ባንካቸው በ100 የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ንብረቱን ገዛ (ምሳሌ ንብረቱ በእሳት የመቃጠል አጋጣሚ)። አሁን አፓርትመንቱ የባንኩ ነው፡ ፡ ባንኩ አፓርትመንቱን በ120 የውጭ ምንዛሬ ዋጋ ለሴትየዋ ሸጦላት ባለቤትነቱን ከ90 ቀናት በኋላ አስተላለፈላቸው። ገንዘቡን በ20 ዓመት ውስጥ ለባንኩ ለመክፈል ተስማሙ። የብድሩ ዋጋ 20 የውጭ ምንዛሬ መጠን ነው። (120-100 = 20)

ቁልፍ መልዕክቶች

- የብድር አገልግሎቶችን/ውጤቶችን በደንብ ለመጠቀም ሁሉንም የብድር መክፈያ ጊዜዎች በደንብ መረዳት ይኖርብዎታል።
- መበደር በጊዜው ከመክፈል ኃላፊነት ጋር ይመጣል።
- መበደር ጠንካራ ንግድ ነው። አቅልለው አይዩት!
- የብድር አገልግሎትን ለመምረጥ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማወቅና በእያንዳንዳቸው ባሕሪያቶች ላይ መረጃ መሰብሰብ ያስፈልግዎታል። ከመረጃው በመነሳት ለፍላጎትዎ የበለጠ የሚስማማዎትን የብድር ዓይነት መምረጥ ይችላሉ።

4. ባሕዕዳ እንዳይሆኑ ይጠንቀቁ!



የሥልጠና መርኻ መ.ሉ.1

ከፍተኛ ዕዳ እንዳለባቸው ማሳወቅ

ክፍል 1 ሁሕዋና ትርሐስ በቪዲዮ ስልክ እየተወያዩ ነው ፡፡

ትርሐስ:	ራሕዋ ትናንትና ከአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋም አንድ ሰው ቤታችን መጥቶ ነበር። የገንዘብ ዕዳ እንዳለብሽ ተናገረ ምን እንደምነግርሽ/እንደምልሽ አላውቅም!
ራሕዋ:	እህቴ ምንም አትጨነቂ ስለእኔ ምንም እንደማታውቂ ንገሪው ። ይረሳዋል።
ትርሐስ:	እርግጠኛ ባልሆንም አይረሳውም። ብዙ ገንዘብ የተበደርሻቸው ይመስላል! እንዲሁም ሊባኖን ከመሄድሽ በፊት ከመንደራችን አንድ ሰው ገንዘብ እንዳበደረሽ ደርሼበታለሁ።
ራሕዋ:	የትኛው ሰው? ማዕዶት ጓደኛየ?
ትርሐስ:	አይ, ማለቴ... ቆይ...ማዕዶትም ገንዘብ አበድራሽነበር?
ራሕዋ:	ስለእሱ አትጨነቂ የኔ እህት ገንዘቡን ወደ ፊት እልክላቸዋለሁ።
ትርሐስ:	ራሕዋ ባለፈው ሳምንት የምትከፍይውን ገንዘብ እንደምታገኚ ነግረሽኝ ነበር።
ራሕዋ:	አውቃለሁ! ግን ማግኘት አልቻልኩም። አዝናለሁ እህቴ፣ መሄድ አለብኝ! ደህና ሁኚ!



ክፍል 2 ሁሕዋና ጊደኛዋ ማዕዶት በስልክ እየተነጋገሩ ነው ፡፡

ማዕዶት:	እንዴት ነሽ ራሕዋ?
ራሕዋ:	አቤት... ማን ልበል?
ማዕዶት:	ማዕዶት ነኝ ከኢትዮጵያ። ታስታውሽኛለሽ?
ራሕዋ:	አስታውስሻለሁ እንዴት ነሽ ማዕዶት?
ማዕዶት:	ጥሩ አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዚህ ነገሮች ሁሉ በጣም ከባድ ሆነዋል። ስሚ የደወልኩልሽ ምክንያት ወደ ሊባኖስ እንድትሄጂ ያበደርኩሽን ብር እንድትከፍይኝ እፈልጋለሁ።
ራሕዋ:	እእ... ገንዘቡን በሚቀጥለው ሳምንት ለመላክ እሞክራለሁ። እንዲሁም እዚህ አገር ለሚገኝ ኢ መደበኛ አበዳሪ መክፈል ይኖርብኛል።
ማዕዶት:	እዛ ካለ ሕገወጥ አበዳሪም ተበድረሻል?
ራሕዋ:	አዎን! ገንዘቡን ለአስቸኳይ ጉዳይ ፈልጌው ነበር። ግን አሁን ይህ ሕገወጥ አበዳሪም ሁልጊዜ ከአገራችን ሰዎች ስለሚበደር ሊረዳ ይችላል።
ማዕዶት:	ራሕዋ አልገባኝም። እዚያ የሄድሽው.ገንዘብ አግኝተሽ ልትቆጥቢ ነበር። ግን አሁንም ትበደሪያለሽ!
ራሕዋ:	ማዕዶት ነገሮችን በጣም ታከብጃለሽ። ሁሉም ነገር በቁጥጥር ስር ነው።
ማዕዶት:	ማናልባት አንቺ ነገሮችን በጣም አቅልለሽ ታያለሽ/ ትወስጂያለሽ። ሁሉንም እንዴት ትከፍይናለሽ?
ራሕዋ:	ማዕዶት አዝናለሁ። በደንብ እየሰማሁሽ አይደለም፣ ይቆራረጣል። እደውልልሻለሁ፣ ደህና ሁኚ።

ጥያቄዎች

- ራሕዋ ምን እያደረገች ነው?
- ከብዙ አበዳሪዎች ለምን ትበደራለች?
- ራህዋ ከማን ብድር መውሰድ አለብኝ በማለት ስለተለያዩ አበዳሪዎች ምን ታስባለች?
- በራሕዋ ላይ ምን ይደርስባታል ብለው ያስባሉ?

ትርጉም

ከመመጠን በላይ ዕዳ መሆን ማለት አንድ ሰው የኩራን/የኪሲን ብድር ዕዳ ለመክፈል አለመቻል ማለት ነው።

⚠ **አስፈላጊ: ከፍተኛ የብድር ባለዕዳ በመሆንዎ ዕፍረት ሊሰማዎትና ከቤተሰብዎና ከጓደኞችዎ ጋር ያልዎትን ግንኙነት ሊጎዳ ይችላል። ራስዎን ሳያገሉ ለሚያምኗቸው ሰዎች ስለችግርዎ ይንገሩ/ይነጋገሩ።**

ከመጠን በላይ ከሆነ የብድር ዕዳ ለመራቅ የሚረዱ ምክሮች፣

- *ለመክፈል የሚችሉትን የገንዘብ መጠን ብቻ ይበደሩ።*
- *ዕዳዎን ከገቢዎ ምጣኔ ጋር ያስሉ፣ የወር ገቢዎንና በየወሩ ለብድርዎችዎ መክፈል ያብዎትን (ወርሀዊ የዕዳ ግዴታዎች)ያስሉ። ሁለቱን ቁጥሮች ያወዳድሩና ምጣኔውን ያስሉ። ብዙ ጊዜ መልሰው የሚከፍሉት የዕዳ መጠን የደመወዝዎን 30 ከመቶ*
- *ብድርዎን በሰዓቱ መክፈል ካልቻሉ ለአበዳሪዎ ታማኝ በመሆን የችግሩን ምክንያት ያስረዱ።*
- *ብድርዎን እንዴት መክፈል እንደሚችሉ ከአበዳሪዎ፣ከጓደኞችዎን ከቤተሰብዎ የሚሰጠውን ምክር ያዳምጡ።*
- *ዕዳዎን ከፍለው ለመጨረስ አንዳንድ የየቀን የኑሮ ወጪዎችዎን ይቀንሱ።*
- *የዕዳ ክፈፍያዎ ሳይደናቀፍ መክፈል እንዲችሉ ለሚያጋጥሙ አስቸኳይ ወጪዎች የሚሆን የአስቸኳይ ጊዜ ቁጠባ ይቆጥቡ።*
- *ወደ ገንዘብ ተቋም በመሄድ የባንኩን ታላፊ ያነጋግሩ።*

ዕርምጃ ይውሰዱ! ድጋፍ ለመጠየቅ እስከሚረፍድበት ጊዜ ድረስ አይጠብቁ።



የሥልጠና መርጃ መ.ፋ.2

የሚና መጫወቻ ካርዶች

የ ሚ ና መ ጫ ወ ቻ ካ ር ዶ ች

ካርድ1

እርስዎ ከራሕዋ ጓደኞች ሲሆኑ እሷም ከብዙዎቻችሁ እዳ አለባት። ዕዳዎሽዋን መክፈል ስላልቻለች ለሚደወልላት ስልክም አትመልስም።

ስለ ራሕዋ ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለመወያየትና ለመወሰን የሚረዳ አጭር ንድፍ ሀሳብ ያዘጋጁ።

የ ገ ጸ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት

የ ሚ ና መ ጫ ወ ቻ ካ ር ዶ ች

ካርድ2

እርስዎ ኢትዮጲያ ያሉ የራሀዋ ቤተሰብ አባል (እህት ፣እናት ፣ አባት) ነዋት። ራሀዋ ወደ ሊባኖስ ስትሄድ በጣም ብዙ ገንዘብ የተበደረች ሲሆን ላለፉት ወራቶች ገንዘብ ባለመላኳ ስለእሷ ተጨንቀዋል። ስለ ራሕዋ ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ለመወያየትና ለመወሰን የሚረዳን አጭር ንድፍ ሀሳብ ያዘጋጁ።

የ ገ ጸ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት

የ ሚ ና መ ጫ ወ ቻ ካ ር ዶ ች


ካርድ3

እናንተ ራሀዋ ሊባኖን ከመሄዷ በፊት ገንዘቡን ያበደራት አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋም አባላት ናችሁ።

ስለራሀዋ ሁኔታ ምን ማድረግና ምን መካፈል እንዳለባችሁ ለመወሰን የሚረዳ አጭር ንድፍ ያዘጋጁ።

የ ገ ጸ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት





ጥቂት መፍትሔዎች

ከፍተኛ ዕዳ ውስጥ ገብተው ከሆነ እነዚህ መፍትሔዎች በአበዳሪው ተቋም ቀርቦልዎታል።

- ዕዳው የሚከፈልበትን ጊዜ እንደገና ማስቀመጥ ማለትም በየወሩ እንደገና የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን መቀነስና ብድሩ የሚከፈልበትን ጊዜ ማራዘም።
- ለተወሰነ ጊዜ ክፍያውን ማቋረጥ።
- በጣም ውድ ዕዳዎችዎን (ከፍተኛ የወለድ መጠን የሚያስከፍሉትን) ለመዝጋት/ ለመክፈል ንብትዎን ይሸጡ።

ስለ ብድር ተቋምዎ የማስማማት አገልግሎቶችን የሚሰጡ አካላትን ለመጠየቅ አያመንቱ!

ቁልፍ መልዕክቶች

- ለመበደር ሲወስኑ መክፈል እንዳለብዎት ይወስኑ።
- ዕዳን ለመክፈል መበደርን ያስወግዱ!
- ከብድር የሚገኝ ገንዘብ የእርስዎ አይደለም!

አባሪዎችና ቁልፍ ሰነዶች

ገንዘብ ሊያበድሩ ለሚችሉ ተቋማት የሚጠየቁ ጥያቄዎች

- ምን ዓይነት ብድሮችን ይፈልጋሉ? በእነዚህ ብድሮች ምን ዓይነት ፕሮጀክቶችን ይደገፋሉ(ቤት መግዛት፣ ለንግድ መነሻ፣መኪና መግዣ....)?
- የወለድ መጠኑ ስንት ነው?
- እንዱሁም ምን ምን ክፍያዎችን
- ዓመታዊ የክፍያ ስሌት ምንድን ነው (ዕውነተኛው የወለድ ዋጋ ክፍያዎችን ጨምሮ)
- ለብድሩ ዋስትና እንዲሆነኝ የሚዋሰኝ ሰው አገኛለሁ? ከሆን ምን ዓይነት ዋስትናዎች?
- የውጭ አገር ሠራተኛ ከሆንኩ የዋስትናው ሁኔታ ልዩነት አለው?
- ሌላ ካለ ምን ያህል ማዋጣት አለብኝ?
- የወለድ ክፍያው ድግግሞሽ ምንድን ነው?
- የዕዳው ክፍያ የሚጀምረው መቼ ነው? (የወሩ መጀመሪያ.....)
- ዘግይቶ ቢከፈል ምን ቅጣቶች ይኖራሉ?
- የዕዳው ክፍያዎች የት ነው የሚፈፀሙት?
- የብድሩን ዋስትና ለመጨረስና ገንዘቡን ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?
- የብድር ማመልከቻየን ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ መመላለስ አለብኝ?
- ብድሩን ለማግኘት ለአበዳሪው ምን ምን ሰነዶችን ማቅረብ ይኖርብኛል/ያስፈልጋል?
- ብድሩን ከተሰጠው ጊዜ በፊት ብከፍል የቀረውን ወለድ መክፈል አለብኝ?
- ይህን ብድር ብወስድ ግዴታና ግዴታ ያልሆኑ የኢንሹራንስ አማራጮች አሉ? ካለስ ምን ያህል ያስከፍላሉ ለምንድን ነው የሚሆነው?
- ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ለተዘጋጁና ለተመላሾች ጭምር ያንተ አገልግሎቶች/ውጤቶች/ ምርቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ?
- ዕዳየን መክፈል የምፈልግበት ቢሮ ከምኖርበት/ ከንግድ ቦታየ ምን ያህል ሩቅ ነው?
- ብድሬን ለማግኘት ስብሰባዎችን መካፈል አለብኝ?
- ይህ ስብሰባ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል?
- ከሌሎች ተቋማት ብድር እንዳለብኝ አጣርተሃል?

ለመልመጃዎች መልስ:

የተለያዩ የገንዘብ ብድር/ማሳደጊያ መንገዶች ጥቅምና ጉዳት (የሥልጠና መርጃ መ.3.1)



የተለያዩ የገንዘብ ብድር/ማሳደጊያ መንገዶች ጥቅምና ጉዳት

	ጥቅሞች	ጉዳቶች
የንብረት ሽያጭ/ሀብት	• ባለሱቆች ንብረትዎን ከገዙ በኋላ እንደገና መልሰው እንዲገዙአቸው ይፈቅዱልዎታል፣	• የንብረት ዋጋ ማጣት አደጋ • ምርታማ ከሆነ የቤተሰብ ተጨማሪ ወጪ መጨመር ወይም ከቀን ቀን ብዙ ወጪ ማውጣት
ቁጠባዎች	• ለመጠቀም ፈጣን • የግል ሀብት •ወለድ አይከፈልበትም • በገንዘቡ የፈለጉትን ያደርጋሉ (የውጭ ጣልቃ ገብነት የለበትም)	• ቁጠባዎን መጠቀም • ገንዘቡ ለረጅም ጊዜ መቆጠብ ያለበት ሲሆን ምናልባት ሁሉን ፍላጎትዎን ላያሟላ ይችላል። • ለአስቸኳይ ጊዜ የሚሆንዎት ገንዘብ/የፋይናንስ ምንጭ ያጥርዎታል
ከሕገ ወጥ አበዳሪ መበደር (ቤተሰብ፣ባለሱቅ....)	• ፈጣን • በአካባቢው ልውውጥ የሚደረግበት • የአፈፃፀም መመሪያ የሌለው	• በጣም ውድ • አደጋ/መጥፎ፡ መክፈል ካልቻሉ አበዳሪው አላሰፈላጊ ግዴታ ውስጥ ሊያስገባዎት ይችላል • አበዳሪው ቢጎዳዎት ሕጋዊ ሽፋን አያገኙም • ዕዳ ውስጥ በቀላሉ የሚያስገባ ነው
ከሕጋዊ የፋይናንስ ተቋማት መበደር (ከባንክ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ ከቪኤስኤልኤ፣ኤስኤሲሲአ፣ የቁጠባና ብድር ኮኦፕሬቲቮች)	• ፈጣን • በቀላሉ የማግኘት • ቅርበቱ • በሕጋዊ መስፈርቶች መሰረት የተመዘገበ • ምክር መስጠት የሚችል የቡድን ክፍል (በማሕበራዊ በኩል/ በጋራ መደገፍ)	• በአጠቃላይ ትንሽ ብድር ነው የሚሰጠው • ለፕሮጀክትዎ የሚስማማ የብድር ዓይነት ላይኖር ይችላል • አንዳንዴ የወለድ መጠኑ ከፍተኛ ነው • አንዳንድ አበዳሪዎች የሚሰጡት የተመዘገበ ንግድ ሲኖር ብቻ ነው።

ለመልመጃዎች መልስ:

ከብድር ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችና ትርጉሞች (የሥልጠና ድጋፍ መ.2.1)

ወለድ	ተበዳሪው የአበዳሪውን ገንዘብ ለመጠቀም ከብድሩ በተጨማሪ ለአበዳሪው የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው።
ቅጣቶች	ኩሉ/ኩሲ የተበዳሩትን መክፈል ሊያቅታቸው ለአበዳሪው የሚከፍሉት ጽምር ገንዘብ (ምሳሌ ንብረት መውረስ፣ መኪና፣ቁጠባ...)
የብድር ደላላ	ከባንኮችና ከኬኩ የገንዘብ ተቋማት ተለማሚ/ርካሽ ብድር ለደንበኛው በማግኘታቸው ከደንበኛው የሚከፈል የሙያ ክፍያ ነው (በአጠቃላይ የቁጠባ ቤቶች ብድር)።
ዋና	ወለድን ላይጨምር ከአባዳሪው የተገኘ ዋና ብድር
ዋስ/ ማስያዣ	ብድርዎን መክፈል ሊያቅትዎ የሚከፍልልዎት ሉው ሊሆን መጀመሪያ ብድሩ ሊፈቀድ ከአበዳሪው ጋር በሚጸረገው የለምምነት ወረቀት ላይ ኩሉ/ኩሲ ኩንጺፈርሙ ይጸረጋል። ፈርማውም ኩንደንብረት ሊቆጠር ይችላል፣
የግል መዋጮ	ከአበዳሪው ተቋም ተጨማሪ ብድር ከመውሰድዎ በፌት ለኘሮጀክቱ ከተፈቀደው ጠቅላላ ጽምር ላይ በመቶኛ የተወሰነ ገንዘብ የሚሰጥ ሊሆን ይህም መዋጮ የንብረት ወይም የቁጠባ መወረስን ያረጋጋል።
ሞርትጌጅ	ከገንዘብ ተቋማት ብድር ለማግኘት ንብረት በማዝያዝ ብድር መውሰድ ሊሆን ተበዳሪው ብድሩን ባይከፍል አበዳሪው ንብረቱን ሸጦ ዋናውን ብድርና ቅጣቱን ይወስዳል። ባለንብረቱ ለአበዳሪው ግዴታውን አለከከፈለ ንብረቱን ያለተዳጽሁል።
አስቀድሞ ብድሩን መክፈል	ከለምምነቱ ጊዜ በፌት ብድሩን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፌል መክፈል።
እንደገና ማሰብ	ካለቅጣት ለምምነትን መለረዝ። ሁኔታዎችን በለከነ መንገድ ማየት" ከቅፅበታዊ ብድር መውሰድ ይከላከላል።
የዕፎይታ ጊዜ	ብድሩ በተለጠበትና የብድሩ የመጀመሪያ ክፍያ በተፈፀመበት መካከል ያለው ጊዜ ነው (አሁን ይግዙ በኋላ ይክፈሉ)

ለመልመጃዎች መልስ:

የገመቹን የብድር ወጪ ማስላት (የሥልጠና መርጃ መ.3.2)

የአግልግሎቱ ስም	ጎግድ ባንክ	አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ማሕበር	መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት
ዓመታዊ የመክፈል መጠን በመቶኛ (ኤፒአር)	21.5% በዓመት	18% በዓመት	16.5% በዓመት
የብድሩ ጊዜ	3 ዓመቶች (36 ወራቶች)	2 ዓመት (24 ወራቶች)	1 ዓመት ተኩል (18 ወራቶች)
በእያንዳንዱ ወር የሚከፈለው መጠን(ወርሀዊ ክፍያዎች)	ብር 1,137.97	ብር 1,497.72	ብር 1,892.79
መከፈል ያለበት ጠቅላላ መጠን (የወለድ ጊዜ x ወርሀዊ ክፍያ)	ብር 1,137.97 x 36 = ብር 40,966.92	ብር 1,497.72 x 24 = ብር 35,945.28	ብር 1,892.79 x 18 = ብር 34,070.22
የብድሩ ዕውነተኛ ወጪ (መከፈል ያለበት ጠቀላላ መጠን ሲቀነስ በገመቹ የተጠየቀው የካፒታል መጠን)	ብር 40,966.92 – ብር 30,000.00 = ብር 10,966.00	ብር 35,945.28 - ብር 30,000.00 = ብር 5,945.28	ብር 34,070.22 - ብር 30,000.00 = ብር 4,070.22

ማስታወሻዎች

ለመልመጃዎች መልስ:

የብድርና የአበዳሪውን ባሕሪይ ለይቶ ለመምረጥና ለማሰመን የተዘጋጀ ሰንጠረዥ (ያለቀ)

(የሥልጠና መርጃ መ.3.3)

አበዳሪውንና ብድሩን ለመምረጥ የገመቹ መስፈርት

ምክንያቶች	የንግድ ባንክ	አነስተኛ ፋይናንስ ማሕበር	መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት
የብድሩ ዋጋ/ ዓመታዊ የመክፈል መጠን	• ትልቁ ዓመታዊ የመክፈል መጠን	• አማካይ አመታዊ የመክፈል መጠን	• አነስተኛ ዓመታዊ የመክፈል መጠን አነስተኛው ዕውነተኛ የብድር ዋጋ
ብድሩን ለማግኘት ቀላል/ ሁኔታዎች	• ገመቹ ከ3 ወር በላይ የዚህ ባንክ ደንበኛ ከነበረ ይቻላል። • ብድሩን መልሶ መክፈል እንደሚችል ማጋገጥ ይኖርበታል።	• ለገመቹ የግል መዋጮ ምናልባት በጣም ብዙ ይሆንበታል (30,000.00 ብር ዋጋ ላለው ፕሮጀክት 6.000,00 ብር ማዋጣት ይኖርበታል) • ለ3 ወር የሥልጠና ኮርስ መውሰድ ስላለበት መጠበቅ ይሮርበታል።	• አይቻልም ምክንያቱም የገመቹ መልሶ የመክፈል አቅም በቂ አይደለም። ብድሩን መልሶ ለመክፈል ችሎታ እንዳለው ማሳመኛ የለውም። • ለገመቹ የግል መዋጮ ተቀባይነት አለው (30,000.00, ብር ዋጋ ላለው ፕሮጀክት 3.000,00 ብር ማዋጣት ይኖርበታል) • ዋስ ካለው ይቻላል
እሱ/እሷ ሊበደሩ የሚችሉት መጠን	• በቂ መጠን	• በቂ መጠን	• በቂ መጠን
የመክፈል ድግግሞሽ	• በየወሩ	• አዎ (ለገመቹ ድጋፍ / ክትትል ለማግኘት በጣም ያስፈልገው ይሆናል)	• በየወሩ
ድጋፍና የፋይናንስ አገልግሎቶች ያልሆኑ መኖር	• አይደለም	• አዎ (ለገመቹ ድጋፍ / ክትትል ለማግኘት በጣም ያስፈልገው ይሆናል)	• አዎ (ለገመቹ ድጋፍ / ክትትል ለማግኘት በጣም ያስፈልገው ይሆናል)
መደምደሚያ	• ይህ በጣም ውዱ ብድር ነው ሆኖም ገመቹ የዚህ ባንክ ደንበኛ ቢሆን ኖሮ መጠበቅ አይኖርበትም ነበር። ምንም የሚያገኘው ድጋፍ የለም ግን በቂ የመክፈል አቅም አለው።	• ብድሩ ውድ ነው ግን ሥራ ፈጣሪዎች ድጋፍ አለው። ለገመቹ በጣም ብዙ ሊሆንበት ቢችልም የግል መዋጮን ከግምት ያስገባል።	• ይህ አነስተኛው ውድ ብድር ነው። ግን የገመቹ የመክፈል አቅም በቂ አይደለም። ብድሩን መክፈል ችሎታ እንዳለው ማረጋገጥ አይችልም።



ሠ

የገንዘብ መክፈያና ማስተላለፊያ መገልገያዎችን ይምረጡ

ሠ1. በክፍያ ካርዴ ማድረግ የምችለው
- ☐ **ሀ.** ወጪ ማድረግና መክፈል
- ☐ **ለ.** ማውጣት ብቻ
- ☐ **ሐ.** በባንክ ሂሳቤ ውስጥ ገንዘብ ባይኖረኝም ወጪ ማድረግ

ሠ2. የባንክ ካርዴ አሁን ስለተሰረቀብኝ ምን ላድርግ?
- ☐ **ሀ.** ሌባው የይለፍ ቁጥሬ ስለሌለው አያሳስበኝም። ምንም አላደርግም።
- ☐ **ለ.** ካርዱን እንዲዘጋው ወዲያውኑ ባንኬን አሳውቃለሁ
- ☐ **ሐ.** አዲስ ካርድ እንዲያወጣልኝ ወዲያውኑ ባንኬን አነጋግራለሁ

ሠ3. የገንዘብ ማስተላለፊያ የሚፈቅደው፡
- ☐ **ሀ.** የባንክ ሂሳብ ደብተር ማውጣት
- ☐ **ለ.** ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ገንዘብ ማንቀሳቀስ
- ☐ **ሐ.** ግዥዎችዎን ለመፈፃም የክፍያ ካርድ ለማግኘት፣

ሠ4. ወደ ቤት ገንዘብ ለመላክ አስተማማኙ ዘዴ ምንድን ነው?
- ☐ **ሀ.** ወደ ቤት ገንዘብ ለማምጣት ባልደረባ መጠየቅ
- ☐ **ለ.** መደበኛ ገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኛን መጠየቅ
- ☐ **ሐ.** ዘመድ መጠየቅ

መልሶች፡ ሠ1፡ሀ፤ ሠ2፡ሐ፤ ሠ3፡ለ፤ ሠ4፡ሐ

1. የክፍያ መንገዶችን በጥንቃቄ/በደህንነት ይጠቀሙ

በመጀመሪያው ሞዴል ለፍላጎትዎ የሚስማሙትን የብድርና ቁጠባ ዓይነቶችን እንዴት መምረጥ እንዳለብዎት አይተናል። አሁን ደግሞ የተለያዩ የክፍያ ዓይነቶችን እንዴት በተሻለ መጠቀም እንደሚቻል እንመለከታለን ለምሳሌ ለገዙት ዕቃ መክፈልን።

ግዥ ለመፈፀም ቢፈልጉ ክፍያ መፈፀም የሚቻልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

የተለያዩ የክፍያና የክፍያ ሥራ መንገዶች

- እጅ በእጅ
- በባንክ ካርድ
- በኢንተርኔት መክፈል
- ቀጥታ ከሂሳብዎ የሚቀነስ በባንክ አስተላላፊዎች
- ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ
- ኤሌክትሮኒክስ የክፍያ አገልግሎቶች
- በሞባይል ቀጥታ ክፍያ (በአገሪቱ ውስጥ አገልግሎቱ ካለና መስመሩ ከተያያዘ)
- ዕቃ በዕቃ...

በዚህ ሞዴል መጨረሻ የመልመጃዎች መልስ ውስጥ ባለው ሰንጠረዥ የእያንዳንዱ የክፍያ ዓይነት ጥቅምና ጉዳት የተገለፀ ስለሆነ በተጠቀሰው ቦታ ይመልከቱ።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.1.

ከድጃ፣የወርቅነሽ ጓደኛ/ባልደረባ የመጀመሪያ ካርድዋ ተሰጣት።

ወርቅነሽ በሊባኖን ቆይታዋ ከድጃ የምትባል ጥሩ ጓደኛ አፍርታለች።

ከድጃ አሁንም የምትኖረው ሊባኖን ነው። በስደተኛነት ተመዝግባለች። ትናንትና በስልክ ባደረጉት ንግግር ከድጃ በዓለም አቀፍ ድርጅት በኩል በደረሳት ካርድ ጥቂት የገንዘብ ድጋፍ እንደደረሳትና ይህም እንደ ስደተኛ መመዝገብዋን የሚገልፅ መሆኑን ለወርቅነሽ ነገረቻት። ከዲጃም በጣም ደስ ብሏታል። ምክንያቱም በካርዱ ላይ ያለውን ገንዘብ በኤቲኤም አውጥታ ከግሮሰሪ ጥቂት ፍጆታዎችን ትገዛበታለች።

ወርቅነሽም ከብዙ ዓመት በፊት የተወሰኑ ሱፐርማርኬቶች ከኢትዮጵያ ጥቂት የንግድ ባንኮች ጋር በመተባበር እነዚህን ካርዶች ተቀብለው እንደነበር ትዝ አላት። እነዚህ ካርዶች አሁንም እንዳሉ አላወቅችም ነበር።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.2.

የዳዊት የመጀመሪያ ካርድ

በመጨረሻም ዳዊት የባንክ ሂሳብ ከፈተ። ይህ ሂሳብም ዳዊት መጠቀም የጀመረውን የባንክ ካርድ ያካትታል። በመጀመሪያ በኤቲኤም ገንዘቡን አውጥቶ የመብራት ክፍያውን ከፍሎ ቀሪ ገንዘቡን አረጋገጠ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ከኃይለኛ ጉንፋኑ ገና ያላገገመ ስለሆነ በቅርብ ቀን ወደ ተከፈተ አዲስ ሱቅ በመሄድ ግማሽ ኪሎ ስጋ፣ እንጀራና ግማሽ ሊትር ወተት ገዛ። ቤቱ እንደደረሰ ሣዑዲ አረቢያ የሚኖረው ጓደኛው አባይነህ ጋ በመደወል ስለአዲሱ ካርዱ ነገረው፡ ፡ አባይነህም እሱም ካርድ እንዳለውና ዳዊት ወደ ሣዑዲ አረቢያ ሲመለስ ካርዱን ኢትዮጵያ ላለው የቁጠባ ሂሳቡ ሊጠቀም እንደሚችል ነገረው። ዳዊትም በአዲሱ ካርዱ በጣም ተደሰተ።





የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.3.

ራሕዋ የትርሐስ እህት ካርድ ትጠቀማለች

የትረሐስ እህት ራሕዋ ሊባኖስ ከገባች ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አሰሪዋ ደመዝዋን የሚከፍልበት ካርድዋን ከባንክ ወሰደች። በመጀመሪያ ብዙ ወጪዎች ስላሉዋት በካርዱ ብዙ ትጠቀማለች። ቀናቶች ሲያልፉ ራሕዋ ካርድዋን ካለምንም ጥንቃቄ ለሁሉም ወጪዎቿ ሁሉ ትጠቀማለች። ሁልጊዜ ወጪዎቿን በሳምንቱ ውስጥ ማረጋገጥ እንዳለባት ታስባለች ሆኖም ለማድረግ ጊዜ አላገኘችም። በመጀመሪያው ወር መጨረሻ ካርድዋን ካገኘች በኋላ ወጪዎቿን የሚሸፍን ገንዘብ በካርዱ ውስጥ እንደሌለ ተገነዘበች። ወለድ መክፈል እንዳለባትና ካልከፈለች ከባድ ሁኔታ እንደሚገጥማት ተረዳች።

ትርጉም

በቅድሚያ የተከፈለ ወይም የገንዘብ/የጥሬ ገንዘብ ካርዶች

በቅድሚያ የተከፈለ ካርድ አውቶማቲክ የክፍያ ማሺን(ብዙ ጊዜ በምህፃረ ቃል ኤቲኤም የሚባል) በተባለ ውስጥ ካርድዎን በማስገባት ከባንክ ሂሳብዎ ገንዘብ እንዲያወጡ ይፈቅድልዎታል። ገንዘብ ከማውጣት በተጨማሪ በሂሳብዎ የቀረውን የገንዘብ መጠን ማረጋገጥ ይችላሉ። በዚህ ካርድ ምግብ፣ነዳጅ፣ ልብስ ይገዛሉ እንዲሁም የሚከፍሉት ሰው ካርድ የሚቀበል ከሆነ የቤት ኪራይዎንም በዚህ ካርድ መክፈል ይችላሉ። የተጠቀሙት ገንዘብም ወዲያውኑ በባንክ ካልዎት ቀሪ ሂሳብ ላይ ይቀነሳል። አንዳንድ ካርዶች ሌሎች አገልግሎቶችን ከፍለው በሞባይል ስልክዎ ላይ እንደገና ተመዝግቦ እንዲታይ ያደርጋል። እያንዳንዱ ባንክ የራሱ ኤቲኤሞች መረብ አለው። ግን ብዙ ጊዜ የራስዎን ባንክ ካርድ በመጠቀም ከየትኛውም ባንክ ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ። ሆኖም ኤቲኤም በተጠቀሙ ቁጥር የባንክዎች ሌላው መረብ ስለሆነ ባንክዎ የአገልግሎት ያስከፍልዎታል። መጠቀም ያለብዎት በባንክ ሂሳብዎ ያስቀመጡትን ቀሪ ብቻ ነው። በአገሩ መሰረት እንደፈለጉ እንደገና በመሙላት በኤቲኤሞች፣ በባንክ በማስተላለፍ፣ወይም የመረብ ወኪሎችንም ቢሆን መጠቀም ይችላሉ። ይህንን ካርድ ያገኙት በድርጅት በኩል ከሆነ በየጊዜው ስለሚሞሉልዎት(ለምሳሌ በየወሩ) በየጊዜው ወደሂሳብዎ የሚገባውን ገንዘብ መቁጠር ይችላሉ።

የክፍያ ካርድ

ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒክስ በባንክ እንዲፈፀም የሚፈቅድ የክፍያ ካርድ ነው። በተጨማሪም ከኤቲኤም ገንዘብ ለማውጣት፣ከብዙ ሱቆች ለገዙት ዕቃ ገንዘብ ለመክፈል የክፍያ ካርድ መጠቀም ይችላሉ።
ግዥ የፈፀሙበት የገንዘብ መጠን ወዲያውኑ ከባንክ ሂሳብዎ ስለሚቀነስ ግዥ በሚፈፅሙበት ወቅት በባንክ ሂሳብዎ ውስጥ በቂ ገንዘብ ሊኖርዎ ይገባል። በቤት ባንክዎ ወይም በሞባይል ስልክዎ በየጊዜው ቀሪ ሂሳብዎን ይከታተሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ከባንክ ሂሳብዎን በዝርዝር የሚገልፅ ሰነድ እንዲሁም ከሂሳብዎ የተቀነሰውን ድምር መጠንና ቀሪ ሂሳብዎን ጨምሮ የሚገልፅ ሰነድ ከባንክ ሊያገኙ ይችላሉ።

ክሬዲት ካርድ

በአጠቃላይ የብድር ካርድ እንደ ቅድሚያ የተከፈለ/የጥሬ ገንዘብ ካርድ አንድ ዓይነት ግብይቶችን ማድረግ እንዲችሉ ይፈቅድልዎታል፡ ፡ ዋናው ልዩነት ፈጣን ብድር እንዲጠቀሙ ይፈቅድልዎታል/ይረዳዎታል። በባንክ ሂሳብዎ ገንዘብ ባይኖርዎት የብድር ካርድ ከሸጠልዎት የገንዘብ ተቋም (የገንዘብ ተቋማት፣ ከሱቆች ክፍል...) ብድር በመውሰድ ከሱቅ ግዥ መፈፀም ይችላሉ።
በብድር ካርድ ግዥ ስምምነት ሁኔታ ግዥ የፈፀሙበት /የተበደሩት ገንዘብ ከባንክ ሂሳብዎ ላይ ይቀነስብዎታል (ከኮንቬንሺናል የብድር አገልግሎተቶች/ ምርቶች ትንሽ በበለጠ የወለድ መጠን በአንዴ ወይም በብዙ ጊዜ ይከፈላል)። የብድር ካርድ ከሸጠልዎ የገንዘብ ተቋም በየጊዜው የተቆረጠብዎትን የብድር መጠን ድምርና ወለዱን የሚያሳይ መግለጫ/ስቴትመንት ይደርስዎታል። በአሁኑ ጊዜ በቀላቀሉ መረጃውን በኢንተርኔት መረዳት ይችላሉ።

ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳዎች /ኤሌክትሮኒክስ ቦርሳዎች



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.4.

ጫልቱ የአገልግሎት ክፍያዋን በሞባይል ስልክዋ ከፈለች



የገመቹ ባለቤት ጫልቱ ከጎረቤትዋ ከአያንቱ ጋር ታወራለች። አያንቱ ወደ ፀጉር ቤትዋ አብረው እንዲሄዱ ነግራት እንገናኝ ተባባሉ።

ጫልቱ ግን መሄድ ብትፈልግም ለልጅዋ ልደት መስራት ያለባት ብዙ ሥራ ይጠብቃታል። ለአያንቱ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያ መፈፀም ስላለባት ወደ የመብራት ክፍያ ቦታ እንደምትሄድም ነገረቻት። ጫልቱም ክፍያ ቦታ መሄድ አይጠበቅብሽም ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ በመጠቀም በስልክሽ መክፈል ስለምትችይ መተገበሪያውን ማውረድ ብቻ ይጠበቅብሻል አለቻት። ጫልቱም ስለዚህ ሁኔታ ቀደም ሲል ሰምታ ስለማታውቅ በጣም ተገረመች።

አያንቱም ደረጃ በደረጃ እንዴት መተገበሪያውን ማውረድና ክፍያውን መፈፀም እንዳለባት አሳየቻት። ጫልቱም እንዴት አፕሊኬሽኑን ማውረድ እንዳለባት ጥያቄዎች አሏት። ከቴክኖሎጂ ጋር ብዙም ስላልተለማመደች ስህተት እንዳትሰራ ፈራች ሆኖም አያንቱ ይህንን ክፍያ ለመፈፀም እንደምትረዳት ነገረቻት። ጫልቱም መተገበሪያውን አውርዳ በዳደኛዋ ዕርዳታ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ክፍያዋን ፈፀመች። አሁን ከጎረቤትዋ ጋር ፀጉር ቤት የምትቆይበት ጊዜ አላት። ጫልቱ በጣም ደስ አላትና ይህንን ለገመቹ ለመንገር ብዙ መጠበቅ የለብኝም አለች!



የግል ሁኔታ ጥናት ቁ.5.

ትረሐስ የኪው አር ኮድ በመጠቀም ከፈለች

ትርሐስና እናትዋ ለተብርሃን በቅርባቸው ባለው ትልቅ ከተማ መቀሌ ውስጥ የተከፈተውን ሱቅ ለመጎብኘት ወሰኑ። በጣም የሚያምር ዘመናዊ ሕንፃ መሆኑን ሰምተዋል። እየሄዱ እያለ ለተብርሃን በቅርብ ቀን ለሚከበረው የዓደኛዋ ልደት ስጦታ መግዛት እንዳለባት አስታወሰች። ብዙ ቀለም ያለው ሻርፕ የሚሸጥበት ሱቅ አገኙ። አንድ ከመረጡ በኋላ ገንዘብ ተቀባይዋ በኮቪድ -19 ምክንያት በካርድ ወይም በዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ ለሚከፍል ማንኛውም ደንበኛ 5% ቅናሽ እንደሚያደርጉ ነገረቻቸው። ለተብርሃን ምን እንደሆነ አታውቅም ትረሐስ ግን በስልክዋ ላይ የገንዘብ ቦርሳ ዲጂታል መተገበሪያ እንዳላት አስታወሰች። ይንንም የሰማችው ከጥቂት ሳምንታት በፊት በአንድ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት በኩል ለገጠር ሠራተኞች በተሰጠው የገንዘብ አያያዝ ትምህርት ስልጠና ላይ ነበር። ሴትየዋንም በካርዱ መክፈል ትችል እንደሆነ ጠየቀቻት። ሴትየዋም አረጋግጣላት ኪውአር ኮድ እስከምታዘጋጅ እንድትጠብቃት ነገረቻትና ትረሐስም የኪው አር ስዕሉን ገንዘብ ያዥዋ ጋ ሄዳ ስካን ስታደርገው ገንዘቡ ወዲያውኑ ከዲጂታል ቦርሳዋ ወጪ ሆኖ ተከፈለ። ትረሐስም እንዲህ ዓይነት ክፍያ ስትፈፅም የመጀመሪያዎ ስለሆነ በጣም ተገረመች።


ትርጉም


በዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ ወደ ኬኬክትሮኒክ ዲቫይዝ፣ኮንካየን ከገልግሎት ወይም ሶፍትዌር ፕሮግራም በማመሳከከት ከንድ ወገን ከኬላ ወገን ጋር ዕምዎችንና ከገልግሎቶችን በኬክትሮኒክስ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ከንዲጸረግ ዖኪቅዳክ።

	ጥቅሞች	ጉዳቶች
ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ	• ከሱቆች ገንዘብ ማውጣት ይችላሉ፡ ባንክ ወይም የእጅ በእጅ ክፍያ ቦታ መሰለፍ አያስፈልግም። • የአገልግሎት ክፍያዎችን ወይም ለሰው ለመክፈል ገንዘብ ከራስዎ ጋር መያዝ አያስፈልግዎትም። • ዲጊታል የገንዘብ ቦርሳዎ በሚስጥራዊ ቁጥር የተጠበቀ ነው፣ገንዘብዎ ይጠበቃል፣ • ባንክ ቤት ሲሄዱ እንደሚያደርጉት ገንዘብ ለማስገባትም ሆነ ለማውጣት ምንም ፎርም መሙላት አያስፈልግዎትም። • ከባንክ ወይም ከኤቲኤም ገንዘብ ከማውጣት ከሱቅ ማውጣት ይቀላል። • ቸርቻሪዎች ዕውነትም ገንዘብ ያጥራቸዋል። • የባንክ ሂሳብ መክፈት አያስፈልግዎትም። ልውውጦች ወዲያውኑ ይፈፀማሉ።	• ሚስጢራዊ ቁጥርዎን/ፒን ሊረሱ ይችላሉ። • ሞባይል ስልክዎ ተሰርቆብዎት ይሆናል። • ባልዎት በጀት ለመወሰን ያስቸግራል።

የደህንነት ጉርሻዎች ለዲጂታል ቦርሳዎች/ዋሌቶች

- ለማንም ሚስጢራዊ ቁጥርዎን/ፒን ኮድዎን አይንገሩ።
- ሚስጢራዊ ቁጥርዎን/ፒን ኮድዎን ቅጂ በፍፁም ከሲም ካርድዎ አጠገብ ወይም አንድ ላይ አያስቀምጡ።
- ሚስጢራዊ ቁጥሮን/ፒን ኮድዎን እንደ መገናኛ በስልክዎ ውስጥ አያስቀምጡ።
- በተለይ ወኪሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ለተለያዩ ግብይቶች ክፍያዎችን ለማየት ይጠይቁ።
- ለሰው ገንዘብ በሚልኩበት ጊዜ ስሙንና መጠኑን ሁለቴ ከማረጋገጥዎ በፊት የሚስጢር ቁጥሩን/ፒን ኮዱን አያስገቡ።..






የጉዳይ ጥናት ቁ.6.

ዳዊት ሚስጢራዊ ቁጥሩን ረሳ

ዳዊት ጥቂት የቤት ወጪዎችን ለማድረግ ገንዘብ ከባንክ ማውጣት አለበት። ጓደኛው ጌዴዎን ቦታውን እንዲጠብቀለት ስለጠየቀውና ስለረፈደበት ከአንድ ኤቲኤም ተጠግቶ ገንዘብ ለማውጣት ሚስጢራዊ ቁጥሩን ቢፅፍም ኤቲኤሙ ሚስጢራዊ ቁጥሩ ስህተት መሆኑን አሳወቀው። ዳዊት ተገርሞ ቁጥሩን ደግሞ ቢፅፍም ማሺኑ አልተቀበለውም። ለሰከንድ ቢያስብም በጣም ተምታትቶበታል። በዚሁ ጊዜ ጓደኛው ጌዴዎን ደውሎ እንዲፈጥን ነገረው። ዳዊትም እየቸኮለ ለሦስተኛ ጊዜ ከሚስጢራዊ ቁጥሩ አንዱን በመቀየር ቢሞክርም ኤቲኤሙ ሳይቀበለው ካርዱንም ወሰደው። ዳዊትም ገንዘቡን ባለማውጣቱና ካርዱም በመወሰዱ በጣም ተናደደ!

ለክፍያ ዘዴዎ/ስልትዎ የጥንቃቄ/የደህንነት መግለጫዎች/ጉርሻዎች

- ሁልጊዜ ከበጀትዎ ገደብ/ጣራ አለመውጣትዎን እያሰቡ የክፍያ ስልትዎን/መንገድዎን በጥንቃቄ ይጠቀሙ።
- ካርድዎን፣የቼክ ደብተርዎን፣ የገንዘብ ቦርሳዎን/ዋሌቶንና ሞባይል ስልክዎን ደህንነቱ የሚጠበቅበት ቦታ ያስቀምጡ።
- ለማንም ሰው የክፍያ ካርድዎን ወይም የቼክ ደብተርዎን በፍፁም አያበድሩ።
- በባዶ ቼክ ላይ በፍፁም እንዳይፈርሙ (የብር መጠኑን ሳይገልፁ)።
- ሚስጥራዊ ቁጥርዎን በባንክ ካርድዎ ላይ አይፃፉ ወይም በአካባቢዎ አያስቀምጡ።
- ሚስጢራዊ መረጃዎን በፍፁም በኢሜል፣በኤስኤምኤስ፣በፋክስ..... አይላኩ፣
- በኢንተርኔት ግዥዎችን በሚፈፅሙበት ጊዜ ጥንቃቄ ያድርጉ። የሚጠቀሙትን ድረገፅ ደህንነት ያጣሩ (የድረገፁ አድራሻ በ"https" መጀመር አለበት፣ በስክሪኑ በታችኛው ቀኝ በኩል የፓድሎክ ምልክት መኖር አለበት...)
- በጥንቃቄና በየጊዜው የሂሳብዎን የባንክ መግለጫ /ባንክ ስቴትመንት ይከታተሉ።
- ማስረዳት የማይች[illegible] ድምር ከሂሳብዎ ከወጣ በአስቸኳይ ለባንኩ ሪፖርት ያድርጉ።



⚠ **አስፈላጊ: በተለይ የተለያዩ የክፍያ መንገዶችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ገንዘብዎን ማስተዳደር ውስብስብና በጣም አድካሚ ሥራ ሊሆንም ይችላል። ለአእምሮዎ ሰላም እንዲሆን ከላይ ያሉትን የደህንነት መግለጫዎች ይከተሉ።**

ቁልፍ መልዕክቶች

- ብዙ የገንዘብ መክፈያ መንገዶች አሉ፡ እጅ በእጅ፣መክፈያ ካርድ ወይም ክፍያ ኦፕሬሽን፣ የባንክ ማስተላለፊያ፣ ቀጥታ ወጪ መክፈያ / ቋሚ ትዕዛዝ፣ በሞባይል ስልክ ክፍያ ወይም በኢንተርኔት....
- እያንዳንዱ የመክፈያ መንገድ የተለያየ ነው። በሁሉም የፋይናንስ ውጤቶች እያንዳንዱን ዋጋ ያካትታል፣ ጥቅምና ጉዳትም አለው፣ ሁልጊዜ መክፈል በሚፈልጉት የወጪዎች ዓይነት ላይም ይወሰናል።
- የጥሬ ገንዘብ ካርድ ገንዘብ እንዲያወጡ ያስችልዎታል። የወጪ ካርድን ከቸርቻሪዎች ዕቃ ለመግዛት ሊጠቀሙ ይችላሉ (በባንክ ሂሳብዎ ያለውን ገንዘብ በመጠቀም)
- እንዲሁም ገንዘብ በማውጣትና ለሚፈፀሙ ግዥዎች ለመክፈል ያስችልዎታል፣የክፍያ ካርድ ሳይዘገይ ብድር እንዲያገኙ ያደርግዎታል (በግዥ ጊዜ በባንክ ሂሳብዎ አስፈላጊው ገንዘብ ዝግጁ ባይሆንም)።
- የገንዘብ መክፈያ መንገዶችን መጠቀም አደጋ ያስከትላል! ሁልጊዜ የገንዘብ መክፈያ መንገድዎን ከጥንቃቄ ጋር ይጠቀሙ!

2. ገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኞችን ማወቅ

በአገር ውስጥና በውጭ ወደ ገንዘብ መላክና መቀበል ስንመጣ የእርስዎን አማራጮች ልንመለከት ስለሆን የእያንዳንዱን ዘዴ ጥቅምና ጉዳት ከግምት እናስገባለን።

የጉዳዮች ጥናት ቁ.7

ትረሐስ ገንዘቡን አላገኘችም

ትረሐስ ለራሕዋ አስቸኳይ ጥሪ አደረገች። አነስተኛ የብድር ተቋሙ ገንዘቡ እንዲከፈለው እየጠየቀ ስለሆነ እንደገና ስለገንዘቡ ለመጠየቅ አንድ ሰው ወደ ቤታቸው መጣ። ራሕዋ በሆነው ተፀፅታ ለትረሐስ ገንዘቡን አሁኑኑ እንድትልክ ነገረቻት።ራሕዋ አንድ የሕገወጥ ገንዘብ ማስተላለፊያ መረብ ባለው ሰው በኩል ገንዘብ ላከች። ለዚህ ሊባኖን ለሚኖረው ሰው ጥሬ ገንዘቡንና የትረሐስን አድራሻ ጨምራ ሰጠችው። ሰውየውም ኢትዮጵያ ለሚገኘው ወኪሉ ደውሎ የተቀባይን ስምና አድራሻ ይሰጠዋል። ኢትዮጵያ የሚገኘው ወኪልም ለትረሐስ ደውሎ እቤቷ ወስዶ እንደሚሰጣት ወይም አንድ ሱቅ ድረስ መጥታ እንድትወስድ ይነግራታል።
ከብዙ ቀናት በኋላም ትረሐስ ገንዘቡን አላገኘችም ስልክም አልተደወለላትም ።ራሕዋ ሰውየውን ለማግኘት ሞክራ ነበር ግን ጠፍቷል። ከሁለት ሳምንት በኋላ ገንዘቡ በጭራሽ ስላልደረሳት ትረሐስ ከቁጠባዋ አውጥታ የእህቷን ዕዳ ከፈለች።





የጉዳዮች ጥናት ቁ 8.

ወርቅነሽ ሕጋዊ አበዳሪ ትጠቀማለች

ወርቅነሽ ለወንድሟ ገንዘብ መላክ ትፈልጋለች፣ አባይነህ ደግሞ በመንገድ ላይ አደጋ ደርሶበት ለመታከሚያ ገንዘብ የለውም። ወንድሟም የባንክ ሂሳብ ቁጥር ስለሌለው በገንዘብ አስተላላፊ ወኪል በኩል ገንዘቡን ልትልክለት ፈለገች። ሁልጊዜ የምትጠቀመው አንድ አስተላላፊ ስለሆነ የሥራ ባልደረባዋ በቅርብ ቀን ከሚሰሩበት ሆቴል አጠገብ በርካሽ ዋጋ የሚልክ አዲስ ገንዘብ አስተላላፊ መኖሩን ነገራት። ወርቅነሽም ደንበኛዋን ትታ ወደ አዲሱ ገንዘብ አስተላላፊ ለመሄድ ወሰነች። በገንዘብ ማስተላፊያ ማመልከቻ ፎርም ላይ ሞላች። ገንዘብ አስተላላፊውም አባይነህ የሚኖርበት አካባቢ የሚሰሩ ገንዘብ አሰተላላፊዎችን ዝርዝር የያዘ ወረቀት ሰጣት። ወርቅነሽም ለወንድሟ ደውላ በአካባቢው የሚቀርበውን ወኪል አድራሻ ሰጠችው። ከዛ ቀን በኋላ አባይነህ ወኪሉን አግኝቶት መታወቂያውን በማሳየት ገንዘቡን ወሰደ።ወርቅነሽም ለአባይነህ ለላከችው ገንዘብ የመላኪያ ክፍያ መክፈል ያለባት ሲሆን እሱም የበፊቱ ደንበኛዋ ከሚያስከፍላት ያነሰ ነበር።መልካም ዜና! አባይነህም ወዲያው ደውሎ ገንዘቡን መቀበሉን ገለፀላት።

ትርጉም

ሕገ ወጥ ገንዘብ ከለተካካፌ ሠራተኞች/ኮኘሬተሮች

ከነዚህ ተቋማት ቁጥጥርና ክትትል/መለክ ምክከታ በመንግለት ከዓጸፊግባቸውም።

ሕጋዊ ገንዘብ ከለተካካፌ ሠራተኞች/ኮኘሬተሮች

ከነዚህ ተቋማት ቁጥጥርና ክትትል/መለክ ምክከታ በመንግለት ዓጸፊግባቸዋል።

ሕጋዊ ገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኞች/ኦፕሬተሮች	ሕገ ወጥ ገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኞች/ኦፕሬተሮች
• ፖስታ ቤት (በአካባቢ ቢሮዎች ወይም ኢንተርኔት) • ገንዘብ ማስተላለፊያ ኢንተርፕራይዞች በገንዘብ ማስተላለፍ ልምድ ባላቸው (በኤጀንሲ በኩል ወይም በኢንተርኔት) • ባንኮች (በባንክ ቅርንጫፍ ወይም በኢንተርኔት) • ሞባይል ስልክ ገንዘብ ማስተላለፊያ አገልግሎቶች	• የሱቅ ሻጮችና ነጋዴዎች • የታክሲና መኪና ሾፌሮች • ጓደኛና ቤተሰብ

ገንዘብ አስተላላፊው ማንም ይሁን ማን ገንዘብ ለማስተላለፍ ሕጋዊም ይሁን ወይም ሕገወጡን ከመምረጥዎ በፊት ዝርዝር መስፈርቶችን ማየት ያስፈልጋል።

- የገንዘብ መላኪያ ወጪ (በላኪው የተከፈለ)
- የገንዘብ መቀበያ ወጪዎች (በተቀባዩ የተከፈለ)
- የቦታ ርቀት/አቀማመጥ (ለላኪውና ለተቀባዩ)
- ደህንነት
- ፍጥነት
- ገንዘብ ምንዛሪ ኮሚሽን (የሚቀራረብ ከሆነ)


ጥያቄዎች

- አንተ ለሰዎች ወይም ወደ ውጭ ገንዘብ ትልካለህ?

  ☐ አዎ ☐ አይደለም

- አዎ ከሆነ በምን ምክንያት?

- ምን ዘዴ ይጠቀማሉ?



ቁልፍ መልዕክቶች

- ገንዘብ ለማስተላለፍ ከአሰራር ጋር መላመድ አስፈላጊ ነው (የሚሰጡ ሰነዶች፣ወጪዎች፣ የሠራተኞች የግንኙነት መረብ.....)
- የተለያዩ የገንዘብ ማስተላለፊያ መንገዶች፡ ጥሬ ገንዘብ ለጥሬ ገንዘብ፣ከባንክ ሂሳብ ወደ ጥሬ ገንዘብ፣ ጥሬ ገንዘብ ወደ ባንክ ሂሳብ፣ ከባንክ ሂሳብ ወደ ባንክ ሂሳብ፣ ከማባይል ስልክ ወደ ሞባይል ስልክ....
- እንደ መላኪያ ወጪ፣የምንዛሪ ኮሚሽን/ቀረጥ፣ የመረከቢያ ወጪ፣ የጂኦግራፊ/የአካባቢ ቅርበት ወዘተ...) ያሉትን ባሕሪዎች በመመልከት ለፍላጎቶችዎ የበለጠ የሚስማሙትን መወስ እንዲችሉ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዘዴዎን/መንገድዎንና የራስዎን ፈፃሚ/ኦፕሬተር እንደ እራስዎና ገንዘብ እንደሚልኩለት ሰው ሁኔታ ይምረጡ።
- ደህንነቱ በሚያስተማምን መንገድ ገንዘብ ይላኩ፣ ሕጋዊ መንገዶችን በመከተል ለዘመዶችዎ ገንዘቡን የሚያወጡበትንና የሚልኩበትን ሁኔታ ያመቻቹ።

የሥልጠና መርጃ ሠ.2.1

ሕገወጥ ገንዘብ አስተላላፊዎች/ኦፕሬተሮች





የሥልጠና መርጃ ሠ.2.2

ሕጋዊ ገንዘብ አስተላለፊዎች/ኦፕሬተሮች







የሥልጠና መርጃ ሠ.2.3

በባሕሪያቸው የተመረጡ የማስተላለፊያ ዘዴዎች

የወርቅነሽ ዘዴ

ወርቅነሽ በጣም ጥሩ በሆነ ዋጋ ጨርቆች ከአዲስ አቅራቢ አገኘች። ለአዲሱ አቅራቢ ገንዘቡን የከፈለችው በባንክ በኩል የቤት ውስጥ ባንክን ተጠቅማ ነው።

የጫልቱ ዘዴ

የገመቹ ባለቤት ጫልቱ ጥቂት ክፍያዎችን ለመክፈል ዲጂታል ዋሌቷን ትጠቀማለች። እንዲሁም ገንዘብ ለማስተላለፍ ኢ - ዋሌት አገልግሎት ትጠቀማለች።

የዳዊት ዘዴ

ዳዊት ለመጀመሪያ ጊዜ ለአባቱ በሞባይል ዋሌት ገንዘብ ላከ። አባቱም በሞባይል ዋሌቱ ገንዘቡን ተቀበለ። ዳዊት ሳውዲ አረቢያ እያለ ለጓደኛው ለፍስሐ ጥቂት ገንዘብ በዚሁ መንገድ መላክ እንደሚችል ተስፋ አደረገ።

የራሕዋ ዘዴ

ራሕዋ ካለፈው መጥፎ ተሞክሮ በኋላ ለትረሐስ በገንዘብ አስተላላፊ ሰራተኛ በኩል ገንዘብ ትልካለች።

3. ገንዘብ እንዴት መቀበልና መላክ እንደሚቻል

የሥልጠና መርጃ ሠ.3.1
ገንዘብ በመላክ እና በመቀበል ላይ ያሉ ሂደቶች

ዘዴ፡ 1: በገንዘብ አስተላላፊ ሠራተኛ/ኦፕሬተር

- ባንክን ወይም የፋይናንስ ተቋማትን ያነጋግሩ ወይም ይጎብኙ (በአካል በመሄድ ወይም በኦንላየን)
- ቀላልና ፈጣን በሆነው የገንዘብ ማስተላለፊያ ቅፅ ይሙሉ፣
- የባንክ ሠራተኛውን ያነጋግሩና ለእሱ/ለእሷየሚቀጥለውን መረጃ ይስጡ:
    1. የተቀባዩን ስምና የባንክ ሂሳብ ቁጥሩን (ገንዘቡን የሚልኩለት ሰው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ካለው)፣
    2. የተቀባዩን ስምና የመታወቂያ ካርድ ቁጥር ወይም ሌላ የተቀባዩን የመታወቂያ ሰነድ ቁጥር (ተቀባየ/ገንዘብ የተላከለት ሰው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ከሌለው)፣

- በባንኩ ወይም በኤጀንሲው የተገለፀውን ጊዜ (ከጥቂት ደቂቃዎች እስከ ብዙ ቀን ሊወስድ የሚችለውን) መሰረት በማድረግ ለላኩለት ሰው ያስተላለፉላቸውን የገንዘብ መጠን ይንገሯቸው። ተቀበቀዩም ከባንኩ ወይም ከኤጀንሲው በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ ሂሳባቸው እንዲገባ በማድረግ (እርስዎ እንደገለፁት) ገንዘቡን ሊቀበሉ ይችላሉ።

- ወደ ባንክ ወይም ወኪል ጋ ይሂዱና ለባንክ ሠራተኛው የተላከውን ገንዘብና የላከውን ሰው በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ይስጡ።
- ለባንክ ሠራተኛው የእርስዎን መታወቂያ ወረቀት ወይም ሌላ የእርስዎ ማንነት የሚያረጋግጥ ሰነድ ያሳዩ።
- የባንክ ሠራተኛው ወይም ወኪሉ በኮምፒዩተር ሲስተም ጋረጋገጠ በኋላ ገንዘቡን ይሰጥዎታል።

ዜዴ 2: ደንበኛ በሆንኩበት ባንክ መጠቀም

- የባንክዎን ድረ ገፅ ያስገቡ። የሚጠቀሙበትን ስምና የይለፍ ቁጥርዎን ሞልተው ያጠናቁ።
- በሲስተሙ ውስጥ ከገቡ በኋላ ገንዘቡ ተቀንሶ እንዲላክ የፈለጉትን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይምረጡ።
- ገንዘብ አስተላልፍ/ገንዘብ ላክ የሚለውን ይጫኑ/ይንኩ። አንዳንዴ ይህ አሰራር ክፍያዎች በሚለው ስር ይገኛል።
- አንዴ በአስተላልፊ ክፍል ውስጥ ከገቡ የሚከተሉትን መረጃዎች ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል፡
    - የተፈፀመበት ቀን
    - መድረሻ፡ እዚህ ላይ ስማቸውንና/ወይም የተቀባዩን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ሞልተው ማጠናቀቅ ይኖርብዎታል።
    - የውጭ ምንዛሪ: ብዙ ጊዜ የአካባቢው/የአገር ውስጥ ገንዘብ ነው። ነገር ግን ሌላም ዓለም አቀፍ ምንዛሬ ሊሆን ይችላል።
    - መጠን: የሚተላለፈውን የገንዘብ መጠን ያስተላልፉ።
    - ጉዳዩ: የክፍያውን ጉዳይ ይምረጡ (ሀብት፣ ጥቃቅን፣ኪራይ ወይም ሌላ በመረጡት ፓኔል ውስጥ የሚመጣ)
    - መግለጫ: ይህ ለሚከፈለው ሰው መልዕክት መላክ ነው።
    - የተቀባዩ ኢሜል: ለተቀባዩ/ለተከፋዩ ማሳሰቢያ ይደርሰዋል።
- ይቀጥሉን ይጫኑ ወይም ያስተላልፉ የሚለውን ሲጫኑ በተመረጠው ቀን ገንዘቡ ይሄዳል። አንዳንድ ባንኮች ተጨማሪ የደህንነት ማረጋገጫዎችን (አጭር የጽሁፍ መልዕክት ድርጊቱን እንዲያረጋግጡ በስልክዎ ሊላክልዎት ይችላል፣ ለዚህ ድርጊት በተጨማሪ የተፈጠረ የይለፍ ቁጥር ሊሆን ይችላል) ሊፈልጉ ይችላሉ። በአጠቃላይ ገንዘብ ማስተላለፉ በትክክል መጠናቀቁን የሚገልፅ መረጃ በድረ ገፁ ወይም በኢሜልዎ ያገኛሉ።

- የባንክዎን ተቋም ድረገፅ ያስገቡ። የሚጠቀሙበትን ስምና የይለፍ ቁጥርዎን አስገብተው ያጠናቅቁ።
- አንዴ ሲስተሙ ውስጥ ከገቡ ገንዘቡን ለማን እንደላኩ የሚገልፀውን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይምረጡ። የባንክ ሂሳብ ቁጥሩን በዝርዝር ለማየት ሲገቡ አዲስ የመጣ የተላከውን የገንዘብ መጠንና ማንና መቼ እንደተላከ የሚገልፅ ዝርዝር መግለጫ ይመጣል።

ዘዴ 3: በዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ/ በኢ ዋሌት በኩል

- መተገበሪያውን በስልክዎ ላይ ይጠቀሙ። ገንዘቡን የሚወስደው/ገንዘቡ የተላከለት ሰው የሚጠቀመው መተገበሪያ ገርሶ ጋር አንድ አይነት መሆን ይኖርበታል።
  - የሞባይሎ ስልኮ ማውጫን የሚለውን በመጫን እና "ገንዘብ ላክ" የሚለውን አማራጭ ይምረጡ
  - በ"ለሚላክለት ሰው" ከስልክ ማውጫዎ፣ ከሞባይል ስልክ ቁጥርዎ ወይም ከኢሜይል አድራሻዎ ከመዘገቡት አድራሻ አንዱን መምረጥ ይችላሉ።
  - ለመላክ ያሰቡት የገንዘብ መጠን ያስገቡ፣ ገንዘቡን የሚላኩበትን ምክንያት ይምረጡ (ለምሳሌ፡- የተበደሩት ገንዘብ ወይም ትላንትና ለምግብ ከሰው የተበደሩትን ገንዘብ ለመመለስ) እና ቀጣይ ቁልፉን ይጫኑ።
  - የሚከፍሉበትን ዘዴን ይምረጡ። በኤሌክትሮኒክስ አማካኝነት በሚጠቀሙባቸው መተገበሪያዎች ፣በተለያዩ ባንኮች የሚሰጡ አገልግልቶች እንደ ሲቢ ብርና ቴሌ ብር (ኤቲም ካርድ ወይም የባንክ ሂሳብ) ጋር ያገናኟቸው ማናቸውም የመክፈያ ዘዴዎች ሊሆን ይችላል። በአዲስ ካርድ በኩል ወይም በሌላ ዘዴ ክፍያ መፈጸም ከፈለጉ መተገበሪያው ዝርዝሮችን ይጠይቅዎታል። ቀጥልን በመጫን በጠየቁት የመክፈያ ዘዴ መሠረት ገንዘቡ መላኩን ያረጋግጣል።
  - ገንዘቡ ለተቀባይ ስለመድረሱ/ ወይም ገንዝብ እንደተላከዎሎት የሞባይል መተግበሪያው ሊያረጋገግጥሎት ይችላል
  - የሞባይል መተገበሪያውን ሲከፍቱት በሂሳብ መግለጫው ላይ ያንቀሳቀሱት ገንዘብ መጠንና ቀሪ ገንዘበዎን ሊመለከቱ ይችላሉ። የገቢዎትን እና የተላከሎት ንገንዘብ መጠን በመተገበሪያ ሂደት ላይ ሊመለከቱት ይችላሉ።

ማስታወሻዎች



የሥልጠና መርጃ ሠ3.2

የገንዘብ ማስተላለፊያ ቅፅ (ለኢንርናሽናል ባንክ ማሰተላለፊያ ቅፅ)



የገንዘብ ማሰተላለፊያ ቅፅ

ቀን

የገንዘቡ መጠን:

የገንዘቡ ዓይነት

የላኪው መረጃ

የአያት ሥም፡

ሙሉ ስም፡

አድራሻ:

ስልክ ቁጥር :

የትውልድ ቀን /የተወለዱበት ቦታ:

የመታወቂያ ወይም የፓስፖርት ቁጥር

የተቀባይ መረጃ

የአያት ሥም፡

ሙሉ ስም፡

የገንዘብ ተቀባዩ መታወቂያ የሌለው ከሆነ የሚጠየቅ ሚስጥራዊ ጥያቄ:

ተጨማሪ አገልገሎት ከፈለጉ መኖሩን አረጋገጡው ተጨማሪ ክፍያ ከፍለው መጠቀም ይችላሉ፡

- [ ] በሚከተለው አድራሻ እንዲተላለፍልኝ እፈልጋለሁ
- [ ] ለተቀባዩ ስልክ እንዲደወልልኝ አፈልጋለሁ
- [ ] መልዕክት እዲደርሰው ይደረግልኝ

የደንበኛው ፊርማ

የሥልጠና መርጃ ሠ 3.2

የገንዘብ ማስተላለፊያ ቅፅ
(ለኢንተርናሽናል ባንክ ማሰተላለፊያ ቅፅ)

የገንዘብ ማሰተላለፊያ ቅፅ

ቀን

የገንዘቡ መጠን:

የላኪው መረጃ

የአያት ሥም:

ሙሉ ስም:

አድራሻ:

የባንክ ሂሰብ ቁጥር:

የተቀባይ መረጃ

የአያት ሥም:


ሙሉ ስም:

አድራሻ:

IBAN ቁጥር (የአለም አቀፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር፡- የአሃዙ ቁጥር ከ 34 መብለጥ የለበትም):

BIC ቁጥር (የባንኩ መለያ ቁጥር, የአሃዙ ቁጥር በ 8 እና በ11 መሃከል መሆን ይኖርበታል) ወይም SWIFT መለያ:

የደንበኛው ፊርማ





ጠቃሚ መልዕክቶች/መረጃዎች

- ገንዘብ ስለማስተላላፍ መከተል ስለሚገባዎት አሰራሮች ማወቅ በጣም ጠቃሚ ነው። (የሚያስፈልጉ ሰነዶች፣ስለዋጋ እና ስለ ገንዘብ አሰተላላፊ ተቋማት ማወቅ ጠቃሚ ነው)
- የተለያዩ የገንዘብ ማሰተላለፊያ መንገዶች አሉ፡- የሚከተሉት በተግባር ላይ ያሉ የገንዘብ ማሰተላለፊያ ዘዴዎች ናቸው። ጥሬ ገንዝብ በማሰተላለፍ ጥሬ ገንዘብ እንዲቀበሉ ማድረግ፣ ጥሬ ገንዘብን ወደ ተቀባይ ባንክ ሂሳብ ቁጥር ማሰተላላፍ፣ከላኪ ባንክ ሂሳብ ቁጥር ወደ ተቀባይ ሂሳብ ቁጥር ማሰተላላፍ ፣በክፍያ ካርድ በጥሬ ገንዘብ ማሰተላለፍ፣ በባንክ ክፍያ ካርድ ወደ ባንክ አካውንት ማሰተላላፍ፣ ከባንክ ካርድ ወደ ሌላ ባንክ ካርድ ማሰተላላፍ፣ ከባንክ ካርድ ወደ ተቀባይ ሞባይል ገንዘብ ማሰተላላፍ፣ ከላኪ ሞባይል ወደ ተቀባይ በሞባይል ገንዘብ ማሰተላላፍ ሲሆኑ በየጊዜው ቴክኖሎጂ እየተሸሻለ ስለሚሄድ ሌሎች የተሻሉ የመላኪያ ዘዴዎች ይኖራሉ ተብሎ ይታሰባል።
- አዳዲስ የሚመጡ የገንዘብ መላኪያ ዘዴዎች ከድሮው በተሻለ መልኩ ገንዘብ ለመላክ ምቹ ሊሆኑ ስለሚችሉ ራስዎን ከእነኚህ ዘዴዎች ጋር ለማሰተወወቅ ዝግጁ ይሁኑ።
- የእርስዎን ግላዊ ሁኔታ እና ገንዘብ የሚልኩለትን ሰው ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በተቻለ መጠን ገንዘብ የሚያሰተላፉበትን ተቋም ይመረጡ ተቋሙን ሲመርጡ የገንዘብ ማሰተላላፊያ የሚከፈለውን ዋጋን፣ ስለሚከፈለው የውጭ ምንዛሪ ኮሚሽን፣ ገንዘብ ለመቀበል ስሚከፈለው ክፍያ እና ስለ አካባቢው ቅርበት ግምት ውስጥ ያስገቡ።

አባሪ እና አስፈላጊ ሰነዶች

ገንዘብ ሲያሰተላፉ የባንክ ባለሙያውን መጠየቅ ያለቦዎት ጥያቄዎች

- *ለዘመድ/ለቤተሰብ እንዴት ገንዘብ መላክ እችላለሁ?*
- *ገንዘብ ለመላክ ምን ዓይነት ቅጾችን መሙላት አለብኝ?*
- *ገንዘብ ተቀባዩ ምን ዓይነት ቅጾችን መሙላት አለበት?*
- *ገንዘብ ለመላክ ምን ዓይነት የመታወቂያ ሰነድ ያስፈልጋል?*
- *ገንዘብ ለመቀበል ምን ዓይነት መታወቂያ ሰነድ ያስፈልጋል?*
- *ገንዘብ ለመላክ በምፈልግበት ባንክ የባንክ አካውንት ሊኖርኝ ይገባል?*
- *ተቀባዩ ሰውየተላከለትን ገንዘብ ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይወስድበታል?*
- *በስልኬ ውስጥ ባለው መተግበሪያ ገንዘብ ካስተላለፍኩ ገንዘቡን የሚቀበለው ሰው ተመሳሳይ መተግበሪያ ያስፈልገዋል?*
- *የገንዘብ ማሰተላለፊያ ዋጋ ስንት ነው?*
- *ገንዘብ ተቀባዩ ሰው የምልከውን ገንዘብ በሙሉ ያገኛል ወይስ የተላከውን ገንዘብ በሙሉ ለማግኘት ተጨማሪ ክፍያ ይጠይቃል?*
- *ገንዘብ ተቀባዩ ሰው ገንዘቡን ስለመቀበሉ በምን ዘዴ ላረጋግጥ እችላለሁ?*
- *ገንዘብ የተላለፈለት ሰው ገንዘብ እደተላከለት እንዴት ሊያውቅ ይችላል?*
- *ገንዘብ ማስተላለፌን መሰረዝ ወይም ማስተካከል እችላለሁ?*
- *ገንዘብ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ ገንዘብ ተቀባዩ በሚኖርበት አገር ምን ዓይነት የምንዛሪ ተመን አገልግሎት ላይ ይውላል? የምንዛሪው ተመን ምን ያህል ነው?*
- *ገንዘብ በአሜሪካን ዶላር ብልክ ተቀባዩ ገንዘቡን የሚያገኘው በምን ዓይነት ምንዛሪ ነው?*
- *ገንዘብ ለማሰተላለፍ ባንክ ድረስ መሄድ አለብኝ ወይስ በኢንተርኔት ወይም በፖስታቤት በኩል አገልግሎቱን ማገኘት እችላለሁ?*
- *ገንዘብ የምልክለት ሰው በሚገኝበት ቦታ የባንክዎ ቅርንጫፍ ወይም ወኪል ይኖራል?*
- *ገንዘብ የምልክለት ሰው ዲጂታል መተግበሪያ ከሌለው በስልኬ ገንዘብ መላክ እችላለ ከሆነ እኔ የላክኩትን ገንዘብ የትና እንዴት ማውጣት ይችላል?*

የመልጃዎቹ መልሶች:



የመክፈያው ዘዴ	ጥቅሞቹ	ጉዳቶቹ	ከገልግሎት
ጥሬ ገንዘብ	• ለአጠቃቀም ቀላል ነው • ህጋዊ ገንዘብ በመሆኑ ሰፊ ተቀባይነት አለው • ወጪ የለውም • ወዲያውኑ ግብይት ሊያከናውኑበት ይችላሉ	• የመሰረቅና የመጥፋት አደጋ አለው • ከተሰረቀ ወይም ከጠፋ ምንም አይነት መፍትሄ የለም • መጠኑ ብዙ የሆነ ጥሬ ገንዘብ ለማዘዋወርወይም ለመክፈል የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ገደብ ስለሚኖር በቀላሉ ለማሰተላለፍ አይቻለም • በጥሬ ገንዘብ የሚተላለፍ ግብይቶች መረጃ የላቸውም። በጀትን ለመቆጣጠርና ለማሰተዳደር አሰቸጋሪ ነው።	• በየቀኑ ለሚደረጉ ግብይቶች አነሰተኛ ገንዘብን መጠቀምን መቻል • በተወሰነ ጊዜ እና በተለየ አጋጣሚ የሚያወጡትን የገነዘብ መጠን ለመወሰን ያስችላል • የፈለጉትን እቃ ወደያውኑ መግዛት ያስችላል
የባንክ ካርድ	• ደህንነቱ የተጠበቀ ነው(በአጠቃላይ ሲታይ) • የተንቀሳቀሰው ገንዘብ መጠን፣የት ቦታ እንድሆነና ግዢ የፈጸሙበት የገንዘብ መጠን መረጃውን ማገኘት ይቻላል • ሚስጥራዊ የይለፍ ቃል ስላለው ቢሰረቅ እንኳን ሌላ ሰው እንዳይጠቀምበት መቆለፍ ይቻላል • ትልቅ ዋጋ ያላቸው ግዢዎችን በቀላሉ ማደረግ ይችላሉ • በሌላ አገር ካለ አካውንት ጋር ማገኛኘት ይቻላል (በሚኖሩበት ቦታ ብቻ ላይሆን ይችላል) • ለሌሎች ተጨማሪ አገልገሎት መጠቀም ይቻላል :- ለምሳሌ የህግ አገልግሎት፣ የአየር ትኬት ለመግዛት እና ሌሎች ገንዘብ ነክ አገልግሎቶች ማግኘት ይቻላል • ታማኝና ተጨማሪ ጥቅሞች ከሚሰጡ ደርጅቶች ጋር ማገኛኘት ይቻላል	• አንዳንድ ጊዜ ጉልህ የሆኑ አመታዊ ክፍያዎች ፣ገንዘብ ሲያወጡ የአገልግሎት ክፍያ እና ውጭ አገር ክፍያ ሲፈፅሙ ተጨማሪ ክፍያ ይጠይቃል • ያወጡት ወጪ ዝርዝር መረጃውን ያለመያዝ ስጋት አለው • በጀት ሲዘጋጅ ሊረሳ ይቻላል • በሁሉም ቦታ ሊሰራ አይችልም: ካርዱ የሚሰራው አገልግሎቱ ባለበት የሽያጭ ማዕከል ብቻ የተወሰነ ነው	• የእለት ተዕለት ግብይትና ክፍያዎችን ለመፈፀም • ወቀታዊ የሆነ ትልቅ ግዢ ለመፈፀም • እቃዎችን፣አገልግሎቶችና ተዛማጅ ጉዳዮችን ለመግዛት ለምሳሌ የአውሮፕላን ትኬትና በካርዱ መገልፈግል ከተቻለ ኢንሹራንስ ለመክፈል"

የመክፈያው ዘዴ	ጥቅሞቹ	ጉዳቶቹ	ከገልገሎት
በባንክ ማለተካካፍና ቀጥታ ተቀናሽ ሂሳብ	• ጥ|ሬ ገንዘብ መያዝ አያሰፈልግም የትም መሄድ አያሰፈልግም • በሰምንት ውስጥ በየትኛውም ግዜ ግዢ መፈጸም ይቻላል • ጥሩ ግብብይት ማግኘት ያስችላል	• ችግር ከተፈጠረ ማንንም መጠየቅ አይቻልም • ከማይታወቁ ድህረ ገጾች ግዢ የሚፈጽሙ ከሆነ የመጨበርበር አደጋ አለው • ከድህረ ገፅ በቀጥታ የሚገዙ ዕቃዎች የመተላላፍ ችግር ሊኖር ይችላል • በጀትን ሲያሰተዳዳሩ የወጪዎች መረሳት ችግር ይኖራል • የወጡ ወጪዎች ያለመመዘገበ አደጋ አለው	• ጥሩ ግብብየጥ ይገኝበታል • በንጽጽር ሲታይ ፈጣን ግዢ ይፈጸምበታል (አልባሳት፣መጻህፍት የቲያትር ትኬቶ እና የአውሮፕላን ትኬት በፍጥነት • በበበየነ መረብ በቻ የሚገኙ ዕቃዎችን ለመግዛት • የባንክ የሂሳብ ከሌሎት ክፍያዎችን ለመፈጸም ለምሳሌ የሞባይል ክፍያ • አካለዊ ግንኙነት ሳይደረግ ክፍያን ለመፈጸም (ኮቪድ-19)
ዲጂታል የኪስ ቦርሳዎች	• የባንክ ሂሳብ ቁጥር አያሰፈልግም የሞባይል ቁጥር እና ሲም ካርድ ብቻ መኖር አገልግሎቱን መጠቀም ይቻላል • በቀላላ ገንዘብ ለማሰተላለፍ/ለመላክ ያስችላል	• የስርቅ መሰረቅ አደጋ አለው • የሚስጥር/ይለፍ ቃል መረሳት አደጋ አለው • ከበጀት ጋር በተያያዘ የሚሰከተለው ችግር አለ	• ከሰዎች ጋር ሳይገኛኙ ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ ማሰተላለፍ (ኮቪድ 19) • ከሰዎች ጋር ግንኙነት ሳይደረግ ክፈውያ መፈጸም (ኮቪደ19) • በደረሰኝ በቀረቡ ክፍያዎችን ለመፈጸም

በተለያዩ የባንክ መካካል ያሉ ካርዶች ማነጻጸሪያ ሠንጠረዥ

ካርድ	ቅደመ-ክፍያ/ ጥሬ ገንዘብ	ተቀናሽ ሂሳብ	ብድር
ዓህንን ካርዱ የት መመጠቀም ዓችካኩ	• በባንኮዎት ኤቴኤም/እና ከሌላ የግንኙነት መረብ።. • የካርድ ክፍያ ከሚቀበሉ ሱቆች ውስጥ	• በባንኮዎት ኤቴኤም/እና ከሌላ የግንኙነት መረብ።.. • የካርድ ክፍያ ከሚቀበሉ ሱቆች ውስጥ	• በባንኮዎት ኤቴኤም/እና ከሌላ የግንኙነት መረብ።.. • የካርድ ክፍያ ከሚቀበሉ ሱቆች ውስጥ
በካርዱ ምን ያጸርጉበታል?	• ያለዎትን ቀሪ ሂሳብ ያረጋግጡ • ገንዘብ ያውጡ. • ገንዘብ በሂሳብዎ አስከአለዎት ድረስ ለገዙት ዕቃ ክፍያ ይፈጽሙ	• ያለዎትን ቀሪ ሂሳብ ያረጋግጡ • ገንዘብ ያውጡ. • ገንዘብ በሂሳብዎ አስከ አለዎት ድረስ ለገዙት ዕቃ ክፍያ ይፈጽሙ • ገንዘብ ወደ ሌላ ሂሳብ ያሰተላልፉ. • የሞባይ ካርድ ይሙሉ	• ያለዎትን ቀሪ ሂሳብ ያረጋግጡ • ወጪና ገቢ ያድርጉ. • ገንዘብ በሂሳብዎ አስከ አለዎት ድረስ ለገዙት ዕቃ ክፍያ ይፈጽሙ. • ባንክዎ ሂሳብ ቁጥር ገንዘብ ባይኖርም • በዱቤ ለገዙት ዕቃ ክፍል • ገንዘብ ወደ ሌላ ሂሳብ ያሰተላልፉ.. • የሞባይ ካርድ ይሙሉ
ክፍያዎቹ ወዲያውኑ ዓቢጸም ወዖለ ዓዘግዖ?	• ወዲያውኑ	• ወዲያውኑ ተቀናሽ ይሆናል	• የዘገየ ያልከፈሉት የግዢዎን ጠቅላላ ሂሳብ በወሩ መጨረሻ ላይ ይከፍላሉ። በጊዜ ውስጥ እስከከፈሉ ድረስ እና ቀሪ ሂሳብ እስከሌሎት ድረስ የወለድ ክፍያ አይጠየቁም።
ዓህንን ካርዱ ለመመጠቀም ወጪዎች/ክፍያዎች የትኞቹ ናቸው?	በአግልግሎት ሰጪው በሚሰጠው አገልግሎት የሚወሰን። ለማነጻጸር ሁሉንም መረጃዎች ማግኘት ያስፈልጋል።		



የመልጃዎቹ መልሶች:

የገንዘብ አሰተላላፊ ተቋማት ጥቅምና ጉዳት(ሠ1)

የገንዘብ አሰተላላፊ ተቃም		ጥቅሞች	ጉዳቶች
መደበኛ		• የገንዘብ ዝውሩ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አሰተማማኝ ነው • በረጅም ጊዜ ትልቅ መጠን ያለው ገንዘብ መበደር መቻል • አሰተማማኝ • ሚስጥራዊ • የአግልግሎት አማራጭ መኖር • በይፋ በሚታወቅ የባንክ ህግና ደንብ ድርጅቶቹ የታቀፉ መሆኑ • የብድር አገልግሎት በማገኝት ያለቦትን ችግሮች መወጣት መቻሉ • በሂሳብ አሰራር ላይ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶች ማገኘት • እንደሚጠቀሙበት ዘዴ አገልግሎቱ ፈጣን መሆኑ መሆኑ • ገንዘብ ለማሰተላለፍም ሆነ ለመቀበል የመወሰን ስልጣን መኖር ለምሳሌ በሞባይል ስልክ ብቻ ገንዘብ ማገኝት	• ከከተማ ራቅ ብለው ለሚገኙ ሰዎች ተደራሽ ያለመሆን • ባንክ ተጠቀመው ሲወጡ የመዘረፍ ስጋት መኖር • የስራ ሰዓት ውስን መሆን • ለትንሽ ገንዘብ መጠን ለማጣትም ቢሆን የሚያሰፈልገው መስፈርት መብዛት • የአገልግሎት ዋጋ ከፍተኛ መሆኑ • አገልግሎት ለማገኘት ረዥም ጊዜ መጠበቅ ላልተማሩ ሰዎች ለመጠቀም ከባድ መሆኑ • አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ገንዘብ መጠን ላማሰተላለፍ ገንዘብ እጥረት
መደበኛ ያልሆነ		• ዋጋ (በሚጠቀሙት አገልግሎት የሚወሰን) • በቀላሉ አገልግሎቱን ማገኘት • በአካባቢ አገልግሎቱን ማገኘት • ፈጣን መሆኑ (በሚጠቀሙት አገልግሎት የሚወሰን) • እምነት (ገንዘቡን የሚያሰተላልፉት ለረጅም ጊዜ በሚያውቁት አስተላላፊ ስለሚሆን) • የሚሞሉት አሰተዳደራዊ የሆነ ፎርም ያለመኖር	• ይህንን አገልግሎት ሌሎች የገንዘብ አዘዋዋሪ ድርጅቶች አይሰጡትም • ገንዘቡን የሚቀበሉበት ቦታ (በሱቆች ህዝብ በተሰበሰበት አደባባይ በመሆኑ) አሰተማማኝ አይደለም ለዝርፊያና ለግድያ ጋልጣል • ትልቅ መጠን ያለው ገንዘብ በህገ ወጥ መንገድ ከሃገር መውጣት (ብዛት ያለው ገንዘብ ይዞ መዘዋወር በህግ ማሰጠየቅ)) • የመዘረፍ ስጋት • ሃሰተኛ ገንዘብ



የገንዘብ ተቋማትን ማወቅና በብቃት መጠቀም

ረ/1. የፋይናንስ ተቋማት የመንግስተ ወይም የግል ድርጀት ሆነው ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ፣ ቁጠባ ፣ብድርና የክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው

- ☐ ሀ. እውነት
- ☐ ለ. ሃሰት

ረ/2. በዚህ አካባቢ በርካታ ባንኮች መኖራቸውን ተገንዝቤያለሁ

- ☐ ሀ. ወደ ባንኮቹ በመሄድ ሳቢ የሆነ የቁጣባ ወይም የብድር አግልግሎት መሰጠታቸውን መረጃ ማግኘት አለብኝ
- ☐ ለ. የባንኮቹ ፍላጎት ለሃብታም ሰዎችና ለኩባንያዎች ብቻ ነው ምንድነው ጥቅሙ
- ☐ ሐ. ወደ ባንኮቹ ሄጄ ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ ነገር ግን ብዙ ገንዘብ የለህም እንዳይሉኝ እፈራለሁ

ረ/3. የፋይናንስ ተቋማት የደንበኞቸውን ደህንንተ የሚጠበቁበት መርህ ያለሆነው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

- ☐ ሀ. ከመጠን በላይ ዕዳ እንዳይኖር መከላከል.
- ☐ ለ. ፍትሃዊና አክብሮት የተሞላበት የደንበኞች አያያዝ
- ሐ. ግልጽነት
- መ. ለደንበኞች ስጦታ ማበርከት
- ሠ. ታላፊነት ያለው ዋጋ /ተመጣጣኝ ዋጋ/
- ረ. የቀሬታ አፈታት ዘዴዎች

መልስ ረ/1 ሀ ረ/2 ሀ ረ/3 መ

1. የገንዘብ ተቋማትና ማወቅ

ትርጉም

የገንዘብ ተቋማት : የገንዘብ ተቋማት የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ሆነው ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ቁጠባ ፣ ብድርና የክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው።

ትርጉም

ባንኮች: ባንክ ማለት የባንክ ስራ ስንዲሰራ በመንግስት ፍቃድ የተሰጠው ተቋም ሲሆን በዋናነት ከህብረተሰቡ ገንዘብ በመቀበል የቁጠባ እና እና የብድር አገልግሎት የሚሰጥ ነው። ባንኮች በመንግስት ወይም በግል ይዞታ ስተያዩ አገልግሎቶች በተሰማሩ መዋዕለ ንዋይ ስንዲያፈሱ ገንዘብ ስነዲያተጠራቅሙ እና በህበረት ስራ ተደራጅተው የተለያ ምርቶች ስንዲያመርቱና ህበረተሰቡ በጋራ ስንዲጠቅም ያደርጋሉ።

ስነሥተኛ የገንዘብ ተቋማት: ጥቃቅን የኩይናስ ተቋማት ማለት ገቢያቸው ስነሥተኛ /ዝቅተኛ ስሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎች ወይም ግለሰቦች የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው። ተቋማቱ ስነሥተኛ ገንዘብ ካላቸውና በመደበኛ ባንክ አገልግሎት ማገኘት የማይችሉ እና ስነሥተኛ ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ አካላት በትንሽ የአገልግሎት ክፍያ የባንክ አገልግሎት ስንዲያገኙ ያደርጋሉ።

የኩይናንስ ኩባንያዎች: በመንግስት ፍቃድ የተሰጣቸውና ስትርፍ የተቋቋሙ ድርጅቶች ናቸው ። ሃገር ግን ከአባላቶቻቸው ሆነ ከህበረተሰቡ ገንዘብ በመቀበል ስያጠራቅሙም ወይም የቁጠባ አገልግሎት ስዬሰጡም።



ጠቃሚ ጉዳዮች

የገንዘብ ተቋማትን ለመምረጥ በሚገባ ማሰብ ያስፈልጋል

- *የገንዘብ ተቋማትን ባህሪ /አጠቃላይ ሁኔታ*
- *በተቋሙ የሚሰጠው የአካውንት አይነቶች የክፍያ ዘዴዎች እና የማስተላላፍ አገልግሎቱ እርስዎ ሊያሳኩት ካሰቡት አላማ ጋር የሚሄድ መሆኑን*

የሥልጠና መርጃ ሊ 1.1

የገንዘብ ተቋማት የሚጠየቁ ጥያቄዎች?

ተቋማትን በሚመርጡበት ጊዜ ማጤን/ከግምት ውስጥ ማሰገባትያለብዎት /ባህረያት/አጠቃላይ ሁኔታ	መጠየቅ ያለበት ጥያቄ
የገንዘብ ተቋማቱ ባህሪያት • ለአካባቢው ያላቸው ቅርበት • ፋይናንስ ተቋሙ ያለው መልካም ስምና ታማኝነት • ከፋይናንስ አገልግሎት ውጪ የሚሰጡት አግልግሎት ጥራት/ለምሳሌ የንግድ ስራ ስልጠና የሂሳብ አያያዝ ትምህርት) • የርቀት አገልግሎት እና ዋጋው (ቀሪ ሂሳብን በኢንተርኔት መጠየቅ፣ የሞባይል አጭር የፅሁፍ መልእክት ማግኘትና በስልክ የባንክ አግለግሎት ማግኘት • የሰራተኞችና የአገልግሎቱ ጥራት (አግልግሎቱን ለማገኘት የሚጠብቁበት ጊዜ፣ የደንበኞች አያያዝ ፣ የሚጠቀሙበት ቋንቋ እና የአገልግሎት ፍጥነት • በሚፈልጉበት ጊዜ ተቋሙን ማገኘት መቻል (ለመመዝገብ፣በተደጋጋሚ መገናኘት እና አባሉ ውሳኔ የመሰጠት ኃይል) • ስለሚከፈሉ ክፍያዎች ፣ስለቅደመ ሁኔታዎች እና ለደንበኞች ስለሚሰጠው አገልግሎት ያለው ግልፅነት • አገልግሎት ፈላጊዎች ስለሚሰጥ አገልግሎት (ለተማሪዎች፣ደሞዝ ተከፋይ ሰራተኞችና እና ለጡረተኞችና ለመሳሰሉት) • የሚደረጉ የበጎ አድራጎት ሥራዎች(የትብብር መዋጮዎች ፣ለሌሎች ድጋፍ ማደረግና በማህበረሰብ ልማት ድጋፍ ማደረግ) • ገንዘብ ለቤተሰባቸው ለሚልኩ ወይም የተላከላቸውን ገንዝብ የሚቀበሉ ሰዎች ዘመዶቻቸው ባሉበት አካባቢ ተቋሙ መኖሩና ተቋሙ ለመኖሪያ አባባያቸው ያለው ቅርበት	
የፋይናንስ ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት ባህሪ/የሚቁጥቡ ሲሆን • የቁጠባው ተደራሽነት/በቀላላ ገንዘብ ማውጣት መቻል እና አጠቃሙ አመቺ መሆን • የቁጠባ ሂሳብ የመክፈት ሁኔታዎች • ደህንነት • የወለድ ምጣኔ • በፋይናስ ተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎተችን በቀላሉ ማገን መቻል • የቁጠባ ክፍያ(ቅጣት እና ተጨማሪ ክፍያ) • የገንዘብ ፍሰት • የአግልግሎቱ ስነ ምግባር(ቀጣይነት ያለው የፋይናስ አገልግሎተ፣በአካቢው የሚገኝ እና እስላማዊ የፋየናንስ አገልግሎት እና የመሣሰሉት)	

የሥልጠና መርኃ ሊ 1.2

የገንዘብ ተቋማት የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሊመልሱት ከሚችሉት መልሶች ጋር

የገንዘብ ተቋማትን ሲመርጡ ሊያጤኑ የሚገባቸው ባህሪያት/ጉዳዮች	መጠየቅ ያለበት ጥየቄ
የገንዘብ ተቋማቱ ባህሪያት	
አካባቢያዊ ቅርበት	• የገንዘብ ተቋም ቅርንጫፍ በአቅራቢያዬ አለ ? በቤት አቅራቢያ ፣በስራ ቦታዬ አካባቢ ወይም በልጆቼ ትምህርት ቤት አካባቢ • የክፍያ ወይም የኤጤኤም ካርድ ካለኝ በአካባቢዬ የኤቴኤም ማሽን ይኖር ይሆን ? (በቤቴ አቅረራቢያ፣በመስሪያቤቴ አካባቢእና በሌሎች ምቹ በሆኑ አካባቢዎች ለመምሳሌ በጅምናዚየም አካባቢ ?
የገንዘብ ተቋሙ መልላም ተሞክሮና ታማኝነት (እራስዎትን፣ ጓደኞችን እና ቤተሰበዎን መጠየቅ ያለቦት ጥያቄ)	• ይህ የፋይናስ ተቋም ጥሩ ተሞክሮ አለው? • ቤተሰቦቼ ስለዚህ ፋይናንስ ተቋምን ያስባሉ? • ይህ የፋይናስ ተቋም የራስ መተማማን እንዲኖረኝ ያነሳሳኛል? • የፋይናንስ ተቋሙ ችግሮች እነዳሉበት በመገኛኛ ብዘሀን ፣ከጓደኞቼ እና ከቤተሰቦቼ ሰምቼ ይሆን ? • በፋይናንስ ተቋሙ ችግር ያገጠመው/ የደረሰበት ሰው አውቅ ይሆን ? ምን ዓይነት ችግር? እንዴት ችግሩ ተቃለለ?
ከገንዘብ አገልግሎት ውጪ የሚሰጡት አግልግሎት ጥራት/ ለምሳሌ የንግድ ስራ ስልጠና የሂሳብ አያያዝ ትምህርት	• ለደንበኞች የስልጠና አገልግሎት ይሰጣል ከሆነ በምን ርዕስ ነውስልጠናውመጠቀም የሚችለው ማነው? በነፃ ነው? • የፋይናንስ ተቋሙ በትብብር ወይም በሰፖነስርሺፕ ተግባራት ይሳተፋል? • በሰበዓዊ ተግበራት ይሳተፋል? • ደንበኞችን መዋለ ንዋያቸውንና ሂሳባቸውን እንዲያሰተዳደሩ የሚረዱ አማካሪዎች አለዎት?
የርቀት አገልግሎትና ዋጋ(ቀሪ ሂሳብን በኢንተርኔት መጠየቅ ፣በሞባይል አጭር መልዕከት ወጡትን ወጪ ማሳወቅ እና ሞባይል ባንኪንግ	• የርቅት አገልግሎት ይሰጣሉ? • ደንበኞች ያላቸውን ቀሪ ሂሳብ በኢንተርኔት በቀጥታ ማየት ይችላሉ? • ከሆነስ አግልገሎቱን ለማግኘት ሂሳብ የሚከፍት ሰው ክፍያን አይጨምርም ? • በሞባይል አጭር መልዕክት ከ የምከፈለው ክፍያን እንዳውቀው ይደረጋል?

የገንዘብ ተቋማትን ሲመርጡ ሊያጤኑ የሚገባቸው ባህሪያት/ጉዳዮች	መጠየቅ ያለበት ጥየቄ
የ ገ ን ዘ ብ ተ ቋ ማ ቱ ባ ህ ሪ ያ ት	
የአግልግሎትና የሰራተኞች ጥራት (የመጠበቂያ ጊዜያት ፣ለደንበኞች ያለ ክብር፣የሚነገረው ቋንቋ ፣ የስራው ቅልጥፍና እና የመሳሰሉት	• ባንኩ የሚከፈተው በምን ሰዓት ነው? • ደንበኛው አገልገሎቱን ከሰራተኛው ለማግኘት ? በአማካይ ምን ያህል ሰዓት ይወስዳል • አገር አቀፍ የኤቴኤም የግንኙነት መረብ አለ? • በሌላ ኤቴኤም ገንዘብ ወጪ ሲደረግ ያሰከፍለኛል? (በሌላ አካባቢ፣በውጭ አገር ወይም የሌላ ባንክ የሆነ ኤቲኤም)?
በጉብኝት/ በተቋሙ በተገኙበት ጊዜ የሚወሰን	
አሰፈላጊ ከሆነ አባል ለመሆን የሚሟሉ ሁኔታዎች	• የፋይናስ ተቋሙ አባል ለመመሆን ቅደመ ሁኔታዎች አሉ? ምንድናቸው? • ለምዝገባ ምንያህል ይጠየቃል ? የሚከፈለው በየሳምንቱ፣በየወሩ ፣በየዓመቱ ወይስ ? • አባላት በምን መቼ ይሰበሰባሉ? • አንድ ሰው ስብሰባውን እነዲሰበሰብ ይገደዳል? ከሆነስ ስበሰባው ላይ መገኘት ያለቻለ ሰው ምን ይቀጣል ? • የአባላት የመወሰን ስልጣናቸው ምንያህል ነው?
ስለሚከፈሉ ክፍያዎች ፣ስለቅደመ ሁኔታዎች እና ለደንበኞች ስለሚሰጠው አገልግሎት ያለው ግልፅነት	• በገንዘብ ተቋማት ግቢ ውስጥ ሰለሚከፈሉት ክፍያዎች ቅደመ ሁኔታዎች ይታያሉ? • ተቋሙ ገላጭ የሆኑ መረጃዎች በበራሪ ወረቀትና በበየነ መረበብ ላይ ያደርጋል? ከሆነስ መረጃውን ከበራሪ ወረቀቱና በምክር ማገኘት እችላላሁ? • መረጃዎቹን በቀላሉ መረዳት እችላላሁ? • አካወንት መክፍትና መዝጋት እንዴት አችላለሁ ምንያህል ያስከፍላል?
ለተወሰኑ ደንበኞች የተዘጋጀ አገልግሎት (ለተማሪዎች፣ለደሞወዝ ተከፋዮች እና ለጡረተኞች)	• ለእነንደኔ ዓይነት ለሆነሰው በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ የገንዘብ ነክ አገልግሎት አለ? ((ለወጣቶች፣ለባለሱቆች ለሰራተኞች፣ለሴቶች ለነጋዲዎች ወዘተ..)
የሚደረጉ የበጎ አድራጎት ሥራዎች	• ተቋማችሁ በበጎ አደራጎት ስራ ውስጥ ይሳተፋል? ከሆነስ ተጠቃሚው ማነው አካል ጉዳተኛ ልጆች ፣የታመሙ ሰዎች ወዘተ?
ገንዘብ ለሚልክ ሆነ ለሚቀበል ዘመድ ተቋሙ በውጭ አገር ሆነ በአካባቢው መኖር	• ገንዘብ ስልክም ሆ ስቀበል የገንዘብ ተቋሙ ቅርንጫፍ ቤተሰቦቼ በሚኖሩበት አካባቢ አለ? (ቤታቸው አቅራቢያ፣ በመስሪያ ቤታቸው አካባቢና አመቺ በሆነ ስፍራ),

የፋይናንስ ተቋማትን ሲመርጡ ሊያጤኑ የሚገባቸው ባህሪያት/ጉዳዮች	መጠየቅ ያለበት ጥየቄ
የ ፋ ያ ና ን ስ ተ ቋ ማ ቱ ባ ህ ሪ ያ ት	
የቁጠባ ተደራሽነት/በቀላሉ ገንዘብ ማውጣት	• በምን ያህል ጊዜ ገንዘብ ማውታት እችላለሁ? • በአንድ ጊዜ መወጣት ያለበት አነሰተኛ የገነዘብ መጠን አለ? • ከቁጠባ ሂሳብ ገንዘብ ሳወጣ የመምከፈለው ቅጣት አለ?
ለአጠቃቀም አመቺነት	• ደንበኞች ለቁጠባ ሂሳባቸው የሂሳብ መግለጫ የቀበላሉ? በምንያል ጊዜ? • ተቋሙ የስልክ/በበየነመረብ የሚሰጥ የቀጥታ አገልግሎት አለው?
የቁጠባ ሂሳብ ለመክፍት ያሉ ሁኔታዎች	• የቁጠባ ሂሳብ ለመክፈት ትንሹ የገንዘብ መጠን ስንት ነው ? • ምን አይነት ሰነዶች ማቀረብ/ማሳየት አለብኝ?
ደህንት	• የደንበኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ምን አይነት መደህን ወይም ዋሰትና አሉ?
የወለድ ምጣኔ	• ለቁጠባ ሂሳብ የወለድ መጠኑ ምን ያህል ነው? • ከሌላ ተቋም ጋር ምጣኔው እንዴት ይነጻጸራል? • ወለዱ በምን ያህል ጊዜ ይከፈላል? • ወለዱ እንዴት ይሰላል የወለድ መጠኑ ቋሚ ነው? ወይስ በየጊዜው ይለዋወጣል?
በገንዘብ ተቋሙ የሚሰጡ ሌሎች አገልግሎቶችን ማገኘት መቻል	• የገንዘብ አገልግሎት አግንቼ ሌሎች ተጨማሪ አገልግሎት ማገኘት እችላለሁ? በተሻለ የወለድ ምጣኔ ነው?
የቁጠባ ዋጋ (ክፍያ እና ቅጣት)	• ዋጋው ምን ያህል ነው? (ገንዘብ ለማሰተላለፍ ምን ያህል ያስከፍላል ገንዝብ ከኤቴኤም ለማውጣትስ?) • የቀጣባ ሂሳብን ለማሰተዳደር ምን ያህል ያሰከፍላል?
የገንዘብ ፍሰት	• ገንዘብ ለማውጣት ቀላላ ነው ቅደም ተከተሉ ምንድነው? • ከፈለኩት ተቅላላ ገንዘቤን ማውጣት እችላላለሁ? • ከተወሰነ ቀን በፊት ገንዘቡን ማውጣቴ የሚሰከፍልኝ ክፍያ ይኖራል?
የአልግሎቱ ስነምገባሮች(ቀታነት ያለው አግልግሎት፣አካባቢው፣አስላማዊ አግልግሎት)	• ገንዘብ ለማውጣት ቀላላ ነው ቅደም ተከተሉ ምንድነው? • ከፈለኩት ተቅላላ ገንዘቤን ማውጣት እችላላለሁ? • ከተወሰነ ቀን በፊት ገንዘቡን ማውጣቴ የሚሰከፍልኝ ክፍያ ይኖራል?

የእርሶ ተሞ

ከንጸ ግቤ ፣ግካዊ ሁኔታና ከና ገንዘብ ፍካንቴ መሰረት የሚከተሉትን ባህሪያት ያለውን የገንዘብ ተቋም ከመርጣለሁ

ምሳሌ፡ ለቤቴ ለቅርያቢያ የሆነ

1. . . . . .
2. . . . . .
3. . . . . .

ጠቃሚ መልእክት

- የገንዘብ ተቋማትን ሲመርጡ ባህሪያቱን በመገምገም ለርሶዎ ፍላጎት ተሰማማሚ የሆነውን ምረጡ
- የየገንዘብ ተቋማት መረጃን ከበራሪ ወረቀቶች ወይም የተቋሙን ሰራተኛ በመጠየቅ ሊያገኙ ይችላሉ
- የቁጠባ ወይም የብድር አገልግሎትን ሲመርጡ ከሌሎች በተለየ የወለድ ምጣኔውነ በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል

ማስታወሻዎች

2. የገንዘብ ተቋማትን በሁስ መተማማን መጠቀም!



የግል ሁኔታ ጥናት 1

ዳዊት ስለ ገንዘብ ተቋማት ተናገረው

ዳዊት ከጓደኛው ጌዲዮን ጋር ቡና እየጠጣ ነው። ጌዲዮን በባንክ መጥፎ ልምድ አጋጥሞታል። መረጃ ለመጠየቅ ወደ ባንክ እንደገባ የባንኩ ሰራተኛ አካውንት እንዲከፍት አሳምኖት ነበር ነገር ግን የባንክ ሂሳቡን ከከፈተ በኋላ ከፍተኛ ክፍያ እንዳለው እና በትክክል ለማይጠቀምበት አገልግሎት እየከፈለ እንደሆነም ተገንዝቧል። በችኮላ ውሳኔ በመድረሱ እየተጸፀተ ነው። ነገር ግን ዳዊት የባንክ ሂሳብ ከመክፈቱ በፊት ወደ ተለያዩ ባንኮች በመሄድ መረጃዎች እንደሰበሰበ ገለጸለት ። የባንክ ሰራተኞች የሚሰጡትን መረጃ አልቀበልም ማለት ከበድ ቢሆንም ከባንክ ሰራተኞቹ ጋር ባደረገው ውይይት በርካታ መረጃዎችን አግኝቷል ። በመጨረሻም ምንም ክፍያ ሳያስከፍሉ እና አነስተኛ ቀሪ ሂሳብ ከማይጠይቁት ባንኮች በአንዱ አካውንት ለመክፈት ወሰነ። ከዳዊት ጋር ባደረጉት ውይይት መሰረት ጌዲዮን አካውንቱን እንዴት እንደሚዘጋ ለማወቅ ወሰነ እና ልክ እንደ ዳዊት ለፍላጎቱ የሚስማማውን ለማግኘት የፋይናንስ ተቋማትን በመጎበኘት መረጃ የማሰባበሰብ ወሰነ።

ጥያቄዎች

- ጌድዮን ለምን ገንዘብ ተቋማቱን አላመናቸውም?

የገንዘብ ተቋማት ደንበኞች ታላፊነትና መብት እናዳላቸው ማውቅ ያስፈልጎታል!

ስለመብቶቹ እንማር!



⚠ **ጠቃሚ:** በገንዘብ ተቋማቱ መጥፎ ልምዶች ካጋጠሞት ገንዘቦን በአደራ ላመሰቀመጥ ይሰጋሉ ወይም ይጨነቃሉ ከመወሰነዎ በፊት ራስዎን ይጠይቁ መብት እንዳለዎ ያስታውሱ!

የሥልጠና መርጃ ሪ 2.1

የመግለጫ ካርዶች

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 1

ባንክ ሂሳብ ለመክፈት ከፈለጉ መሞላት አለብኝ። እኔን ከሞሉኝ በኋላ የጀመሩትን ሂሳብ ለመከክፈት የጀመሩትን ሂደት ለማጠናቀቅ ለባንኩ ሰራተኛ የመታወቂያ ወረቀቶትን ያቅርቡ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 2

በባንኩ በር አካባቢ በሚገኘው መቀመጫ ተቀምጨጭለሁ።የስራ ድርሻዬ ደንበኞች የባንክ የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፍቱ መርዳት ነው።የቁጠባ ሂሳብ ለመክፈት የማመልከቻ ፎርም ልሰጥዎት እችላላሁ።ተስማሚ ሊሆኖት የሚችል የቁጠባ ሂሳብ ዓይነት ለመክፈት እንዲወስኑ ልረዳዎት እችላለሁ። ባንኩ ስለሚሰጠው አገልግሎትና ስለሚሞሉት ፎርሞች ጥያቄዎች ይጠይቁኝ። ቁጠባ ሂሳብ ለመክፈትምን ዓነት ሰነድ እነደሚያስፈልግዎት ይጠይቁኝ። ነገር ግን ገንዘብ አንዳሰቀምጥልዎትና ገንዘብ እንድከፍሎት እኔን አይጠይቁኝ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 3

ሁሉን የባንኩን ሠራተኞች ሥራቸውን በትክክል ስለመስራታቸው እቆጣጠራለሁ። እንዲሁም እርስዎ ማየት የሚችሉት ሠራተኞች እና በስተጀርባ ሆነው በቢሮአቸው ውስጥ የሚሰሩ፣ የሰዎችን ሂሳብ የሚያስተዳድሩ እና ሌሎች ስራዎችን የሚሰሩ ሠራተኞችን እቆጣጠራለሁ። ሌሎች ሠራተኞች ሊፈቱት ያልቻሉት ችግር ሲያግጥሞት ወደ እኔ ይምጡ። ባንክ ሂሳብ እንድከፍትሎት ወደ እኔ አይምጡ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 4

የኔ ተግበር ገንዘብ መያዝና የሂሳብ እንቅስቃሴዎችን መመዝገብ ነው።ደንበኞች ገንዘብ ሊያሰቅምቱ ሲመጡ ገነዘባቸውን ተቀበወዬ ወደ ሂሳባቸው ገቢ አደርጋለሁ እነዲሁም ገንዘብ ለሚያወጡ ገነዘብ ወቺ አደርጋለሁ።ደነበኞች ወደ እኔ ከመምጣታቸው በፊት አሰፈላጊውን ፎርም ሞልተው ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይዘው መቅረብ አለባቸው። ምንያህል ገንዘብ በሂሳብዎ እነዳልዎትና የተላከሎት ገንዘብ መድረሱንሊተይቁኝ ይችላሉ።እኔን ግን የባንክ ሂሳብ እንድከፍትሎት አይጠይቁኝ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 5

የኔ ተግባር ባንኩን የባንኩን ሠራተኞች ደንበኞቻችንን መጠበቅ ነው።ይሄንን ለማደረግ በባንኩ የሚደረገውን እንቅስቃሴ አይኔን ሳልነቅል እከታተላለሁ።ፎርም እነዴት እነደሚሞላ እና ባንክ ሂሳብ እንዴት እንደሚከፈት እኔን መረጃ አይጠይቁኝ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 6

ባንኩ የሚሰጠውን የአገልግሎት ዓይነትና የሚሰክፈለውነ ዋጋ አሳያለሁ።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 7

በባንክ የሚከናወኑ ስራዎችን ለማገኘት የሚፈለጓቸውና ሚሞላቸው ፎርሞች በሙሉ እኔ ውስጥ ተቀምጠዋል።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 8

ከሂሳብዎ ገንዘብ ላመውጣት ከፈለጉ እኔ አጠናቀው መሙላት የስፈልጎታል።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 9

እኔን በመጠቀም ጥሬ ገንዘብ ወይም ሳንቲም ሳይጠቀሙ ለሌላ ሰው ክፍያ መክፈል ይችላሉ። እኔን ከሞሉና ከፈረሙ በኋላ አኔ ላይ ለሚታየው ሰው እንዲከፈል ለባንክ ፈቃድ ይሰጣሉ።ከሂሳብ ቁጥረዎ ባንኩ ወጪ በማደረግ ለተጠቀሰው ሰው እንዲከፈል ያደርጋል።

የ መ ግ ለ ጫ ካ ር ዶ ች ቁ ጥ ር 1 0

ገንዘብ ወደ ሂሰቦ እንዲገባ ፈከፈለጉ ሁሉንም ዝርዝር ጉዳይ የሂሳብ ቁጥሮትን ያጠናቅቁ

የዚህን መልመጃ ትክክለኛ መልሶች ከዚህ የትምህርት ከፍል መጨረሻ ላይ ያገኙታል።

ቁልፍ መልዕክቶች

- ለእርስዎ በፍላጎቱ መሠረት የሚስማማትን የገንዘብ ተቋም ለመመረጥ ተቋሙ የሚሰጠውን አገልግሎት ባህሪ ማጥናት አለበዎት።
- የገንዘብ ተቋሙን ባህሪ ለመገንዘብ በራሪ ወረቀቶችን ስለተቋሙ የተፃፎ ጽሁፎችን እና የሚፈልጉትን ጥያቄ የተቋሙን ሰራተኛች ነጻ ሆነው ይጠይቁ ለጥየቄዎ መልስ መስጠት ተግባራቸው ነው!
- ወደ ገንዘብ ተቋም ወይም ባንክ መግባት የባንክ ሂሳብ መክፈት ማለት አይደለም። መረጃ ከመሰበሰብ መጀመር ይችላሉ።
- በጽንሰ ሃሰብ ደረጃ ባንክ ለመጠቀም አስፈላጊው ሰነድ ካቀረበ ማንም ሰው ሰው ከፋይናንስ ተቋም አገልግሎት ማግኘት ይችላል። የርሶወን ፍላጎት የሚያሟላ ተቋም ማግኘት አስፈላጊ ነው።
- እንደገንዘብ ተቋም ደንበኛ መብት አለዎት!

አሁን የባንክ አካውንት ለመክፈት ቅፅ ለመሙላት እንለማማዳለን።
አጠቃላይ የማመለልከቻ ፎር እንሞላለን

የሥልጠና መረጃ 2.2

የባንክ ሂሳብ ለመክፈት የማማልከቻ ቅፅ

ባንክዎት

በ ..... የሚሞላ

የባንክ ሂሳብ ለመክፈት ማመልከቻ

የሂሳብ ባለቤት 1	**የሂሳብ ባለቤት 2**
ግላዊ ሁኔታ	**ግላዊ ሁኔታ**
ማእርግ: ☐ አቶ ☐ ወ/ሮ ☐ ወ/ት	ማእርግ: ☐ አቶ ☐ ወ/ሮ ☐ ወ/ት
የአያት ስም:	የአያት ስም:
ስም:	ስም:
የመኖሪያ አድራሻ: ፖሰታ:	የመኖሪያ አድራሻ: ፖሰታ:
ከተማ:	ከተማ:
አገር:	አገር:
የቤተሰብ: ☐ ያገባ: ☐ በፍቺ የተለያየ: ☐ የፈታ: ☐ ባሏ የሞተባት: ☐ ያላገባ:	የቤተሰብ: ☐ ያገባ ☐ የፈታ ☐ ያላገባ
የልጆች ስም:	የልጆች ስም:
የትውልድ ቀንና ቦታ:	የትውልድ ቀንና ቦታ:
ዜግነት:	ዜግነት:
ስልክ(የቤት):	ስልክ(የቤት):
ስልክ (ሞባይል):	ስልክ (ሞባይል):
ኢሜል:	ኢሜል:
የስራ ሁኔታ	**የስራ ሁኔታ**
የተጣራ የወር ገቢ: ☐☐☐☐☐☐☐☐	የተጣራ የወር ገቢ: ☐☐☐☐☐☐☐☐
☐ በስራ ላይ ያለ ☐ ፈላጊ ☐ ተማሪ ☐ ጡረተኛ	☐ በስራ ላይ ያለ ☐ ፈላጊ ☐ ተማሪ ☐ ጡረተኛ

የሂሳቡ ዓይነት

☐ የግል ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ☐ የጣምራ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ☐ የቁጠባ ሂሳብ

የባንክ ካርድ አገልግሎት

☐ ኤቲኤም ካርድ ☐ ኢንትርኔት ባንኪንግ
☐ የክፍያ ካርድ ☐ በኢንሹራንስ በኩል የሚከፈል
☐ ክሬዲት ካርድ

ፊርማ

ሀሳብ ባለቤት 1	የሂሳብ ባለቤት 2	የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ

ቀን __/__/__

የሥልጠና መርጃ ሊ 2.3

ገንዘብ ለማውጣት የኤቲኤም ካርድን መጠቀም

አሁን ከቁጠባ ሂሳብ በኤቲኤም እንዴት ማውጣት እንዳለበን እንለማመዳለን

ቅደም ተከተል 1 ኤቲኤም ካርዱን ማስገባት




የኤቲኤም ካርድዎትን በአውቶማቲክ የገንዘብ መክፈያ ማሽን ባለው ማሰገቢያ በኩል ካርድዎን ያስገቡ

ቅደም ተከተል 2 ባለ አራት አሃዝ የሚስጢር የይለፍ ቁጥሮዎትን ያስገቡ




በአውቶማቲክ ገንዘብ መክፈያ ማሽን መጻፊያ ቦታ ባለ አራ አሃዝ የሚስጢር የይለፍ ቁጥርን ይፃፉ። ሚስጥር ቁጥሮትን ሲጽፉ ማንም ሰው እንዳያይቦት ይጠንቀቁ እንዲሁም የምስጥር ቁጥርዎትን ለሌላ ሰው አሳልፈው አይስጡ። የተሳሳተ የምስጥር ቁጥርዎትን ከሶስት ጊዜ ባላይ ደጋግመው አያሰገቡ ካስገቡ የኤቲኤም ካርዶ ሊታገድብዎት ይችላል።

ቅደም ተከተል 3 ግብይትን/የገንዘብ እንቅስቃሴን መመረጥ




በዚህ ክፍል ብዙ አማራጮችን የሚወጣው ገንዘብ ልክ፣ ቀሪ ሂሳብ ጥያቄእና የመሳሰሉት በማሳያው ላይ ይመለከታሉ። ለዚህ ጉዳይ ገንዘብ ማውጣት የሚለውን ይመረጡ።

ቅደመ ተከተል 4 የሂሳብ ቁጥርዎን መምረጥ



የኤቲአም ካርድዎ ከተለያዩ የባን ሂሳብ ቁጥር ጋር ከተገናኘ ከየትኛው ባንክ ገንዘብ ማውጣት እንደፈለጉ መምረጥ ያስፈልጎታል።

ቅደም ተከተል 5 የገንዘብ መጠን መምረጥ



በዚህ ክፍል ማውጣት የፈለጉትን ገንዘብ መጠን በመጻፍ ግባ የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ። ነገር ግን ለማውጣት የፈለጉት ገንዘብ ካለዎት ቀሪ ሂሳብ መብለጥ የለበትም አለበለዚያ ጥያቄው የተሳካ አይሆንም።

ቅደም ተከተል 6 ገንዘብን መቀበል



በዚህ ክፍል በታችኛው የአውቶማቲክ ገንዘብ መክፈያ ማሽን ገንዝብ በሚወጣበት ቀዳዳ ገንዘቦዎትን መቀበል አለቦት።

ቅደም ተከተል 7 በኤቲ ኤም ሌላ አገልግሎት ለመጠቀም መመረጥ ወይም አገልግሎቱን ማጠናቀቅ።



በዚህ ጊዜ ሌላ የሚፈልጉትን አገልግሎት ለመጠቀም ከፈለጉ መቀጠል ይችላሉ አገልግሎቱን ከጨረሱ ኤቴኤም ካርድዎትን መውሰደዎን እርግጥኛ ይሁኑ።

የባንክ ደንበኛ ከሆኑ ኃለፊነትና መብት እንዳለዎት ማወቅ አለብዎት!

ማስታወሻዎች

የሥልጠና መርጃ ሊ 2.4

መርጃ ካርድ - የደንበኞች መርሆች ጥበቃ

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 1

የዶሮ እርባታ ባለቤት ነኝ።

አቅረቢያዬ ካለ የጥቃቅንና አነሰተኛ ብድር መስጫ ተቋም ብድር ለመወሰድ ተፈራርሜያለሁ።የገንዘቡ መጠን ለስራ የምፈልገው ያህል ነው።ብድርሩን ለመክፈል የተሰማማሁት በየወሩነው።

ነገር ግን ዶሮቹን ለሽያጭ አቅርቤ ገንዘብ ማገኘት የምችለው ከከሰስት ወር በኋላ ነው። ብድሩ ፍላጎቴን የሚያሟላ አይመሰለኝም።

ትክክል ነው?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 2

ባለፈው ዓመት ቤት ለመግዛትና ለሃይማኖታዊ በዓል ዝግጅት ሁለቴ ከባንክ ተበድሬያለሁ።

በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር ሞተር ሳይክል ለመግዛት ፍላጎት አለኝ። ነገር ግን ባንኩ ሶስተኛ ብድር ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም።

ትክክል ነው?
ስለብድሩ ምን ላድርግ?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 3

የባንክ ደንበኛ ነኝ።።።

ከተቋሙ የሚሰጠውን የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት በተመለከተ የሚያሰፈልግውን መሰፈርትና ክፍያዎች ለመረዳት በረሪ ወረቀት ወስጄ ነበር ነገርን በበራሪው ወረቀት ላይ ያለው ጽሀሁፍ ጥቃቅን በመሆኑ የተጻፉትን መስፈርቶች መረዳት አልቻልኩም።

ምን ላድርግ?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርዶች ቁጥር 4

በባንኩ ተንቀሳቃሰሽና የቁጠባ ሂሳብ አለኝ። ለተንቀሳቃሽ ሀሂሳቡ የሚከፈል ክፍያ ስላላ ደስተኛ አይደለሁም። እንዲሁም ለቁጠባ ሂሳቤ የሚከፈለኝ ወለድ በጣም ዝቅተኛ ነው። ሚዛናዊ አይመሰልም።

ትክክል ነው?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 5

ከስራ በመባረሬ ምክንያት ያለብኝን የባንክ እዳ ለመክፍል አልቻልኩም። ብድሩን ለመክፍል ባለመቻል ባንኩ ምን ያደርጋል ብዬ እጨነቃለሁ።

ወደ ቤቴ መጥተው የኔና የቤተሰቤን ንበረትና ሃብት ይወስዱ ይሆን የከፋ ችግር ያጋጠመኝ ይሆን?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 6

በባንኩ የሆነወን ሁሉ በጣም እቃወማለሁ።

ወዴት ልሄድ እችላለሁ ባንክ ውስጥ ሊረዳኝ የሚችል ሰው ይኖር ይሆን?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 7

የግል ተንቀሳቃሽ የባንክ ሂሳቤን የሚከታተሉ የባንኩ ሰራኞች ባለፈው ወር ከፍተኛ የገንዘብ መጠን እንተቀበልኩ ያውቃሉ።

ካለኔ ፈቃድ እሱ ከቤተሰቦቼ ጋር መወያያት ይችላል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት



ትክክለኛ አገልግሎት ማቀድና መሠጠት

የገንዘብ ተቋትየሚሰጡት አገልገሎትና የስርጭት መንገዶች የደንበኞችን ፍላጎት እንዳይጎዳ ሆኖ መታቀድ አለበት። የስርጭት መንገዶቹ የደንበኞችን ባህሪ መሰረት አደርጎ መታቀድ አለበት።

ከመጠን በላይ ባለዕዳ መሆኑን መከላከል

ገንዘብ መበደር እንደ መብት ማየት ትክክል አይደለም።አዎ የተለመደ ነገረ ነው። ባንኩ ደንበኞቻቸውን በከፍተኛ እዳ ውስጥ እንዳይገቡ ጥበቃ ያደረጋሉ። የፋይናንስ ተቋማት ደንበኞች ከባንኩ የሚሰጣቸው ብድር መልሰው ሊከፍሉት የሚችሉት መሆኑን መርህ ያስፈልጋቸዋል። ብደር የተበዳሪውም ስጋት መሆን የለበትም። ደንበኞች የሚወስዱት የሚወሰወዱት ብድር ችግር የሚከት መሆን የለበትም፡

ግልፅነት

የባንኩን ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይኖርበታል መረጃ ማግኘት መብትዎ ነው። የፋይናንስ ተቋማት ግልጽ በሆነ የክፍያ ሰርዓት ተወስነው ክፍያ የመፈጸም መርህ ሊያከበሩ ይገባል። በሌላ አነጋገር የፋይናንስ ተቋማት ከክፍያ ጋር በተያያዘ የሚሰጡት አግልግሎት ደንበኞች ሊረዱት በሚችል ግልጽ በሆነ ቋንቋ ተጽፎ መገለጽ ይኖርበታል።

ምክንያታዊ ዋጋ

የባንኩን አማካሪተጨማሪ መረጃ ይጠይቁ።የፋይናስ ተቋማት ለአገልግሎት የሚያሰከፍሉት ክፍያ የደንበኞችን የመክፈል አቅም ያገናዘብ መሆኑን ማረጋገጥ ና ደንበኞቹን በስራቸው ጥሩ ትርፍ ማግኘት እንዲችሉ ማደረግ አለባቸው። የፋይናነስ ተቋማቱ ደንበኞቹ የሚያሰቀምጡት ገንዘብ የተሻለ ወለድ አግኝተው አተራፊ እንዲሆኑ ማንኛውን ጥረት ማደረግ አለባቸው።

ፍትሃዊትና ደንበችንኞ በአክብሮት መያዝ

የገንዘብ ተቋማት ደንበኞቻቸውን ፍትሃዊና አክብሮት የተሞላባት ሁኔታ በማሰተናገድ መወሰን አላባቸው።በማንኛውም በደንበኞች መካከል ልዩነት መኖር የለበትም።ተቋማቱ ብድር ለሚወስዱ እና ብድር ለሚከፍሉ ደንበኞች በሰራተኞቹ የሚፈጸም ሙስና ፣ቁጡ የሆነ ወይም ተሳዳቢ የሆነ ባህሪ ያለቸውን ሰራተኛ እርምጃ የሚሰድበት አሰራር መኖሩን ማረጋጋጥ አለበት።

ቅሬታ የመፍቻ ዘዴ

የገንዘብ ተቋማት ችግሮች ሲፈጠሩና በደንበኞች ቅሬታ ሲቀርቡ በሰዓቱ ጣልቃ ገብተው ችገሩ የሚፈታበት ዘዴ መዘርጋ አለባቸው። ችግሮቹን የመፍቻ ዘዴዎቹ የደንበኞችን ችገር ከመፍታቱ ባሻገር የተቋሙን አገልገሎት ያሻሽላል።

የደንበኞችን ግላዊ መረጃ

የደንበኞች ግላዊ መረጃ ምሰጥራዊነቱ በአገሪቱ ባለው ህግና ደንብ መሠረት መከበር አለበት። የደንበኛው ግላዊ ለተወሰነ ጉዳይ መጠቀም የሚቻለው ደንበኛው ሲፈቀድ ወይም በህግ ሲፈቀድ ብቻ ነው።



የሥልጠና መርጃ ሊ 2.5

የቁጠባ አገልግሎት የሚፈልጋቸው ሁኔታዎች





1

ወርቅነሽና ከበደ በሰፈራቸው በሚገኝ የፈቃደኞች የበጎ አደራጎት ማህበር በተዘጋጀ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሂሳብ አያያዝ ትምህርት ተከታትለዋል። የትምህርቱም ርዕስ ለክረምት ገንዘብ መቆጠብ የሚል ነበር። አሁን ግን በየወሩ ትንሽ ገንዘብ በመቆጠብ መሬት ገዝተው ቤት ለመስራት ወስነዋል።ወርቅነሽና ከበደ ሁለቱም በጥምር የሚያንቀሳቅሱት የቁጠባ ሂሳብ ለመክፈት ወስነዋል።

» እነ ወርቅነሽ የሚስማማቸውን አግልግሎ የሚሰጥ የፋይናንስ ተቋም እንዲያገኙ እርስዎ ምንዓይነት ጥያቄ ይጠይቀሉ?

የ ፋ ይ ና ን ስ ት ም ህ ር ት





2

ገመቹ የቤተሰቦቹን ቤት አድሶ ለተወሰነ ጊዜ እነዲኖሩበት ገንዘብ ለማሰቀመጥ ይፈልጋል።ለአንድ አመት ያህል በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ማጠራቀም ፈልጓል። ገንዘቡን ለማጥፋት እንዳይገፋፋ የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት የቤተሰቡን ቤት ለማሰደስ ለማሳካት አሰቧል።በተለያየ አጋጣሚ ጉዳዩን ከጨልቱ ጋር በመወያየት የኮንትራት ቁጠባ በመክፈት በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ ሊያስቀምጡ ወስነዋል።

» ለገመቹ የሚስማማውን አግልግሎት የሚሰጥ የፋይናንስ ተቋም እንዲያገኙ እርስዎ ምን ዓይነት ጥያቄ ይጠይቀሉ?

የ ፋ ይ ና ን ስ ት ም ህ ር ት

የ ሁ ኔ ታ ካ ር ዶ ች





3

ዳዊትና ጓደኛው ጊዲዮን ስለገጠማቸው የገንዘብ ጉዳይ በስልክ ተወያይተዋል።ሁለቱም ባለፉት ወራት ሁለቱም ሳያቋርጡ ሲቆጥቡ ነበር።ዳዊት ገንዘቡን ከባንክ ማውጣት እንደማይፈልግና ከባንኩ ከፈተኛ ወለድ ማግኘት እንደሚፈልግ ለጊዲዮን ነገረው። ዳዊት የተወሰነ ጊዜ የቁጠባ ሂሳብ መክፈት እንዳለበት ተስማሙ።

» እነ ዳዊት የሚስማማቸውን አግልግሎት የሚሰት የፋይናንስ ተቋም እንዲያገኙ እርስዎ ምንዓይነት ጥያቄ ይጠይቀሉ?

የ ሁ ኔ ታ ካ ር ዶ ች





4

ትርሃስ ሊባኖስ ሄዳ ከህቷጋር መስራት ትፈልጋለች።ከጉዞዋ ጋር የተያያዘ ወጪዋን የወደፊት አሰሪዋ ይሸፍናል።ነገር ግን የቆጠበችውን ገንዘብ አገር ውስጥ በማትኖርበት ጊዜ ወላጆቿ ለችግር ጊዜ እና ያልታሰበ ወጪ ሲያጋጥማቸው ገንዘቡን መጠቀም መቻላቸውን ማረጋገጥ ፈልጋለች። ለጉዳዮቿ ከቁጠባ ሂሳቧ ለማወጣት የሚገፋፉአት ጉዳዮችን በመተው መደበኛ ቁጠባ በመክፈት ገንዘብ በማጠራቀም ያሰበችው ግብ ላይ ለመደረስ ወስናለች።

» ትርሃስ የሚስማማትን አግልግሎት የሚሰጥ ባንክ እንድታገኝ እርስዎ ምንዓይነት ጥያቄ ይጠይቀሉ?

የሥልጠና መርጃ ሪ 2.6

የገንዘብ ተቋማትን ሲጎበኙ የሚሞላችው ፎርሞች

የተገበኘው ተቋም:

1 / 3

ቃለ መጠየቁን ያደረገው ሰው ሚና/ተግባር:

የጎበኙትን የገንዘብ ተቋም ስለሰጥዎት አግልገሎት በሚከተለው ሰንጠረዥ ይሙሉ

አገልግሎት

የገንዘብ ተቋሙን ሲመርጡ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ባህሪያት	ተቋሙን ሲጎበኙ የሚሰጥ መልስ
የገንዘብ ተቋማት ባህሪያት	
ለአካባቢው ያለው ቅርበት	
የገንዘብ ተቋሙ መልካም ስምና ታማኝነት	
ከገንዘብ ውጪ የሚሰጣቸው አገልግሎት ጥራት (የንግድ ሥራ ስልጠና እና የገንዘብ አያያዝ ትምህርት)	
የርቀት አገልግሎት (በኢንተርኔት የሚጠየቅ የቀሪ ሂሳብ ጥያቄ፣ ወጪን በአጭር የፅሁፍ መልክት ማሳወቅ የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት	
የአገልግሎትና የሰራተኞች ጥራት (የባንኩን አገልግሎት ለማገኘት የጥበቃ ጊዜ፣የሚነገር ቋንቋ እና የአግልግሎት ቅልጥፍና	
የሚያስፈልግ ከሆነ የመገናኘት ሁኔታ፣ለመመዝግብ የመገኛኘት ድግግሞሽ ጊዜ የአባላቱ የመወሰን ስልጣን	
ስለሚያስፈልጉ ቅደመ ሁኔታዎችና ስለሚከፈል ክፍያ በተመለከተ ለደንበኞች የሚሰጥ መረጃ ጥራት	

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የገንዘብ ተቋሙን ሲመርጡ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ባህሪያት	ተቋሙን ሲጎበኙ የሚሰጥ መልስ
የገንዘብ ተቋማት ባህሪያት	
ለተወሰኑ ደንበኞች የሚሰጥ አገልግሎት (ለተማሪዎች፣ ለደሞዝተኞች ለጡረተኞችና እና ለመሳሰሉት)	
የሚሰጥ የበጎ አደራጎት ሥራ (የድጋፍ ገንዘብ ወጪን መሸፈን እና የመሳሰሉት	
የተቋሙ አገልግሎት ገንዘብ ለሚልኩ ወይም ለሚቀበሉ በውጭ አገር ወይም ለአካባቢያቸው ቅርብ በሆነ ቦታ መኖር	
የገንዘብ ተቋማት ባህሪ (ለቁጠባ)	
የቁጠባ ተደራሽነት/በቀላሉ ገንዘብ ማውጣ	
ለአጠቃቀም ምቹ መሆን	
የቁጠባ ሂሳብ ለመክፈት የሚያስፈልጉ ቅደመ ሁኔታዎች	
ደህንነት	

የየፋይናንስ ተቋሙን ሲመርጡ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ባህሪያት	ተቋሙን ሲጎበኙ የሚሰጥ መልስ
የገንዘብ ተቋማት ባህሪ (ለቁጠባ)	
የወለድ ምጣኔ	
የገንዘብ ተቋሙ ከገንዘብ ነክ አገልግሎት ውጪ የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ተደራሽነት	
የቁጠባ ዋጋ (አግልግሎት ዋጋ እና ቅጣት)	
የገንዘብ ፍሰት	
የአግልግሎት አሰጣጥ ስነ ምግባር (አሰተማማኝ ፋይናንስ አገልግሎት ምቹ የስራ አካባቢ)	

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ማስታወሻዎች



የመልጃዎቹ መልሶች:

የመግለጫ ካርዶች (የሥልጠና መርጃ ረ 2.7)

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 1 መልስ

የቁጠባ ሂሳብ ለመክፍት የማመልከቻ ፎርም

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 2 መልስ

የደንበኞች አገልግሎት ሠራተኛ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 3 መልስ

የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 4 መልስ

የባንክ ሰራተኛ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 5 መልስ

የጥበቃ ሠራተኛ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 6 መልስ

የማስታወቂያ ሰሌዳ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 7 መልስ

የባንክ ፎርሞች የሚቀመጥበት መደርደሪያ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 8 መልስ

የገዘብ ማውጫ ፎርም

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 9 መልስ


ቼክ

ለመግለጫ ካርድ ቁጥር 10 መልስ

የመክፈያ ፎርም

የመልጃዎቹ መልሶች:

የመግለጫ ካርዶች - የደንበኞች ጥበቃ መርህ (የሥልጠና መርጃ ረ 2.8)



የመግለጫ ካርድ ቁጥር 1

የዶሮ እርባታ አለኝ። አቅራቢያዬ ከሚገኝ ከአነሰተኛ ብድር ተቋም ለግብርና አግልግሎት የሚውል ብድር ለመወሰድ ተሰማማቼያለሁ። የምበደረው የገንዘብ መጠን የምፈለገውን ያህል ነው።

በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ዶሮ ሽጬ ብዙ ገንዘብ አገኛለሁ። ነገር ግን ብድሩን ለሰጠኝ ተቋም መከፈል ያለበኝ በየወሩ ነው ይህን ለማደረግ ሌላ ገቢ የለኝም። የወሰድኩት ብድር ለምሰራው ሥራ ተስማሚ አይመስለኝም።

ትክክል ነው?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር የዋሉ የደንበኞች ጥበቃ

ትክክለኛ የአግልግሎት ንድፍና አሰጣጥ

የገንዘብ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎትና የስርጭት መንገድ ሲታቀድ የደንበኞችን ፍላጎት የሚጻረር መሆንን የለበትም። የተቋሙ አገልገሎት አሰጣጥ እና ስርጭቱ የደንበኞች ባህሪና ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆኑ ይገባዋል።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 2

ባለፈው ዓመት ቤት ለመግዛትና ለሃይማኖታዊ በዓል ዝግጅት ሁለቴ ከባንክ ተበድሬያለሁ። በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለመዘዋወር ሞተር ሳይክል ለመግዛት ፍላጎት አለኝ።

ነገር ግን ባንኩ ሶስተኛ ብድር ለመስጠት ፈቃደኛ አይደለም። ትክክል ነው ምን ማደረግ እችላለሁ።

ምን ላደርግ እችላለሁ?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር ላይ የዋለ የደንበኞች ጥበቃ መርህ

ከመጠን በላይ ባለዕዳ እንዳይሆኑ መከላከል

አዎ በጣም ትክክል ነው።ገንዘብ መበደር መብት ነው የሚባል ነገር አይደለም።ባንኮች ደንበኞች ከመጠን በላይ ባለእዳ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ በማደረግ ይከላለከላሉ። ይህንን ለማደረግ የፋይናስ ተቋማት ደንበኞች የሚወሰዱት ብድር መልሰው ሊከፍሉት የሚችሉትን ያህል እንዲሆንና ከመጠን በላይ ባለእዳ እንዳይሆነ በመርህ ማረጋገጥ አለባቸው።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር ፫

እኔ የፋይናንስ ተቋም ደንበኛ ነኝ ከገንዘብ ቁጠባ ጋር በተያያዘ ከባንክ የወሰድኩት በራሪ ወረቀት የተቀመጠውን ቅደመ ሁኔታና ክፍያዎች ለመረዳት ሞክሬ ነበር።

ነገር ግን በበራሪ ወረቀቱ ላይ ያለው ጽሁፍ በጣም ጥቃቅን በመሆኑ ለመረዳት ተቸግሬያለሁ።

ምን ላድረግ?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር ላይ ዋለ የደንበኞች ጥበቃ

ግልጽነት

የባንኩን ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይኖርቦታል መረጃ ማግኘት መብትዎ ነው። የፋይናንስ ተቋማት ግልጽ በሆነ የክፍያ ሰርዓት ተወስነው ክፍያ የመፈጸም መርህ ሊያከበሩ ይገባል። በሌላ አነጋገር የፋይናንስ ተቋማት ከክፍያ ጋር በተያያዘ የሚሰጡት አግልግሎት ደንበኞች ሊረዱት በሚችል ግልጽ በሆነ ቋንቋ ተጽፎ መገለጽ ይኖርበታል።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር ፬

በገንዘብ ተቋሙ ተንቀሳቃሽና የቁጠባ ሒሳብ አለኝ
ለተንቀሳቃሽ ሂሳብ የሚከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ከፍተኛ በመሆኑ ደስተኛ አይደለሁም እንዲሁም ለቁጠባ ሂሳቤ የሚከፈለኝ ወለድ በጣም ዝቅተኛ ነው

ሚዛናዊ አይመስልም ትክክል ነው?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር ላይ የዋለ የደንበኞች ጥበቃ መርህ

ምክንያታዊ ዋጋ

የባንኩን አማካሪ ተጨማሪ መረጃ ይጠይቁ።የገንዘብ ተቋማት ለአገልግሎት የሚያሰከፍሉት ክፍያ የደንበኞችን የመክፈል አቅም ያገናዘብ መሆኑን ማረጋገጥና ደንበኞቹን በስራቸው ጥሩ ትርፍ ማግኘት እንዲችሉ ማደረግ አለባቸው።የገንዘብ ተቋማቱ ደንበኞቹ የሚያሰቀምጡት ገንዘብ የተሻለ ወለድ አግኝተው አትራፊ እንዲሆኑ ማንኛውን ጥረት ማደረግ አለባቸው።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር ፭

ከስራ በመባረሬ ምክንያት ያለብኝን የባንክ እዳ ለመክፍል አልቻልኩም። ብድሩን ለመክፍል ባለመቻል ባንኩ ምን ያደርጋል ብዬ እጨነቃለሁ

ወደ ቤቴ መጥተው የኔና የቤተሰቤን ንበረትና ሃብት ይወስዱ ይሆን?የባሰ ያደርጉ ይሆን?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

የተተከበረ የደንበኞች ጥበቃ መርህ

ደንበኞችን በማክበር ሚዛናዊ ሆኖ ማገልግል

የገንዘብ ተቋማት ደንበኞቻቸውን ፍትሃዊና አክብሮት የተሞላባት ሁኔታ በማሰተናገድ መወሰን አላባቸው።በማንኛውም ደንበኞች መካከል ልዩነት መኖር የለበትም።ተቋማቱ ብድር ለሚወስዱ እና ብድር ለሚከፍሉ ደንበኞች በሰራተኞቹ የሚፈጸም ሙስና ፣ቁጡ የሆነ ወይም ተሳዳቢ የሆነ ባህሪ ያለቸውን ሰራተኛ እርምጃ የሚሰድበት አሰራር መኖሩን ማረጋጋጥ አለበት።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 6

በተፈጠረው ነገር ከባንኩ ጋር ላልስማማ እችላለሁ።
ማንን ላገኝ እችላለሁ?

በባንክ ውስጥ ሊረዳኝ የሚችል ሰው ይኖራል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር ላይ የዋል የደንበኞች ጥበቃ መርህ

የደንበኞች ቅሬታ መፍቻ ዘዴ

የገንዘብ ተቋማት በደንበኞቻቸው ላይ ያሉ ችግሮች እና ቅሬታዎች በወቅቱ ጣልቃ በመግባት በወቅቱ የሚፈቱበት ዘዴ መኖር አለበት።የቅሬታ ዘዴ መፍቻ ዘዴውን በመጠቀም የደንበኞችን ተፈታ የተቋሙን አገልግሎት ያሻሽላል።

የመግለጫ ካርድ ቁጥር 7

ተንቀሳቃሽ ሂሳቤን የሚከታተለው የባንክ ሰራተኛ ባለፈው ሳምንት የተቀበልኩት ትልቅ የገንዘብ መጠን ያውቃል።

ከኔ እውቅና ውጪ ስለዚህ ጉዳይ ከቤተሰቤ ጋር መወያየት ይችላል?

የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ተግባር የዋለ የደንበኞች ጥበቃ መርህ

የደንበኞች መረጃ ግላዊነት

የደንበኞች ግላዊ መረጃ በአገሪቱ ባለው ህግና ደንብ መሰረት ሚስጥራዊነቱ መጠበቅ አለበት። የደንበኞች መረጃ ጥቅም ላይ የሚውለው በደንበኛው ስምምነት ወይም በህግ ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜ ነው።





ስጋት አሰተዳደርና ኢንሹራንስ

FINANCIAL EDUCATION QUIZ

ሸ.1 ከሚከተሉት አረፈተ ነገሮች ከስጋት ጋር የማይዛመደው የቱ ነው?

- ☐ **ሀ/** ኪሳራ ውስጥ መግባት
- ☐ **ለ/** መናደድ
- ☐ **ሐ/** የስራ ላይ አደጋ መድረስ
- ☐ **መ/** የስጋት አደጋ ተጎጂ መሆን

ሸ/2 ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ ስጋት ለመከላከል ከሚወሰዱ ጥንቃቄዎች ያለሆነው የቱ ነው?

- ☐ **ሀ/** ቁጠባ ማደረግ
- ☐ **ለ/** ኢንሹራንስ መግባት
- ☐ **ሐ/** ገንዘብ መላክ
- ☐ **መ/** የወባ ትንኝ መከላከያ አጎበር መጠቀም

ሸ/3 ኢንሹራንስ መግባት ኪሳራን ሊከላከልልን ይችላል ☐ **ሀ/** እውነት ☐ **ለ/** ውሸት

ሸ/4 ክልከላ ምንድን ነው

- ☐ **ሀ/**ከኢንራንስ ካምፓኒዎች ስለሚሰጡት አገልግሎቶች ቅደመ ሁኔታዎች ለደንበኞች የሚሰጥ ሰነድ ነው
- ☐ **ለ/**በውል ውስጥ ያልተካተቱ ወይም ያልተሸፈኑ የተወሰኑ ሁኔታዎች
- ☐ **ሐ/**በፖሊሰ ውስጥ የተሸፈኑትን ከሳራን ለመክፈል ጥያቄ ማቀረብ

ሃ ፯/ሀ ሣ ፪ /ሀ ሃ ፩ /ሀ – ፡ ሀዓመ

1. አደጋን ማስተዳደር


አደጋ በትንሽም ሆነ በትልቅ ሁኔታ ሊከሰት የሚችልና በራስና በቤተሰብ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው።አደጋ ሊከሰት የሚችልበት እድል እና ሊያደርሰው ሚችለው ጉዳት ክትንሽ አሰስከ ከፍ ያለ እንደ ባህሪውና በሰዎች እና በአካባቢው ላይ በሚያሳደረው ተፅእኖ መሰረት ተለያየ ነው።


ትርጉም

ክደጋ ፡ ማለት የማያሰዳለቱና ጉዳት የሚሰከትቱ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ነው።


የሥልጠና መርጃ ሸ 1.1

የአደጋ ካርዶች





ህመም/በሽታ



ሞት



እሳት



እርሶንና ቤተሰበዎን ሊያገጥማቸሁ የሚችለውን አደጋ ከግምት ውሥጥ በማስገባት ሊገጥሙ በሚችሉ የአደጋ ድግግሞሽ መሠረት አደጋዎችን በሳጥን ውሥጥ ይጻፉ።ለምሳሌ ሞት የሚከሰተው አንዳንድ ጊዜ ሲሆን ለቤተሰብ ትልቅ አደጋ ነው።

		ዋጋ		
		ትርጉም ያለው አይደለም	መጠነኛ	በከፍተኛ ሁኔታ
ድግግሞሽ	ተደጋጋሚ			
	መካከለኛ			
	አልፎ አልፎ			ለምሳሌ፡ ሞት

እንደምትመለከቱት የሚከሰቱልዩ ልዩ አደጋዎች አነሰም በዛም እንደሚከሰተው አደጋው ባህሪ በሰውና በአካባቢ ላይ ከመጠነኛ አሰከ አሰከፊ ጉዳት ውጤት ያስከተላሉ።



አሰታውሱ

እራስዎን ከአደጋ ለመከላከል የተለያዩ የአደጋ መከላከያ ዘዴዎች አሉ

- ከአደጋ መራቅ/አደጋ ከሚያመጡ ነገሮችን ማሰወገድ
- ለሚደረስ አደጋ ኢንሹራንስ መግባት
- የሚደርሱ አደጋዎችን ቀድሞ በመተንበይ እራስን ዝግጁ ማደረግ

እራስዎንና ቤተሰቦዎን ከአደጋ ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎች አሉ እነኚህን ዘዴዎች (በሟንጥላው) በባዶ ቦታ ላይ ይጻፉ

የሥልጠና መርጃ ሽ 1.2

የኔ ጥላ



ጠቃሚ መልዕክት

- አንዳንድ አደጋዎች ስለሚታወቁ ጉዳታቸውን ለመቀንስ እርምጃ መውሰድ ይቻላል
- ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ገንዘብ መኖር በጣም አስፈላጊ ነው ፣ካለዎት ድንገተኛ አደጋ አይሰጨንቅም። ለዚሁ አገልግሎት ገንዘብ ማሰቀመጥ የአደጋ ተጋላጭነት ይቀንሳል።
- ለድንገተኛ አደጋ የግል ቁጠባ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል። ለአደጋ ኢንሹራንስ መግባት ያሰፈልጋል።
- ቤተሰቦዎን ከአደጋ ለመከላከል ጥንቃቄ ማደረግ ያሰፈልጋል።

2. አድንገተኛ አደጋ ገንዘብ ለመመደብ ጠቃሚ ምክር

- ለሚደርስቦት ድንገተኛ አደጋ ገንዘቡ ቀስ በቀስ ተጠራቅሞ ሊያድግ ስለሚች ትንሽ ገንዘብ በቀን ወይም በየሳምንቱ ያስቀምጡ።
- ለአደጋ ጊዜ የሚያሰቀምጡትን ገንዘብ ሰው የማያገኝበት ቦታ በቤትዎ ውጭ ያሰቀምጡ።ከተቻለ የቁጠባ ሂሳብ መክፈት ተመራጭ ነው።
- ሁል ጊዜ ተመሳሳይ ገንዘብ ማሰቀመጥ አስፈላጊ አይደለም በሚያገኟቸው አጋጣሚ መሠረት የተለያየ መጠን ይቆጥቡ
- ትንሽ የገንዘብ መጠን ገቢ ካለዎት አላሰፈላጊ ወጪዎችን ለመቀነስ የሚቻልዎትን ያድርጉ



የግል ሁኔታ ጥናት 1

የአደጋ ጊዜ የሚውል ገንዘብ መመዝገቢያ ዘንጠረዥ

ወርቅነሽ ከከበደ ጋር በመሆን ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ገንዘብ ለማዘዘጋጀት ወስናለች። ይህንን ለማድረግ የቤተሰቡ ያለፈውን ዓመት ገቢ ለማሳየት በመወሰን ሰንጠረዥ አዘጋጀች። ሰንጠረዡ የሚከተለውን ይመስላል።

የወርቅነሽ ቤተሰብ የአንድ ዓመት ገቢ

ወር	Amount (ETB) ገንዘቡ መጠን በብር
ጥር	10,000
የካቲት	10,500
መጋቢት	9,800
ሚያዚያ	10,000
ግንቦት	10,450
ሰኔ	9,800
ሀምሌ	9,700
ነሐሴ	10,850
መስከረም	10,100
ጥቅምት	9,700
ህዳር	10,500
ታህሳስ	10,850
ጠቅላላ	122,250

ስለወርቅነሽና ቤተሰብዋ ጥያቄዎች:

- የወርቅነሽ ቤተሰብ ባለፉት 12 ወራት ምን ያህል ጠቅላላ ገቢ አገኙ? (ቋሚና ተለዋዋጭ ሊሆን እንደሚችል ግንዛቤ ይውሰድ)
- የቤተሰቡ አማካይ ገቢ ስንት ነው?
- የአደጋ ጊዜ ለመመደብ ምን ያህል ጠቅላላ ገንዘብ ያስፈልገቸዋል?

ያስታውሱ

የርስዎ ለአደጋ ጊዜ ወጪን ለመሸፈን ለማዋል ያቀዱት በአንጻራዊነት ለአነስተኛ አደጋዎች ነው። ብዙን ጊዜ በቤተሰብዎ ላይ ለሚደርስ አደጋና ለከፍተኛ ህክምና የሚያስፈልግ ገንዘብ ላያስቀምጡ ይችላላ።

ስለ ድንገተኛ አደጋ ጊዜ ካቀዱ ያሰቡትን ግብ ያሳካሉ። ለአደጋ ጊዜ የአሰቀመጡት ገንዘብ ካለ ንግድ ለመጀመር፣ቤትዎን ለማደስ፣የእርስዎንና የልጆችን ትምህርትን ለማሻሻል የቆጠበትን ገንዘብ ከማውጣት ይታደገዎታል።

3. የኢንሹራንስ/መድህን ፖሊሲዎን መርዳት



መድህን/ኢንሹራንስ ሀሳቡ ምንድነው?

የኢንሹራንስ /መድህን መርህ ከሚያጋጥሞት ድንገተኛ አደጋ፣ህመም፣ስርቆትና መሳሰሉት በሚከፍሉት ገንዘብ አደጋ በተከሰተ ጊዜ ለደረሰብዎት ጉዳት ወጪዎን መሸፈን ነው።

ትርጉም

መድህን /ኪንሹራንስ: ከዳጋን ለመከላከል በመድህን ድርጅቱ ተመዝገበው ከንትራት በመዒራረም ከዳረሰበዎት ከዳጋ የገንዘብ ካሳ የሚከፍል ነው።

የጋራ ጥቅም ማህበር: ከጋራ ጥቅም በአባለት ባለቤትነት የተመሰረተ ከትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን የአባላቱን ፍላጎት መሰረት የዳረገ የመድህን/ የኪንሹራንስ ኩባንያ ነው።

የመድህን/የኪንሹራንስ ኩባንያ: የኪንሹራንስ/መድህን ኩባንያ የሚሰጥ ሆኖ ዋናው ግቡ ትርፍ ለማግኘት የሚሰራ የንግድ ኩባንያ የሆነ ነው።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁጥር 2

ገመቹ የእግር ጉዳት

ገመቹ በትላንትናው ዕለት በስራ ላይ የነበረ የከባድ መኪና ባትሪ ሲቀይር ለደቂቃዎች ትኩረቱን በማጣቱ ባትሪው ቀኝ እግሩ ስለወደቀበት አደጋ አጋጥሞታል። በአጋጣሚ በጣም አልተጎዳም።መጀመሪያ እግሩ በሃይል አልተጎዳም ነገር ግን ማታ ላይ በጣም አበጠ።በአጋጣሚ ገመቹ የድርጅቱ ቋሚ ተቀጣሪ ሠራተኛ ነው።


ድርጅቱ ለሁሉም ሠራተኞቹ ለህክምና፣ለመድሃኒት፣ለሆስፒታል ህክምና የመድህን ሽፋን አለው። ለዚሁ አገልግሎት ድርጅቱ ከእያንዳንዱ ሠራተኛ ከደመዛቸው ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።ገመቹ እንዲህ አይነት አደጋ ያጋጠመው ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። ወደ ኢንሹራን ካምፓኒው በመደወል ማደረግ ያለበትን ሂደትና ስለመስፈርቶቹ ለመጠየቅ ወስኗል።ለህክምና ለሚያወጣቸው ወጪዎች ስለማይከፍል ገመቹ ተረጋጋ።



የግል ሁኔታ ጥናት ቁጥር 3

የዳዊት አባት አቶ ፍስሃ የእግር ጉዳት

አንድ ቀን የዳዊት አባት አቶ ፍስሃ በስራ ላይ እያሉ ከባድ የሆነ መሣሪያ እግራቸው ላይ ወድቆ የእግራቸውን አውራ ጣት ተሰበረ።የሚፈሰውን ደም ለማስቆም ሚችሉትን ሁሉ በማደረግ ቁስሉን አሰሩት።ህምሙን ለመርሳት ሞከሩ ነገር ግን ማታ ላይ የእግራቸው አውራ ጣት በጣም አበጠ። ከፍተኛ ህመም እየተሰማቸውም ቢሆን በሚቀጥለው ቀን ወደ ስራ ሄዱ። አለቃቸው ሠራተኞች ከስራ ለመቅረት ፍቃድ ሲጠይቁት በጣም ስለሚናደድ ስራቸውን እንዳያጡ ስለፈሩ ለቅርበ አለቃው አውራ ጣታቸው ስለመሰበሩ አልተናገሩም።



ከዚህም በተጨማሪ ወደ ህክምና ቢሄዱ ለምርመራ እና ለህክምና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ በቂ ገንዘብ ስሌላቸው ፈርተዋል።የሚሰሩበት ፋብሪካ እንደሳቸው ላሉ ሰራተኞቹ የኢንሹራንስ ሽፋን እንደሌቸው እርግጠኛ ሆነዋል። ማታ ላይ ህመሙን መቋቋም ባለመቻላቸው ወደ ሆስፒታል ሄዱ። ዶክተሩ ኤክስ ሬይ መነሳትና መድሃኒት እንደሚያስፈልጋቸው ነገራቸው።ነገር ግን ለህክምናው በቂ ገንዘብ የላቸውም።ዳዊት የህክምናውን ወጪ ለመሸፈን መደበኛ ካልሆኑ አበዳሪዎች ብድር ለመውሰድ ወሰነ።ተመሳሳይ ችግር በድጋሚ ቢከሰት እንደገና ገንዘብ ከመበደር መቆጠብ ይፈልጋሉ።

ጠቃሚ: አንዳንደ ጊዜ ጭንቀት በአካላችን ላይ ተፅዕኖ አለው። የገነዘብ አያያዝ የሚያስጨንቅዎ ከሆነ በሰዎነትዎ ላይ የጤና ችግር ያመጣል።


የሥልጠና መርጃ ሽ 2.1

የሃብት ማሰሮ ጨዋታ፡ መጫወቻ ካርዶች

የ ሃ ብ ት ማ ሰ ሮ ጨ ዋ ታ

3 የማስማሰያ ምልክት







መድሃኒት

የ ገ ጓ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት

የ ሃ ብ ት ማ ሰ ሮ ጨ ዋ ታ

7 የማስማሰያ ምልክት







ሆስፒታል

የ ገ ጓ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት

የ ሃ ብ ት ማ ሰ ሮ ጨ ዋ ታ







ጥሩ ጤና

የ ገ ጓ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት

የ ሃ ብ ት ማ ሰ ሮ ጨ ዋ ታ

4 የማስማሰያ ምልክት







ታኪም

የ ገ ጓ ዘ ብ አ ያ ያ ዝ ት ም ህ ር ት




በጤናዎ ላይ ለሚያጋጥሞት እክል መቼና ምን ያህል እንደሚከፍሉ በፍጹም ሊያውቁ አይችሉም።አንዳንድ ጊዜ ለጤናዎ ከሚያገኙት ገቢ በላይ ከፍተኛ ወጪ ሊያወጡ ይችላሉ።ኢንሹራንስ መግባት የሚስፈልገው በዚህ ምክንያት ነው።

የአደጋ ስጋት መከላለከል ዋናው ሚስጥር ሁላችንም በአንድ በጋራ ቋት ውስጥ መዋጮ ማስቀመጣችን ነው።ከዚህ ቋት ውስጥ ሁሉም በአንድ ጊዜ ገንዘብ ማወጣት አያስፈፈልግም።ነገር ግን ኢንሹራንስ ሊሰራ የሚችለው ሁሉም መዋጮውን ከከፈለ ነው።

በኢንሹራንስ የጤና አገልግሎት ማግኘትዎን ለማረጋገጥ ለዚሁ አግልግሎት በቅድሚያ መክፈል አለብዎት። የሚያገኙት የጤና አገልግሎት በሚያዋጡት የገንዘብ መጠን ላይ የተመሰረት ነው።የሚያወጡት መጠን ከፍ ባለ መጠን የተሸለ የጤና አገልግሎት ያገኛሉ።

ቁልፍ መልዕክት

- ኢንሹራንስ፡ ገንዘብን በማሰቀመጥ የማህበራዊ ጥበቃ መሣሪያ ነው።
- ኢንሹራንስ መግባት አደጋን መከላከል ነው
- ኢንሹራንስ ፡ የጋራ መፍትሄ ነው።



⚠ **ትኩረት: በተለይ ደሞዝ እየተከፈላቸው በመንግስት ተመዝበው ታክስ የሚከፍሉ በቋሚነት በድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ አንዳንድ ሰራተኖች የኢንሹራንስ ሽፋን አላቸው።። ነገር ግን የአንሹራንስ ሽፋን እንዳላቸውና እንዴት እንደሚጠቀሙ አያውቁም። አንዳንድ ጊዜ የኢንሹራንስ ሠራተኞች ሰስለኢንሹራንስ አጠቃቀም ዘዴና የአንሹራንስ ውስብስብ አሰራርን በሚገባ አያሰረዱም።ህበረተሰብን መሰረት ያደረጉ የጤና መድህን ሽፋን የሚሰጡ ሰለሆንነ የጤናን መድን ሽፋን እነኒህን ተቋማት መጠቀም ጥሩ አማራጭ መሆኑን ያስታውሱ።**



ያስታውሱ

እውቀት ኃይል ነው። በኢንሹራስ ምን እንደተሸፈነ፣ ክፍያው እና እንዴት ክፍያ እንደሚጠይቁ ማወቅ ይኖርቦታል።
የኢንሹራንስ ካርድ ካለዎት በጥንቃቄ ይያዙ።

4. የኢንሹራንስ ፖሊሲን መጠቀም

ሰዎች በህይወት ቆይታቸው የተለያየ አደጋ ያጋጥማቸዋል።አንዳንዱ አደጋ ሁሉንም የሚያጋጥም ሲሆን ሌሎች አደጋዎች በተወሰኑ ሰዎች የሚደረስ ነው።


ስደተኞች ሚያጋጥማቸውን አደጋዎች እንመለከት


ጠቅላላ አደጋ	በስደተኞች ላይ የሚደርሱ አደጋዎች
• የሞት አደጋ • ህመም • ድንገተኛ አደጋ • የመሰረቅ አደጋ	• ከቤተሰብ መራቅ ምክንያት ጭንቀት • ከስራ የመባራ አደጋ • የአካል፣የስነልቦና እና ወሲባዊ ጥቃት መደበኛ ባለሆነ ሁኔታ የተሰደዱ ስደተኞች ላይ የሚደርስ ጥቃት • የደሞዝ ያለመከፈል • በውጭ አገር እያሉ መታመም፣መሞትና ድንገተኛ አደጋ ማጋጠም • ሥራ አጥነት • በስራ ላይ አደጋ ማጋጠም • የስራ ላይ በሽታ ማጋጠም • የስራ ኮንትራት ማለቅ • በህግ የሚያስጠይቁ ጉዳዮች ማጋጠም





የሥልጠና መርጃ ሽ 3.1


የአደጋ ካርዶች














ጥያቄዎች

- የኢንሹራንስ ሽፋን/ፖሊሲ አለዎት ከሌሎት እንዲኖርዎ ለመግባት ይፈልጋሉ? ☐ አዎ ☐ አይ
- የአንሹራንስን ቁልፍ የሆኑ ቃላቶችን/መጠሪዎችን ያውቃሉ? ☐ አዎ ☐ አይ

የስያሜዎችን ትርጓሜ በጋራ እንመልከት

መሰፈረታዊ የኢንሹራንስ ቃላቶች	
ካሳ ወይም ክፍያ	ኢንሹራንስ ለገባ ሰው ለድንገተኛ አደጋ፣ ለእሳት አደጋ ፣ለህመም እና ለመሳሰሉት አደጋ ሰደረስ ትክክለኛ ማስረጃ ተያይዞ የክፍያ ጥያቄ በኢንሹራንስ ኩባንያው የሚከፈል ያካሳ ክፍያ ነው።
ፖሊሲ/የመድህን መመሪያ	በደንበኛውና በኢንሹራንስ ኩባንያው መካካል ስለ ኢንሹራንስ ሽፋን ሁኔታ፣ የሽፋኑ ጊዜ፣ ሽፋን የሚደረግባቸው የአደጋ ዓይነቶችና የማይሸፈኑ የሚገልጽ የስምምት ሰነድ ነው።
አረቦን	ለኢንሹራንስ ሽፋን ለመድን ሰጪው ድርጅት የሚከፈል ዋጋ ነው። ክፍያ በሩብ ዓመት በወር ወይም በዓመት ተከፋፍሎ ሊከፈል ይችላል።
ዋስትና የተገባለት ሰው /ተጠቃሚ	ኢንሹራንስ በተገባው መሰረት አደጋ ሲደርስበት ከኢንሹራንስ ኩባንያው ክፍያ የሚያገኝ ሰው።
የክፍያ ጥያቄ	አደጋ ሲደርስ በተገባው ኢንሱራንስና ፖሊሲ መሰረት የሚቀርብ ጥያቄ
የመድህን ካርድ	በኢንሹራንስ ኩባንያ በፖሊሲው መሰረት አረቦን ለከፈለ ደንበኛ የሚሰጥ ካርድ

ተሟላ የካሳ ክፍያጥያቄ ለማቅረብ ቅደም ተከተሉን በመከተልና ለካሳ ጥያቄ የሚየሰፈልጉ ሰነድዎችን ማሟላትዎን ያስታውሱ!



የሥልጠና መርጃ ሽ 3.2

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀራረብ ደረጃዎች

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀርቀርብ ደረጃዎች

በመስራት ላይ ያለ የኢንሹራንስ የካሳ ጥያቄ አደጋው ከደረሰ በኋላ ወዲያውኑ በተቻለ ፍጥነት ክፍያ የሚጠየቅበት የኢንሹራንስ ቅፅ ይሙሉ (እንደ ኢንሹራንስ ውሉ መሰረት በ12 ወራት ውስጥ ሊሞላ ይችላል።

የፋይናንስ ትምህርት

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀርቀርብ ደረጃዎች

በመስራት ላይ ያለ የኢንሹራንስ የካሳ ጥያቄ አደጋው የሚያስፈልጉትን መድህን በገባው ሰው የተፈረመ የክፍያ መጠየቂያ ፣ ተፈላጊ ሰነዶች ፎቶኮፒው ፣ የአባልነት ካርድና የመታወቂያ ካርድዎ ነው።

የፋይናንስ ትምህርት

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀርቀርብ ደረጃዎች

በመስራት ላይ ያለ የኢንሹራንስ የካሳ ጥያቄ ከጠበቁት በታች ከተፈልዎ ቅሬታዎን ያስገቡ ለምን እንደሆነ ለማወቅ ይሞክሩ!

የፋይናንስ ትምህርት

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀርቀርብ ደረጃዎች

በመስራት ላይ ያለ የኢንሹራንስ የካሳ ጥያቄ የተከፈልዎት ካሳ መከፈል ካለበት ጥቅም ጋር ያነፃፅሩ።

የፋይናንስ ትምህርት

የመድህን ካሳ ጥያቄ አቀርቀርብ ደረጃዎች

በመስራት ላይ ያለ የኢንሹራንስ የካሳ ጥያቄ በሰባት ቀን ውስጥ ካልተከፈልዎት የመድህን ሽፋን የሰጥዎትን ኩባንያ ቀርበው በማናገር ጉዳዩ የደረሰበትን ደረጃ ይከታተሉ (በኢንሹራንስ ውሉ ላይ የተቀመጠውን ሁኔታ ይመልከቱ)።

የፋይናንስ ትምህርት



ቁልፍ መልዕክት

- ፍላጎቶትን የሚያሟላ የኢንሹራንስ ካምፓኒ ለማገኘት መጀመሪያ በኢንሹራን ሲሸፈን የሚችለውን ሊጋጥም የሚችለውን አደጋ መለየት ያስፈለጋል።
- ኢንሹራንስ የተለየ የስራ ቃላቶች ይጠቀማሉ እነኚህን የስራ ቋንቋዎች ለመረዳትና በኢንሹራንስ ያሉትን አግልግሎቶች ለመጠቀም ስለቃላቶቹ ማወቅ /መመማር ያስፈልጋል።
- ኢንሹራንስ የተገባለቸው የሚከሰቱ አደጋዎች የካሳ ጥያቄ ሲቀርብ የተለየ ሰነድ ሊያስፈልግ ይችላል።

5. ትክክለኛውን የኢንሹራንስ አገልግሎት መመረጥ

አሁን ገጸባህሪያችንን ኢንሹራን ገብቶ ያሉትን ጥርጣሬዎች ለመፍታት እንረዳዋል።

የሥልጠና መርጃ ሸ ፋ.1

የጤና መድህን የግል ሁኔታ ጥናት

የግል ሁኔታ ጥናት #1 ወርቅነሽ

የወርቅነሽ ወንድም አባይነህ ከወራት በፊት ከስራ ወደ ቤቱ ሲመላለስ ላጋጠመው አደጋ የየጤና ኢንሹራንሱን ለመወሰድ ወስኗል ። በክረምት ወረቅነሽና ቤተሰቡን ለማየት መጥቷል። ከቀናት በኋላ ከበደ እራስ ምታትና ትኩሳት አመመው ። ለመታከም ወደ ሆስፒታል ሄዶ ዶክተሩ ኮቪድ 19 ስለያዘው መተኛት እንዳለበት ነገረው።

የአባይነህ የኢንሹራንስ ሽፋን የከበደን የህክምና ወጪ ሊሸፍን ይችላል? ለምን?

የግል ሁኔታ ጥናት #2 ገመቹ

ገመቹ ለወላጆቹ የሚሆን አዲስ የህክምና ኢንሹራንስ ሽፋን ለማደረግ የቀረበለትን የኢንሹራንስ ፖሊሲ አረቦን ለመክፈል ፈርቷል። ነገርግን ወላጆቹ እያረጁ ስለሆነ ከፍተኛ ህክምና እንደሚያሰፈልጋቸው ያውቃል። በተለይ አባቱ ባለፉት ወራት ጉልብታቸው እያታመመ ስለሆነ ምናልባት በአፋጣኝ ቀዶ ጥገና ማደረግ ሳያሰፈልጋቸው አይቀርም። ምንም እንኳን የኢንሹራንሱ አረቦኑ ሽፋን ሊሰጥ የሚችለው ለአንድ ዓመት ቢሆንም አባቱ ኦፕራሲዎን ከመሆናቸው ከአንድ ወር በፊት ጀምሮና ከቀዶ ጥገና ከተደረጉ በኋላ ለሁለት ወራት ገመቹ የሶስት ወራት የመድህን አረቦን ለመግዘት ፈልጓል።

ገመቹ የሶስት ወራት የኢንሹራንስ ሽፋን አረቦን መግዛት ይችላል? ለምን?

የግል ሁኔታ ጥናት #3 የተርሃስ አባት አቶ አርያ

መጠነኛ አደጋ በቤተሰቡ ላይ ከደረሰ በኋላ አቶ አርእያ ለቤተሰቡ የኢንሹራንስ ሽፋን ፖሊስ አረቦን ለሱና ለባለቤቱ ለተብርሃን ገዝቷል። የገዛው የኢንሹራንስ ሽፋን ዓይነት በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የጤና ኢንሹራንስ ነው። ይህ አይነት የኢንሹራንስ ሽፋን እንደሱ በገጠር አካበቢ ለሚሰሩ የተለመደ ነው። በመጀመሪያው ዓመት ማንኛቸውም የጤና ችግር አላጋጠማቸውም። ለተብርሃን ለከፈሉበት የጤና መደህን አረቦን ስአልተጠቀሙበትአቶ አርእያ ክፍያ ተመላሽ እነዲደርገግልት አስባለች።

ለአቶ አርያ ገንዘቡ እንዲመለስለት መብት አለው? ለምን?

ቁልፍ መልእክቶች

- ኢንሹራንስ ውስብሰብ ይመስል ነበር ። ነገር ግን አሁን መሰረታዊ የኢንሹራን አሰራርን ስለተረዱ ለኢንሹራን የሚከፈለው ዋጋ ለሚያቀረበው የአደጋ ሽፋን ጥበቃ ተመጠጣኝ መሆኑን መረዳት ይችላል።
- የጤና ኢንሹራንስ መግዛት ከፈለጉ የትኛው የቤተሰብ አባል የኢንሹራንስ ሽፋን ማግኘት እንዳለበት መወሰን አለበዎት። አንንዳድ የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ለእያንዳንዱ ባዘመዘገቡት ተጨማሪ የቤተሰብ አባል መሰረት ተጨማሪ አረቦን ያስከፍላሉ።አንዳንዶቹ ለአራት የቤተሰብ አባል ጥቅል ሽፋን ሲሰጡ ከአራት በላይ ቤተሰብ ከአስመዘገቡ ተጨማሪ ክፍያ ይጠይቃሉ።
- ለእያንዳንዱ ቤተሰብ አባል ለኢንሹራንስ ሽፋን ስለሚከፈለውን አረቦን አሰላል ደንቦቹን ማወቅ በጣም አሰፈላጊ ነው።
- የኢንሹራንስ ፖሊሲዎች ሁሉም አንድ አይነት አይደሉም።ኢንሹራንስ ከመግዛትዎ በፊት ስለ ቅደመ ሁኔታዎቹ በቅድሚያ ማወቅ ጠቃሚ ነው።ጥርጣሬ ካለዎት የኢንደሹራንስ ወኪለዎትን፣አሰሪዎን ወይም የሠራተኛ ማህበሩን ማማከረዎን እርግጠኛ ይሁን።
- የኢንሹራንስ ፖሊሲ መግዛት ከፈለጉ ወይም ጥያቄ ካለዎት የኢንሹራንስ ወኪለዎትን፣አሰሪዎን ወይም የሠራተኛ ማህበሩን ስለጉዳያ ወዲያውኑ ያማክሩ።

ማስታወሻዎች

አባሪና ቁልፍ ሰነዶች

ለድንገተኛ አደጋ ገንዘብ ለማሰቀመጥ ያሉ ተግዳሮቶች	ምክር
የማገኘውን ገቢዬን ለቤተሰቦቼና ለወላጆቼ መስጠት እመርጣለሁ (በተለይ ለወጣቶችና ለስደተኞች ግዴታው ከፍተኛ ነው)	• በግልዎ መቆጠብዎ ለሚያጋጥሞት ድንገተኛ አደጋ ቤተሰቦዎት እርዳት ሊያደርጉሎት በማይችሉ ጊዜ እረሳዎትን መርዳት ይችላሉ • ለሚገጥሞት ድንገተኛ አደጋ በትንሹም ቢሆን በየቀኑ፣በየሳምንቱ ገንዘብ ያስቀምጡ ቀስ በቀስ የሚያጠራቅሙት ገንዘብ ያድጋል።
ገንዘብ በክፍሌ ሳስቀምጥ ሊጠፋ ወይም ሊሰረቅብ ይችላል ብዬ እፈራለሁ።	• ገንዘብዎን ከቤትዎ ውጭ በሚያስተማምን ቦታ ካሰቀመጡ ማንም ሊደርስበት አይቸችልም። • ለአደጋ ጊዚ ብለው በቀላሉ በፈለጉት ጊዜ ሊያወጡት የሚችል የቁጠባ ሂሳብ ይከፈቱ
ገቢዬ ቋሚ አይደለም። ወቅታዊ ነው።	• ባገኙት የክፍያ መጠን ያህል ቁጠባ ያድርጉ
የማገኘውን ገቢ በሙሉ ዕዳዬን ለመክፍል እጠቀምበታለሁ።	• ከፍተኛ ወለድ ካለቸው እዳዎች በመጀመር እዳዎን ለመክፈል የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጁ • በተመሳሳይ ጊዜ ለድንገተኛ አደጋ የሚሆን ትንሽ ገንዘብ በየቀኑ ወይ በየሳምንቱ ቢያሰቀምጡ ገንዘቡ ቀስበቀስ ይጠራቀምሎታል።
መሰረታዊ የሁንት ፍላጎቴን መሸፈን አልችልም	• አላስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ለመቀነስ የሚችሉትን ያድርጉ። • ምንም እንኪን ገቢው ትንሽ ቢሆን ማንም ሰው በትንሹም ቢሆን መቆጠብ ይችላል። ትንሽም ብር በየቀኑ፣በየሳምንቱ እና በየወሩ ያስቀምጡ።

የጥያቄዎቹ መልሶች:

የጤና ኢንሹራንስ/መድህን የግል ሁኔታ ጥናቶች

የሥልጠና መርጃ ሸ 4.1



መልስ ለግል ሁኔታ ጥናት #1

የአባይነህ የኢንሹራንስ ሽፋን የከበደን የጤና ወጪ ሊሸፍን ይችላል? ለምን?

አይቻልም። የአባየነህ የኢንሹራንስ ሽፋን የከበደንን ሊሸፍን አይችልም። የዚህ አይነት የኢንሹራንስ ሽፋን ሊሰጥ የሚችለወው ለቅርብ ቤተሰብ ብቻ ነው። (ለባል፣ለሚስት ለልጆች) በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ ሰው የኢንሹራንስ ሽፋን ሊያገኝ የሚችለው ለዛ ሰው አረቦን ሲከፍል ብቻ ነው።



መልስ ለግል ሁኔታ ጥናት #2

ገመቹ ለሦስት ወር ያህል የኢንሹራንስ ሽፋን ለመግዛት ይችላል? ለምን?

ገመቹ ለሶስት ወር የመድህን ሽፋን ለመግዛት አይችልም። የአረቦን ከፍያዎች እንዲፈጸም የተዘጋጀው ለአንድ ዓመት ነው። የወራቱን ቁጥር መቀየር አይችልም።የዓመቱን የመድህን አረቦን መክፈል አለበት።



መልስ ለግል ሁኔታ ጥናት #3

አርያ ተመላሽ ገንዘብ የማግኘት መብት አለው? ለምን?

የትርሃስ አባት ተመላሽ ገንዘብ የማገኘት መብት የላቸውም። ምክንያቱም የገቡት የኢንሹራንስ ሽፋን አገልግሎት የሚሰጠው ለአደጋ ነው።ምንም እንኳን አንድም ቤተሰብ አባል ታሞ ሃኪም ጋር ባይሄድም የተከፈለ አረቦን አይመለሰም።




ወርቅነሽ


እማ!!
ቀንሽ አንዴት ነበር ማሬ?
ጥሩ ነበር። ነገር ግን ከእ ግዲህ በኋላ በማታው ፈረቃ መስራት እንደማልፈልግ ለአለቃዬ መንገር እፈልጋለሁ። በጣም ደክሞኛል። አስከ ሳምንቱ መጨረሻ ሁለት የአንገት ልብሶችን ሰርቼ መጨረስ
ለአለማየሁ የህጻን አልጋ ለማሰራት እያሰብኩ ነው ።ነገር ግን ይህን ማደረግ እንችል እንደሆነ ያለንን የዚህ ወር ባጀት መከለስ ያስፈልገናል።
ጥሩ ሃሳብ! ልጁን አስተኚው እኔ ለኛ ቡና ላፍላ።
እስከምትጨርስ እኔ ለቤተሰብ ስለማደርገው ቋሚ መዋጮ የግሌን ባጀት እገመግማለሁ/እከልሳለሁ። ሆቴል ከምሰራው የማገኘው 5000 ብር እና በእጅ ከሚሰራ የጥልፍ ስራ የማገኘው 3000 ብር የተጣራ ገቢ አለኝ። ጥሩ ወር ነበር!
እንዲሁም ለሞባይሌ ሚሞሪ ካርድና አዲስ ቀሚስ መግዛት እፈልጋለሁ። ለቤተሰቤ የተለመደውን ቋሚ መዋጮ አዋጣለሁ እንዲሁም ለራሴ 2000 ብር አሰቀምጣለሁ።
ጥሩ ይመስላል!
አሁን የእኛ ቤተሰብ ባጀት። እንዳልኩት እንደተለመደው ከግል ባጀቴ ለቤተሰቤ 6000 ብር አዋጣለሁ።
በየቀኑ ከምሰራው የግንባታ ስራ 4500 ብር አዋጣለሁ ብዬ አሰባለሁ።እንዲሁም ጎሮቤታችን አሮጌ ጠረጴዛ ገዝቶ የጠገንኩበት 500 ብር አለኝ።


እሺ አሁን ደሞ ወደ ወጪያችን እንሂድ/ ስለወጪያችን እናውራ ። መጀመሪያ ፍላጎታችንን እዘረዝራለሁ። ለቤት ኪራይ ፣ለመብራት ለውሃ ክፍያ ባጀት መመደብ ያስፈልገናል። እንዲሁም 3500 ብር ለምግብ እና 750 ብር ለትራንስፖርት ገምቼያለሁ።
100 ብር ለህክምና! ምናልባት ለስልክ ቅደመ ክፍያ እንዳይረሳ፡
ስለ አለማየሁ አልጋ የሆነ ነገር ብልሃል?
ኦ.... አዎ! አልጋውን ለመስራት ቁሳቁሶች ያስፈልጉኛል። ምንአልባት 1000 ብር ሊበቃ ይችላል። ቤተሰቦቼ አለማየሁን በጣም ናፍቀውታል። በሚቀጥለው ወር ደብረብርሃን ሄደን ልናያቸው እንሞክር።
ዝግጁ ነው!
የባ. ምግቤ
ቋሚ ባ.
ወርቅነሽለቤተሰብ የሚታደርገዉ ድጋፍ
የቋሚ ባ. ንዑስ ድምር
ተለዋዋጭ ባ.
ከበደ ከማንሳታ ስራዉ የሚያገኘዉ ገ.
የአሮጌ የእንጨት ጠረጴዛ ሽያጭ
የተለዋዋጭ ባ. ንዑስ ድምር
ጠቅላላ ገ.
ወጪዎች
አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች
ምግብ
የሞባይል ካርድ
ሕና/ህክምና
መብራትና ዉሃ
ትራንስፖርት
የቤት ኪራይ
የአስፈላጊ ወጪዎች ንዑስ ድምር
አማራጭ ወጪዎች
ለህጻን አልጋመሰሪያ የሚያገለግሉ ዕቃዎች
ለደብረብርሃን ጉዞ
የአማራጭ ወጪዎች ንዑስ ድምር
ጠቅላላ ወጪ ድምር
ከወጪ ቀሪ ገ.
መጠን
ብር 6000
ብር 6000
ብር 4500
ብር 500
ብር 5000
ብር 11000
ብር 3500
ብር100
ብር 100
ብር 150
ብር 750
ብር 3500
ብር 8100
ብር 1000
ብር 500
ብር 1500
ብር 9600
ብር 1400



ወርቅነሽ ምን ታስቢያለሽ ታዲያ? ቦታው ላንቺ እንደሚሆን ታስቢያለሽ?
ኦ... አዎ ቦታው በጣም አቅም አለው።
ደሴ ላይ ሆኜ ምርጥ ቡና ስሸጥ ይታየኛል!
እሺ ጥሩ ነው። በአካባቢው ባለ ባንክ ደንበኛ ነኝ።የማገኘውን ገቢ የማስቀምጠው በዛው ባንክ ነው።ለሱቅ የሚሆን ገንዘብ በባንክ አሰቀምጣለሁ።
ታገኝዋለሽ? የኔ ጓደኛ። ነገር ግን ቦታው ለስድስት ወር ብቻ ለኪራይ ሊቀርብ እንደሚችል አስታውሺ።
እኔም እንዲሁ እዛው ደንበኛ ነኝ! ምናልባት ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የማጠራቀሚያ ሂሳብ ለመክፈት ሞክሪ። እኔም አንድ አለኝ ለተወሰነ ጊዜ ገንዘብ የማውጣትን ግፊትን ለማስወገድ በጣም ጠቃሚ ነው።
ትልቅ ሃሳብ! ስለ ጉዳዩ አረጋግጣለሁ
ከጥቂት ቀናት በኋላ
ስለ መረጃው አመሰግናለሁ። አስብበታለሁ።
ያገኙት መረጃ ጠቃሚ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ።
SET A TIME DEPOSIT SAVINGS ACCOUNT


እስካሁን እኔ እንደፈለኩት ባይመስልም ነገር ግን የተሻለ እየሰራሁ ነው።
በጣም ጥሩ ይመስላል ራስሽን አታስጨንቂ!! አዲሶቹ ብርድልብሶዎች ቆንጆዎች ነበሩ ሁሉም ሸጠሻቸዋል!!
ከተማው ውሥጥ በጣም ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ሱቅ አውቃለሁ። ነገ መሄድ አለብኝ?ከኔ ጋር መምጣት ትፈልጊያለሽ?
ቢሆን ደስ ይለኛል! ከጥቂት ቀናት በፊት የራሴን ስራ ባጀት አዘጋጅቼያለሁ። ለሥራ ብዬ በባንክ የምቆጠበውን ለምሰራው ስራ የምጠቀምበትን ጥሬ ዕቀ እገዛበታለሁ።
ትክክል ነሽ። እናቴ በእኔና በዘዴዬ ልትኮራ ትችላለች። በዚህ ሳምንት በፈትል ጥጥ ከፊት ለፊቱ መስቀል የተጠለፈበት ቀሚስ መስፋት እፈልጋለሁ ነገር ግን ለዚህ ሥራ የሚውል እቃ ያስፈልገኛል።
በጣም አመሰግናለሁ።
የገዛሽው ይሄው። 400 ብር ነው።



ሰላም አባይነህ? እንዴት ነህ?
ሰላም ወርቅነሽ አትጨነቂ አሁን አደጋ አጋጥሞኛል። ከቤቴ ርቄ ነው ያለሁት ምንም ገንዘብ የለኝም። ለህክምና መክፈል ያስፈልገኛል። ትንሽ ገንዘብ ልትልኪልኝ ትቺያለሽ?
አ ...አይሆንም! ደህና እንደሆንክ ተስፋ አደርጋለሁ። አዎ በርግጥ ትንሽ ገንዘብ እልክልሃለሁ። ባለፈው ባሰየሁህ መሠረት የባንክ የቁጠባ ሂሳብ ከፍተሃል?
አልከፈትኩም። እንደተለመደው ገንዘቡን በወኪል አሰተላላፊው በኩል መላክ ይኖርብሻል።
እሺ ከሆቴሉ ቀጥሎ ባለው አዲስ የገንዘብ አሰተላላፊገ እጠቀማለሁ። ተመልሼ እደውልልሃለሁ።
ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ...
ተጠናቋል! አባይነህ! ከበፊቱ የተሻለ፤ ፈጠንና ዋጋው አነሰተኛ የሆነ አገልግሎት ሰጪ ነው። እባክህ ገንዘቡን እንደደረሰህ/እንደተቀበልክ አሳወቀኝ።
አዎ ወርቅነሽ ሁሉ ነገር ጥሩ ነው። አሁን ገንዘቡን ሰጡኝ። በጣም አመሰግናለሁ እህቴ!
EXPRESS TRANSFER



ከጥቂት ወራት በኃላ.....
Risks are inevitable
It is essential to have some
savings to cope with minor
emergencies.
አስታውስ
ለአደጋ ጊዜ የሚሆን ገንዘብ ለማሰቀመጥ
በርካታ ወራት ብሎም አመታት ሊወስድ
ይችላል።
ነገር ግን
ተስፋ አትቁረጡ ከተቻለ ዛሬ
ማስቀምጥ ጀምሩ/ር። ሳምንት
እንገኛኝ!
ዋው ጥሩ ክፍለ
ጊዜ ነበር።
አይደለም እንዴ?
አዎ ለአደጋ ጊዜ የሚሆን
ገንዘብ ለማስቀመጥ በጣም
ተበርታትቼያለሁ።
ቤታችን ሄደን ገቢያችንን
እንገምግም/እናጢን።
በዛው ቀን ትንሽ ቆይቶ...
መጀመሪያ የቤተሰቡን
ያለፈውን ዓመት ባጀት
መገምግም አለብን።
ደህና...
በጥር ወር 10,000፣
በየካቲት 10,500,እና
በመጋቢት 9,800 ...
እሺ ተጠናቋል።
አሁን ለአደጋ ጊዜ ምን ያል
መመደብ አለብን?
ደህና አሰልጣኞችን
ከወርሃዊ ገቢያችን አማካይ በትንሹ ሶስት ጊዜ
ማስቀመጥ አለብን ብሏል።ነገር ግን ከበዛ በትሹ
መቆጠብ እንችላለን።
ዝግጁ ነው።
እኔ በጣም ደስተኛ ነኝ
ለኛ በጣም ጠቃሚ
ነው።
አዎ አሁን
የመሄጃ ጊዜ ነው።
አውቶብሱ በግማሽ ሰዓት
ጊዜ ውስጥ ይንቀሳቀሳል።
ቤተሰቦቼ እየጠበቁኝ
ነው።


ገመቹ



ልጆቹን ማስተኛት አሰፈላጊ ይመስለኛል።
ቀኑን በሙሉ ሲጫወቱ ስለነበር ይደክማቸዋል።
ለድጋፍህ አመሰግናለሁ። እኔና ጫልቱ ከእዚህ በኃላ ለተወሰነ ጊዜ ቡና እየጠጣን እዚህ እንቆያለን ። ስለቁጠባችን እቅድ ማዉጣት አለብን።
ግቦቻችንን መከለስ፣ ወጪዎቻችን መገምገም እና ግባችንን እናሳካለን ብለን ያስቀመጥነዉን ቀን/ጊዜ እንደገና ማየት አለብን።
አዎ እንደሚታወቀዉ የሱቃቸንን ግድግዳ ማሰራት አለብን። እንደገናም የሱቃችንን ስም የሚያሳይ ማሰታወቂያ ባነር ማሰራት እፈልጋለሁ። የእነእዚህ አጠቃላይ ወጪ 3000 ብር እንደሚደርስ ነገረዉኛል።
ለሚቀጥለዉ የቢሊሱማ ልደት ቢሲኪሌት ሊገዛለት በጣም እፈልጋለዉ። ዘንድሮ ሊሳካ አልቻለም ግን ከአሁኑ ጀምረን መቆጠብ ከጀመርን ግን ማሳካት እንችላለን።
ምንም ረጅም ጊዜ ይፍጅ እንጅ ስለ ግል ቤታችን ማሰብ አለብን አዎ ቤተሰብ ጋር መኖር ጥሩ ነዉ ግን የራሳችንን የግል ቤት መስራት ህልም አለኝ።
አዎ አዉቃለዉ ለእዚህ ግብ በግምት እሰከ 100 000 ብር (መቶ ሺህ ብር) እንደሚጠይቅ አንድ ጓደኛ ነግሮኛል አንድ ተጨማሪ ክፍል ለሱቃችን መስራት(መገንባት) አለብን ይህ እስከ ሦስት ዓመት ሊፈጅብን ይችላል።
ሆ አዎ! ይህ በጣም ጥሩ ነዉ። እኔም የተሻለ የፋይናንስ ዉሣኔ ለመስጠት እንዲችል ነፃ የፋይናንስ ትምህርት መከታተል እፈልጋለሁ።
እዚህ ጋር ደርሰናል ! አሁን በየወሩ ምን ያህል እየቆጠብን ግባችንን ሊናሳካ እንደምንችል የበለጠ አዉቀናል።


የቁጠባ ዕቅድ
ግቦቹ
ግቡን የማሳካቱ ጊዜ
የገቢ ማሳኪያ ወጪ
ግቢን ከማሳኪያ ጊዜ በፊት የሚኖሩ ወራት(ግቢን ለማሳካት የሚፈጅባን ወራት)
ሌላ የገቢ ምንጭ (ለማራጭ ከሆነ)
ግቢን ለማሳካት እንዲቻል በየወሩ መቁጠብ ያለብኝ መጠን
አጭር ጊዜ ግብ (ከ12 ወራት ያነሰ)
የሱቁን ግድግዳ ለመጠገንና የማስታወቂያ ባነር ማሰሪያ
የአዘሀ ዓመት ሀዲር
ብር 3000
3 ወራት
ብር 1000
የመካከለኛ ጊዜ ግብ (ከአንድ እስከ ሶስት ዓመት)
የቢሊኡማ ብስክሌት ግዢ
የሚቀጥለዉ መስከረም ዓመት
ብር 9000
12 ወር
ብር 750
የረጅም ጊዜ ግቦች (ከ3 ዓመት በላይ)
የቢታችንን መሸረያ ዕቃዎች ግዢ
ከሦስት አመታት በኃላ ታህሳስ
ብር 100000
36 ወራት
የመንግስት የተመላሾች ማቋቋሚያ ብር4600
የተመላሾች ፕሮግራም
ብር 1500
ለግቢ ማሳኪያ በየወሩ የሚቆጥበዉ መጠን
(በቅኝ አግድም ያሉት ድምር)
ብር 3250



ገመቹ ምን ሁነሃል? የተጨነቅክ ትመስላለህ።
ሆ አዝናለሁ ማሬ ደህና ነኝ ግን ትናንት ዲነግዴ እንደገና ኪስ እንድገዛለት ጠየቀኝ ልጁ ጥሩ ልጅ ነዉ እንዲገዛለት የሚገባዉ ነዉ ።
አ ላለማዘን ሞክር፣ ትክክል ነህ ዲኔግዴ ሊገላዘት የሚገባዉ ነዉ።
ሆኖም አሁን የምንችለዉ ያህል መቆጠብ ይኖርብናል። ምናልባት እስከ ልደቱ ድረስ መቆየት ይኖርብን ይሆን?
አዎ ልክ ነህ። ግን ነገሩ እንደዚህ አይደለም ዛሬ ጎሬቤታችን ባይሳ
ለመብራት የሚከፍለዉ ስሌለዉ ገንዘብ እንዳበድረዉ ጠየቀኝ ።
አ አላወቅሁኝም እኔ ዛሬ ጫት ከአያንቱ ጋር ነበርኩ እርሷም ምንም አልነገረችኝም።
እርሱ ከሳዑዲ ስመለስ ለእኔ ጥሩ ነገር አድርጎልኝ ነበር ፣ አልሰጥህም ማለት ስላልቻኩ ገንዘቡን አበደርኩት።
ልክ ነዉ ፣ ገንዘቡን እንዳገኘ መልሶ እንደሚከፍልህ እገምታለሁ።
እኔም እንደዚያ እገምታለሁ ምክንያቱም ወጪያችን ብዙ ነዉ።
በእዚያ ሳምንት ዘግይቶ..
ዶክተር መድኃኒት እንደሚያስፈልገዉ ቢገልፅልንም ዋጋዉ ዉድ ሲሆን በቂ ገንዘብ የለንም
ገንዘብ ከሌለ አበዳሪ መበደር ይኖርብኛል።
አሁን ባይሳን ግንዘቤን እንዲመልስልኝ አናግሬዉ ነበር አሁንም በቂ ገንዘብ የለዉም።


ከጥቂት ወራት በኃላ ...
MFI
የዛሬዉ ክፍለ ጊዜ በጣም ጥሩ ነበር። የፋይናንስ ትምህርቱ ኮርስ በጣም እየረዳኝ ነዉ ።
አዎ ለእኔም ጭምር።
የስልጠና ኮርሶች በጣም ጠቃሚ እንደሆኑ እገምታለሁ በመሆኑም ነዉ ገንዘቤን መቆጠብ የቻልኩት።
አዎ ገንዘብን ለሌላ ጉዳይ አለመዋል ከባድ ነዉ ግን ዛሬ የብድርና ቁጠባ ተቋም ሰራተኛ ይኼንን በራሪ ወረቀት ሰጠኝ። በኮንትራት ስለሚደረግ ቁጠባ ነው።
ዋዉ።
ይሄ ትልቅ ዓላማ ነዉ ገንዘብን ለተለያዩ ጉዳዮች የማዉጣት ጉጉት እንዴት ተቋቋምክ?
በአሁኑ ጊዜ ዋነኛዉ
ግቤ ሳላቋርጥ በመቆጠብ ቤት መስራት ነዉ ቁጠባ አለኝ ግን በቂ አይደለም።
በመሆኑም በእዚህ አካዉንት የተወሰነ ገንዘብ በቋሚነት በየወሩ መቆጠብ እችላለሁ ለተወሰነ ግብ ማሳኪያ ማለትም እንደ ቤት መስሪያ ዕቃዎች/ግብዓት ሚሚያ የሚያገለግል በዉል ላይ የተመሰረተ ቁጠባ አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማት አሉ
በጣም የሚያጓጓ ነዉ! አኔም ስለ እዚህ ነገር መረጃ ማግኘት እኔ በገንዘብ ረገድ ትንሽ ዝርክርክነት አለብኝ
ግብህን ለማሳካት የምትፈልግ ከሆነ ገንዘብህን በሚገባ መያዝ አለብህ አሁን ወደ ስራ ለመሄድ ወደ ዉሥጥ መግባት አለብኝ ነገ እንገናኝ ባይሳ!


ገመቹ አሁን እዚህ አለ እባክህ እርዳን ። ማቀዝቀዣችን ተሰብሯል ምግቡን ወደ አያንቱ ቤት ልንወስድ ነዉ።
አይ አይደለም ወደ ማቀዝቀዣ ሱቅ መዉሰድ ያስፈልገን ይሆን?
ላለን ምግብ በጣም ትንሽ ነዉ?
ጓደኞቼ በጣም አመሰግናለሁ ይህ ለጥቂት ቀናት ነዉ ቶሎ ብዬ አዲስ መግዛት አለብኝ።
ትልቅ ሃሳብ ነዉ ብዙ ነገር በአንድ ጊዜ የሚያቀዘቅዝ ማቀዝቀዣ መግዛት እችላለዉ ስለእዚህ አስብበታለሁ አመሰግናለሁ።
አዲሱን ቤትህን ሰትጨርስ ሱቅህን እዚያ መዉሰድህ ስለማይቀር ለቤትህና ለሱቅህ የሚበቃ ትልቅ ማቀዝቀዣ ለምን አትገዛም?
ጫልቱ ልትረጂኝ ትችያለሽ ወይ? ከገንዘብ አበዳሪ ተቋማት ተበድረን አዲስ ማቀዝቀዣ መግዛት እንችል ዘንድ የምክፈል አቅማችንን ማስላት እየሞከርኩ ነዉ። እስቲ ይሄንን ተመልከቺ።
ከገንዘብ አያያዝ ስልጠና የተማርኩት ከምታገኝዉ ገቢ ከ 30% በላይ የሆነ መክፈል የሚጠይቅ ዕዳ እንዲኖርብህ አያስፈልግም። ለማንኛዉም ልየዉ ።
በእዚህ ስሌትህ መዉሰድ ያለብህ ከመደበኛ ስራ የምታገኝዉን ገቢን ብቻ ነዉ። ከሱቅህ የምታገኝዉ ተለዋዋጭ በመሆኑ እዚህ ስሌት ዉስጥ መግባት አይችልም።
አዎ ትክክል ነዉ አመሰግናለሁ ማሬ ስለእዚህም ስለብድር አሰጣጣቸዉ ከብድር ተቋማት መረጃ እሰበስባለሁ።



COMMERCIAL BANK
MFi
NGO
ከሰዓት በኃላ
ሃይ ገመቹ! እንዴት እየሄደ ነዉ?
አሁን የትኛዉ ለእኛ የሚስማማ እንደሆነ መምረጥ ነዉ፡
አዎ ወደ ባንክ፣ ኤም ኤፍ አይ ገንዘብ አበዳሪ ተቋም እና ወደ መንግሰታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመሄድ ስለአሰራራቸዉ የሚገልፁ እነዚህን ብሮሹሮች አምጥቻለሁ።
ትንሹና ቀላሉ ብድር መንግሰታዊ ያልሆነዉ ድርጅት ነዉ ግን ደግሞ በየወሩ የሚመለሰዉ የብድር ክፍያ መጠን ብዙ ስለሆነ መንግስታዊ ያልሆነዉ ድርጀት ብድር ምርጫችን ሊሆን አይችልም።
እንደ ሌላ አስፈለጊ ጉዳይነት ሊወሰዱ የሚችሉ ነገሮች ይኖሩ ይሆን?
ልንበደረዉ የምንችለዉ መጠን ወይም ፋይናንስ ያልሆነ አገልግሎት ያላቸዉ ከሆነ
የብድር መጠኑ ይኼን ያህል ችግር አያመጣም፣ ግን ኤም ኤፍ ኣይ (የገንዘብ ብድርና ቁጠባ ተቋም) ብቻ ነዉ ድጋፍና ፋይናንስ ያልሆነ አገልግሎት የሚሰጠዉ ስለእዚህ የብድር መጠናችንና አጠያየቃችን ሁኔታ መፈተሽ ያስፈልገናል።
ጥሩ ይመስላል ወደ ቤት ተመልሰን ሌላ አማራጭ ይኖር እንደሆን እንይ።
በገንዘባችን ላይ የተሻለ ዉሳኔ ለመዉሰድ እንዴት እንደምንችል በሚገባ በመማራችን በጣም እኮራለሁ ሁልጊዜም ግባችንን ወደ ማሳካት እየተቃረብን ነዉ።


ዳዊት


ረፋዱ ላይ
አህ አይደለም! ዳዊት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ክፍያ አልከፈለም እንዴ ? ዳዊት ብዙ ጊዜ ይሄን አያደርግም። አሁን እደውልለታሁ....
የኔ ልጅ ተጠንቀቅ! መልካም ቀን ይሁንልህ።
እኔም መሄድ አለብኝ። ቀኑን ሙሉ ፋብሩካው ላይ የምሰራው ስራ አለኝ ።
"እንደተናገርኩት በተቻለ መጠን መቆጠብ አለብኝ በመሆኑም ሣዑዲ አረቢያ በምደርስበት ጊዜ ለአስቸኳይ የሚሆን ገንዘብ ይኖረኛል። ጌዴዎን መደበሩ ፓ ስሚጠብቀኝ መሄድ አለብኝ ። ውይይታችንን ማታ እንቀጥላለን።
በኋላ
አዝናለሁ ስላንተ ክፍያ የተመዘገበ ምንም መረጃ የለኝም። የተቆረጠው የመብራት መስመር እንዲቀጠል መክፈል አለብህ ወይም ተከፍሏል የሚል የተመታበት የክፍያ ደረሰኝ ማቅረብ ይኖርበሃል።
ይሄ ይገርማል ..! እሺ ደረሰኙን ይዤ እመለሳለሁ።
እኔ አላምንም! በትክክል ከፍያለሁ! አሁኑኑ ወደ ኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ቢሮ እሄዳለሁ። እሺ እማማ!
ተመልከት! ይህ ደረሰኙ ነው! አውቀዋለሁ! እንደዚህ ለጊዜው የፋይናንስ ሰነዶችን መያዝ አስፈላጊ እንደሆነ በገንዘብ አያያዝ ትምህርት ተምሬአለሁ።
DO NOT THROW -PAPERS
የኔ ልጅ መብራቱ ተቀጥሎልናል! ደረሰኙን ማስቀመጥህ በጣም ጥሩ ነው!
ዕውነት ነው እማማ ! ሁሉም በመስተካከሉ ደስ ብሎኛል!


ስለዚህ ጌዴዎን ንግድህን እንዴት እንዳሳደከው ለከፍያለው ንገረው ። የሁለታችሁም ንግድ በጣም ተመሳሳይነት አለው።
ደህና...ለብዙ ወራቶች ሊባኖስ ሰርቼ ባጠራቀምኩት ጥቂት ገንዘብና የተጠቀምኩበትን አሮጌ የእንጨት ውጤቶች በመሸጥ ያገኘሁትን ጥቂት ገንዘብ ነው።
እና ትንሽ ለመቆጠብ የሸጥከው በቂ ነው?
ሁልጊዜ ከመበደር ይልቅ መቆጠብ እመርጣለሁ። አውቃለሁ ለአስቸኳይ ነገሮች በቂ ገንዘብ ላይኖረኝ ይችላል። ነገር ግን ምንም ዓይነት ወለድ አለመክፈልና በገንዘቤ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እራሴ መወሰንን እመርጣለሁ፡
ንግዴን ለማስፋፋት በየሳምነቱ ጥቂት ገንዘብ ለብቻ በቁጠባ ሂሳቤ ስለማስቀም በየወሩ ትንሽ መሻሻሎችን አድርጌያለሁ። ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት የሱቁን ግድግዳ ቀለም መቀባት ችያለሁ።
እንዴታ! የቆጠበከውን ከተጠቀምክ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው።
ከፍያለው አንተስ? እንዴት ጀመርክ?
የጀመርኩት በቁጠባ ነው ሆኖም ለወጣቶች ልዩ ብድር ከሚሰጥ ____ አበዳሪ ብድር ወስጄ ነው። ብድሩን በየጊዜው በወቅቱ መክፈል ይኖርብኛል። ነገር ግን በየወሩ መጨረሻ በግዴታ መቆጠብ ይኖርብኛል።
በተጨማሪ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በከተማው ጥሩ የንግድ እንቅስቃሴ በሚደረግበት ቦታ ሱቅ ለመከራየት ከባለቤቴ ወንድም ብድር ወስጃለሁ። ትልቅ አጋጣሚ ነበር ግን አሁን ሁለት ብድሮች አለብኝ ሁሉም ጥሩ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።



ከባለቤትህ ወንድም?
አዎ፣ ለባለቤቴ ወንድም ወለድ መክፈል አለብኝ። በጊዜው ካልከፈልኩ ከእርሱና፣ ከባለቤት እንዲሁም ከመላው ቤተሰብ ጋር ችግር ይገጥመኛል!
አዎ! ዕውነት ነው። ገንዘብ መበደር ጉዳት ይህ ነው። ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ከቁጠባ ይልቅ በበድር በጣም በፈጠነ መንገድ ገንዘብ ያገኛሉ። በሱቁ ውስጥ እያንዳንዱን ትንንሽ ነገር ለመለወጥ ለወራቶች መቆጠብ አለብኝ።
አዎ! አሁን ግን ብዙ ጫና እየተሰማኝ ስለሆነ በጣም ከባድ ዕዳ ውስጥ እንዳልገባ እፈራለሁ።
አዎ! ከዛ መጠንቀቅ ይኖርብሃል! አንድ የቅርብ ጓደኛየ ወደ ሣዑዲ አረቢያ ለመሄድ ብድር አገኘ። ነገር ግን ብድሩን መክፈል ስላልቻለ እሱና ቤተሰቡ ትልቅ ችግር ውስጥ ናቸው።
?!
ነገር ግን ሌላ ምን ላድርግ እችላለሁ? በቂ መቆጠብ አልቻልኩም። ያለው ብቸኛ አማራጭ ገንዘብ መበደር ብቻ ነበር ።
ደህና! አንዳንድ ጊዜ ንብረትህን የማትፈልገው ከሆነ ልትሸጠው ትችላለህ። ምናልባት የማትጠቀምበትን ውድ ጌጣጌጥና እንደ ጠረጴዛና ወንበር የመሳሰሉ የቤት እቃዎች ሊሸጡ ይችላሉ።
ምናልባት ልክ ነህ። ሌላ ጊዜ ፕሮጀክቶቼን የማንቀሳቅስበት ሌላ መንገድ ማሰብ አለብኝ። ወይም ከእናንተ ጋር መስራት እችላለሁ! አመሰግናለሁ ጓደኞቼ!
አመሰግናለሁ። ከአንተ ጋር መነጋገር በጣም ደስ ይል ነበር።
አዎ! ስለ ፋይናንስ አማራጮች ጥቅሞችና ጉዳቶች ብዙ ተምሬአለሁ።



ከጥቂት ሳምንታት በኋላ....
ዳዊት እንዴት ነህ? ዛሬ የተጨነቅህ ትመስላለህ...
አዎ! አዝናለሁ። ከጥቂት ቀናት በፊት አባቴ የሥራ ላይ አደጋ ስለደረሰበት ኤክስ ሬይና መድሀኒት ያስፈልገዋል። በመሆኑም ለሕክምና የሚሆን በቂ ገንዘብ ስለሌለን ገንዘብ መበደር ይኖርብኛል።
አሃ ገባኝ። እና ቁጠባህ እዚህ ነው? አሁንም ዕቅድህ ለሣዑዲ አረቢያ ጉዞህ ለመጠቀም ነው?
አዎ! በሚገባ። እሱ ዋናው ግቤ ነው። ዕቁብ ለእኔ በጣም ጠቃሚዬ ነው።
ከዚያ ቀን በኋላ.....
ዳዊት ደህና ነህ? ምን እየሰራህ ነው?
አዎ!አዎ! ልነግርህ ነው። እባክህ ትንሽ ታገሰኝ .....
እና የፈለከውን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ዓይነት ታውቀዋለህ?
ይመስለኛል። መደበኛውን የቁጠባ ሂሳብ እፈልጋለሁ። ደህንነቱ የተጠበቀና ለአስቸኳይ ጉዳይ (እርስዎን እንደገጠመዎት አደጋ-ባንኩም የወጪ ካርድ ይሰጠኛል) ገንዘቡን ብፈልገው ማውጣት እችላለሁ። ለፍላጎቴ የበለጠ የሚስማማኝን የባንክ ሂሳብ ለማግኘት ወደ ተለያዩ ባንኮች እሄዳለሁ።
ከጉዞየ በፊት ቁጠባየን እንድጠቀም መነሳሳትን አልፈልግም። ለሥራየ ምስጋና ይድረሰውና እየሰራሁ የቆጠብኩት ጥቂት ጥሬ ገንዘብና ዕቁብ አለኝ። ስለዚህ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ለመክፈት እያሰብኩ ነው። መረጃዎችን በአንላየን እያየሁ ነበር።


ከጥቂት ሰምንታት በኋላ...
እይ እማማ! ወደ ባንክ ሄጄ የወጪ ካርዴን ሰጡኝ። ለመጠቀም ዝግጁ ነው። ወደ ኤቲኤም እየሄድኩ ስለሆነ የምትፈልጊው አለ?
አዎ እባክህን ጥቂት ስጋ፣እንጀራና ወተት ግዛልኝ።
በጣም ጥሩ። ይህ በጣም ቀላል ነበር።
Thank you for your visit
እንዴት መክፈል ይፈልጋሉ?
የባንክ ካርድ አለኝ። ይቀበሉኛል?
አዎ! በሚገባ። በአሁን ጊዜ ብዙ ደንበኞች በዚህ ዓይነት ነው የሚከፍሉት።
እንዴት ነው የሚደረገውው? ካርዱ ይሰራል?
አዎ! ቀሪ ገንዘቤን አረጋገጥኩ፣ ጥቂት ገንዘብ ወጪ አድርጌ ከሱቅ ለገዛሁት ዕቃ ከፈልኩ። ለጓደኛየ ለአባይነህ ስለዚህ ካርድ ለመንገር ሣውዲ አረቢያ እደውላለሁ።
አባይነህ ካርዱ የሚደንቅ ነው! ሣውዲ አረቢያ ውስጥ ልጠቀመው እችላለሁ ብለህ ታስባለህ?
አዎ ጓደኛዬ። በዓለም ላይ በየትም ቦታ ልትጠቀመው እንደምትችል ሰምቻለሁ። በኢትዮጵያ፣ በውጭ አገር በካርዱ ላይ ያለው ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ከሆነ፣ ወደ አገር ቤት ከመምጣት በፊት ወደ ባንክህ ሄደህ መነጋገር ይኖርብሐል።



እሺ! ተዘጋጅቻለሁ።
አሁን መተገበሪያውን
ክፈት።
ቀስ፣ቀስ...
ቆይ ልየው...
ተከናወነ!
ደህና፣
አሁን የሚሰራ መሆኑን
ለመሞከርና ለማየት
ጥቂት ገንዘብ
በኢ- የገንዘብ ቦርሳ በኩል
እልክልሃለሁ።.
send money
You have received money
ተመልከት!
ይኸው ገንዘቡ። ዋው
ተደንቄአለሁ። ቀላልና
ፈጣን
ልጄ ስላንተ ደስ ብሎኛል።
ሁሉንም ግቦችህን ታሳካለህ ብየ ተስፋ
አደርጋለሁ።
ስላስተማርከኝ
አመሰግናለሁ። ኢ-ዋሌትን
መጠቀም እቀጥላለሁ ብየ
አስባለሁ።
ደህና፣ የቁጠባ ሂሳብ አለኝ፣
የወጪ ካርድና አሁን ደግሞ ኢ-ዋሌት። ሣዑዲ አረቢያ
በምኖርበት ጊዜ በኢ-ዋሌት በኩል ገንዘብ ልልክልህ
እችላለሁ።


ትርሃስ



ዛሬ ያንቺን ጓደኛ ሰመሃልን ገበያ ውስጥ አያኋት ስለ እህትሽ ጠየቀችኝ። ራህዋ ሊባኖስ ውስጥ እንዳለች ስነግራት ደስተኛ ነበረች።
ከባድ መሆኑን ባውቅም ከራህዋ ገር እንደምንገናኝተስፋ አለኝ።
ስለእኛ አትጨነቅ ይህንን አጋጣሚ ካገኘን በጣም ደስተኞች ነን።
ደህና.... ራህዋ ከቤቷ ርቃ ስለሄደች ትንሽ አዝኛለሁ።
አዎ ትክክልነው። ምንም እንኳ ገንዘብ እየላከች ብትረዳንም በጣም ትናፍቀናለች።
ይገባኛል። ነገር ግን ምስጋና ለሷ ይሁንና እሷ በላከችው ገንዘብ ክፉ/መጥፎ ጊዜን አልፈንበታል።
አዎ ያንን አውቃለሁ።ራህዋ ለመሰደድ መወሰን ለኛ ገንዘብ በረከት/ምንጭ ሆኗል።
በሌላ በኩል በቤት ውስጥ የሚረዳኝ ቀንሷል። አንቺ ከሄደሽ ደሞ በጣም ይብሰል።
በጣም አትዘኝ እማማ እኔ ወደ ሊባኖስ የሚሄደው ገንዘብ ለመያዝ ነው።ነገር ግን ወደ አገሬ ተመልሼ የራሴ ሱቅ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ።
ስለ አንቺና እህትሽ በጣም ደስተኛ ነኝ። ልምዱ ስላላችሁ የራሳችሁን ውሳኔ መወሰን አለባችሁ። ነገር ግን እኔ አዚሁ ሆናችሁ የብዙ ልጆች አያት ብሆን አወድ ነበር።


ተመልከት አባዬ ካለፈው ወር የበለጠ መቆጠብ ችያለሁ።
በጣም ይደንቃል! ነገር ግን ገንዘብ ለማሰቀመጥ ሌላ ቦታ ያስፈልግሽ ይሆናል።
አዎ.....እያሰብኩበት ነበር።አንዳንዳንድ ጊዜ ገንዘቤን በፍራሽ ስር ማሰቀመጤ ምቾት አይሰጠኝም። ብዙ ጊዜ ለረጅም ሰዓት ስራችንን ምንሰራው ከቤታችን ውጪ ስለሆነ የማናውቀው ሰው ቤታችን ሊገባ ይችላል።
ገንዘቤን በባንክ ባስቀምጥ ይሻለኛል ወይ ብዬ አሰባለሁ።የባንክ ሂሳብ ይከፍትሉኝ ይሆን? እንዴት ነው የሚሰራው?በኋላ ገንዘቤን ማውጣት ባልችል ምን ይፈጠራል? ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ?
ለምን ሄደሽ አትጠይቂያቸውም? አንቺ ሁል ጊዜ አዲስ ነገር ለማወቅ ትወጃለሽ።
በሚቀጥለው ቀን
አባዬ.....ምክርህን ስምቼ ወደ ባንክ ሄጄ ነበር። ከተለያዩ ተቋማት በርካታ መረጃዎችን አግኝቻለሁ።አሁን አውቄያለሁ መደበኛ የባንክ ሂሳብ መክፍት መሞከር ይኖርበኛል። በከፈትኩት የባንክ ሂሳብ ገንዘቤን አስቀምጣለሁ ገንዘብ ሲያሰፈልገኝ አወጣለሁ።
ትልቅ ነገር ነው ትርሃስ። በሚቀጥለው ሳምንት አብረን ልንሄድ እንችል ይሆናል።
ደስ ይለኛል እንዲሁም ስልኬም በደንብ አይሰራም ሌላ አዲስ ለመግዛት ምን ያህል እንደሚያሰውጣኝ ማወቅ ያስፈልገኛል።


ሰላም ሙህዲን እንዴት ነህ ?
አባቴ ሰላምታ አቅርቦሎሃል።
እንደሁልጊዜው እባክህ ይህንን ግዢ አንተ ጋር ባለው መዝገብ መዝግብልኝ ።
እርግጠኛ ነኝ ትህራስ።
ይኸው ደረሰኝሽን ያዥው። ቤተሰቦቿሽን ሰላም በይልኝ።
ለምን እሰከ አሁን ደረሰኝ መሰጠቱን እንደቀጠለ አልገባኝም። በየወሩ ተመሳሳይ ወጪ ስለማወጣ አምንዋለሁ።
ትርሃስ በዛ ሱቅ ያለብሽን እዳ ዛሬውኑ መዝጋት/መክፈል አለብሽ።
ገንዘብ አለሽ?
ዛሬ?
ሳምንት ነው ብዬ አስቤ አልነበረም እንዴ?
ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ.....
አዝናለሁ ትርሃስ ጠቅላላ ሂሳቡ 1,150.00 ብር ነው።ተመለከቺ ጠቅላላ የገዛሽው መጠን እነዚህ ናቸው።
አምምም.... እርግጠኛ ነህ? እንዳለፈው ወር ያለብኝ 1000.00 ብር ነው ብዬ አስቤ ነበር።
በጣም እርግጠኛ ነኝ። በዚህ ወር ዋጋ ጨምሯል። እንዲሁም የገዛሽው ብዙ ነገር ነው።
ኦ...አይ። እኔ ደረሰኝ አሰቀምጬ አላውቅም.....አሁን 1150.00 መክፈል እንዳለብኝ አስባለሁ።ከዚህ በኋላ ደረሰኞችን አስቀምጣለሁ።


በጣም ተደንቄያለሁ መቀሌ ከመጣሁ ረጀም ጊዜ ሆኖኛል። አዲሱ የገበያ ቦታ ግዙፍ መሆኑን ሰምቼያለሁ።
አዎ እማዬ ብዙ ሱቆች ያሉት ዘመናዊ ህንጻ ነው።
ተመልከቺ ያንን የአንገት ልብስ/ሻርፕ በሚቀጥለው ሳምንት ልደቱን ለሚያከብረው ጓደኛዬ ተስማሚው ነው። ወደ ውስጥ እንግባ!
ጥሩ ምርጫ ነው። እንዴት ለመክፈል ፈልግሽ?? በዚህ ወር በዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ ካርድ ለሚከፍል ደንበኛ የ5% ልዩ ቅናሽ አለን።
ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ???
ኦ...በእርግጥ? በሞባይሌ ላይ የዲጂታል የገንዘብ ቦርሳ መተግበሪያ አለኝ። ነገር ግን በፍጹም ተጠቅሜበት አላውቅም። ልጠቀምበት እችላለሁ?
አዎ። እባክሽን ይህን ምስል በ QR እንዲነበብ/ስካን/ በማደረግ ወዲያውኑ ከዲጂታል የገንዘብ ቦርሳዎ ገንዘቡ ተቀናሽ ይደረጋል።
ዋው!በጣም ይደንቃል! እኔም ዲጂታል የገንዘብ ቦርሳን መጠቀም እፈለጋለሁ.... ለመጠቀም በጣም ቀላል ይመስላል።ጥሬ ገንዘብ መያዝ አያስፈልገኝም።
አሺ አማዬ ወደ እቤት ስንመለስ መተገበሪያው ሞባይል ላይ እንዴት እንደሚጫን እረዳሻለሁ።


አድምጪኝ ረሃዋ በዚህ ጉዳይ አልቀልድም። ትላንትና ከአነሰተኛ የገንዘብ ተቋም የሚሰራ ሰው ቤታችን መጥቶ ነበር። ከተቋሙ ገንዘብ እንደወሰድሽ ተናግሯል።በዚሁ ሁኔታ ተረብሻለሁ።
አትጨነቂ እህቴ ስለኔ ምንም እንደማታውቂ ንገሪው። ይረሳዋል።
0:09
11:45 AM
Rahwa
0:07
11:47 AM
አብደሻል/የምትሰሪውን አታውቂም? ብዙ ገንዘብ ከነሱ ወስደሻል..... ገንዘብ የወሰድሽ ከአነሰተኛ የብድር ተቋም ብቻ ሳይሆን ከጓደኞችሽም ገንዘብ ተበድረሻል...ትክክል?
ደህና አዎ ነገርግን ገንዘቡን በኋላ ላይ መልሼ እልክላቸዋለሁ።ገንዘቡን የፈለኩት ወደ ሊባኖስ ለመሄድ ነው።
ይህንን ጉዳይ በጥሞና ማየት ያስፈልገሻል
አላውቅም... ባለፈውም ሳምንት ተመሳሳይ ነገር ነው የነገርሽኝ።
ደህና ሁኚ! አዝናለሁ እህቴ መሄድ አለብኝ በኋላ ላይ እደውልልሻለሁ።
ከጥቂት ቀናት በኋላ.....
የተበደረችውን አስከምትከፍል ድረስ ከእንግዲህ በኋላ ከራሀዋ ጋር መነጋገር አልፈልግም።
ይበልጥ ነገሩን የሚያባብሰው ከጓደኛዋ ማእዶት ጋ ገበያ ተገኛችተን ስለ ራህዋ ጠየቀችኝ ምክንያቱም ከሷ ብዙ ገንዘብ ተበድራለች።በጣም አሳስቦኛል.....
ZZZ


እህህ!
የጀርባዬ ህመም
ሊገድለኝ ነው
መድህን/ኢንሹራንስ አለሽ?
እኔ ከአሁን ጀምሮ ለ ስድስት ወር የሚያገለግል የማህበረሰብ
አቀፍ ኢንሹራንስ አለኝ ምንም እንኳ አስካሁን
ባልጠቀምበትም ደህንነት ይሰማኛል።
መመዝገብ አለበሽ.....
ከጥቂት ሳምንት በኋላ.....
ጀርባሽ እንዴት ነው?
አስከ አሁን እንደተጎዳ ነው?
አሁን በጣም ተሸሎኛል አመሰግናለሁ።
ስለ ማህበረሰብ አቀፍ መድህን የሰጠሽን ምክር
ተቀበዬለሁ ። እኔና ለተብርሃን ተመዝገበናል።
ስለጠቃሚው ምክርሽ አመሰግናለሁ።
ጥሩ ጓደኛ ነሽ።
አሁን ውለታሽን ልመልስ።
ወደ ገንዘብ አያያዝ ትምህርት ከኔ ጋር መምምጣት አለብሽ፡
ገንዘብን በአግባቡ ለመያዝ በጣም ይረዳሻል።
አንቺም እንዲሁ
ጥሩ ጓደኛዬ ስለሆንሽ ያንቺን ምክር
እቀበላላሁ/እከተላለሁ።
ወደ ሚቀጥለው ስብሰባ አብረን
እንሂድ!

ትርጉም

ጠቅላላ

ግብ
- ግብ ማለት ወደፊት ሊያሰኩት የፈለጎት ጉዳይ ነው።

መደበኛ ኢ-መደበኛ
- በአጠቃለይ መደበኛ ማለት የተወሰነ ቅርፅ ያለው ማለትም በመንግስት የታወቀ በታወቀ የህግ የሚመራና መዋቅር በመንግሰት የሚታወቅ አሰራር ነው።
- መደበኛ ያልሆነ(ኢ- መደበኛ) ፡- በተቃራኒው በህህግ የማይመራና ምንም ዓይነት መዋቅር የሌለው በመንግስት ያልተመዘገበ አካል ሲሆን። ለምስሌ በኢመደበኛነት የሚካሄዱ ንግዶች በመንግስት ያልተመዘገቡና ግብር የማይከፍሉ ናቸው።

በጀት
- በጀት ማለት ገንዘብን በመጠቀም ግብን ለማሳካት የወደፊት ዕቅድ የሚወጣበት አሰራር ነው።

የቅጥር ውል
- በአሰሪና ሠራተኛ መካካል የሁለቱን መብትና ግዴታዎችን የሚገልፅና ለሁለቱም ተዋዋዮች የሚጠቅም ህጋዊ ስምምነት ነው።
- የስራ ውሉ ግዴታዎችን ኃላፊነቶችን እና መብቶችን ማካተትአለበት። የስራ ውሉ የስራ ሁኔታዎች እነደ ክፍያ የስራ ሰዓት እና የቅጥሩን ሁኔታ መጥቀስ አለበት።
- የቅጥር ውል በሁለት ተዋዋይ ወገኞች መካካል በፈቃደኝነት የሚፈረም ነው።፤የስራ ቅጥር ውል ሁለቱም ወገኖች ሊረዱት በሚችል ግልጽ በሆነ ቋንቋ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ሁለቱም ወገኖች ፈርመውበት ተዋዋይ ወገኞች አንዳንድ ቅጂ ይወሰወዳሉ።

የፋይናንስ ተቋም
- የፋይናንስ ተቋም የመንግስት ወይም የግል ተቋም ሆኖ እንደ ቁጠባ፣ብድር እና የመሳሰሉትን ገንዘብ ነክ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

የቁጠባና ብድር ህበረት ስራ
- የቁጠባና ብድር ህበረት ስራ በተለዩ አባላት አነሰሽነት በዲሞክራሰዊ መንገድ የተመሰረተ የህበረት ስራ ማህበር ነው። ይህ የመረዳዳት ህበረት ስራ የአባላቱን የገንዘብ ፍለጎት ለማሟላት የሚተጋ ሲሆን የሚቆጣጠሩትና የሚያሰተዳደሩት አባላቶቹ ናቸው።

የቁጠባ ሂሳብ

መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ
- መደበኛ የቁጠባ ሂሳብ ወይም የሂሳብ ደብተር የቁጠባ ሂሳብ (አንዳንድ ጊዜ በፍላጎት የማጠረቀሚያ ሂሳብ ይባላል) በገንዘብ ተቋማት የሂሳብ ባለቤቱን በፈለገው ጊዜ ገንዘብ ለማሰቀመጥና ለማውጣት የሚደረግበት ነው፡ ፡ የሚያሰቀምጠውና የሚያወጣው ገንዘብ በቅድሚያ አይወሰነም።ለቁጠባ ሂሳብ ወለድ የሚከፈለው በዓመት ነው፡ ፤የቁጠባ ሂሳብ ሁልጊዜ በቀጥታ ለመክፍል አያገለግልም።

ዝግ የቁጠባ ሂሳብ
- ዝግ የቁጠባ ሂሳብ ደንበኛው የሆነ ጉዳይን ለማሳካት በዝግ ሂሳብ ገንዘብ በፋይናንስ ተቋም የሚያሰቀምጥበት አአሰራር ነው። የሂሳቡ ባለቤት የሚያሰቀመጠውን ገንዘብ መጠንና ጊዜ በመወሰን ገንዝብ ያስቀምጠጣል ። ገንዘቡን ለማጠራቀም የወሰነው ጊዜ ገደብ ሲያለቅ/ሲደርስ ሁሉንም ገንዘብና ወለድ ያወጣል።የወለድ መጠኑ ግን በቅድሚያ የተወሰነ ነው።

በጊዜ የተገደበ የቁጠባ ሂሳብ
- ባንኩ ደንበኛው ጥቅል ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያሰቀምጥ ፈቅዶለት ደንበኛው ያሰቀመጠውን ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ እንዳያወጣ ቃል ያስገባል። ደንበኛው ካሉት አማራጮች አንዱን መመረጥ ይችላል። የዚህ አይነት የቁጠባ ሂሳብ በጊዜና በገንዘብ መጠን ስለሚገደብ ሁለጊዜ የተሻለ ወለድ ለደንበኛው ይከፈላል።

ብድር

የብድር ወለድ ምጣኔ
- ገንዘብ ተበዳሪው ከተበደረው ገንዘብ ተጨማሪ ለአበደረው ተቋም የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው።

ዋና ብድር
- ወለድን ሳይጨምር የብደሩ ዋናው መጠን

የብድር ሁኔታዎች
- ተበዳሪው በብድር የወሰደውን ገንዘብ የሚጠቀምበት እና የሚመልስበት ጊዜ የሚያሳይ

የብድር መያዣ
- ተበዳሪው የተበደረው ገንዘብ መመለስ ባይችል ለብድሩ መጠን ለባንኩ የሚያስይዘው ተመጣኝ ንብረት ሲሆን መሬት፣ተሸከርካሪ እና የቁጠባ ሂሳብ ሊሆን ይችላል።

የእፎይታ ጊዜ
- ብድር ከተወሰደ በኋላ የመጀመሪው ክፍያ ከመጀመሩ በፊት ሚሰጥ የእፎይታ ጊዜ።

የማሰቢያ ጊዜ

የብድር ውልን መሰረዝ።በአንዳንድ ሃገራት የብድር ውል ተፈርሞ ለተወሰኑ ቀናት ወይም ሳምንታት በህግ እንዲጸድቅ አይደረግም።በዚህ ጊዜ አበዳሪው ገንዘብ አይሰጥም ተበዳሪውም ገንዘብ አይቀበልም። የማሰቢያ ጊዜው ብድሩን አስቦበት ስለሚወስድ ውጤታማ ጥበቃ ያደርጋል።

በጊዜው ብድርን መክፈል

ተበዳሪው/ዋ ያለባቸውን ዕዳ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል የብድር መክፈያ የጊዜ ገደብ ከመጠናቀቁና በቅጣት ተቸማሪ ክፍያ ሳይተየቁ በማንኛው ጊዜ መክፈል የመክፈል ነጻነት አላቸው።

ዋስ
- የተበደሩን ብድር መመለስ የማይችሉ ሲሆን ብድሮት የሚከፍል ዋስ የሆነ ሰው ነው። የብድር ውሉን ሲፈራረሙ ዋስ የሚሆን ሰው ስምምንቱን በጋራ መፈረም ሊያሰፈልግ ይችላል።

ከመጣን በላይ ባለእዳ መሆን
- እዳውን/ዋን በጊዜው ለመክፍል ያለመቻል

የክፍያ ዘዴዎች

የገንዘብ ካርድ/ኤቲ ኤም ካርድ

ከአውቶማቲክ የገነዘብ መክፈያ ማሽን ከሂሳብዎ በባንኩ ፈቃድ ገንዘብ የሚያወጡበት ካርድ ነው። በካርዱ ገንዘብ ከማውጣት በተጨማሪ ያሎዎትን ቀሪ ሂሳብ ከሂሳብ ቁጥርዎ ወደሌላ ሂሳብ ገንዘብ ማሰተላላፍ እና ገንዘብ ለማጠራቀም ሊጠቀሙበት ይችላላ።አንዳንድ የኤቲኤም ካርዶች የፖስታ ቴምብር ለመሸጥ፣የስልክ የአየር ሰዓት ለመግዛት እንደ ኤሌክትሪክ የመሳሰሉ ክፍያዎች ለመፈጸም ያስችላሉ።እያንዳንዱ ባንክ የራሱ የሆነ ለኤቲአም የሚያገለግል ኔትወርክ ወይም የአሰራር መረብ አለው።ብዙ ግዜ ኤቲአሙን ከሰጠዎት ባንክ ውጪ ገንዘብ ለማውጣት በሌላ ባንክ ኤቲኤም ማሽን ሊተቀሙ ይችላሉ። ነገር ግን አገልግሎቱን በተጠቀሙ ቁጥር ለአገልግሎቱ ያስከፍሎታል።

የመክፍያ ካርድ

የከፍያ ካርድ ሌላው በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ክፍያ የሚጽሙበት አሰራር ነው፡የክፍያ ካርድ ገንዘብ ከማውጣቱም በተጫማሪ በተለያዩ ግብይት ስፍራዎች ለአደረጉት ግብይት ለገዙአቸው እቃዎች ካርዱንበመጠቀም ክፍያ ሊፈጽሙይችላለሉ። ግብይቱን በሚፈፅሙበት ጊዜ በሂሳቦ ላይ በቂ ገንዘብ መኖር አለበት። ያደረጉት ግዢ ወዲያውኑ ከሂሳቦ ተቀናሽ ይደረጋል። ባንኩም በመደበኛነት ባደረጉት ግብየት መሠረት ከሂሳብዎ ተቀናሽ የተደረገውን ዝርዝር ሂሳብ መግለጫ ይልክሎታል።

ክሬዲት ካርድ

በአጠቃላይ ክሬዲት ካርድ በክፍያ ካርድ እና በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ተመሳሳይ ግብይይት ለማደረግ ይፈቅዳል። ዋናው ልዩነት የክሬዲት ካርድ ፈጣን የሆነ ብድር እንዲያገኙ ያደርጋል።በሌላ አነጋገር ገንዘብ በባንክ ሂሳብዎ ሰይኖር የክሬዲት ካርድዎን የሰጥዎት የገንዘብ ተቋም ፣ሱፐር ማርኬት እና ሌሎች አገልገሎት ሰጪ ተቋማት ብድር በማገኘት በያዙት ክሬዲት ካርድ አማካኝነት ግዢዎችን ሊፈጽሙ ይችላሉ።

- በገቡት የክሬዲት ካርድ በተገባው የኮንትራት ውል በመመስረት በክሬዲት ካርድ የሚገዝዎቸውን ግዢዎች ከባንክ ሂሳብዎ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል።ከሂሳብዎ ተቀናሽ ሲደረግ በአንድ ጊዜ ወይም ደረጃ በደረጃ ለሆን ይችላላል።በክሬዲት ካርድ ሲገለገሉ የሚክፍሉት ወለድ ከመደበኛው የወለድ ተመን ከፍ ያለ ለሆን ይችላል።የክርዲት ካርዱን ከወሰዱት ተቋም ስለሚከፍሉት ብድር፣የከፈሉትን የብድር መጠን የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ ከተቋሙ ይደርስዎታል።

የገንዘብ ዝውውሮች

መደበኛያልሆኑ የገንዘብ የማሰተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞች

- እነኚህ ተቋማት መንግስት ቁጥጥርና ክትትል አያድርገባቸውም። ይህን አገልገሎት የሚሰጡት በችርቻሮ ሱቆች በሰዎች ትውውቅ (በጓደኝነት) እና ይህን ስራ በሚሰሩ የመልዕክት ሰራተኞች ነው።

መደበኛ የገንዘብ የማሰተላለፍ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋሞች

- እነኚህ ተቋማት በመንግስት ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግባቸው ናቸው። መደበኛ የገንዘብ ዝውውርን አገልግሎት የሚሰጡት ባንኮች፣ህጋዊ ገንዘብ አስተላላፊ ተቋማት፣ጥቃቅን አነሰተኛ ተቋማት፣የብድርና የቁጠባ የህብረት ስራ ማህበራት እና የሞባይል ባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ናቸው።

አደጋና/ስጋት/ እና ኢንሹራንስ

አደጋ

- አደጋ ከፍተኛ ጥፋት ወይም ጉዳት ሊያሰከትል ይችላል።

ኢንሹራንስ

- መድህን /ኢንሹራንስ፡- አደጋን ለመከላከል በመድህን ድርጅቱ ተመዝገበው ውል በመፈራረም አደጋ ሲከሰት ለደረሰበዎት አደጋ የገንዘብ ካሳ የሚከፍል ነው።.

የኢንሹራንስ ኩባንያ

- የኢንሹራንስ/መድህን አገልግሎት የሚሰጥ ሆኖ ዋናው ግቡ ትርፍ ለማግኘት የሚሰራ የንግድ ኩባንያ የሆነ ነው።

ለጋራ ጥቅም የተቋቋመ የህበረት ሥራ ማህበር፡

- ለጋራ ጥቅም በአባለት ባለቤትነት የተመሰረተ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን የአባላቱን ፍላጎት መሰረት የደረገ የመድህን/የኢንሹራንስ አገልግሎት ይሰጣል።

የኢንሹራንስ ውል ሰነድ

- በደንበኛውና በኢንሹራንስ ኩባንያው መካካል ስለ ኢንሹራንስ ሽፋን ሁኔታ፣የሽፋኑ ጊዜ፣ሽፋን የሚደረግባቸው የአደጋ ዓይነቶችና የማይሸፈኑ የሚገልጽ የስምምት ሰነድ ነው።

አረቦን

- ኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኝ ውል የገባው ሰው ለመድን ሰጪው ድርጅት የሚከፈል ገንዘብ/ዋጋ ነው።

የኢንሹራን ጥቅም

- በኢንሹራንስ ኩባንያው የክፍያ ጥያቄ ላቀረበ ሰው ወይ ለባለመብት የሚከፈል ክፍያ ነው።

የኢንሹራንስ ተጠቃሚ

- ኢንሹራንስ በተገባው መሰረት አደጋ ሲደርስበት ከኢንሹራንስ ኩባንያው ክፍያ የሚያገኝ ሰው።

የካሳ ጥያቄ

- አደጋ ሲደርስ በተገባው ኢንሹራንስና ፖሊሲ መሰረት የሚቀርብ ጥያቄ ነው።

የኢንሹራንስ ካርድ

- በኢንሹራንስ ኩባንያ በፖሊሲው መሰረት አረቦን ለከፈለ ደንበኛ የሚሰጥ ካርድ ነው።

የማይሸፈኑ

- በተለያዩና እና በተወሰኑ ሁኔታዎች በኢንሹራንስ ውል ውስጥ ያልተጠቀሱና ሽፋን የማያገኙ ሁኔታዎች ናቸው።

የሰልጣኞች መጽሃፍ

የአለም አቀፉ የስራ ድርጅት የገንዘብ አያያዝ ትምህርት

ለስደት ተመላሾችና ለስደት ለተዘጋጁ ዜጎች የሚያገለግል
የስልጠና መፅሐፍ

ይህ የስልጠና መፅሐፍ የተዘጋጀዉ በእንግለዝ መንግስት የጋራ ብልፅግናና ዕድገት ቢሮ ድጋፍ በሚንቀሳቀሰዉ በክፍለ አህጉራዊ የስኬታማ ፍልሰት አስተዳደር ፕሮጀክት አማካኝነት ነዉ።

ይህ የዓለም ስራ ድርጅት የገንዘብ አያያዝ የስልጣኞች መፅሐፍ በዋነኛነት ዓላማ ያደረገዉ የገንዘብ አያያዛቸዉን ለማሻሻል ለሚፈልጉ ከስደት ተመላሾችና ለስደት የተዘጋጁ ዜጎችን ለመርዳት እንዲቻል ነዉ። ይህ መፅሀፍ የሚከተሉትን ርዕሶች ማለትም የገንዘብ አያያዝ ግብ መንደፍ፣ በራስ በሞተማመን ቁልፍ የሆኑ የገንዘብ አያያዝ ስርዓቶች እንደ ቁጠባ፣ብድር፣ ክፍያ ፣የአሌክተሮኒክስ የክፍያ ቦርሳ፣እንሹራንስ እና የመሳሰሉትን ፣ የገንዘብ ተቋማት የሚፈልጉትን አሰራሮችን በመረዳት ስምምነት ለመፈፀም፣ሰለገንዘብ ማስተላለፍና ከገንዘብ አያያዝ ጋር ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን አካቷል።

መፅሐፉ ገንዘብ አያያዝን የተመለከቱ መረጃዎችና ፅንሰሃሳቦችን ልበወለዳዊ ገፀባህሪያትን በማስቀመጥና የግል ሁኔታ ጥናትን፣ ልዩ ልዩ መልመጃዎችንና የተለያዩ ዋቢ ምንጮችን እንዲጠቀሙ ተደረጎ የተዘጋጀ ነዉ።ይሔዉ መፅሐፍ በተጨማሪም የዓለም ስራ ድርጅት የገንዘብ አያያዝ ትምህርትና ስልጠና የተመለከቱ ቁልፍ ጉዳዮንና የራስን ገንዘብ እንዴት በሚገባ መያዝና መጠቀም እንደሚቻል የተመለከቱ ትምህርቶችን ይዟል። መፅሐፉ በዓለም ስራ ድርጅት የገንዘብ አያያዝ ስልጠና ኮርስ ለሚካፈሉ የወንድና ሴት ሰልጣኞች ሁሉ በሚጠቅም መልኩ የተጋጀ ነዉ። መፅሀፉን በስልጠናዉ ወቅት እንደማገናዘቢያና እንደ ማስታወሻ ደብተር መጠቀም ያስፈልጋል። በመፅሐፉ ዉስጥ የተጠቀሱትን ገፀ ባህሪያትን ዉክልናን ልምድ ባማከለ መልኩ የተዘጋጁ በቀልድ መልክ የተቀናበሩ ርዕሶች ተካቷል መፅሐፉ በሰልጣኞቹ የሚሰሩ መልመጃዎችና የሚሞሉ ቅጾችን አካቷል ።

ISBN: 9789220362723 (print)
ISBN: 9789220362730 (web PDF)

International Labour Organization

Financial Education

Better Regional Migration Management

UKaid from the British people